# የ1966 ሕዝባዊ አብዮት እና መኢሶን
# አንዳንድ ማስታወሻዎች



አንዳርጋቸው አሰግድ

የካቲት 2016 ዓ.ም.

© 2016 ዓ.ም
የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

ISBN :- 978-99990-53-16-7

# የ1966 ሕዝባዊ አብዮት እና መኢሶን አንዳንድ ማስታወሻዎች

አንዳርጋቸው አሰግድ

የካቲት 2016 ዓ.ም.

## ማውጫ


ገጽ

መቅድም ........................................................................................................ iii

መግቢያ ........................................................................................................ viii

ማስታወሻ ........................................................................................................ vi

አዘውትሮ ከሚነገሩት እና ከሚፃፉት ........................................................................ 1

በመኢሶን ላይ የሚቀርቡትን ሂሶችን እና አስተያየቶችን በተመለከተ....................... 8

ስለመኢሶን ትብብር ........................................................................................ 23

የትግል ስልት ለውጥ........................................................................................ 32

ከመኢሶን ስህተቶች ........................................................................................ 42

በ"ያ ትውልድ" ላይ ከሚቀርቡት ሂሶች እና አስተያየቶች .................................... 55

ለሂሳዊ ዳሰሳ እና ፍተሻ ................................................................................ 66

"ነጭ ሽብር/ቀይ ሽብር"...................................................................................... 81

የፖለቲካ ግድያ እና የፖለቲካ ሥልጣን............................................................ 88

ማጠቃለያ........................................................................................................ 93

ዋቢ መጻፍት እና ፅሕፍት...................................................................................... 100

# መቅድም

አንዳርጋቸው አሰግድ ከሃያ አምስት አመታት በፊት "በአጭር የተቀጨ ጉዞ፣ መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ" የሚለውን መፅሐፉን ለአንባቢዎች አቅርቧል። አሁን ደግሞ፣ ይህቺን አንዳንድ አጫጭር ማስታወሻዎች ለአንባቢዎቹ ይዞ ቀርቧል። እነዚህ ማስታወሻዎች ቀደም ካሉት ዓመታት እስከ1969 ዓ.ም. ዓበይት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ጉዳዮችን ጠቅለል አድርገው በአጫጭሩና በተጨባጭ የሚዳስሱ ናቸው። በዚህም እስከዛሬም ድረስ አከራካሪ በሆኑት ታሪካዊ የአገራችን ሁኔታዎችና የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩሩና የሚያሰምሩ ናቸው። አንዳርጋቸው፣ በታሪኮቹ አውድ ውስጥ የተመጣጠኑ ማስረጃዎችን እያስደገፈና የተመዘገቡ ኹነቶችን እያካተተ፤ እንደበፊቱ መፅሐፉ ለንባብ አብቅቷል። በዚህም ጥረቱ፣የአንባቢዎችን ሚዛናዊ ኅሊናን ይጋብዛል። የወጣት አንባቢዎችንም ሆነ የየካቲት 66ቱንም የለውጥ ፈላጊ የፖለቲካ ትውልድንም የግንዛቤ አእምሮ ይኮረኩራል።

ለመጀመሪያው "በአጭር የተቀጨ ጉዞ" መፅሐፉ ዝግጅት፣ አንዳርጋቸው ለብዙ አመታት ምን ያህል እንደደከመበትና እንደተጨነቀበት እኔው እራሴ የቅርብ አጋዡ በመሆኔ የዓይን ምስክር ነኝ። በመጀመሪያው መፅሐፉ፣ ታሪካዊ ኹነቶች እንደተካሄዱ፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና መንግሥት የወሰዷቸውን አቋሞች በጊዜው እንደፃፏቸው ወይም እንደገለጿቸው ከታተሙ ወረቀቶቻቸውና ጋዜጦቻቸው እንዳሉ በተጨባጭ በማስረጃዎች እየጠቃቀሰ አቅርቦልናል። ይኸው "በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ" መፅሐፍ ምንም እንኳን የመኢሶን ታሪክ ቢሆንምና አንዳርጋቸውም በአቀራረቡ የፖለቲካ ወገንተኝነት ቢያሳይም ቅሉ፤ በማስረጃዎቹ ተጨባጭነት ግን፤ ሚዛናዊነትና ገለልተኝነት ይታይበታል። ይህቺም የአንዳርጋቸው አጫጭር ማስታወሻዎች፣ ለእርሱና በእርሱ በኩል ስለየካቲቱ 66 የፖለቲካ ትውልድ የማሳረጊያ ፅሑፍ ሆና የቀረበች ትመስላለች።

የየካቲቱ 66 የፖለቲካ ትውልድ ሁለት ዋና ዋና የታሪክ ኃላፊነቶች የተሸከመ መሆኑን እገነዘባለሁ። ይህ የታሪክ ኃላፊነት ሸክም ደግሞ ከበድ ያለና ድርብ የታሪክ ጭነትም ጭምር ሆኗል። ባንድ በኩል፣ የትውልዱ ንቁ የፖለቲካ ተስታፊዎች፣ ቀደም ሲል ባመኑባቸው የተለያዩና በሚመሳሰሉ የአጭርና የረጅም የፖለቲካ ፕሮግራሞች፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብቶችና ለአገር ጥቅም ይበጃል ላሏቸው ለውጦች ታግለዋል። በርካታዎች በሕይወታቸው መስዋዕትነት ከፍለዋል። ሌሎችም በእስር ተንገላተዋል፤ በስደትም ከአገር ውጭ ተንከራትተዋል። በዚህም ምክንያት ማለት ይቻላል፤ ትውልዱ የኢትዮጵያን ሕዝብ መብቶች እና ለአገር ብሔራዊ ጥቅሞች ተገቢ የፖለቲካ ጥያቄዎችን በማንሳትና ለለውጥ ለመታገል ባሳየው ፅኑ ፍላጎትና ቁርጠኝነት በታሪክ ፊት የትውልድ ማንነቱንና ምንነቱን እንደትውልድ መዝግቧል።

በሌላ በኩል፣ ይኸው የየካቲት 66 የፖለቲካ ትውልድ ለአገሪቱ ችግሮች ሁሉ በታሪክ ኃላፊነት እንዲወስድ ይጠየቃል። በዚህም፣ በታሪክ ፍርድ ቤት ውስጥ ገለልተኛ ዳኞች በሌሉበትና እንዲያውም ከሳሾች እራሳቸውም በዳኝነት ችሎት በተሰየሙበት እየተከሰሰ ነው። የአንዳርጋቸው ለዚህ ለሁለተኛው የታሪክ ኃላፊነት ወይንም ተጠያቂነት ክስ በአግባቡ በመመለስ ድርሻውን የተወጣ ይመስለኛል። ከየካቲት 66 የፖለቲካ ትውልድ ዓላማዎች ውስጥ በመጠኑም የተሳኩትም ይሁኑ፤ በአጭር የተቀጩትን ከነትግል ስልቶቻቸው ድካም ጭምር ቀርበዋል።

ዛሬ ለሚቀርቡት ክሶች ወይም ትችቶች፣ አጥጋቢ መልስ አይደለም ቢባል ክፋት የለውም። ሆኖም ግን፣ ከሳሽና ፈራጅ ዳኛም ሆነው ለሚቀርቡት ክሶች ግን፤ ምንም ዓይነት መልስ አጥጋቢ አይመስላቸውም። ምክንያቱም፣ የእነርሱ ትችትም ሆነ የፍርደ ገምድል ውሳኔ ብቻ ፍጹማዊ ስለሚመስላቸው። ያም ሆነ ይህ፣ በዚያ ትውልድ ላይ የተፈለገው ዓይነት ትችት ዛሬም ሆነ ነገ ቢቀርብ፤ የየካቲቱ የፖለቲካ ትውልድ በጥቅል የሕዝብ ወገንተኝነቱና ኢትዮጵያዊ አገር ወዳድነቱ እንደማያጠያይቅ፣ የሕግ ጠበቃዎችን ሳያቆሙ በታዩት የታሪክ ማስረጃዎች ብቻ ማረጋገጥ ይቻላል።

ከአንዳንድ ከቀድሞም ይሁኑ ከአሁኑ ወጣት ትውልድ ኢትዮጵያውያን አካባቢ፣ የዚያ ትውልድ ታሪክ ምዕራፍ አይዘጋም ወይ? ስለዚያ ትውልድ የፖለቲካ ታሪክ መስማትና ማንበብ አይበቃንም ወይ? እያሉ ሲያማርሩና ሲንገፈገፉ ይደመጣሉ። ይሁንና፣ እንደኛ፣ ይህ ታሪክ የኢትዮጵያ የአንድ ትውልድ ታሪክ እንደመሆኑ በሁሉም ገፅታዎቹ መተረክ የግድ ይኖርበታል። የኢትዮጵያን ታሪክ ከሥረ መሠረቱ ባጠቃላይ አፍቅሮ፣ የሚጣፍጠውን ብቻ እየነጠሉ እንደቆሎ መዝገን፣ የተሟላ የታሪክ ንባብም ሆነ የታሪክ እውቀት በጭራሽ አይሆንም። ማንኛውም የታሪክ እውቀት፣ ጣፋጭ ጣፋጩን ብቻ እያጣጣሙ፣ መራሩን ግን እያጣጣሉ የታሪክ ተማሪም ሆነ የታሪክ ምሑር መሆን በጭራሽ አይቻልም። ይህን ዓይነት የተዛባ የታሪክ ንባብም፤ አስቂኝም አሳፋሪም ጭምር ነው የሚሆነው።

ሁለተኛም፣ የ1966ቱ የፖለቲካ ትውልድ የተጋፈጧቸው ብዙ የአገሪቱ ችግሮች፣ በዚያን ጊዜ የተፈታተኗቸው በርካታ የፖለቲካ ጥያቄዎች እና የወጣጠሯቸው የአገሪቱ ጉዳዮች እስከአሁንም ድረስ ትውልድ ተሻግረው ኢትዮጵያኖችን እያፋጠጡን ጭምር ነው። የፖለቲካ ሥልጣን አያያዝና የመንግሥት ባሕሪና ቅርፅ፣ ድህነትና ሥራ አጥነት፣ የመሬትና የንብረት አያያዝ፣ የብሔር ጥያቄዎች፣ የሰላማዊና የመሣሪያ ትግል ዘይቤዎች ወዘተ... እስከዛሬም ያልተፈቱ ጥያቄዎችና ችግሮች ሆነው ከትውልድ ትውልድ ተሻግረዋል። ስለዚህም፣ ያለፉትና የአሁኖቹ የኢትዮጵያ ትውልዶች በርካታ የምንጋራቸው፣ ትውልድ ተሻጋሪ የጋራ ችግሮች እንዳሉን መገንዘቡ ተገቢ ነው። ሁለትና ሦስት ትውልድ የሚሻገሩ ችግሮች ደግሞ፣ ያለጋራ ምክክርና ትብብር በአንድ ትውልድ ዕውቀትና ብርታት ይፈታሉ ብሎ ማቀድም የማይቻል የታሪክ ፈተና ነው።

ሦስተኛም፣ በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ካለፈው የየካቲት የፖለቲካ ትውልድ ከተሠሩትም ስህተቶች ሆነ ከስኬቶች ትምህርቶችን መቅሰም የሚቻልበትን ጠቃሚ የታሪክ ዕድልንም መፍጠር ይቻላል። አንዳርጋቸውም በዚች ማስታወሻዎቹ ትኩረት ከሰጠው አንደኛውና ጉልህ ነጥብ ደግሞ ይኸው ነው።

አራተኛም፣ የየካቲት 66 የፖለቲካ ትውልድ የአገራችንን አብዛኛውን ችግር (የብሔረሰብን ጥያቄ ጭምር) እንደቆሰቆሰና እንደፈጠረ ተደርጎ የሚቀርብ የተዛባ አመለካከት አለ። ስለዚህም፣ ትውልዱ እንዳለ የፖለቲካ እርግማን እንዲወርድበት ሆኖ ይቀርባል። እዚህ ላይ ብዙ ጊዜ የሚነሳው ወቀሳ የብሔር ጥያቄ ነው። ይህም ትችት ቢሆን፣ የጥያቄውን ታሪካዊ አመጣጥና ቀደም ብሎ በመንግሥት ምሥረታ ታሪክ ሂደት ውስጥ የተከሰተ ፖለቲካዊ ባሕሪውን ባለመገንዘብና ባለማጤን የሚቀርብ ነው። በተረፈ ግን፣ መልሶች እንዲሰጣቸው የተነሱትን የሕዝቡን ድህነትን ችግርና ከዓፄያዊ መንግሥት ፍፁማዊ አገዛዝ የፈለቁ የመብት ችግሮችን፤ ትውልዱ እንደፈጠራቸው አድርጎ ማንም ለመተቸት አይሞክርም። ምክንያቱም፣ ትውልዶችን እየተሻገሩ የመጡ ችግሮች መሆናቸው ግልፅ በመሆኑ ነው። እንዲያውም ጥያቄዎቹን አንስቶ በተገነዘበው መልኩ የለውጥ መፍትሔ እንዲመጣ የዚያን ዘመኑ ወጣቱ ትውልድ በድፍረት ለሕዝብ መብቶች መሟገቱ በታሪክ የሚያስመሰግነው እንጂ የሚያስወቅሰው አይደለም። አሁንም ቢሆን እንደ ሕዝብ መብት ጥያቄነቱ፣ ከመንግሥት አቀራረፅና የሥልጣን ድልድል፣ እንዲሁም ከአገሪቱ ኢኮኖሚ ጥያቄዎች ጋር ተጋምዶ የሚታይ ውስብስብ በመሆኑ፤ መፍትሔ አሰጣጡም እንደቀድሞው ሁሉ ቀላል ባለመሆኑ በአንክሮ ሊታሰብበትና በኢትዮጵያውያን በጋራና በትዕግስት ሊመከርበት ይገባል እንጂ፤ ጥያቄውን በማጣጣልና በስሜታዊነት መጯጯሁ ምንም ፋይዳ አይኖረውም።

በእርግጥም የየካቲቱ ትውልድ በፖለቲካ አመለካከቶችና በትግል ስልቶች ተለያይቶ ክፉኛ ተጋጭቷል። የነዚህም ግጭቶች መንስኤዎችና አካሄዶችንም በጥሞና መመርመሩና መተቸቱ የአሁኑም ሆነ መጭው ትውልድ ትምህርት የሚቀስምበት ይሆናል። አንዳርጋቸውም በዚህች ማስታወሻዎቹ ውስጥ ይህንንም ጉዳይ በአፅንኦት ዘርዝሮ አቅርቧል። ለትውልዱ የሚቀርበው ወቀሳ ለተዛነፉት ጎኖቹ መተቸቱ አግባብ አለው። ትውልዱ አይተችም ወይም ፍጹማዊ ነው ማለትም ደግሞ ስህተት ነው። ሆኖም፣ ትውልዱ የአገራችንን ችግሮች ራሱ አልፈጠራቸውም። ጉዝፍ ጉዝፍ ችግሮቹን ከፈጠሩ ከማኅበራዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች ጋር የተገጣጠመ ትውልድ ስለነበር ነው። የአገሪቱ ችግሮች ትውልዱን የተጋፈጡትን ያህል፤ ትውልዱም ችግሮቹን ተጋፍጧቸዋል። የሕዝቡንና የአገሪቱን ችግሮች እየዘረዘረ አስረድቷል፤ አሳይቷል። በአንፃሩም፣ አግባብ ያላቸውን ጥያቄዎች አቅርቧል። አያይዞም፣ የለውጥ ጎዳናን ጠቁሟል። በእርግጥም የቅርብ የፖለቲካ ታሪኩን መለስ ብለው በአንክሮ ለሚያጠኑት፣ የየካቲቱ 66 ሌጋ የፖለቲካ ትውልድ በፈቃዱ የወሰደውን ከባድ የታሪክ ኃላፊነት ከአቅሙም በላይ የተሸከመው ነበር ማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል፣ ያለፈውን ትውልድ መተቸት አግባብ ይኖረዋል ብየ ብገነዘብም፤ ከዚያ ወዲህና አሁንም ጭምር ለሚያጋጥሙት የአገሪቱ ችግሮች ደግሞ፤ የአሁን ወጣት ትውልድ በቀድሞው ላይ በመላከክ የራሱን የታሪክ ኃላፊነት ከመውሰድ ገሸሽ ማለት አይገባውም። አንድም፣ አዲሱ ወጣት ትውልድ በራሱ የሚጠየቅባቸው ታሪካዊ ኃላፊነቶች ስላሉ ነው። ሁለተኛም፣ የአሁኑን ችግሮች ለመመለስም ሆነ ለመቋቋም፤ ተሳስቷል ከሚለው የቀድሞው ትውልድ የቀሰመው ትምህርት አለመኖሩም የሚያጠያይቅ ነው። ይህ በራሱ ታሪካዊ ችግር ሆኖ የሚታየውን ያህል፤ በአጠቃላይ በቀድሞው ትውልድ ላይ በመላከክ ማዘናገትና መዘናጋት ጎጂ ነው። ስለዚህም፣ ትውልድ ተሻጋሪ የሆኑ ችግሮች ላይ ለመወያየትና ልምድንም ለመለዋወጥ፤ ለተረካካቢ ትውልዶች፣ ለአገርና ለወገን ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው። ከዚሁ ጋርም በተያያዘ መልኩ፣ የአሁኑ ትውልድም በአገርና በሕዝብ መብቶች ጉዳዮች ላይ በጥቅል ከሚውስደው ታሪካዊ ኃላፊነት አኳያ፤ የራሱንም ምነንትና ማነንት በታሪክ አስመዝግቦ ማለፍ ይጠበቅበታል። ይህንንም ሲያደርግ፣ የአሁኑ ወጣት ትውልድ እንደቀድሞው ሁሉ፤ በጥቅሉ በታሪክ ፊት በተራው የሚወቀስበትንና የሚመሰገንበትንም ሁኔታ አስቀድሞ መገንዘብ ይኖርበታል። ጉዳዩ "ነግ በኔ" ነውና።

በየካቲቱ ትውልድ ውስጥ ሕይወታቸውን አሳልፈው ከተሰውት በስተቀር፤ በሕይወት የተረፉትም በአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ በየሙያ ዘርፋቸውና በአቅማቸው ኢትዮጵያዊ ወገኖቻቸውን አሁንም ድረስ የሚረዱ በርካታ ናቸው። ስለዚህም፣ የየካቲት ትውልዱ እንዳለ እንደከሰመም መመልከቱ ስህተት ነው።

በመጨረሻም፣ በአንዳንድ ተረካቢ የወጣቱ ትውልድ ዘንድ፤ "ትግል ለምን ያስፈልጋል?" በሚል በውይይት ላይ ሲያነሱ ሰምቼአለሁ። "ትግል የሚለው ቃል ራሱ ከስምምነት ይልቅ ግጭትን ያመለክታል" እያሉም ያሳስባሉ። ቃሉ፣ ግጭት የሚያባብስ በመሆኑ ስጋት ላይ እንደጣላቸውም ይገልፃሉ። በየካቲቱ ትውልድ በስፋት ጥቅም ላይ የዋለና እስካሁንም የተሰራጨ ቃል በመሆኑ፤ ግጭት ለመቆስቆስ የተጠነሰሰ ቃል አድርጎ ማየቱ ስህተት ነው። ትግልን ያስከተለው ሁኔታ እኮ ያልተፈቱ የአገር ችግሮች በመኖራቸው ነው። በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ ምንጊዜም የማይጠፉ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችና ማኅበራዊ ፍላጎቶች ምክንያት ግጭቶች የማይቀሩ በመሆናቸው ነው።

ትግል ሲባልም ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ የማፈላለጊያ ዘዴ ሆኖ በመታየቱ እንጂ፤ ግጭት ለማቀጣጠል ሲባል ጥቅም ላይ የዋለ አይደለም። ቃሉን በሌላ ቃል እንለውጠው ቢባል እንኳን፣ በምትኩ "ዘመቻ" ማለት ወይም "እንቅስቃሴ" ማለት ይቻላል። ሆኖም፣ የቃላት ልውውጦሽ ካልሆነ በስተቀር ዙሮ ዙሮ ያንኑ የሚካሄደውን የፖለቲካ ድርጊት ነው የሚገልፀው። ይልቁንስ፣ ዋናውና ተገቢው ጥያቄ እንደየሁኔታው ምን አይነት የትግል ዘዴ ነው የሚያስፈልገው ነው? ለፖለቲካ ለውጥ ከመሣሪያ ብቸኛ አማራጭ ይልቅ ሊሎች ሰላማዊ የፖለቲካ ትግሎች ይበልጥ እድል ሊሰጣቸውና እንደ ፖለቲካ ባህል ሊዳብሩና ሊለመዱ አይገባቸውም ወይ? የሚለው ነው።

እነዚህን የመሳሰሉት ጥያቄዎችንና ጉዳዮችን ሁሉ አንዳርጋቸው በዚህች ማስታወሻው ውስጥ ይዳስሳቸዋል። የየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ 50ኛ ዓመት ዛሬ እንደታሪካዊ ኹነት ሲታሰብ፤ የአሁኑ ወጣት ትውልድ ሊመለከታቸውና ሊመረምራቸው በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ለውይይት ይጋብዛቸዋል። በተረፈው፣ የግማሽ ምዕት ዓመት የአገሪቱን ፖለቲካዊ ክንውኖችን ማብጠልጠልና በሚዛናዊ አእምሮ የመመርመሩ ድርሻ የአንባቢዎች ይሆናል።

ፕሮፌሰር ጴጥሮስ ቶጃ

አለንታውን፤ ፔንሲልቬንያ

መጋቢት፣ 2016 ዓ.ም.

**ማስታወሻ**

በዚህ ድረ ገፅ የታተመው የአንዳርጋቸው አሰግድ ፅሑፍ በመጋቢት 2016 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ታተመ።

አንባቢዎችና በቅርብ የሚያውቁት ወዳጆቹ የተዘነጉ አበይት ጉዳዮች ወይም መብራራት የሚገባቸው ጉዳዮች መኖራቸውን አስገነዘቡት።

አንዳርጋቸው የደረሱትን አስተያየቶች በማሰብና ግልጽ ማብራሪያ በመስጠት የመፅሐፉን ይዘት ለማጎልበት፤

ሀ) ከደርግ ጋር ስለመኢሶን ጊዜያዊ ትብብር እና

ለ) የትግል ስልት ለውጥ

በሚሉት አርዕስት ስር ሁለት ፅሑፎችን አዘጋጀ።

መፅሐፉ በድጋሚ ስላልታተመ ፅሑፎቹ በዚህ ድረ ገፅ ዕትም ውስጥ ታክለው እንዲቀርቡ ተደርገዋል።

# መግቢያ

የየካቲት1966 ሕዝባዊ አብዮት ከተከናወነ 50 ዓመታት ተቆጠሩ። በዚህ ግማሽ ክፍለ ዘመን በአብዮቱ ምክንያት፣ ሂደትና ተዋናዮቹ ላይ በርካታ መጻሕፍትና ሐተታዎች ለንባብ በቅተዋል። በርካታ ውይይቶች ተካሂደዋል። ዘንድሮ 50ኛ ዓመቱ ሲዘከር፤ "ምን ተካሄደ? እንዴት ተከናወነ? የፖለቲካ ተዋናዮቹ እነማን ነበሩ? እንደምን ተወናዮ?" የሚሉትን ጥያቄዎች የማንሻና የመወያያ ጊዜ ነው። ምን ትምህርት ተቀሰመ? የሚለው ጥያቄ ጠንከሮ የሚቀርብበት ጊዜ ነው። ውይይቱ ከፖለቲካዊ ወገናዊነት እና ከስሜተኝነት ፀድቶ ሊካሄድ ይገባል። ወይንም፣ ውይይቱ ከፖለቲካዊ ወገናዊነት እና ከስሜተኝነት ፀድቶ የተካሄደውን ያህል ነው፤ ከጋራ የታሪክ አመለካከት፣ አስተውሎ ላይ ለመድረስ ለሚደረገው ጥረት አስተዋፅኦ የሚኖረው።

ማስተዋሻዎቹን የማቀርበው፣ ስለሕዝባዊው አብዮቱና መኢሶን ተደጋግመው በሚነሱ/በሚሰጡ አስተያየቶችና ትችቶች ላይ በማተኮር ነው። ለዚህም፣ በአብዮቱ ክንዋኔ ላይ ባጭር ባጭሩ እመለሳለሁ። አጠቃላይ ሂደቱን ከየወቅቱ ሁኔታዎች ጋር እያገናዘብኩ ለማቅረብ እሞክራለሁ። ማስታወሻዎቹ በመኢሶን ላይ የተወሰኑት፣ በተሻለ የማውቀው መኢሶንን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ስለሆነ ነው። በኢሕአፓ እና በመኢሶን ጉዳዮች ላይ የተመላለስኩት፤ አብዛኞቹ ትችቶች እና አስተያየቶች የሚሰጡት በሁለቱ ድርጅቶች እና ታግዮቻቸው ላይ ስለሆነ ነው። ከየወቅቱ ሁኔታዎች ጋር እያገናዘብኩ ለማቅረብ የምሞክረው፣ በአንድ ዋና ምክንያት ነው። ኹነቶች በተከሰቱበትና በተከናወኑበት ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ (አውድ ውስጥ) ተካትተው ካልታዩና በማስረጃ እየተደገፉ ካልተመሳከሩ፣ የተዛቡ አመለካከቶች ይስፋፋሉ፤ ይሰፍናሉ፤ ያወዛግባሉ፤ አረዳድ ይዛባል።

በዚህ አጭር ፅሑፍ፣ ለጥያቄዎቹ አንዳንድ መልሶችን ለመስጠትና አንዳንድ አስተያየቶችን ለማቅረብ እጥራለሁ። በሌላ በኩል፣ እንኳን የትላንትናው የኢትዮጵያ አብዮት ቀርቶ፤ የ18ኛው እና የ20ኛው ክፍለ ዘመን የፈረንሳይና የራሺያ አብዮቶች ታሪክም እስከዛሬ ድረስ ብዙ ብዙ ያመላልሳሉ፤ ያነጋግራሉ፤ ያከራክራሉ። የ1966 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮትም፣ ገና ለብዙ ብዙ ዓመታት የሚገመገምና የሚተነተን ሆኖ ይቆያል። የአብዮቱ ዘመን ታጋዮች የሚፅፉት እና የሚናገሩት በየራሳቸው የተሳትፎ ታሪክ ላይ ተወስነው እንደሆነ ይታወቃል። ትረካዎቹን እንደግብዓት ተጠቅሞ፣ አገናዝቦ እና በማስረጃዎች አመሳክሮ መተንተን የአካዴሚያዊ ተማራማሪዎች ፈንታ ነው። በዚህ ፅሑፍ የቀረቡት ማስታወሻዎች፣ መጠነኛ አስተዋፅኦ ለማበርከት የበቁ እንደሚሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ።

በፅሑፉ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ፣ አዘውትሮ በስህተት ሲነገሩና ሲፃፉ የኖሩን ዓቢይ ጉዳዮች አስታውሳለሁ። በሁለተኛው ክፍል፣ በመኢሶን ዓቢይ ስህተቶች ላይ ተመልሼ በአጭር በአጭሩ አትታለሁ። በሚቀጥለው ክፍል፣ በመኢሶን እና "ያ ትውልድ" በሚባለው ላይ በሚቀርቡት ሂሶች እና አስተየይቶች ላይ እመለሳለሁ። ከዚያም፤ አንዳንድ ጉዳዮችን በሂሳዊ ዳሰሳ እና ፍተሻ አነሳለሁ፣ በ"ነጭ እና ቀይ ሽብር" እና በፖለቲካ ግድያና የፖለቲካ ስልጣን ጥያቄዎች ላይ ተመልሼ አትታለሁ። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ በአንፃራዊ በረጅሙ የተመለስኩት፣ የወቅቱን አውድ ከማስታወስ ባለፈ፤ የነገሮችን አነሳስ እና ሂደት ማስታወስ ያስፈልጋል ብዬ ስላሰብኩ ነው።

ከመቀጠሌ በፊት ግን፤ የፅሑፉ ይዘት በአብዛኛው በ1991 እና በ2007 ዓ.ም. በኢትዮጵያና በሰሜን አሜሪካ ከታተመው መፅሐፌ እና በተለያየ ጊዜ ካቀረብኳቸው ፅሕፍት የተወሰደ እንደሆነ መግለፅ ይኖርብኛል። ከአንዳንድ ተጨማሪዎች እና ማስተካከያዎች በስተቀርም፤ እስከዚህ አልተለወጠም።

የፅሑፉን ረቂቅ አንብበው አስተያየታቸውን የለገሡኝን፣ አስፈላጊ እርማቶችን ያደረጉልኝን ጓደኞቼን እና መቅድሙን የፃፈልኝን ፕሮፌሰር ጴጥሮስ ቶጃን ከልብ አመሰግናለሁ።

አንዳርጋቸው አሰግድ
ጁባ፣ ደቡብ ሱዳን (የካቲት 2016 ዓ.ም.)

# አዘውትሮ ከሚነገሩትና ከሚፃፉት

አብዮት በርካታ ለውጦችና ኹነቶች እየተደራረቡ የሚከናወኑበትና የሚፈፀሙበት የፈጣን ታሪክ ሂደት ክስተት ነው። ስለሆነም አንደኛ ምን፣ መች፣ በማን፣ ለምንና የት ተፈፀመ? ለሚሉት ጥያቄዎች የተለያዩ መልሶችና አስተያየቶች ይሰጣሉ። ሁለተኛ፣ አብዮት በዲሞክራሲ አልባ አውድ ውስጥ የሚከናወን ክስተት ስለሆነ፤ በማስረጃዎች ከተደገፉ ትርክቶች ይልቅ፣ በወገንተኝነት ሐሊናና አቋም እየተነገሩና እየተፃፉ ይስፋፋሉ። እንዲያም ሲል፣ ለተዛባ አረዳድና አመላካከት መስፋፋት ብቻ ሳይሆን፤ ለተዛባ ፍርድ ያጋልጣሉ። እርምት የሚያስፈልጋቸውን አንዳንድ ዕውነታዎች የሚከተሉት ጥቂት ምሳሌዎች ያስረዳሉ።

### "ደርግ የመርማሪ ኮሚሺንን አቋቋመ"

መርማሪ ኮሚሺን የተቋቋመው፣ እነፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ከመታሠራቸው ከአንድ ወር በፊት፤ በልጅ እንዳልካቸው መኮንን መጋቢት 19፣ 1966 ዕለት ነበር። የደርግ ቡድን የተቋቋመው ከአራት ወራት በኋላ በሰኔ 23፣ 1966 ነው።

### "ደርግ የፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ካቢኔ ባለሥልጣናትን አሠረ"

የፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ካቢኔ ባለሥልጣናት የታሠሩት ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ለንጉሠ ነገሥቱ ባቀረቡት ጥያቄና በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ፤ በኮሎኔል ዓለምዘውድ ተሰማ ይመራ በነበረው ወታደራዊ ቡድን ሚያዚያ 18፣ 1966 ዓ.ም. ዕለት ነበር። የደርግ ቡድን የተቋቋመው ከሦስት ወራት በኋላ በሰኔ ወር ነው።

### "ደርግ የ60ዎቹን ግድያ በወሰነበት ስብሰባ ላይ መኢሶን ተሳተፊ ነበር"

እንደተጠቀሰው እየተባለ በመኢሶን ላይ በሀሰት ይዘመት እንጂ፤ መኢሶን ጭፍጨፋውን በመኮነን እና "ቀንደኛ መሪዎቹን ሠፊው ሕዝብ ወደፊት ይፋረዳቸዋል" በማለት የሠፊው ሕዝብ ድምፅ (ሰሕድ) በሚባለው ልሳኑ በግላጭ ያወጣው መግለጫ የሚከተለውን ነበር።

> "ኅዳር 14 ሳይታሰብ፣ ሳይጠረጠር ስድሳ ሰዎች በድንገት ተረሽነው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ዓለም በቃኝ አፈር ሥር ተቀበሩ። ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ ለ30 ዓመታት ያህል በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተንሰራፍተው በመቀመጥ፣ ሠፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ስጋውን በልተው፣ ደሙን ጠጥተው በአጥንቱ ያስቀሩ የኃይለ ሥላሴ ፍጡሮች ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ የነበረውን የጭቆና መንግሥት በመቋቋም፣ በማንበርከክና በመጣል ከሠፊው ሕዝብ ወገን ተሰልፈው የነበሩ ናቸው።
>
> "(እነዚህ) ለብዙ ወራት እሥር ቤት ቆይተው፣ ሕግ ወጥቶ፤ ፍርድ ቤት ተቋቁሞ፤ ፍርዳችሁን ትቀበላላችሁ በመባል ሲጠባበቁ ቆይተው (አሁን) በድንገት ያለምንም ምክንያት በጥይት ተደበደቡ ለመሆኑ የርሸናው ውሳኔ የተወሰደው፣ የሚረሸኑትስ ምርጫ የተከናወነው በእንዴት ያለ መንገድ ይሆን? ደግሞስ የሠፊው ሕዝብ ወገን የሆኑት ታጋዮችን ከበዝባዦች ጋር በአንድነት መረሸን ከሥልጣን ጥማት የመነጨ ዕብደት እንጂ ሌላ ምንን ያሳያል?
>
> "በነሻምበል በላይ ፀጋየ፣ ሻምበል ወልደዮሐንስ ዘርጋው፣ በነምክትል አሥር አለቃ ተክሌ ኃይሌና በሌሎችም (ሻምበል ደምሴ ሽፈራው፣ የመቶ አለቃ ተስፋየ ተክሌ፣ ጁኒየር ኤክማን ዮሐንስ ፍትዊና ተራ ወታደር በቀለ ወልደ ጊዮርጊስ) የሠፊው ሕዝብ ወገኖች ላይ የተወሰደውን የጭካኔ እርምጃ ሠፊው ሕዝብ እነመቶአለቃመንግሥቱ ኃይለማርያምንና ሻምበል ሲሳይ ሀብቴን ወደፊት ይፋረዳቸዋል"[1]

---

[1] ሰሕድ ቁ. 16፣ ታኅሣሥ 4፣ 1967።

**"ደርግ የኢትዮጵያ ኅብረተሰባዊነት ያለውን መመሪያ ካወጀ በኋላ፣ የውርስ እርምጃዎችን ወሰደ"**

ደርግ የውርስ እርምጃዎችን መውሰድ የጀመረው በመስከረም 2፣ 1967 ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥቱን ከማስውገዱ በፊት ገና በ4ኛ ክፍለ ጦር እያለ ነበር። አንዳንዶቹ፣ ብሔራዊ ሀብት ልማት (ነሐሴ 19)፤ የአንበሳ አውቶቡስ ማኅበር (ነሐሴ 23)፤ የቅዱስ ጊዮርጊስ የቢራ ፋብሪካና የሽልማት ድርጅት (ነሐሴ 26)፤ የበጎ አድራጎት ድርጅት 5 ሆስፒታሎች፣ 3 ክሊኒኮች፣ 2 የሕፃናት ማሳደጊያዎች፣ 2 የጡረታ ቤቶች፣ ሆቴሎች፣ ሕንፃዎችና የእርሻ ልማት ድርጅቶች (መስከረም 1፣ 1967) ነበሩ። የኢትዮጵያ ኅብርተሰባዊነት የታወጀው ታኅሣስ 12፣ 1967 ዓ.ም. ነው።

**"መኢሶን የመሬት ለአራሹን አዋጅ አርቅቆ ለደርግ ሰጠ"**

ጥቂት የመኢሶን፣ የኢሕአፓና የኢጭአት አባላትና ወዳጆች የአርቃቂው ኮሚቴ ኣባል የነበሩ ቢሆኑም ቅሉ፤ የየካቲት 1967 የገጠር መሬት አዋጅ የተረቀቀውና ለደርግ የቀረበው በወቅቱ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር ተቀጣሪ በነበሩት የባለሙያዎች (ኤክስፐርቶች) ቡድን ነበር። ባለሙያዎቹም፣ ገና ከ1960 ጀምሮ ስለባለርስት እና ጭሰኛ ግኑኙነት እና ስለመሬት ይዞታ መሻሻል የተለያዩ አዋጆችን ሲያረቁና ለንጉሠ ነገሥቱ ምክር ቤቱ ሲያቀርቡ የነበሩ ነበሩ። ደርግ ገና በ4ኛ ክፍለ ጦር እያለም፣ የጭላሎ እርሻ ልማት ድርጅት ሠራተኞች አንድ ረቂቅ ለደርጉ ሰጥተው ነበር። ይሁንና፤ "መሬት ለአራሹ ቢባልም፣ መሬት እኮ! የአርሶ አደሩ የግል ንብረት አልሆነም" ሲባል ተደጋግሞ ይሰማል።

**"መሬት እኮ! የአራሹ የግል ንብረት አልሆነም"**

የገጠር መሬት በዕርግጥም የአራሹ ገበሬ የግል ንብረት አልሆነም። ምክንያቱም፤ መሬት ለአራሹ ማለት አንደኛ፣ አርሶ አደሩ ጥሮ ግሮ የሚያገኘውን ምርት ለማንም ባለርስት ነኝ ባይ፣ መገበሩ ይቅር ማለት ነው። የጉልበት አገልግሎት መስጠቱ ይቅር ማለት ነው። ከመተዳደሪያ መሬቱ መባረር እና መፈናቀል ይቅር ማለት ነው። አርሶ አደሩ የማንም ባለርስት ነኝ ባይ ባለዕዳ መሆኑ እና ለእስር እና ለእንግልት መዳረጉ ይቅር ማለት ነው። ሁለተኛም፣ መሬት በግብርና የሚተዳደር የአራሽ ግለሰብ፣ ቤተሰብ እና የአራሾች ማኅበር መጠቀሚያ ይዞታ ብቻ ይሁን ማለት ነው። ወይንም፣ መተዳደሪያው ግብርና ያልሆነ ግለሰብ ወይንም ማኅበር፣ በመሬት መጠቀም አይችልም ማለት ነው።

የየካቲት 25፣ 1967 የገጠር መሬት አዋጅ በዚህ መንፈስ አንዲት ስንዝር መሬት ሳያርሱ እና ጭሰኛ ይባሉ የነበሩትን እያስገበሩ ይኖሩ የነበሩትን ባለርስቶች ሥልጣን አስወገደ። የገጠር መሬትን የመንግሥት ይዞታ አደረገ። በግብርና ለሚተዳደሩ ብቻ፣ በመሬት የመጠቀምን መብት (use right) ሰጠ። የየቀበሌው መሬት በየ20 ጋሻው (800 ሄክታር) በተደራጁ የቀበሌ የገበሬ ማኅበራት እንዲተዳደር እና እንዲከፋፈል ወሰነ። እያይዞም፣ ማንም አራሽ መሬቱን የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስም ሆነ በወለድ አግድ ለማስያዝ የማይችል መሆኑን ደነገገ። ይህም የተደነገገው አንዳንዶች እንደሚሉት በፀረ የግል ንብረት ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከት ምክንያት አልነበረም። በሦስት ዋና ምክንያቶች ነበር።

አንደኛ፣ በነበረው ሁኔታ ውስጥ መሸጥ መለወጥን መፍቀድ፣ የቀበሌ ገበሬ ማኅበራቱን ሥልጣን ማፋለስ እና ዓባላቱን ለእርስ በእርስ መጠራጠር እና ሽኩቻ መዳረግ ይሆናል። ሁለተኛ፣ መሬትን ለመግዛት ይችሉ የነበሩት ዞሮ ዞሮ አቅሙ ያላቸው ግለሰቦች እና ማኅበራት እንደመሆናቸው፤ ውጤቱ በአንድ ወገን፣ የመሬት ደላሎችን እና የአዳዲስ የመሬት ከበርቴዎችን መፈልፈል ይሆናል። በሌላውም ወገን፣ የመሬት አልባ ገበሬዎችን መፈጠር እና መበራከት የሚያስከትል ይሆናል። ሦስተኛ፣ የአገሪቱ የፋብሪካዎች፣ የማዕድናት እና የአገልግሎት ድርጅቶች እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ፤ መሬት አልባ የሚሆኑትን ገበሬዎች የማስተናገድ አቅም

የላቸውም። በዚህ ነበራዊ ሁኔታ ውስጥ መሬትን የሚሸጥ የሚለወጥ ሽቀጥ ማድረግ፤ የገጠር ሥራ አጦችን ተበራክቶ መፈጠርን እና ማኅበራዊ እንግልትን እና ድቀትን ያስከትላል።

አሁን አሁን፣ መሬት የግል ንብረት እንዲሆን እና እንደማንኛውም ሸቀጥ የሚሸጥ/የሚለወጥ ቁስ እንዲሆን የሚሞግቱ ፓርቲዎች እና ግለሰቦች ተፈጥረዋል። ይሁንና፣ የት እና መቼ ባደረጉት ጥናት ላይ ተመሥርተው እንደሆነ አይታወቅም። አንዳንድ ጊዜ አንዳንዶች ጥያቄውን የሚያቀርቡት እንዲያውም፤ በንፁህ የግል ንብረት አምልኮ ላይ የተመሠረተ እስከሚመስል ድረስም ነው። እስካሁን ከተደረጉ ጥናቶች እንደሚታወቀው ግን፣ ስለመሬት ይዞታ በርካታ ጥናቶችን በማድረግ የሚታወቁት ዶ/ር ደሳለኝ ራሕማቶ አንድ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ማኅበር ጥናትን ጠቅሰው "የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬታቸውን ለመሸጥ ዕድሉ ቢሰጣቸው እንኳን፤ የመሸጥ ፍላጎት እንደሌላቸው እንደተረጋገጠ" አስምረው ገልፀዋል።[2] የነጋ፣ የአድነው እና የገብረሥላሴ ጥናትም፣ ከተለየ ድምዳሜ ላይ ደርሶ አይነበብም።[3]

ይህንን ማለት ግን፤ የኢትዮጵያ የፋብሪካዎች፣ የማዕድናት እና የአገልግሎት ድርጅቶች ዓቢይ የኢኮኖሚ መስክ እየሆኑ እና ዋናዎቹ ቀጣሪዎች እየሆኑ የመጡትን ያህል፤ የግብርናውም ዘርፍ እየዘመነ ግብዓት አቅራቢ እየሆነ ይሄዳል። የዚያኑም ያህል፤ ከግብርና የሚገነጠለው አራሽ በሌላ ሙያ የመሠማራት ዕድል ይኖረዋል። ሂደቱ በራሱ የሚያስከትለው የመሬት ይዞታ ለውጥ ይኖራል። የሕገ መንግሥቱን አንቀፅ 40/3 እና የየክልል መንግሥታቱ ስለመሬት ይዞታ የደነገጓቸውን አዋጆች መሻሻል ሊጠይቅ ይችላል።

**መኢሶን እና ኢሕአፓ**

አንዳንድ ጉምቱ ባለሥልጣናት ጭምር "መኢሶንና ኢሕአፓ በያሸንፋል/ያቸንፋል እና ላብ አደር/ወዝ አደር ቃላት ተለያዩ" እያሉ ይደሰኩራሉ።[4] ከእንደዚህ ዓይነቱ የሕዝበኛ ተደናቂነት (populist) ቅስቀሳ ግን፣ የሚቀሰም ትምህርትም ሆነ ዕውቀት አይኖርም። ምክንያቱም፣ አተኩሮ እና ጠለቅ ብሎ የሚያጤን ተቺ፤ ቢያንስ የሚከተሉትን ወቅቶችንና ይዘታቸውን ይለያል።

ከየካቲት 1966 አንስቶ የገጠር መሬት አዋጅ እስከታወጀበት እስከ የካቲት 1967 ድረስ፣ በመኢሶንና በኢሕአፓ መካከል ሰፊ የትንተና፣ የትግል ስልት ልዩነት አልነበረም። በዚህ የአንድ ዓመት ወቅት፣ የሁለቱም ጥሪና ትግል ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም የሚል ነበር። ሁለቱም በኅዳር 1967 የተፈፀመውን የቀድሞ ባለሥልጣናት ግድያና በደርግ ይፈፀሙ የነበሩትን ሌሎች ግድያዎች እና እሥራቶች በአንድ ድምፅ አውግዘው የቆሙበት ወቅት ነበር። የገጠር መሬት አዋጅን በአንድ ድምፅ ደግፈው በአንድ የተሰለፉበት ወቅት ነበር። እንደዚሁም፣ ለመተባበር ሲወያዩ የቆዩበት ወቅት ነበር።

መኢሶን ከመሬት ለአራሹ አዋጅ መታወጅ ጋር በተያያዘ ሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ የተባለውን የትግል ስልት ቀየሰ። በዚህም መሠረት፣ የገጠር መሬትን አዋጅ በሙሉ ኃይሉ ለመደገፍ ተሰማራ። ኢሕአፓም ለጊዜያዊ ሕዛባዊ መንግሥት መቋቋም ያደርግ የነበረውን ጥሪ ለአንድ ስድስት ወራት ያህል አንጠልጥሎ፣ አዋጁን በመደገፍ ተሰማራ። የኢሕአፓ መሪ አባላት የነበሩት ተስፋዬ ደበሳይን እና ዮሴፍ አዳነን ጨምሮ በርካታ ዓባላቱ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር ባልደረቦች ሆነው ነበር። ሌላው የኢህአፓ አባል ዓለምአንተ ገብረ ሥላሴ የሚኒስቴሩ ቋሚ ተጠሪ ነበር። ሌሎች እንደ ይርጋ ተሰማ እና ገብሩ መርሻ ያሉት

---

[2] FSS Discussion Paper፣ Searching Tenure Insecurity፣ 2000

[3] B. Nega, B. Adenew and S. Gebre Sellasie፣ Ethiopian Economic Policy Research Institute፣ 2021

[4] ያሸንፋል እና ያቸንፋል የአካባቢያዊ አነጋገር ስልቶች እንጂ፤ የመኢሶን እና የኢሕአፓ ንብረቶች አይደሉም። ስላልሆኑም፤ ዛሬ እናቸንፋለን የሚለው ሁሉ ኢሕአፓዊ፣ እናሸንፋለን የሚለውም ሁሉ መኢሶናዊ አይደሉም። ላብ አደር/ወዝ አደር የሚሉት ቃላት የሠራተኛውን መደብ ለመለየት የዋሉ ናቸው። መኢሶን እና ኢሕአፓ ከአብዮቱ በፊት የሚጠቀሙትም ላብ አደር የሚለውን ቃል ነበር። በአብዮቱ ወቅት አንድ በዩኒቨርስቲ መምህራን የታተም መዝገበ ቃላት ወዝ አደር የሚለውን ቃል ተጠቅሞ ወጣ። መኢሶን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወዝ አደር ማለት ጀመረ።

የኢሕአፓ አባላትም፤ በጋራ ሙለታ እና በቡታ ጅራ በአስተዳዳሪነት ተሹመው ነበር። በርካታ በኢሕአፓ መሥመር የነበሩ መምሕራን እና ወጣቶች በየዘመቻ ጣቢያው አዋጁን ለማስፈጸም ተሠማርተው ነበር።

ነገሮች ከዚህ አንፃር ቢጤኑ፤ ከየካቲት 1967 እስከ ሐምሌ/ነሐሴ 1967 ድረስ በመካከላቸው የነበረው ልዩነት፣ መኢሶን ሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ የተባለውን የትግል ስልቱን በይፋ ማሳወቁ እና፤ ኢሕአፓ በይፋ አለማሳወቁ ነበር። ነገሮች በእንደዚህ እንዳሉም ነበር፤ ኢሕአፓ በነሐሴ 21፣ 1967 ሕልናውን ይፋ ያደረገው። የከፍተኛ አመራር ለውጥ አድርጎ፤ ብርሃነ መስቀልንና ጌታቸው ማሩን በተስፋዬ ደበሳይ፣ ዘርዑ ክኸሸንና ክፍሉ ታደሰ የተካው።

ከእንግዲህም ጀምሮ ለማለት ይቻላል፤ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር የገጠር መሬት አዋጅን "ከመሠረቱና ከፅንሱ ተራማጅና ተደጋፊ ቢሆንም ...'ያዩት እንጂ አይበሉት ፍሬ' ሆኗል" እያለ አጣጣለው።[5] የዕድገት በኅብረት ዘመቻንም "ከቀድሞም የተማሪዎችን ትግል ከፋፍሎ ለመደምሰስ፤ አንድነቱን ለማፋለስና ከዋናው የፖለቲካ ሥልጣን ዕምብርት ለማሸሽ" የታሰበ ሤራ በማለት ተቃወመው። ከየካቲት 1967 ጀምሮ ለስድስት ወራት ያንጠለጠለውን የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥሪ መልሶ አነሳ። ወጣት ዘማቾች ያደራጇቸውን የገበሬ ማኅበራት እየተዉ ወደ "ዋናው የፖለቲካ ሥልጣን ዕምብርት" (ወደ አዲስ አበባ) እንዲመለሱ ጠራ። የሚመለሰውን ወጣት "ፋሺስት" ያለውን ሥርዓት እንዲታገል አነሳሳ።

አዲሱ የኢሕአፓ አመራር ከሰኔ/ሐምሌ 1968 መጨረሻ ወራት ሲደርስ፣ "ፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝም እና ደርጉ (ያው) አንድም ሦስትም ጠላቶች ናቸው" እያለ፤ "የነዚህ ሦስት ጠላቶች መውደም ግድ ነው" ወደሚለው ትንተናና የትግል ስልት ተሻገረ። ወጣቱን "አንድም ሦስትም" ያላቸውን ጠላቶች እንዲታገል አነሳሳ። በነሐሴ 1968 "ማናቸውም አብዮት የሞትና የግድያ ሂደት ነው" ያለውን "ሂደት" አወጀ። የመጀመሪያዎቹን "የግድያ ሂደት" የፖለቲካ ግድያዎች በመስከረም 1969 ፈፀመ።

ሲጠቃለል፣ 1967 እና 1968 ከፋም ለማም ለመወያየትና ለመተባበር የተሞከረባቸው ዓመታት ነበሩ። ስለዚህም ቢባል ትክክል ይሆናል፤ መኢሶንና ኢሕአፓ በአብዮቱ ዘመን በአተናናተንና በትግል ስልት ዓይነት አጥብቀው የተለያዩት አዲሱ የኢሕአፓ አመራር በተለይም "ለግድያ ሂደት" ከጠራበት ከነሐሴ 1968 አንስቶ ነበር። መኢሶን ከየካቲት 1967 አንስቶ በቀየሰው የሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ የትግል ስልት መሥመር መሠረት ታገለ። ይህም፣ ሕጋዊ ሁኔታዎች እስከፈቀዱና እስካስቻሉ ድረስ የአብዮቱን ወገኖች ንቃትና ድርጅት በማገዝ ለገጠር መሬት አዋጅ መተግበርና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት መታገል ማለት ነበር። ከላይ የተመለከቱት ወቅቶች እየተለዩ ቢመረመሩ፤ ወደዕውነታው ለተጠጉ አረዳዶችና አመለካከቶች መዳበር የሚያግዙ ይሆናሉ።

### "ደርግ አሥራ ሰባት ዓመት ገዛ"

ኮሎኔል መንግሥቱና አንዳንድ የደርግ አባሎች በርግጥም በሥልጣን ላይ ለአሥራ ሰባት ዓመታት ቆይተዋል። ይህ ዕውነታ ሲሆን፤ የሰኔ 1966ቱ ደርግ ለአሥራ ሰባት ዓመታት ሙሉ የሥልጣን ባለቤት አልነበረም። ምክንያቱም፤ በጥር 1969 የደርግ ውስጥ ግጭት ከተካሄደና በደርጉ ውስጥ የነበረው የሙቶ አለቃ ዓለማየሁ ኃይሌ እና የሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል ቡድን ከተወገደ በኋላ፤ ስለደርግ መናገር አይቻልም። ጥር 1969፣ የመንግሥት ሥልጣን ከደርግ እጅ ወጥቶ በአንድ በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አብዮታዊ ሰደድ ድርጅት የተያዘበት ዓመት ነው። አብዮታዊ ሰደድ የተባለው ድርጅት ኢሠፓኮ እና ኢሠፓ እያለ የአንድ ፓርቲ አገዛዝን ለማስፈን የተጓዘበት መንገድ የተከፈተበት ዓመት ነበር። በዚህም ሂሳብ፣ የደርግ ዕድሜ ከመስከረም 1967 እስከ ጥር 1969 ድረስ የነበረው የሦስት ዓመት ዕድሜ ይሆናል። የተቀሩት አሥራ አራቱ ዓመታት፣ የአብዮታዊ ሰደድ፣ የኢሠፓኮ እና የኢሠፓ አንድ ፓርቲ አገዛዝ የሰፈነበት ዓመታት ነበሩ።

---

[5] "የገጠሩ ትግል"፣ ዲሞክራሲያ ቅጽ 2፣ ቁጥር 14፣ ጳጉሜ 4፣ 1967

ኢትዮጵያም በዚሁ፣ በአማካይ ከ1969 ዓ.ም. ጀምሮ በአንድ ፓርቲ አገዛዝ ሥር የምትገዛ አገር ሆናለች። ልዩነቱ፣ ኢሠፓ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ስም ለአሥራ አራት ዓመታት ገዛ። ኢሕአዴግ እና ብልፅግና ፓርቲ የሚባሉት ድርጅቶች፣ በኢትዮጵያ ብሔሮች መብት ስም የአንድ ፓርቲ አገዛዝን ለሠላሳ ሦስት ዓመታት ሙሉ አንግሠው ገዙ። በነዚያ የአርባ ሰባት ዓመታት ዘመን በርካታ አገሮች የአንድ ፓርቲ አገዛዝን አስወግድው የመደብለ ፓርቲ ሥርዓትን መሥርተዋል። የዲሞክራሲ አየርን እየተነፈሱ ዘልቀዋል። ኢትዮጵያ ለዚህ ሳትታደል፣ ሃምሳ ዓመታት ቆጠረች። በተቃዋሚነት የተሰለፉት ድርጅቶቿም፤ እርስ በእርስ ሲጋጩና በየዕለቱ ሲሰነጣጠቁ የኖሩባቸው ዓመታት ሆነው ነጎዱ።

### የደርግ እና የመኢሶን ትብብር ዘመን

ከላይ የተመለከተው ዕውነታ እንዳለ ሆኖ፣ የደርግ እና የመኢሶን ትብብር ዘመን የ17 ዓመታት ዕድሜ እንደነበረው ተደርጎም ይነገራል፤ ይፃፋል። ሁለት ወቅቶች እና ይዘታቸው ባግባቡ ቢለዩ፤ ወደዕውነታው ለመቅረብ የሚቻል ይሆናል።

የመጀመሪያው ፣ ከየካቲት 1967 አንስቶ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እስከወጣበት እስከ ሚያዚያ 1968 ድረስ ያለው የአሥራ አምስት ወራት ወቅት ነበር። መኢሶን በዚህ ወቅት፣ ከደርግ ጋር ቀጥተኛ ትብብር ሳያደርግ፣ ዓባላቱን እና ወዳጆቹን በመሬት ይዞታ አስተዳደር፣ በአገር አስተዳደር፣ በትምህርት እና በግብርና ሚኒስቴሮች እና በዘመቻ ጣቢያዎች ውስጥ አሠማርቶ ለአዋጁ መተግበር ታገለ። ሁለተኛው ወቅት፣ ከሚያዚያ 1968 አንስቶ የትግል ስልት እስከተደረገበት እስከ ነሐሴ 1969 ድረስ ያለው የአሥራ ሰባት ወራት ነበር። መአሶን በዚህ ወቅት፣ በሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ፅ/ቤት ውስጥ ባሠማራቸው ዓባላቱ እና ወዳጆቹ አማካይነት ከደርግ ጋር ተባብሮ ለብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በተግባር መዋል ታገለ። ለማጠቃለል፤ መኢሶን ከደርግ ጋር ለ17 ዓመታት ሙሉ አልተባበረም። ወይንም፣ ከአሥራ ሰባት ዓመቱ የደርግ/ኢሠፓኮ/ኢሠፓ ዕድሜ ጋር ሲተያይ፤ ከደርግ ጋር የተባበረው ስምንት ከመቶ ለሚሆኑ ወራት ብቻ ነው። ዘጠና ሁለት ከመቶ የሚሆኑት ወራት፣ የአብዮታዊ ሰደድ፣ የኢሠፓኮ እና የኢሠፓ ሥርዓተ አገዛዝ የሰፈኑባቸው ወራት ናቸው።

### "መኢሶን የኦሮሞ ድርጅት ነው"

የመኢሶን አባላት እና ወዳጆች በርዕዮተ ዓለም፤ በፖለቲካ ፕሮግራም እና በትግል ስልት መስመሮች ተግባብተው እና ተማምነው በአንድ የተሰባሰቡ ግለሰብ ኢትዮጵያዊያን ስለነበሩ፤ በዚህ ላይ መቆየት አያስፈልግም። የትረካው ምንጭ ግን፤ በአንድ ወገን ስሙ በዛም በዚህ የታወቀው ኃይሌ ፊዳ ከመኢሶን መሪ አባላት አንዱ መሆኑ ነው። ሌላም፣ የመኢሶን አባላት እና ወዳጆች ለገጠር መሬት አዋጅ መተግበር በአብዛኛው የተሠማሩት በደቡብ ኢትዮጵያ መሆኑ ነው። በሌላው ወገን ግን፣ የኢሕአፓ አመራር "ፊዳ፣ ፊዲስት" እያለ ሲነዛ የነበረው ፀረ መኢሶን ቅስቀሳ ውጤት ነው። የአሕአፓ አባላት የነበሩ ታጋዮች አንድ ቀን፤ የኢሕአፓ አመራር "ፊዳ፣ ፊዲስት" እያለ በኃይሌ ፊዳ ላይ ይነዛ የነበረው ዘመቻ አፀያፊ እና ነገደኛ (tribalist) ዘመቻ እንደነበር በይፋ እንደሚያምኑ እና እንደሚያሳውቁ ተስፋ አደርጋለሁ።

# በመኢሶን ላይ የሚቀርቡ ሂሶችን እና አስተያየቶችን በተመለከተ

## ሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ

መኢሶን በጥር/የካቲት 1967 ዓ.ም. ባካሄደው የውስጥ ውይይት የአብዮቱን ተፈጥሮ፣ ሂደት፣ የኃይሎችን አሰላለፍና የኃይል ሚዛን (ጥንካሬና ድክመት) ከገመገመ በኋላ፣ ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ያደርግ የነበረውን ጥሪና ትግል አቆመ። በምትኩ፣ ሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ የተባለውን የትግል ስልት ቀየሰ። ውሳኔውን ያበረታቱት የወቅቱ አውራ ምክንያቶች ባንድ ወገን፣ በየካቲት 1967 የገጠር መሬት አዋጅ ለመታወጅ መቃረቡ ሲሆን፤ በሌላው በኩል አገሪቱ በወቅቱ ትገኝ የነበረበት ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች አሳሳቢነት ነበር።

ባጭሩ ለመከለስ፣ የኢትዮጵያ አብዮት ይመራ የነበረው ባንድ ወገን፣ በአማካይ ከሰኔ 1966 ጀምሮ የሥልጣን ባለቤት በሆነው ደርግ ነበር። ደርግ አምኖበትም ይሁን ተራማጅ የሚባለው ክፍል ያነሳቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ በመፈለግ፤ ሌላም ጊዜ እየተደናገጠና እየተርበደበደ ጭምር ገንቢና አፍራሽ፣ ተስፋ ሰጪና ሥጋት ነገር፣ አልሚና አጥፊ፣ አራማጅና አባካኝ እርምጃዎችን ይወስድ ነበር። ወይንም የአብዮቱ ወዳጆችና ተቃዋሚዎች የሚመሰቃቀሉበትና ነጋ-ጠባ በሚፈፀሙት ግድያዎች፣ እሥራቶችና ውርሶች የጭንቀትና የፍርሃት ድባብ በሰፈኑበት ሁኔታ ውስጥ ነበር።

በሌላ ወገን፣ ከውስጥ የኤርትራ ግንባሮችና አንዳንድ የብሔሮች ድርጅቶች፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢዲሕ) የተባለው የመሳፍንት ድርጅት፣ የቀድሞ የመሬት ባለቤቶች፣ ባላባቶች እና ጉልተኞች፣ ቢሮክራሲውና በለውጡ የተነኩ ማኅበራዊ ክፍሎች አብዮቱን በመቃወም በከፍተኛ ደረጃ በሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ውስጥ ነበር። ከውጭም፣ የጎረቤት አገሮችና የምዕራቡ ዓለም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተቀናጅተው ውግዘታቸውንና ለታጠቁ ድርጅቶች የሚሰጡትን የመሣሪያ፣ የገንዘብና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ባጧጧፉበት ወቅት ነበር። በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ገበሬዎች በሚያካሄዱት የመሬትና የንብረት ውርስ እንቅስቃሴዎች እና ባለመሬቶችን የማባረር ድርጊትም፣ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሥርዓተ አልባ ሁኔታዎች ባቆጠቆጡበት ሁኔታ ውስጥ ነበር።

በመሀል አገርም የፖለቲካ ታሪክ ጀርባቸው ከተማሪ እንቅስቃሴ ትኩሳት ብዙም ያልራቀ እና የፖለቲካ ድርጅት ከመባል እጅግ በጣም ሩቅ የሆኑ ጥቂትና ትናንሽ የምሑራንና የተማሪ ቡድኖች በተጨባጭ ከነበራቸው የድርጅት፣ የፋይናንስ፣ የግኑኝነት፣ የተመክሮና የብስለት ወዘተ. አቅም በላይ፤ ዓቢይ ተዋናዮች ሆነው በወጡበት ሁኔታ ውስጥ ነበር። እነዚያ ጥቂትና ትናንሽ ቡድኖች ለሥልጣን ቀርቶ የአብዮቱን ጭራ ለመያዝ ተቸግረው የነበሩና ከቶም ለመተባበር ያልቻሉ ቢሆንም ቅሉ፤ በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ስም ለሥልጣን ተካፋይነት በሚታገሉበት ሁኔታ ውስጥ ነበር። ደግሞም በውርሶች ጉዳይ ከደርጉ ጋር ከፉክክር ውስጥ የገቡ እስኪመስል ድረስ፤ በመምሕራንና በሠራተኛ ማኅበሮች ስም፣ እንደ አውቶቡሶችና ከባድ የጭነት መኪናዎች፣ የቡናና የአደንጓሬ ላኪ ኩባንያዎች፣ ማተሚያ ቤቶች፣ የመስተዋት ሥራዎች፣ የጫማ ፋብሪካዎች፣ የምግብ ማደራጃ፣ የጭነት መርከብና የአሣ ማጥመጃ፣ ትላልቅ ሆቴሎች፣ ሚስዮናዊያን ሥር ያሉ ሆስፒታሎችና የግል ት/ቤቶች ተወርሰው፣ በሠፊው ሕዝብ ቁጥጥር ሥር መዋል አለባቸው የሚሉ ውሳኔዎችን እያሳለፉ መምሕራንን፣ ሠራተኞችንና ወጣቶችን ለተጨማሪ ውርሶች እንዲታገሉ በሚያነሳሱበት ሁኔታ ውስጥ ነበር።

የአገሪቱ አጠቃላይ ሁኔታ ከላይ እንደተመለከተው ቢሆንም፤ ደርግ የገጠር መሬትን አዋጅ በየካቲት 1967 አወጀ። መኢሶን አዋጁ የሚታወጀው የተመለከቱት ውስጣዊና ውጫዊ ውጥረቶች በሰፈኑበት አሳሳቢና አስጊ አውድ ውስጥ እንደሆነ እና ያገሪቱ ጥቂትና ትናንሽ የምሑራንና የተማሪ ተራማጅ ቡድኖች ለመተባበር ቀርቶ በየቅላቸውም በወጉ ለመደራጀት ባልበቁበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑን አጤነ። ከምንም ምንም በፊት፣ የገጠር መሬት አዋጅን በተግባር መተርጎም የሚያግዝና አገራዊ ኃላፊነትን ያስቀደመ የፖለቲካ መሥመር መከተል እንደሚያስፈልግ አመነ።

የውስጥ ውይይቱ በጥር/የካቲት 1967 ዓ.ም. በሚካሄድበት ወቅት በርግጥም በአንድ ወገን፣ የገጠር መሬት አዋጅ ለመታወጅ መቃረቡ እና፤ በሌላውም ወገን የአረብ አገሮች ለኤርትራ ግንባሮች ያፈሱት የነበረው ድጋፍ መጨመር እና ግንባሮቹ ከባድ ጦርነት መክፈታቸው በመኢሶን ውሳኔ ላይ ከፍተኛ ሥፍራና ተፅእኖ ነበራቸው። መኢሶን የኤርትራ ግንባሮች በዚያ የገጠር መሬት አዋጅ በሚታወጅበት ሰዓት የወሰዱትን ከፍተኛ የማጥቃት እርምጃ የገመገው፤ ፀረ-የኢትዮጵያ ሕዝቦች የለውጥና የአርነት ትግል እርምጃ በሚል ነበር። አጠቃላይ ሁኔታውን አተኩሮ ለተመለከተም፣ የኤርትራ ግንባሮች የኢትዮጵያ አብዮት አንድ እርምጃ ወደፊት ለመሄድ ባቀና ቁጥር፣ ጦርነት ከመክፈትና ትርምስን ለማንበግበግ አንዱን ወይንም ሌላውን ድርጅት ከመጠቀም ሰንፈው እንደማያውቁ ላለማስተዋል አይችልም።

መኢሶን ከተጠቀሱት የወቅቱ ሁኔታዎች በመነሳት፣ ባንድ ወገን የገጠር መሬትን አዋጅ በሥራ መዋል ደግፎ ለመሬት እና ለዲሞክራሲ ለመታገል ተነሳሳ። በሌላውም ወገን ያገሪቱን ደህንነትና ልዕልና ለመጠበቅ ያግዛል/ያስችላል ብሎ ያመነበትን የትግል ስልት ለመትለም ወሰነ። በዚህም መሠረት፣ ሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ በተባለው ስልቱ መሠረት፤ ዓባላቱንና ወዳጆቹን በመንግሥት ተቋሞች ውስጥ ጭምር አሰማርቶ ታገለ። በሌላውም ወገን፣ የዲሞክራሲ መብቶች እንዲለቀቁና የሠፊውን ሕዝብ መንቃትና መደራጀት የሚያግዙ ሕጋዊና ዲምክራሲያዊ መስኮች እንዲሰፉ ታገለ።

ከየካቲት 1967 እስከ ሚያዝያ 1968 ከደርጉ ጋር ቀጥታ ትብብር ሳይፈጥር የገጠር መሬት አዋጁን በመደገፍ ታገለ። አብዮቱ የብሔራዊ ዲሞክራቲክ ጎዳናን እንደሚከተል በሚያዝያ 1968 ይፋ ሲደረግ፤ ተያይዞ በተቋቋመው በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤት እና በየካቲት 66 የፖለቲካ ት/ቤት ውስጥ አባሎቹን በማሠማራት እስከ ነሐሴ 1969 ድረስ ከደርግ ጋር ተባብሮ ሠራ። ይህም በጠቅላላው ለአሥራ ሰባት ወራት ወይንም፣ ስምንት ከመቶ ለሚሆን ጊዜ ነበር። ይልቁኑ፤ ከዚህ አኳያ በንፅፅር መታየትና መመርመር ያለበት መሠረታዊ ጉዳይ ኮሎኔል መንግሥቱ  ከጥር 1969 ዓ.ም. አንስቶ አብዮታዊ ሰደድ/ኢሠፓኮ/ኢሠፓ እያሉ ለአሥራ አራት ዓመታት የሄዱበት መንገድ ነው።

ከተባለው ግልፅ እንደሚሆነው የመኢሶን የሁኔታዎች ትንተናና የትግል ስልት፣

> "የአብዮቱን ዕምብርት ጥያቄና የኢትዮጵያ የግራ ኃይሎች ሕዝቡን የሚያሰባስቡበትንና የሚያታግሉበትን (የመሬት ላራሹ) ጥያቄ ደርግ ቀማቸው።"[6]

በሚል ከተነሳው ከኢሕአፓ አመራር "የተቀማሁኝ" አመለካከት እና የራስ ግንዛቤ የተለየ ነበር።

የኢሕአፓ አመራር፣ ኢዲሕ፣ የኤርትራ ግንባሮችና ሕወሓት በየበኩላቸው "የፋሺስት ሥርዓት ነገሠ" ያሉትን የተዛባ "ትንተና" እያስተጋቡና ሕዝባዊ አብዮት እየተካሄደ/እየተከናወነ መሆኑን በመካድ፤ "ፋሺስቱን" ደርግ ለመታገል ተሰለፉ። መኢሶን በዚያ የመሬት አዋጅ በታወጀበትና ለመሬት ለአራሹ ትግል በሚደረግበት ወቅት እና የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት በደራበት ወቅት፤ ደርጉ "ፋሺስት" ሊሆን ቀርቶ ፤ በምንም ሂሳብ ዓቢይ ጠላት አይደለም የሚለውን አቋም ያዘ። የትብብርና የትግል መስመሩ የግጼታ ከነርሱ የተለየ ሆነ።

ስለአብዮቱ ዘመን ትብብር ሲነገርና ሲፃፍ ግን፤ የወቅቱን ሌሎች ትብብሮችንም ማስታወስ ያስፈልጋል። እነዚያ ትብብሮች አስካልተካተቱና እስካልተመረመሩ ድረስም፤ ማንኛውም ሓተታ የተሟላ አይሆንም። ምክንያቱም፣ በወቅቱ የነበረው ትብብር በደርግና በመኢሶን መካከል ብቻ አልነበረም። ኢሕአፓ፣ ኢዲሕ፣ ሕወሓትና ሌሎች ከኤርትራ ግንባሮች፤ ከሱዳን እና ከሶማሊያ መንግሥታት ጋር የፈጠሯቸው የፖለቲካና ወታደራዊ ትብብሮች ነበሩ። እነዚያ ትብብሮች ለኤርትራ ግንባሮችና ለሌሎቹ የጠቀሙ ሲሆኑ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮትና የሥርዓት-ለውጥ ትግል አሉታዊ ነበሩ።  አንዳንዶች ለማቅረብ እንደሚሞክሩት፤ ትብብሮቹ በእርግጥ "በኢትዮጵያና በኤርትራ ተራማጆች መካከል የነበሩ ናቸው" የሚባል ከሆነ፤ የኤርትራ ግንባሮች ተራማጆች እና የአብዮቱ ደጋፊዎች የነበሩ መሆናቸውን ማስረዳት ያሰፈልጋል። ለታክቲክ ነበር ከተባለም፤ የማንኛውንም

---

[6] ክፍሉ ታደሰ፣ 313፣ (ቅንፍ የተጨመረ)።

ሕዝብ መብትና ጥቅም ከፖለቲካዊ መርሆ እና ፕሮግራም አኳያ የሚታይ እንጂ፤ ከስልት እና ከድጋፍ ፍለጋ አኳያ ብቻ ከሆነ፣ መደላድሉ መቼም ቢሆን የስህተት መንገድ ነው የሚሆነው።

ኢሕአፓ፣ ኢዲሕ፣ የኤርትራ ግንባሮችና በአብዮቱ የተነኩ ሌሎች ክፍሎች የመኢሶንን መሥመር ተቃወሙ። ከውጭ ከመጣ "ፋሺስት" ጠላት ጋር የተባበረ ይመስልም ዘንድ፤ "ባንዳ፣ አድር-ባይ፣ ፍርፋሪ ለቃሚ፣ የፋሺስት ምሑራን ጥርቅም"፥ "ፌዲስት" እያሉ ዘመቱበት። ክፍሉ ታደሰ የኢሕአፓ አመራርን አመለካከት እንደገለፀው፣

> መኢሶን (የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት) አቋሙን ሙሉ በሙሉ ቀይሮ፣ መፈክሩን ተቃውሞ ወጣ። በመኢሶን ላይ (ከቀድሞም) የነበረው ጥላቻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄደ።"[7]

ክፍሉ ታደሰ "ያ ትውልድ" የተባለውን መፅሐፉን ያሳተመው ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይደረግ የነበረው ጥሪ ታሪክ ከሆነ ከሃያ ዓመታት በኋላ፣ በ1985 ዓ.ም. ነው። በመሆኑም፤ ክፍሉ ታደሰ ቢያንስ አንደኛ፣ ስለጥሪው ጭብጥነት እና ሂደት ሂሳዊ ግምገማ ማቅረብ ነበረበት። ሁለተኛ፣ የአሕአፓ አመራር መኢሶን "አቋሙን ሙሉ በሙሉ" የመቀየር መብት እንዳለው አለማወቁ እና አለማክበሩ ስህተት እንደበር ማሳወቅ ነበረበት። ሦስተኛ፣ የኢሕአፓ አመራር የነዛው "የጥላቻ" ፖለቲካ ባስከተለው መዘዝ ላይ ተመልሶ፣ ሂሳዊ ግምገማ ማድረግ ነበረበት።

ይህ በዚሁ ይሁንና፣ እስካሁን ከሰማሁትና ካነበብኩት ውስጥ ክፍሉ ታደሰ በግልፅ ካስታወቀው ከኢሕአፓ አመራር "የጥላቻ" ፖለቲካ ባለፈ እና ከግምትና ከትርጓሜ በተሻገረ፤ ወደወቅቱ ውስጣዊና ውጫዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ተመልሰው የመኢሶንን ትንተናና የትግል ስልት ስህተተኛነት የሚያሳዩ ትችቶች/አስተያየቶች አላገኘሁም። ወጣ ባለ የተሰጡ አስተያየቶች የሚከተሉት ሦስቱ ናቸው። (1) መኢሶን ቢሮክራሲው በአዲስ መልክ ሳይዋቀር ከደርጉ ጋር ተባበረ፤ (2) የመኢሶን ድርጅታዊ ድክመት፤ (3) መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ የሠራ መኢሶን።

## ከቢሮክራሲው ጋር መተባበር

የኢሕአፓ መሪ አባል የነበረው ክፍሉ ታደሰ እንደገለፀው፣ የኢሕአፓ አመራር አመለካከት፣

> "አብዛኞቹን የኢትዮጵያ ተራማጆች፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞችና ጭቁን ብሔረሰቦችን ሲጨቁን ከነበረው እና በአዲስ መልክ ያልተዋቀረው መንግሥት አካል ለመሆን ምርጫቸው ስላልሆነ፤ መኢሶን የመረጠውን ጎዳና ትኩረት ሳይሰጡት ቀሩ። መኢሶን ግን ከቢሮ ከበርቴው እየተባበረ ችግሩን እንዳመጣጡ ሊፈታ ወሰነ"[8]

የሚለው ነበር። የአመራሩን የሁኔታዎች አረዳድ እና አካሄድ ወደቀላል ቋንቋ ሲተረጎም፤ ከሁሉም ከሁሉም በፊት የመንግሥት ሥልጣን ሳይያዝ በፊት ማለት እንደሆነ ከተጠቀሰው ግልፅ ነው። የኢሕአፓ አመራር ግን፣ በ1966 ኢትዮጵያ አውድ ውስጥ ሆነ በየካቲት 1967 የገጠር መሬት አዋጅ በታወጀበት ሁኔታ ውስጥ እና፤ የኤርትራ ግንባሮች ከባድ ጥቃት በከፈቱበት ወቅት፤ እነዚያ አንድ የጋራ በራሪ ወረቀት በወጉ ለማውጣት እንኳን መተባበር የተሳናቸው ጥቂትና ትናንሽ የምሑራንና የተማሪ ቡድኖች ሥልጣን ጨብጠውና የንጉሠ ነገሥቱን ዘመን ቢሮክራሲ አስወግደው "በአዲስ መልክ የሚያዋቅሩት" እንደምንና በነማን እንደነበር አይገልፅም።

እንደዚሁም ደግሞ፤ ወቅቱ ውስጣዊና (የደርጉን ውስጥ ጨምሮ) ውጫዊ አሰላለፎች በከፍተኛ ፍጥነት (አንዳንዴም በየዕለቱ) ይለዋወጡ የነበረበት እና ውዥንብር፣ ስሜተኛነት፤ ራስን በራስ ማግዘፍ እና

---

[7] እንደላይኛው (ቅንፍ የተጨመረ)።

[8] እንደላይኛው፣ 318።

አንዳንዶችም በንፁህ ጥላቻና የንቀት መንፈስ ተሞልተው ጭምር የሚወናኙበት ወቅት እንደነበር አስታውሶ፤ ነባሩ ቢሮክራሲ ስለሚወገድበት እርምጃ የኢሕአፓ አመራርን አማራጭ ሃሳብ ማሳወቅ ነበረበት።

ምክንያቱም፣ የገጠር መሬትን አዋጅ በሥራ ለማዋል የተሄደበት መንገድ በአንድ በኩል ከ60ሺህ የማያንሱ ተማሪዎችን፣ መምሕራንን፣ ተራማጆችንና መለዮ ለባሾችን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በማሠማራት ነበር። በሌላው በኩል፣ የላይኛውን (የወረዳ፣ የአውራጃ፣ የክፍለ አገር አስተዳዳሪዎች፣ ዳኛ) እና የታችኛውን የገጠር ቢሮክራሲ (ምስለኔ፣ ጭቃ ሹም፣ አጥቢያ ዳኛ፣ ገራዳ) ለሕዝቡ በሚቀርቡ እና የአካባቢውን ቋንቋ በሚናገሩ ተራማጅ ምሑራን፣ መምሕራን፣ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት፣ የግብርና ሚኒስቴር እና የኤፒድ ሠራተኞች በመተካት ነበር። የገጠር መሬት አዋጅ በየካቲት 1967 ዓ.ም. ሲታወጅ፤ አስፈፃሚው የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር እንኳን የክፍለ አገር፣ የአውራጃና የወረዳ ቢሮዎች አልነበረውም። ለሕዝቡ የሚቀርቡ የተባሉትን ሠራተኞች ለአገር አስተዳደር እና ለመሬት ይዞታ አስተዳደር ሚኒስቴሮች ለመመልመል ሲካሄድ የነበረውን መሯሯጥና ርብርብ፤ የወቅቱ የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ባልደረቦች ያስታውሳሉ።

የኢሕአፓ አመራር ስለዚህም ቢያንስ፤ እነዚህን ዕውነታዎች አስታውሶ ጥንካሬያቸውንና ድክመታቸውን መገምገም ነበረበት። ሌላም እና በዋናነት ደግሞ ግን፣ አዋጁ በወሳኝነት በተግባር የተተረጎመውን ያህል በተግባር የተተረጎመው በዘማቾች እና በአርሶ አደሮች መካከል በተፈጠረው ኅብረት እንደሆነ ይታወቃል። እስከ 21 ሺህ 500 የሚደርሱ የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ተቋቋመው ነበር። የታህሣሥ 1968 ዓ.ም. የገበሬ ማኅበራት ማጠናከሪያ አዋጅም፤ የገበሬ ማኅበራት ሕጋዊ ሰውነት እንዲኣላቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የደነገገ ነበር። ገበሬዎችን፣ ዘማቾችን፣ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስቴር ሠራተኞችንም፤ እንደዚሁ ለመጀመሪያ ጊዜ የወረዳ፣ የአውራጃና የክፍለ ሀገር አስተዳደር ኮሚቴዎች አባሎች ያደረገ ነበር። የገጠር ሴቶችና ወጣቶች ለየቅል የመደራጀት መብት እንዳላቸው ያወቀ ነበር። የፍርድ እና የጥበቃ ኮሚቴዎችን የማቋቋም ሥልጣኖችን ለገበሬ ማኅበራት የሰጠ ነበር።

ስለነበረም፣ የኢሕአፓ አመራር አሁንም ቢያንስ፣ በዕድገት በኅብረት ጥሪ የዘመቱት ተማሪዎች፣ መምሕራን፣ መለዮ ለባሾች እና የገበሬ ማኅበራቱ የገጠር መሬቱን አዋጅ በመተግበር ረገድ የነበራቸውን ሥፍራና ሚና መመዘን ነበረበት። ከዚህም በተያያዘ፣ አመራሩ ዘማቾች ዘመቻውን እየበተኑ የፖለቲካ ሥልጣን ዕምብርት ወደሆኑት ከተሞች እንዲመለሱ ያደረገው ጥሪ እና ቅስቀሳ፣ ለመብታቸው ይታገሉ ለነበሩት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች የፈየደውን እና ያልፈየደውን ማሳወቅ ነበረበት።

በሌላው በኩል፣ እንደ መኢሶን ስሜተኛነትንና ጥላቻን ለሚከላከልና “ነጭ/ጥቁር” በሚል “የትንተና” ዓይነት ለማይመራ ድርጅት፤ ሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ ያለውን መሥመር ወደ ተግባር መተርጎም የግዴታ ውስብስብ፣ ምስቅልቅልና ውጥንቅጥ ነበር። ደህናውን ከመጥፎው፣ በጎውን ከክፉው፣ ዘላቂውን ከጊዜያዊው ለያይቶ በዚያው ፍጥነት ለማስረዳትና ለመደገፍም ሆነ ለመንቀፍ አስቸጋሪ ነበር። እነዚህ ሁኔታዎችም በራሳቸው፤ የመኢሶንን ሂሳዊ ድጋፍ ከሂስ ይልቅ የድጋፍ እንዲመስል አድርገዋል።

ችግሮቹ ከመጀመሪያው የሚመነጩት ደርጉ ራሱ አንድ-ወጥ አካል ካለመሆኑ ነበር። የደርጉ አባሎች እንደ ውስጣዊው የኃይል ሚዛን አሰላለፍ ይኸኛውን ወይንም ያኛውን የደርግ አውራ የሚከተሉ ነበሩ። እንደ ጊዜያዊው የኃይል ሚዛን ካንዱ ወይንም ከሌላው ጋር እየወገኑ እርስ በርስ የሚጋጩና የሚጠፋፉ ነበሩ። በሌላው ወገን ከታች በምሁራኑና በተማሪው ቡድኖች ጥያቄዎች፣ ከላይ ደግሞ በቢሮክራሲው ምክረ ሃሳቦች መካከል ተወድረው የሚዋዥቁ ነበሩ።

ደግሞም አንዳንድ አባሎቹ፣ የአዲሕና የኤርትራ ግንባሮች ዝንባሌዎች ያሏቸው ነበሩ። አንዳንዶቹም ከደርጉ በየጊዜው እየተለዩ አዲሕንና የኤርትራ ግንባሮችን የሚቀላቀሉ ነበሩ። የኢሕአፓ አመራርም፣ ደርጉን “ፋሺስት” እያለ በደርግ ላይ ውጭ ውጪን ይዝመት እንጂ፤ ከደርጉ አመራር መካከል አንዳንዶቹ የራሱ የኢሕአፓ አባላት ነበሩ።  በተጨማሪም ደግሞ፣ በተለይ ሁለት ሁኔታዎች ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ ነበሯቸው።

አንደኛ፣ “የባንዳዎችን ፅሑፎች አታንብቡ፤ ያሳስቷችኋል” እስከማለት ድረስ ዘልቆ ይስፋፋ የነበረው የወቅቱ የኢሕአፓ አመራር ቅስቀሳ የሌላውን የፖለቲካ አቋምና መሥመር አበክሮ የማወቅና የመረዳት ሕሊናን ደፍኗ። በአፅናፋዊ ነጭ/ጥቁር አመለካከት መካከል ያለውን ሠፊ የግራጫ ሕብር አጨለመ። እንዲያም ሲል የፖለቲካ ሜዳውን በፈጠራ ወሬዎችና በስም ማጥፋት ቅስቀሳዎች በከለ። በጥርጣሬና በጥላቻ መንፈሶች ጠቀጠቀ። ሌላው ጠላት ተደርጎ የሚፈረጅበትን ግጭት ነገር ፖለቲካ አስፋፋ። በዚህ አኳያ ሌላው ሌላው ቀርቶ መወያየትን ለማስቻል የተከፈቱት ሕጋዊ መድረኮች ሳይቀሩ (የውይይት ክበቦች፣ የመንግሥት ጋዜጦች፣ ራዲዮና ቴሌቪዥን...) ተጨማሪ የጥላቻና የግጭት ነገር ፖለቲካ ማራመጃ መሣሪያዎች ሆነው አረፉ። በኢትዮጵያ የሜዲያ ታሪክ ውስጥ ግን፣ የመንግሥት መገናኛ ዘዴዎች እንደዛን ዘመን ለግልጽ ውይይት ክፍት ሆነው በይፋ የተለቀቁበት ዘመን አልነበረም።

ወደታሪክ ብንመለስ፣ የመጀመሪያው የ1920ው ዓ.ም. የአፅምሮ እና የብርሃንና ሰላም ዘመን ነበር። ይኸኛው፣ ራስ ተፈሪ ወደ አፄነት ባደረጉት ጉዞና ከ1928 ዓ.ም. የፋሺስት ጣሊያን ወረራ ጋር በተያያዘ ተዳፈነ። ሁለተኛው፣ በኢትዮ/ኤርትራ ፌዴሬሽን ዘመን በኤርትራ ይወጡ የነበሩት የነፃ ጋዜጦች ዘመን ነበር። ይኸኛው፣ ፌዴሬሽኑ ሲፈርስ አከተመ። ሦስተኛው፣ በ1968 የተከፈቱት የመወያያ መድረኮች ነበሩ። እነሱም፣ እንዲወያዩ የተጋበዙት በውል ሳይጠቀሙምባቸው ያባከኗቸው እና ለመከሰማቸው የራሳቸውን አስተዋፅኦ ያበረከቱላቸው የታሪክ አጋጣሚ ሁነው በአጭር ጊዜ ተዳፈኑ።[9]

ባጭሩ የወቅቱ የ“አታንብቡ” የጥርጣሬ ቆስቋሽና የጥላቻ ነገር ዘመቻዎች የትንተና እና የመሥመር ልዩነቶችን የማወቅ ሕሊናን ደፈኑ። በተለይም የወጣቱን ክፍል በዕውቀት ላይ ከተመሠረተ ይልቅ፤ የስማ-በለው ፖለቲካ ተከታይና የቅፅሎች አራጋቢ አድርገው አወናኙ። መኢሶን ወደ ወጣቱ አካባቢ ለመድረስ ያደርግ የነበረውን ጥረት እጅግ አስቸጋሪ አድርጎት የነበረው አንድ ሁኔታም፤ እነዚያ የኢሕአፓ አመራር በሠፊው ይነዛቸው የነበሩት የጥርጣሬ እና የጥላቻ ቅስቀሳዎች ነበሩ። አንዳንድ የኢሕአፓ አባል የነበሩ ከዛ ዘመን ጥላቻ እስከዛሬም ድረስ ያልተላቀቁ መሆናቸውን ሳደምጥ፤ በእጅግ እገረማለሁ። ሁለተኛው ሁኔታ ከየካቲት/መጋቢት 1969 በኋላ ከደረሱት መሠረታዊ የኃይል ሚዛን ለውጦችና መኢሶን ትብብሩን ለማቋረጥ ካደረገው ውሳኔ ጋር ይያያዛል። ዝቅ ሲል ባጭሩ እመለስበታለሁ።

## ድርጅታዊ ድክመት

በዚህ አኳያ፤ በመጀመሪያ የሚሰጠው አስተያየት፡-

> “(የመኢሶን ሂሳዊ/ገንቢ-ድጋፍ) ስትራቴጂ... ከሁሉም በላይ የመነጨው፣ መኢሶን የኢሕአፓን ያህል የወጣቱንና የሠራተኛውን መደብ ለመስረግ ስላልቻለ ይሆናል።”[10]

የሚለው የፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ አመላካከት ነው። ይህንን አስተያየት ወደቀላል ቋንቋ ብንተረጉመው ‘መኢሶን የኢሕአፓን ያህል ወጣቱን እና የሠራተኛውን መደብ ለመስረግ ስላልቻለ፤ በአድርባይነት ደርጉን ተጠጋ’ ማለት ይሆናል። ይሁንና፣ ፕሮፌሰር ባሕሩ አስተያየታቸውን የመሠረቱበትን አጥጋቢ ትንተና በጭራሽ አላቀረቡም።

ፕሮፌሰር ባሕሩ ስለስትራተጂ ከተናገሩ አይቀር፣ አብዮቱ በአገሪቱ መደቦችና የፖለቲካ ኃይሎች ረገድ ስላስከተለው ለውጥና የስትራተጂ ጉዳይ መተንተን ነበረባቸው። እንደዚሁም በወቅቱ የነበሩት የአገሪቱ አጠቃላይ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ይጠይቅ ስለነበረው ስትራተጂ እንጂ፤ ስለመኢሶን “ደካማነት” እና ስለኢሕአፓ ‘ጠንካራነት’ ማተት አልነበረም። ዞሮ ዞሮ፣ የገጠር መሬት አዋጅ የታወጀው በደርግ ነበር።ለአዋጁ መተግበር በእጅግ የደከሙትም ወጣት ዘማቾች እና የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ነበሩ። ፕሮፌሰር ባሕሩ

[9] ከዚያም ወዲህ፣ በኢሕአዴግ የፖለቲካ ጨጉላ ወቅት፣ በ1997 የምርጫ ቅስቀሳ ወራት እና በ2010ሩ የለውጥ ወቅት የዲሞክራሲ ጭላንጭሎች ፈንጥቀው ነበር። ይሁንና እነዚህም በየተራ እየተዳፈኑ፣ ለአንድ ብቸኛ ፓርቲ እና ለጥቂት ግለሰብ መሪዎች ሥልጣን-ገነን (authoritarian) አገዛዝ ሥፍራቸውን ለቀቁ።

[10] ባሕሩ ዘወዴ፣ The Quest for Socialist Utopia፣ 2014፣ 277-78 (ትርጉም የኔ)።

ስለዚህም፤ ደርግ በዚያ ወቅት ዓቢይ ጠላት እንደነበር ማስረዳት ነበረባቸው። ከዚህ በላይ እንደተመለከተውም፣ የአሕአፓን አመራር "ወደ የፖለቲካ ሥልጣን ዕምብርት" ጥሪ እና ቅስቀሳ አስታውሰው፤ ሂሳዊ ዳሰሳ ማድረግ ነበረባቸው።

ሁለተኛ፤ ስለኢሕአፓ "ወጣቱንና የሠራተኛውን መደብ (በሠፊው) መስረግ" ካነሱ ደግሞ፤ ፕሮፌሰር ባሕሩ ይህንኑ በጭብጥ ማስረጃ ማስደገፍ ነበረባቸው። ወይንም የገጠር መሬት አዋጅ በየካቲት 1967 በታወጀበት ወቅት በኢትዮጵያ ምድር የነበሩትን የፖለቲካ ቡድኖች ተጨባጭ ድርጅታዊ ሁኔታና አቅም በዝርዝር አቅርበው፤ ኢሕአፓ ከከተማ ወጣት ተማሪዎች ባለፈ፤ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አርሶ አደሮችና በፋብሪካ ሠራተኞች ውስጥ የነበረውን የድርጅታዊ ጥንካሬ ጭብጥ ማሳየት ነበረባቸው። ለምሳሌ ያህል፣ ክፍሉ ታደሰ አብዮቱ በፈነዳበት ወቅት "ተራማጅ" የሚባሉት "ከ800 የማይበልጡ" እንደነበሩ ይገምታል። በእጅግ የተጋነነ ግምት ነው ብለን እንለፈውና፤ ክፍሉ ቀጥሎ እንደሚገልፀው፣

"800ዎቹ ቢያንስ በአሥራ ሁለት (የተለያዩ) ቡድኖች" የተደራጁ ነበሩ።"[11]

ይህ በሌላ አባባል ሲገለፅ፣ እያንዳንዱ ቡድን በአማካይ ከ65 የሚበልጡ አባላት አልነበሩትም ማለት ይሆናል። የአንዳንዶቹም አባላት ምናልባት፣ ከ5 እና 10 የማይበልጡ ምሥጢራዊ የፖለቲካ ጥናት ህዋሶች እንደነበሩ አያጠያይቅም። ሌሎቹም እንዳመቸ አልፎ አልፎ እየተገናኙ የሚወያዩ የወዳጆች ክበብ ዓይነት ነበሩ። ነገር ግን እነዚሁ በሕቡዕ መሰባሰብ ከጀመሩ የ5 ዓመት ዕድሜ እንኳን ያስቆጠሩ አልነበሩም። ከመካከላቸው የድርጅት "ጋዜጣ" የነበራቸውም፤ ከሁለት/ሦስት አይበልጡም ነበር። በክፍሉ ታደሰ ሂሳብ "ጋዜጣ" ነበራቸው የሚባሉትም "ከ400 ቅጅ በላይ የሚያሰራጩ አልነበሩም።"[12] በዚህ ላይ በትንተና፣ በመሥመር፣ በትግል ስልትና በግለሰብ ደረጃ ጭምር ልዩነቶች የነበሯቸው ነበሩ። ይህንን "በወጣቱና ሠራተኛው መደብ (በሠፊው) የሠረገ" ብሎ በዕርግጠኝነት ለማለት ይቻላልን?

በዚህ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ነበር፤ እነዚያ ጥቂትና ትናንሽ የምሑራንና የተማሪ ቡድኖች ዓቢይ ተዋናዮች ለመሆን የበቁት። ለዚህ የበቁት ግን አንድም፤ ከላይ የነበሩት የገዢ መደቦች ከሕዝባዊው የለውጥ ጥሪና ትግል ፊትና ከሠራዊቱ ማፈትለክ ፊት ተከፋፍለው ባጭር ጊዜ ውስጥ በመፍረክረካቸው ነበር። ከታችም ብሔራዊ/አገራዊ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የፖለቲካ ክብደት የነበረው ከፍተኛና መካከለኛ መደብ ሰላልነበር ነው። በሌላም በኩል ለሥልጣን ባለቤትነት የበቃው ደርግ፣ ግልፅ የፖለቲካና የርዕዮተ-ዓለም ጎዳና ያልነበረው ስለነበር ነው። በመጨረሻም፣ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ዝና በመታገዛቸው ነበር።

ነባራዊው ሁኔታ ይህ ሆኖ ሳለ አንዱ ወይንም ሌላው ቡድን በዚህኛው ወይንም በዚያኛው ማኅበራዊ ክፍል ውስጥ በይበልጥ ስለመሥረቱ ለመናገር የሚቻል አይደለም። ጭብጡም የሚያመለክተው በ1966/67 የሁሉም ቡድኖች አባሎች በአብዛኛው ጥቂት ተማሪዎች፣ አንዳንድ ምሑራን፣ መምሕራንና አንዳንድ የመንግሥት ተቀጣሪዎች እንደነበሩ ነው። በ1968/69 ዘመን በርግጥ፣ በተሻለ እየደረጁ መጥተው ነበር ለማለት ይቻላል። ይህም ሆኖ ግን ቡድኖቹ በዚህ በተሻለ በተደራጁበት ዘመን ባደረጉት ትንተና፣ በቀየሱት የፖለቲካ መሥመር፣ በአደረጃጀት፣ በተከሉት የትግል ስልትና በገቡበት ትብብር የፈየዱትና ያልፈየዱት ሊመረመር ይገባል።

ነገር ግን የኢትዮጵያን አብዮት በሚመለከት የደርጉን ግፎችና ኢሰብዓዊ ድርጊቶችን በማተት ብቻ ለመቋጨት መሞከርም ከዕውነታው የራቀ ይሆናል። የደርጉ ግፎችና ኢሰብዓዊ ድርጊቶች መወገዝ ያለባቸው ቢሆኑም፤ ዘመኑ ስሜቶችን ዋጥ አድርጎ በሰከነ ምሁራዊ ትንታኔ እንዲቃኝ ያስፈልጋል። ይህ እስካልሆነ ድረስ፤ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ አብዮት በሕዝባችንና በአገራችን የነበረውን ሥፍራ በትክክል ለማስቀመጥ የሚቻል አይሆንም። የታሪክ ቀዳዳ ይፈጠራል። አንዳንድ ከፍሎች ባጠቃላይ ስለኢትዮጵያ ታሪክም ሆነ ስለ ድህረ-1983 ኢትዮጵያ የሚያደርጉት በስሜቶች እና በጥላቻ የተመላ "ትንተና" የተመለከተው የታሪክ ቀዳዳ እየሰፋ

[11] ክፍሉ ታደሰ፣ ያ ትውልድ፣ 1991፣ ቅፅ 1፣ 179።

[12] እንደላይኛው፣ 232።

እንዲሄድ የራሱን አስተዋፅኦ እያደረገ ነው። ለሰከነ አካዳሚያዊ እና ምሁራዊ ትረካ ከፍተኛ ጥረት እንዲደረግ የሚቀርበውን አገራዊ ጥሪ አሳንሶ ለማቅረብ አይቻልም።

***መፈንቅለ-መንግሥተኛ***

የመኢሶንን ስልት "መፈንቅለ-መንግሥተኛ" አድርገው ከሚተቹት መካከል የመጀመሪያው ዶ/ር በረከት ሀብተሥላሴ ናቸው።[13] ከዚያም ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ "ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በእንግሊዝኛ ባቀረቡት ፅሁፍ ውስጥ እንደሚከተለው ፅፈዋል።

> "እሱ (መኢሶን) በየዋህነት በሱ የአዝጋሚ መፈንቅለ-መንግሥት ዘዴ (ሌላው ደርግ በ1966 የሄደበት አዝጋሚ ዘዴ መሆኑ ነው) ደርጉን ለመተካትና በመጨረሻም ሥልጣን ለመያዝ ተስፋ አድርጎ ነበር።[14]

ዶ/ር በረከት እና ፕሮፌሰር ባሕሩ ስለመኢሶን መፈንቅለ-መንግሥተኝነት በተመሳሳይ በማንሳተቸው እንጂ፤ ሁለቱስ ባንድ ትንፋሽ ሊነሱ የሚገባቸው ሰዎች አይደሉም። ዋና ዓላማቸው የኤርትራ ግንባሮችን ማስተናገድ የነበረው ዶ/ር በረከት ስለኢትዮጵያና አብዮቷ በዋቢነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ሰው አይደሉም። ዶ/ር በረከት በንጉሠ ነገሥቱና በደርግ ዘመን በኢትዮጵያ ምሑራንና በመንግሥት ጉያ ውስጥ ከትመው፤ የኢትዮጵያ ተማሪዎችንና ወጣቶችን ለአተራማሽ ድርጊቶች ሲገፋፉ የኖሩ ሰው ነበሩ። በኋላም፣ ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራን (ሕግሓኤን) ተቀላቅለዋል። በአስተያየታቸው ያስተጋቡት የተለመደውን የኤርትራ ግንባሮች ፀረ መኢሶን ዘመቻ ነው ተብሎ ሊታለፍ ይችላል። ፕሮፌሰር ባሕሩ ታላቅ የታሪክ ተመራማሪና መምህር ናቸው። በብዙ በተዋጣላቸው ጥናቶቻቸው የዘመናዊት ኢትዮጵያን ታሪክ ያሳወቁንና ያስተማሩን ምሁር ናቸው።

ሆኖም ስለመኢሶን መፈንቅለ-መንግሠተኝነት የሰነዘሩት አስተያየት ወይ ከሰነዶች ያለዚያም ከቃለ መጠይቅ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በተገኙ መረጃዎች ተደግፎ የተሰጠ አይደለም። እንደዚሁም መኢሶን ከነማን ጋር ሲያሤር እንደነበርና ምን እንደሠራ የሚያሳውቅ አይደለም። ትምህርት ሰጪ ይሆን የነበረው፣ የአስተያየቱ ባለቤቶች "ንቃት፣ ድርጅት፣ ትጥቅ" የሚለው የመኢሶን "የረጅም ጉዞ" አካሄድ የመፈንቅለ-መንግሥት ሤራ የሚሆንበትን ምክንያት ቢያስረዱ ነበር። ኢሕአፓ ከነሻምበል ሞገስ እንስቶ በመለመላቸው የደርግ አባላት የጥር 1969ኙን መፈንቅለ መንግሥት ሞክሮ እንደነበርም ማስታውስ እና አስተያየታቸውን መስጠት ነበረባቸው። የመኢሶን ስልት አንደኛው ውጤት በሚያዝያ 1968 የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም መታወጅና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤት መቋቋም ነበር። ይህ የተካሄደው በግላጭና በአዋጅ እየተነገረ ሆኖ እያለ፣ የመፈንቅለ-መንግሥት ሤራ ተደርጎ የሚተረጎምበትን ምክንያት ቢያሳውቁ ነበር።

ከዚሁ በተያያዘ ሕጋዊ መስኮች ተከፍተው ነበር/አልነበረም? ከተከፈቱ መጠቀም ይገባል/አይገባም? ከተገባ የወቅቱ ተራማጆች በውል ተጠቅመውበታል/አልተጠቀሙበትም? የሚሉትንና ተመሳሳይ ጥያቄዎችን እያቀረቡ ቢተነትኑ ነበር። በመጨረሻም፣ የኢሕአፓ አመራር በአንጃነት የፈረጃቸው የኢሕአፓ መሪ አባላት ትንተና እና ስልት ከመኢሶን ትንተና እና የሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ ስልት ጋር ተመሳሳይነት አለው። የአስተያየቱ ባለቤቶች ይህንንም ጉዳይ አስታውሰው ማነፃፀር/ማመሳከር ነበረባቸው። በዚህ ምክንያት በኢሕአፓ ውስጥ የደረሰውን መከፋፈልንና መገዳደልንም አስታውሰው፤ ማተት ይገባቸው ነበር።

**የኢማሌድኅ አባል**

አንዳንዶች "መኢሶን ወደ ደርጉ እንዲጠጋ በይበልጥ የተገፋው በኢሕአፓ አመራር ግድያ ምክንያት ነው" ይላሉ። ይህ አስተያየት የነበረውን ውጥረት እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ የሚገልፅ ቢሆንም፤ የኢሕአፓ አመራር ግድያ ለኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ድርጀት ኅብረት (ኢማሌዲኅ) መፈጠር ዓቢዩ ምክንያት አልነበረም። አይደለም። ምክንያቱም፣ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤት አባል በነበሩት የፖለቲካ

---

[13] በረከት ሀብተሥላሴ፣ Conflict and Intervention in the Horn of Africa፣ 1980፣ 45።

[14] ባሕሩ ዘውዴ፣ 2008፣ 435 (የኔ ትርጉም። ቅንፎች የተጨመሩ)።

ድርጅቶች መካከል ስለትብብር ጉዳይ መወያየት የተጀመረው የኢሕአፓ ግድያ በመስከረም 1969 ከመጀመሩ በፊት፣ በግንቦት/ሰኔ 1968 ነበር። ትብብሩን አጣዳፊና አስገዳጅ ያደረጉት አውራ ምክንያቶችም፣ የወቅቱ ውጫዊ እና የደርጉ ውስጣዊ ሁኔታዎች እንጂ፤ የኢሕአፓ አመራር ይፈፅማቸው የነበሩት ግድያዎች አልነበሩም።

ወቅቱ አገሪቱ በአንድ በኩል፤ የሱዳኑ ኑሜሪ፣ የሶማሊያው ዚያድ ባሬና የአረብ አገሮች ለኢዲሕና ለኤርትራ ግንባሮች የሚሰጡትን ድጋፍ አጠናክረው የቀጠሉበት ወቅት ነበር። የኢዲሕ ጦርና የኤርትራ ግንባሮች ተጠናክረው የተንቀሳቀሱበት እና በርካታ ጥቃቶችን የፈፀሙበት ወቅት ነበር። ዚያድ ባሬ ለወረራ ያኮፈኮፈበት ወቅት ነበር። በሌላው በኩል፣ ኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ የተባለውን ድርጅት ካቋቋሙበት ከግንቦት/ሰኔ 1968 አንስቶ፤ በኮሎኔል መንግሥቱ እና በደርግ ውስጥ የኢሕአፓ አባላት በነበሩት በመቶ አለቃ ዓለማየሁ ኃይሌ እና ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል ፊናዎች መካከል ሽኩቻ እያቀነቀነ እና ከዕለት ዕለት በይበልጥ እየሻከረ የሄደበት ወቅት ነበር።

በአጭሩ ለማስታወስ፣ አብዮታዊ ሰደድ በግንቦት/ሰኔ 1968 ከኮሎኔል መንግሥቱ ሰዎችና ከወዝ አደር ሊግ አባሎች ተውጣጥቶ ተመሠረተ። እነመቶ አለቃ ዓለማየሁን ጨምሮ አብዛኞቹ የደርግ መሪ አባላት መሥራች አባል ሆኑ። “ድርብ አባል” ተብለው ይታወቁ ነበር። ይሁን እንጂ፤ ኮሎኔል መንግሥቱ የሊቀ-መንበርነቱን ሥፍራ ለራሳቸው ሲይዙ፣ እነመቶ አለቃ ዓለማየሁን እና ሻምበል ሞገስን “በደርጉ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ አላችሁ” በማለት ከአብዮታዊ ሰደድ አመራር አገለሏቸው። በነርሱ ፈንታ ለርሳቸው ታማኝ የሆኑትን መለዮ ለባሾችና የወዝ አደር ሊግ አባሎችን የአብዮታዊ ሰደድ ድርጅታቸው መሪ አባሎች አድርገው አስቀመጡ። ቀደም ሲል ጀምሮ የኢሕአፓ አባላት የነበሩት መቶ አለቃ ዓለማየሁ እና ሻምበል ሞገስ ኢሕአፓን ወደመካብ እና በግላጭ ወደመደገፍ ተሻገሩ። በዚህ ረገድ ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት፤ ቀደም ሲል ጀምሮ የኢሕአፓ አባል የነበሩት ሻምበል ሞገስ ነበሩ።

የኢሕአፓ አመራር ቀደም ሲል ጀምሮ የመኢሶንን ስም ሲያጠለሽ እና “ጠረባ ቡድን” ይባሉ በነበሩት ቡድኖቹ አማካይነት የመኢሶንን ወጣት አባሎችና ወዳጆች ሲያስደበድ ነበር። በነሐሴ 1968 “የግድያ ሂደት” ብሎ ያወጀውን የፖለቲካ ግድያ በመስከረም 12፣ 1969 በኮሎኔል መንግሥቱ ላይ ባደረገው የግድያ ሙከራ ለኮሰ። በመስከረም 16 እና 21 ገብረ እግዚአብሔር ተስፋይ፣ አቡበከር አብዱልመጂድ፣ ክንፈ አስፋው፣ ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድ እና ጌታቸው እንግዳ የተባሉትን የመኢሶን አባሎች ገደለ። “የግድያ ሂደቱን” ዓመቱን በሙሉ እየፈፀመ ቀጠለበት።[15] በደርጉ ውስጥ አፍቃሪ ኢሕአፓ የነበሩት የነጀኔራል ተፈሪ በንቲ እና የኢሕአፓ አባላት የነበሩት የመቶ አለቃ ዓለማየሁ እና የሻምበል ሞገስ ክፍሎች እንቅስቃሴም፣ በአማካይ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ በደርጉ እና በሠራዊቱ ውስጥ እየገፋ ሄደ።

መኢሶን አደጋውን ለመከላከል በመጀመሪያ ሁለቱንም የደርግ ቡድኖች በማነጋገር ፍጥጫው ወደ ግጭት እንዳይሻገር ጣረ። ሆኖም ቡድኖቹ በጥርጣሬ የሚተያዩና በዕልህ የተያያዙ ስለነበር እና በተለይም የነመቶ አለቃ ዓለማየሁና ሻምበል ሞገስ ክፍል የኢሕአፓን አመራር ራስን በራስ አግዛፊ ፕሮፓጋንዳ ያመነና በአሸናፊነት መንፈስ ጭምር የተሞላ ስለነበር፤ ውጥረቱን ለማርገብ የተደረጉት ሙከራዎች ፍሬ አልባ ሆኑ።

የፅ/ቤቱ አባል ድርጅቶች (መኢሶን፣ ኢጭአት፣ ወዝ አደር ሊግና ማሌሪድ) እና አብዮታዊ ሰደድ የተባለው ኮሎኔል መንግሥቱ ድርጅት ተወካዮቻቸውን ሰይመውና የኅብረት ኮሚቴ የተባለውን ኮሚቴ በሐምሌ 1968 አቋቋሙ። ገባ ወጣ ከነበር የዘጠኝ ወራት ውይይት በኋላ፣ የመጀመሪያው የኅብረት ኮሚቴ የጋራ ስብሰባ በጥር 22፣ 1969 ተካሄደ። “የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ኅብረት” (ኢማሌድኅ) የተባለው ድርጅት ከስድስት ወራት ተከታታይ ውይይቶች በኋላ፤ በሐምሌ 12፣ 1969 በይፋ ተቋቋመ። ዛሬ ተመልሼ ሳገናዝብ፣ የነዚያ የአሥራ አምስት ወራት የኅብረት ውይይት ጉዳይ ብዙ ጥያቄዎችን ያጭርብኛል።

[15] ጓደኞች፣ የመኢሶን ሰማዕታት፣ 2016

አንዳንድ የመኢሶን አባሎች "ኢማሌድኅ በማይመጣጠኑ ኃይሎች መካካል የተፈጠረ ኅብረት ነበር" የሚል ሂስ ያቀርባሉ። ነባራዊውን ሁኔታ የሚያንፀባርቅ ሂስ በመሆኑ፤ መሠረት ያለው ሂስ ነው ብዬ አምናለሁ። ኢማሌድኅ የተፈጠረው በርግጥም ተመጣጣኝ ጡንቻ ባልነበራቸው የፅ/ቤቱ አባል ድርጅቶች ባንድ በኩል እና፤ በሌላው በኩል ሥልጣንን በያዘውና የቢሮክራሲውን፣ የሠራዊቱን፣ የፖሊሱንና የፀጥታውን ክፍሎች መሠረት አድረጎ እየተደራጀ በመጣው በኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ መካከል ነበር። በዚህም ላይ የኃይሉን ሚዛን ወደ ኮሎኔል መንግሥቱና አብዮታዊ ሰደድ ሠፈር የደፉ መሠረታዊ ለውጦች ባጭር ጊዜ ውስጥ እየተከታተሉ በደረሱበት ወቅት ነበር።

የጥር 1969 የደርጉ ውስጥ ትንቅንቅ በኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ ወገኖች የበላይነት ሲዘጋ፣ የደርግ ዕድሜ እያበቃና በኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድና የወዝ-አደር ሊግ ድርጅቶች ድርብ አባሎች እየተተካ የሄደበት ዘመን ተከፈተ። ብዙም ሳይቆይ ወዝ አደር ሊግ እና ማሌሪድ የተባሉት ድርጅቶች ባንድ በኩል እና የሲቪልና ወታደራዊ ቢሮክራሲው በሌላ በኩል ለኮሎኔል መንግሥቱ አጎበደዱ። የሱማሌን ወረራ ተንተርሶ የሶሻሊስት አገሮች ከፍተኛ ድጋፍ መጉርፍ ጀመረ። አብዮታዊ ሰደድን በይበልጥ ያጠናከረ ሁኒታ ሰፈነ። ኮሎኔል መንግሥቱ "የአብዮቱ ማዕከል"፣ "ቪቫ መንግሥቱ" ከሚባሉበት ምዕራፍ ውስጥ ተገባ። ኮሎኔሉም፣ ራስን በራስ አግዛፊ ከሆነው የማንአህሎኝነት ባሕር ውስጥ የተዘፈቁበት ምዕራፍ ተከፈተ። በዚሁም ለማለት ይቻላል፤ ከቀድሞም "በማይመጣጠኑ ኃይሎች መካካል የተፈጠረው ኅብረት" ይበልጥ ያጋደለ ሆኖ አረፈ።

መኢሶን "በደርጉ ውስጥም ይሁን በመለዮ ለባሹ ውስጥ ያሉት ኃይሎች ሠልፋቸውን ለይተው የሚፋጠጡበት ወቅት በርግጥ ይመጣል" የሚል ግንዛቤ የነበረው ቢሆንም፤ የማይቀረው የደርጉ ውስጥ ትንቅንቅ በዚያ ፍጥነት ይደርሳል የሚል ግመት አልነበረውም። የሱማሌ ወረራ ያንን የሚያክል የውጭ ኃይሎች መግባትን አስከትሎ ሚዛኑን በእጅግ ያዛባል የሚል ግምትም አልነበረውም። ግምቱ እንደውም "ዋነኛው የመፈንቅለ መንግሥት አደጋ የሚመጣው በሲአይኤ ተቀነባብሮ፣ በቢሮ ከበርቴው ላይ ተመሥርቶ፣ ሌሎች አድሃሪ ኃይሎችን አጠቃሎ ከሚካሄደው ፀረ-አብዮት ትግል ነው" የሚል ነበር።

እያደር፣ የሕዝብ ድረጅት ጉዳይ ጊዚያዊ ፅ/ቤት አባል የነበሩት ድርጅቶች ከታች በኢሕአፓ አመራር "የግድያ ሂደት" እና ከላይ ደግሞ ባሸናፊው የኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ ቡድን የሚመቱበት ሁኔታ እየሰፈነ መጣ። መኢሶን፣ በበቂ የደረጀ ኃይል ሳይሆን ተገኘ። በቀላሉ ተጠቃ።

### የሶማሊያ ወረራ

የመኢሶን መሥራች እና ሁለተኛ ዋና ፀሐፊ የነበረውን ዶ/ር ወርቁ ፈረደን[16] ጨምሮ አንዳንዶች፣ መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ ያደረገበት ጊዜ የኤርትራ ግንባሮችና ኢዲሕ ከፍተኛ ጥቃት የከፈቱበት፣ ሱማሊያ ጦሯን አሰርጋ ወረራ የጀመረችበት እና የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት የተጠናከረበት ወቅት መሆኑን በማስታወስ፤ ጥሩ ጊዜ እንዳልነበር ያመለክታሉ። ይህ በመሆኑም መኢሶን "ፈርጣጭ" ለሚለው ፀረ-መኢሶን ፕሮፓጋንዳ እንደተጋለጠ ያሠምራሉ።

ወቅቱ የሚጠይቀው በርግጥም ከመለያየት ይልቅ ለአብዮቱ፣ ለአገር አንድነት፣ ልዕልናና ክብር ተባብሮ መቆምንና መታገልን ነበር። መኢሶንም ሁኔታውን አገናዝቦ በተለይም ኅብረትንና ትብብርን፣ የጦርነቱን አመራርና ስልት፣ መሣሪያ ስለማግኘት፣ የብሔሮችን መብትና የኤርትራን ጥያቄ፣ ብሔራዊ ነፃነትንና ራስን መቻል በሚመለከቱ ጉዳዮች በርካታ ሃሳቦችን አቅርቦ ነበር። መሣሪያ ስለሚገኝበትም፣ ወደ ቪየትናምና ቻይና በመሄድ፤ አገሮቹን ለማግባባት የተለያዩ ጥረቶችን አድርጎ ነበር።[17]

---

[16] ወርቁ ፈረደ፣ ዕድገት ብሎ ውድቀት፣ የወታደር ሶሻሊዝም፣ 1985፣ 132።

[17] በዚህም መሠረት እንቅስቃሴዎች ተጀምረው ኃይሌ ፊዳ የተካተተበት አንድ ቡድን ወደ ቪየትናም ሄዶ ነበር። ወደ ቪየትናም በመጀመሪያ የተሄደው "ቪየትናም ከአሜሪካ የተማረከ በርካታ መሣሪያ አላት፤ የኢትዮጵያም ሠራዊት የሰለጠነው በአሜሪካን መሣሪያ ነው" የሚል አስተሳሰብ ስለነበር ነበር። ሆኖም በሽያጭም እንኳን ሳይገኝ ቀረ። ቀጥሎ፣ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ የተሳተፈበትን ቡድን ኮሎኔል መንግሥቱ መርተው

ወደ ታጠቅ ጦር ሠፈር ለሥልጠና የገባውን ሕዝባዊ ሠራዊት በመመልመልና በማጓጓዝ ረገድ ከፍተኛውን ድርሻ ያደረገውም መኢሶን ነበር። ኃይሌ ፊዳ በእሥር ዘመኑ ለመርማሪዎቹ በሰጠው ቃል እንደገለፀው፤

> "የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ሊቀ መንበር የመጀመሪያውን የእናት አገር ጥሪ ባደረጉበት ጊዜ፣ መኢሶን ጥሪውን በሚገባ እንደሚደግፈውና አባሎቹ በያሉበት ቦታ ሁሉ አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት በሚለው መፈክር ሥር ተሰልፈው ለመዋጋት ተዘጋጅተው ነበር።"

ነገር ግን በድኅረ ጥር 1969 የሥልጣን ባለቤት የሆኑት ኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት" ቢሉም ቅሉ፣ ዋና ጭንቀታቸው የሥልጣናቸው ጉዳይ ነበር። ስለሆነም ኃይሌ ፊዳ ቀጥሎ እንደሚገልፀው፤

> "በተለይም የሕዝባዊ ሠራዊት ምልመላ በተደረገበት ወቅት የእኛ ጓዶች ከተመልማዮች ጋር ታጠቅ ጦር ሠፈር ገብተው ለመሠልጠንና አብረው ለመዝመት ዝግጁነታቸውን ሲገልፁ፤ ከጦር ሠፈሩ እንዳይገቡና አስረክበው እንዲመለሱ ተገደዋል። በተጨማሪም በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤት በኩል የመኢሶንም ሆነ የሌሎች ድርጅቶች ካድሬዎች በሕዝባዊው ሠራዊት ውስጥ ከላይ እስከታች በፖለቲካ ካድሬነትና በመሪነት የሚገቡበትን መንገድ ለጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በፅሑፍ አስታውቀን ነበር።
>
> "… እኔ ራሴ በግሌ ለሊቀ መንበሩ ባቀረብኩት የፅሑፍ ማስታወሻ ውስጥ፣ ካድሬዎች ሠራዊቱን በድርጅት አንፃር እንዳይከፋፍሉ ራሱን የቻለ መመሪያ ሊወጣ እንደሚችልና ከመመሪያው ውጭ ለመሥራት የሞከረ ካድሬ ሁሉ የዲሲፒሊን እርምጃ ሊወሰድበት የሚቻል መሆኑን ጠቁሜ ነበር። ነገር ግን ሃሳቡ ተቀባይነትን አለማግኘቱ ግልፅ በሆነ መንገድ፣ መኢሶንን ከአብዮታዊ ትግሉ የማግለል አዝማሚያ ሆኖ ታይቶናል። ይህ እየታወቀ፣ በኅብረት ድርጅቶች አካባቢ መኢሶን በጦርነቱ ለመሳተፍ አይፈልግም የሚል ዘመቻ ተካሂዶብናል።"

ኮሎኔል መንግሥቱ የወሰዱት እርምጃ መኢሶንን ከሕዝባዊው ሠራዊት የማግለል ብቻ አልነበረም። የአብዮታዊ ሰደድንና የወዝ አደር ሊግ አባሎችን አሰልፈው "መኢሶን የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤትን በሞኖፖል ይዟል"፤ "አበጠ"፣ "ሌላው ኢሕአፓ ነው"፤ "መመታት አለበት"፤ "እንመታለን" እያሉ በግልፅ የሚቀሰቅሱና በመኢሶን አባሎች ላይ ግድያ የሚያስፈፅሙ ነበሩ።[18] ኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ/ወዝአደር ሊግ የበላይነት ከውስጥና ከውጭ ተደራርበው ባደረሱት ፈጣን የአሰላለፍ ለውጦች እየተጠናከረ የሄደውንም ያህል፤ የድርጅት ነፃነትን ጠብቆ በትብብሩ ለመቀጠል የሚያስችሉ ሁኔታዎች በዚያው ፍጥነት እየሟሸሹ ሄዱ። አሁን "የአብዮቱ ማዕከል" የሆኑት ኮሎኔል መንግሥቱም፣ ኢማሌድኅ የቆመባቸውን መሠረቶች ጭምር ወደ መናድ አመሩ።

"መኢሶን የትግል ስልት ያደረገው፣ በሞኖፖል የያዘውን የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ለመልቀቅ ስላልፈለገ ነው" እያተባለም በመኢሶን ላይ ተዘምቶ ነበር። ኃይሌ ፊዳ ለመርማሪዎቹ በሰጠው ቃል እንዳሳወቀው ግን፡-

> "(መኢሶን) የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤትን በሞኖፖል ይዞታል' የሚለው ቅሬታ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰነዘረው በሰኔ 1968 ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በበኩላችን የፅ/ቤቱ መዋቅር የሚለወጥበትን መንገድ ስንፈልግ ቆይተን በመጨረሻ በጥር 1969 ዓ.ም. የመጀመሪያው የኅብረት ኮሚቴ ስብሰባ ሲደረግ የነበረንን አስተሳሰብ ለማቅረብ ችለናል። በጥር 28፣ 1969 ለኅብረቱ አባል ድርጅቶች ባቀረብነው መዋቅር ውስጥ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ሙሉ በሙሉ በኅብረቱ ቁጥጥር እንዲሆን ጠቁመን፤ ይኸው ተቀባይነትን አግኝቶና አዋጅ ወጥቶ ተከናውኗል።"

---

ወደ ቻይና ተጓዙ። ቻይና ካንድ መርከብ ክላሺንኮቭ በላይ የማትሰጥ መሆኗን አስታውቃ አቆመች። ኮሎኔል መንግሥቱም "ይህማ የቤተ-መንግሥት ደጃፍ ለመጠበቅ እንኳን አይበቃም" ብለው ተመለሱ።

[18] ጓደኞች፣ የመኢሶን ሰማዕታት፣ 2016

ኮሎኔል መንግሥቱ በዚያ በሶማሊያ ወረራ ወቅት ግራ ክንዳቸውን እየሰቀሉ “አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት” ቢሉም፤ በዚያው ወቅት ውሎ አድሮ የሥልጣኔ ተቀናቃኝ ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ያሰቧቸውን ድርጅቶች እና ሲቪልና መለዮ ለባሾች ሁሉ በቀኝ ክንዳቸው የሚደቁሱና የሚያጠፉ ነበሩ። ለዚህም የሶማሊያ ወረራ እና ወረራውን አስታኮ የጎረፈው የውጭ ድጋፍ በእጅጉ ጠቀሟቸዋል።

የውጭ ኃይሎች በመሣሪያ ድጋፍ፣ ባማካሪነት፣ በሠራዊት ሥልጠና፣ በፀጥታ ማደርጀት፣ በፋይናንስና በፓርቲ ግንባታ ያጠናከሯቸውን ያህል፣ የኢትዮጵያን ሃቀኛ አገር ወዳዶችና የለውጥ አራማጆች አጥፍተው በ“አብዮታዊ መሪያችን” እና “ቪቫ መንግሥቱ” አሸርጋጅ ካድሬዎችና የ“እሺ ጌታዬ” “ይቻላል ጌታዬ” ቢሮክራቶች መካብን መረጡ። እዚህም ላይ ሦስት ጉዳዮች መታወስ ይኖርባቸዋል።

አንደኛ፤ ከላይ ስለቢሮክራሲው የተባለው በንፁሕ ያገር ፍቅር አቋም ለኢትዮጵያ አብዮትና ሉዓላዊነት ሙያዊ አገልግሎታቸውን ያበረከቱትንና ሕይወታቸውን ጭምር የሰጡትን ቴክኖክራቶች፣ ቢሮክራቶች፣ መለዮ ለበሾችና ምሑራንን እንደማይመለከት ግልፅ ማድረግ ይኖርብኛል። ሁለተኛ፣ በባሮ ቱምሳ ይመራ የነበረው እና የፅ/ቤቱና የኢማሌድኅ አባል የነበረው የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል (ኢጭአት) ከጥቂት ወራት በኋላ የትግል ስልት ለውጥ አደረገ። በአባሎቹ ላይ ግድያና ከፍተኛ የእሥር ስቃይ ተፈፅመበት። ሦስተኛ፣ ለኮሎኔል መንግሥቱ “ማዕከልነት” አጎብድደው ትንሽ ከተጓዙት የማሌሪድና የአብዮታዊ ሰደድ/ወዝአደር ሊግ አባሎች መካከል ጥቂት የማይባሉትም፤ የኮሎኔል መንግሥቱ ግድያና እሥራት ሰለባ ሆነዋል። እነዚህኞቹ ሰለባ የሆኑት ግን፤ “አብጠው” ወይንም ትብብራቸውን ሰላቋረጡ አልነበረም። አንዳንዶቹ ያጎበደዱበት ልክ ኮሎኔል መንግሥቱንና አንዳንድ የወዝ አደር ሊግ መሪዎችን ስላላጠገበ ነበር። ሌሎቹም የመንግሥት ሽብር አገልጋይነት ዘመናቸው በማብቃቱ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ መኢሶን የነበረው ምርጫ ወይ እንደ ወዝ አደር ሊግ እና ማሌሪድ የኮሎኔል መንግሥቱን “ማዕከልነት” ተቀብሎ ለኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ ማጎብደድ ነበር። ያለዚያም የትግል ስልት ለውጥ ማድረግ ነበር። መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ ማድረግን መረጠ። በነዚያ በየካቲት-መጋቢት ወሮች የመኢሶን መሪ አባሎች ነጋ ጠባ የምንወያየው ስለትግል ስልት ለውጥ ነበር። ይልቁኑም፤ የኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ ጥቃት ሳይቀድመን ‘ምን ይደረግ?’ በሚለው ጥያቄ ላይ እንጂ፤ ስለኢማሌድኅ መሳካት/አለመሳካት አልነበረም።

መኢሶን በመጋቢት 1969 ልዩ ብሔራዊ ኮንፈራንስ በሚስጢር አደረገ። የትግል ስልት ለውጥ ለማድረግ ወሰነ። አያይዞም የመሸጋገሪያ ስልት ቀየሰ። ዋና ዋናዎቹ (ሀ) “የማፈግፈጊያና የሽምቅ ትግል ለመጀመር የሚያስችሉ አምባዎች ማዘጋጀትና ማደራጀት፣ (ለ) ትብብሩ በይፋ እስከሚቋረጥ ድረስ በኢማሌዲኅ ውስጥ የሚደረገውን ተሳትፎ መቀጠል፣ (ሐ) ግጭቶችን ከወዲሁ ከሚጋብዙ አድራጎቶች መታቀብ” የሚሉት ነበሩ።

መኢሶን ከደርጉ ጋር የነበረውን የአሥራ ሰባት ወራት ትብብር በነሐሴ 14፣ 1969 አቋረጠ። ይሁንና፣ የሕቡዕ አገባቡ በበቂ የተዘጋጀ አልነበረም። ስለዚህም በአባሎቹ እና ወዳጆቹ ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ጥቃትን ያስከተለበት ነበር። ለዚህም ዋናው ምክንያት ከላይ እንደተመለከተው፣ መኢሶን በትብብሩ ወቅት ከፍተኛ የአመራር እና ሌሎች በርካታ አባሎቹን በሕጋዊ መስኮች ማሠማራቱ ነበር። የአብዮቱ ፍጥነት፣ የአገሪቱ ትልቅነት፣ የተቋሞቿ ብዛት፣ የሰው ኃይል ዕጥረት ወዘተ. ዋና አስረጂ ምክንያቶች የነበሩ ቢሆኑም ቅሉ፤ አሠራሩ ዙሮ ዙሮ የድርጅቱን የሕቡዕ አካል የይፋው ክፍል ጥገኛ ያደረገና ያዳከመ ነበር። በርካታ አባሎቹን ይፋ አውጥቶ ለጥቃት ያጋለጠ ነበር።

ስለነበረም፤ ከመስከረም እስከ ነሐሴ 1969 ባለው ጊዜ ውስጥ ብዙ አባሎቹና ወዳጆቹ የኢሕአፓ አመራር “የግድያ ሂደት” ላለው የፖለቲካ ግድያ ቀላል ዒላማዎች ሆኑ። ሕቡዕ በተገባ በጥቂት ቀኖች ውስጥ ደግሞ፤ በከተሞችና በገጠር እየታደኑ ተገደሉ፤ ሌሎች ታሰሩ፤ ተገረፉ። ከእስር ቤት እየተወሰዱ ተረሸኑ። በሕጋዊ ትግል ርብርቦሽ የሰለለው የመኢሶን የሕቡዕ ኃይል፣ የደረሱትን ጥቃቶች ተሸክሞና ቁስሉን አድርቆ በትግሉ ለመቀጠል የሚያስችለውን የሰውና የማቴሪያል ኃይል አጣ። የመኢሶን አመራር የትግል ስልት ለውጡን

በማዘጋጀትና በማስፈፀም ረገድ ስህተቶችን ፈፅሟል። የአመራሩ የጋራ ስህተቶች ነበሩ። እዚህም ላይ፣ ሁለት ጉዳዮችን ማመልከት ይገባኛል።

አንደኛ፣ መኢሶን ለኢትዮጵያና ለሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነበረውን ጥሩ ሕልም ይዞና የአዕምሮው አድማስ እስከፈቀደለት ድረስ የየወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ከስሜት ውጭ እየተነተነ ለመታገል ጣረ። በተከፈቱት ሕጋዊ መስኮች ተጠቅሞ የሠፊው ሕዝብ ማኅበራት (የገበሬዎች፣ የሠራተኞች፣ የከተማ ኗሪዎች፣ የወጣቶች፣ የሴቶች) የፖለቲካ ንቃት እንዲጎለብትና ተጠናክረው እንዲደራጁ አገዘ። ለመሬት ላራሹ እና ለዲሞክራሲ፣ ለብሔሮች ዕኩልነት፣ ለብሔራዊ ነፃነትና ለራስን በራስ መቻል፣ የኤርትራ ጥያቄ በፖለቲካዊ መንገዶች እንዲፈታና ወዘተ. ታገለ። የተደራረቡ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ባሳረፉት ጫናና በራሱ ጉድለቶች ምክንያት ጭምር ከግቡ ሳይደርስ ቀረ።

ይሁንና ሁለተኛ፣ ሽንፈት ሁልጊዜም ስህተተኛነትን የማያሳየውን ያህል፤ አሸናፊነትም ሁልጊዜ ትክክለኛነትን አያሳይም። ወይንም ሰዎች የጥረታቸውን ፍሬ ባያገኙ ጥረታቸው ፍፁም ስህተት ነበር አያሰኝም። ለመርሆ መቆም፣ በስነ-ምግባር መመራት፣ ፅናት፣ ድፍረት፣ ሕሊናን አለመሸጥ፣ አገር ወዳድነትና ለሠፊው ሕዝብ መወገን ሌሎች መታየት የሚገባቸው መመዘኛዎች ናቸው። ካርል ማርክስ እንዳለው፣

> "ሰዎች የራሳቸውን ታሪክ ይሠራሉ። ሆኖም እንደፈለጉትና እንዳማራቸው አይሠሩትም። ታሪክን የሚሠሩት ካለፈው ተላልፎና ተወርሶ በሠፈነው ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ሁነው እንጂ፣ እነሱ በመረጧቸው ሁኔታዎች ውስጥ ሁነው አይደለም።"

# ስለመኢሶን ትብብር

መኢሶን ከደርግ የተባበረው "በአድርባይነት እና ፍርፋሪ ለመልቀም ነው" እየተባለ የሚነገርውን እና የሚፃፈውን፣ ተራ ወሬ ብሎ ማለፍ ይቻላል። ዛሬ ዛሬ "የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ሽፋን ሆኖ ለማገልገል ነው" እየተባለ የሚወራውም፣ እንደዚሁ ተራ ወሬ ነው። ከነዚህ ወጣ ባለ የሚሰጡት አስተያየቶች ከዚህ በላይ ተታውሰዋል። ሁሉንም አተኩሮ ያጤነ ግን፣ ሁሉም አስተያየቶች ትብብሩን አስፈላጊ ያደረጉትን የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታዎች እና ደርግ ትብብሩን ለማስቻል የወሰዳቸውን እርምጃዎች አካተው የማይነግሩ እና የማይፃፉ መሆናቸውን ላለመገነዘብ አይቻልም። ተደጋግሞ እንደተመለከተው እንዲያውም፤ የ1966ን ሕዝባዊ አብዮት ምንነት እና ሂደት በየወቅቱ አውድ ውስጥ ከትቶ እና በማስረጃዎች አስደግፎ ለመዳሰስ የሚደረገው ጥረት አነስተኛ መሆኑ ነው።

በሚቀጥለው፣ በየወቅቱ ነባራዊ ሁኔታዎች እና ዕውነታዎች ላይ በአጭሩ ተመልሼ አትታለሁ። አያይዤም፣ የደረግን እና የመኢሶንን ትብብር ባስቻሉት የደርግ እርምጃዎች እና ውጤቶቹ ላይ በአጭሩ እመለሳለሁ። የወቅቱ ሁኔታ ምን ነበር? በደርግ እና ለፅ/ቤቱ አባልነት በተጠሩት የመኢሶን አባላት መካከል የተካሄዱት ውይይቶች እና ድርድሮች ምን ነበሩ? ደርግ ለትብብሩ አመቺ ሁኔታዎችን ለማስቻል ምን እርምጃዎችን ወሰደ? ምን ውጤቶች ተገኙ?

### የ1967 መጨረሻ እና የ1968 መጀመሪያ

የ1967 መጨረሻ እና የ1968 የመጀመሪያ ወራት በአንድ ወገን በደርግ እና በከባድ የውጭ ድጋፍ በተንቀሳቀሱት የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ሕብረት (ኢዲሕ) እና የኤርትራ ግንባሮች መካከል ከባድ ውጊያዎች የተካሄዱበት ወራት ነበሩ። በሌላውም ወገን፣ በደርግ እና "ሠፊው ሕዝብ መሪ ድርጅቱን አግኝቷል" በማለት ሕልውናውን በነሐሴ 1967 ባወጀው የኢሕአፓ አመራር መካከል በከባድ የተፈጠጡባቸው ወራት ነበሩ። ከተሜው፣ የትግራዩን ልዑል ራስ መንገሻ ስዩምን፣ የጎንደሩን ጀ/ል ነጋ ተገኘን፣ ቢትወደድ አዳነን፣ የጎጃሙን ቀኛዝማች ስሜነህን፣ ግራዝማች አየለ ቸኮልን እና አጣናው ዋሴን፣ የአፋሩን ቢትወደድ አሊ ሚራሕን እና የልጃቸውን ሓንፍሬን፣ የወሎውን ደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ደስታን እና በመንዝም የወንድማማቾቹን መርዕድ ብሩን እና መሥፍን ብሩን፣ ከበስተደቡብም የመናገሻውን ደጃዝማች ከበደ ብዙነሽን እና ከሲዳሞም

የሻምበል ተፈራ ቸርነትን "የደቡብ አንበሳ ጦር" እየቆጠረ ሲያትት፤ የደርግ መስተዳደር "አንድ ሐሙስ" የሚከርም የመሰለበት ወቅት ነበር።

ኢዲሕ በተለይም ከጂዳው ስብሰባው በኋላ በጎጃም እና በጎንደር ወደ ተጠናከረ ወታደራዊ የትጥቅ እርምጃዎች ተሸጋግሮ ተንቀሳቀሰ። በጎንደር በከፈተው ጦርነት ከፍተኛ እንቅስቃሴዎችን ሲያሳይ እና የክፍለ አገሩ አስተዳዳሪ የነበሩትን አቶ በዛብህ ገብሬን ሲገድል፤ በጎጃም (ብቸና) ከፍተኛ ጦርነት ተካሂዶ ብዙ ሰው አለቀ። ደርግም፣ ከወልዲያ ወደ ጎንደር የሚወስደውን መንገድ በመሥራት ላይ የነበሩትን ወደ 300 የሚጠጉ ቻይናውያን ከአካባቢው እስከማሰወጣት ድረስ ይገደዳል። የሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሕግሓኤ/ሻቢያ) ጦር፣ በአስመራ ይገኝ የነበረውን የቃኘው ጦር ሠፈር መስከረም 2 ዕለት አጠቃ። ዘጠኝ ሰዎች ሲሞቱ፣ ብዙዎች ቆሰሉ። ሁለት አሜሪካኖችን እና ስድስት ኢትዮጵያውያንን ጠልፎ በመውሰድም፤ ለጥቃቱ ዓለም አቀፋዊ አድማስ ሰጠው። ከኤርትራ ግንባሮች መሀከል ሁለቱ ደግሞ (የአብደላ እድሪስ ኢ.ኤል.ኤፍ ሬቮሉሽናሪ ካውንስል እና የኦስማን ሳላህ ሳቤ ኢ.ኤል.ኤፍ.-ፒ.ኤል.ኤፍ/ጀበሓ) ከነሐሴ 27 እስከ ጳጉሜ 1፣1968 ዓ.ም. በካርቱም ባደረጉት የጋራ ስብሰባ፣ ድርጅቶቻቸውን ለማዋሀድ የተስማሙ መሆናቸው ያሳውቃሉ።

ይህ በእንደዚህ እንዳለ፣ የኢሕአፓ አመራር "ፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝም እና ደርግ አንድም ሦስትም ናቸው። የእነዚህ ጠላቶች መውደም የግድ ነው" ያለውን "ትንተና" ይዞ ወጣ። ዘማቾች የዘመቻ ጣቢያዎችን እየዘጉ ወደ "ዋናው የፖለቲካ ዕምብርት" ወደ አዲስ አበባ እንዲጎርፉ እና "ፋሺዝምን" እንዲታገሉ ጠራ። በኢሕአፓ አመራር ተይዞ የነበረው የመምህራን ማኅበር ፅ/ቤት ከነሐሴ 25 እስከ ጳጉሜ 4 ባካሄደው ዓመታዊ ጉባዔው የደርጉን ፀረ-ዲሞክራቲክ ድርጊቶች ካወገዘ በኋላ፣ "ለጥያቄዎች አስቸኳይ መልስ ካልተሰጠው መምሕራን ጠቅላላ የሥራ ማቆም እርምጃ ለመውሰድ የወሰኑ መሆናቸውን" አወጀ። ሌላው፣ በኢሕአፓ አመራር ተይዞ የነበረው የኢሠአማ ፅ/ቤትም፣ ከመስከረም 8 እስከ 11ባደረገው ጉባዔው "የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ እስከ አንድ ወር ጊዜ ድረስ መፍትሔ ካላገኘ፣ አስፈላጊውን እርምጃ የምንወስድ መሆናችንን እናረጋግጣለን" እያለ አወጀ።

ደርግ መስከረም 12፣ 1969 ዕለት በርካታ መምሕራንን በማሰር መለሰ። የአየር መንገድ ሠራተኞች ማኅበር ፀሐፊ መስከረም 14 ቀን የኢሠአማን ውሳኔ በማሰራጨት ላይ እንዳለ ተያዘ። ሠራተኛው የመሪውን መታሠር በመቃወም ግልብጥ ብሎ ወጣ። የደርግ ፀጥታ ኃይል በሠራተኞቹ ላይ የተኩስ እሩምታ ከፈተ። 7 ሠራተኞች ሲሞቱ፣ ከ30 የማያንሱ ቆሰሉ። አስከትሎ የኢሠአማን ፅ/ቤት ዘጋ። በየሥራ ድርጅቶች እና በየሠፈሩ እየሄደም ሠራተኞችን፣ ሥራ አጦችን እና የሚጠረጠሩ የተባሉ ግለሰቦችን በብዙ መቶ እያፈሰ አሠረ።

ድርግ መስከረም 19፣ 1968 ዓ.ም. ዕለት በአዲስ አበባ እና በአካባቢዋ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አወጀ። ት/ቤቶችን ዘጋ። የፀጥታ ኃይሉ "ሠላምን በሚያደፈርስና በሥራ ማቆም እርምጃ ላይ በሚሳተፍ በማንኛውም ሰው ላይ ተገቢውን እና የመጨረሻውን እርምጃ ለመውሰድ (ማለትም ለመግደል ጭምር) የሚችል መሆኑን" አወጀ። እንደዚሁም "መኖሪያ ቤቶችን እና መሥሪያ ቤቶችን ወዘተ. ያለአንዳች ማስጠንቀቂያ ለመፈተሽ እንደሚችል እና ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ያላንዳች ፍርድ ሊያሥር እንደሚችል" ደነገገ። ወረቀት የተባለን ነገር እንኳን የፃፈ፣ ያዘጋጀ እና ያሠራጨ ቀርቶ፤ ሲያነብም የተገኘ እርምጃ የሚወሰድበት መሆኑን አሳወቀ። የመስከረም 19 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በኅዳር 25 እስከተነሳበት ጊዜ ድረስም፣ በመላው ኢትዮጵያ ከባድ የጭቆና ቀኖች ተቆጠሩ። በአዋጁ ሰፍኖ የነበረው ጥቁር ደመና መግለጥ የጀመረው፣ ደርግ በኅዳር 1968 አዋጁን ካነሳ በኋላ እና፤ በኅዳር/ታኅሣሥ ወራት የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤትን ለማቋቋም የተጋበዙት ምሑራን ለተሳትፏቸው ያቀረቡትን ቅድመ ሁኔታዎች ከተቀበለ በኋላ ነበር።

**የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ፅ/ቤት መቋቋም**

በነዚያ አምስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወራት፣ አንዳንድ የደርግ መሪ አባላት ውጥረቱን ለመወጣት የሚቻለው ከተራማጅ ምሑራን ጋር በመተባበር መሆኑን በማመን ውስጥ ውስጡን ሲሠሩ ቆይተው ነበር። በዚህ አኳያ ከፍተኛ ሚና የተጫወተውም፣ ገና ከሰኔ/ሐምሌ 1967 ጀምሮ "ከፍተኛ የሕዝብ አደራጅ ኮሚቴ" በሚል ስያሜ ተቋቁሞ የነበረው ኮሚቴ ነበር። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መነሳት እና በሚያዝያ 1968 ዓ.ም. የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ፅ/ቤት መቋቋም በመጀመሪያ ደረጃም፣ የዚህ የከፍተኛ አደራጅ ኮሚቴ የሥራ ፍሬ ናቸው። ኮሚቴው፣ 7 የደርግ አባሎች እና 4 ሲቪል ሚኒስትሮች የሚገኙበት ነበር። እነሱም ከደርጉ አባሎች መሀከል ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ ኮሎኔል አጥናፉ አባተ፣ ሻለቃ ብርሃኑ ባይህ፣ መቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ፣ ሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤል፣ ሻምበል ደምሴ ዱሬሳ እና ንጉሴ ረጋሳ ሲሆኑ፤ ከሚኒስትሮች መሀከል ልጅ ሚካኤል ዕምሩ፣ አቶ ተካልኝ ገዳሙ፣ አቶ ዘገየ አስፋው እና ዶ/ር ኃይለ ገብርኤል ዳኜ ነበሩ።

ኮሚቴው ወደ ጥቅምት 1968 ላይ ከሦስት መደምደሚያዎች ላይ ደርሶ ወደ ድርጊት ተሻገረ። መደምደሚያዎቹ:-

ሀ) ተራማጆችን የሚያስተባብር የፖለቲካ ፕሮግራም መውጣት እንዳለበት፤

ለ) በተራማጅ ምሑራን የሚመራና ከሞላ ጎደል ነፃ የሆነ ቢሮ ማቋቋም እንደሚያስፈልግ እና ለዚህም፤

ሐ) ከተራማጅ ምሑራን ጋር ውይይት እንደሚያስፈልግ የሚሉት ነበሩ።

ተራማጅ ምሑራንን ስለመጋበዝ እያንዳንዱ የኮሚቴው አባል በግል የሚያውቃቸውን ሰዎች ስም እንዲያቀርብ እና ከዚያም ከኮሚቴው የተውጣጣ የሦስት ሰዎች ቡድን እያንዳንዱን ዕጩ በግል በማነጋገር ፈቃደኝነቱን እንዲጠይቀው ተወሰነ። ሦስቱ አነጋጋሪዎች ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ መቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ እና ልጅ ሚካኤል ዕምሩ ነበሩ። ለኮሚሽኑ የቀረበው የስም ዝርዝር ስንት እንደነበር በትክክል አይታወቅም። አንዳንድ ስሞችም በተደጋጋሚ ሳይቀርቡ አልቀረም። ቡድኑ እንዲያነጋግራቸው የተወሰነው የምሑራን ብዛት 67 ይደርስ እንደነበር ግን፣ ይታወቃል።

በአደራጅ ኮሚቴውና በተራማጁ ምሑራን መሀከል የተከፈተው ውይይት በኅዳር/ታሕሣሥ1968 ዓ.ም. ወራት ተካሄደ። የውይይቱ ውጤት ከተጋበዙት ምሑራን መሀከል 15 ምሑራን ፅ/ቤቱን እንዲያቋቁሙ መጠየቃቸው ነበር። እነዚህም ከነፖለቲካ ቤተሰባቸው የሚከተሉት ነበሩ። ከመኢሶን ኃይሌ ፊዳ፣ ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድ፣ ዶ/ር ከድር መሀመድ፣ መስፍን ካሱ እና ዶ/ር ነገደ ጎበዜ፤ ከኢጭአት አቶ ባሮ ቱምሳ፤ ከኢሕአፓ ዶ/ር ዮናስ አድማሱ፤ ከወዝ አደር ሊግ ዶ/ር ሠናይ ልኬ እና ሸዋንዳኝ በለጠ፤ ከየትኛውም ድርጅት ውስጥ ያልነበሩ ዶ/ር እሸቱ ጮሌ፣ ዶ/ር መለስ አያሌው፣ ዶ/ር አሰፋ መድኅኔ፣ አቶ ተስፋየ ሸዋየ፣ ዶ/ር በዛብህ ማሩ እና አቶ ወንድወሰን ኃይሉ ነበሩ። ይሁንና ወደኋላ ዶ/ር እሸቱ ጮሌና ዶ/ር ዮናስ አድማሱ ከፅ/ቤቱ ራሳቸውን አሰናብተው ተለዩ። የመኢሶን አባል በነበሩት ዶ/ር ንግስት አዳነ እና ዶ/ር ዓለሙ አበበ ተተኩ። ሌላም የአፋር ነፃነት ንቅናቄ መሪ አባል የነበረው አቶ ዩሱፍ ያሲን የፅ/ቤቱ አባል ሆኗል። እንደዚሁም ከኢህአፓ የአሲምባ ጦር ተለየተው በኋላ ማሌሪድን ያቋቋሙት የተስፋዬ መኮንን ቡድን አባላት በፅ/ቤቱ ሥር ተካተዋል።

የኢሕአፓ አመራር "የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ በሕብረት ግንባር ላይ ያለው አቋም" በሚል እስከ ነሐሴ 1968 ዓ.ም. ድረስ ባወጣቸው የዲሞክራሲያ ቅጽ 3 ተከታታይ ዕትሞች (ሁሉም ቀን የሌለባቸው):-
"ለአብዮቱ ከባድ ኃላፊነት አለብን። አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ የሚያስችል፣ ለአብዮቱ ዕድገት የጋት ታህል እንኳን መንገድ የሚከፍት ሁኔታ ከተፈጠረ ያንን መርምረንና እምነታችንን ሳንለቅ በዛ ሁኔታ ለመጠቀም መሞከር በአብዮቱ ውስጥ የምንጫወተው ሚና የጣለብን ግዴታ ነው"

ብሎ የነበር ቢሆንም፤ በፅ/ቤቱ ሕይወት ውስጥ ሳይሳተፍ እና የበኩሉን አስተዋፃኦ ሳያደርግ ቀረ። መኢሶን ግብዣው የተደረገላቸው የመኢሶን አባላት ስም ዝርዝር እንደታወቀ፣ የጠቅላይ ኮሚቴው ስብሰባ ተጠራ። ስብሰባው በአንድ ወገን፣ ንቅናቄው ግብዣውን ሊቀበል በሚያስቸሉት የትብብር ሁኔታዎች እና፤ በሌላም ወገን ተግባራዊ በሆኑ የአቀራረብ እና የአሠራር ጥያቄዎች ላይ ከተወያየ በኋላ፤ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አሳልፎ ግብዣውን ለመቀበል ወሰነ። ደርጉ ከተራማጆች ጋር ለመተባበር ከፈለገ፡-

አንደኛ፣ ለትብብር አመቺ የሆነን የፖለቲካ አካባቢ መፍጠር እንዳለበት። ለዚህም፡-

ሀ) የመስከረም 19ኙን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲያነሳ፤

ለ) የታሰሩ ተራማጆችን እና የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎችን እንዲፈታ፤

ሐ) የዘመቻ ግዳጃቸውን ላልፈፀሙ ዘማቾች "ምሕረት" እንዲያደርግ፤

መ) ተረቅቀው የሚገኙት የሠራተኛ ጉዳይና የገበሬ ማኅበራት ማጠናከሪያ
አዋጆች መታወጅ  እንዳለባቸው እና

ሠ) የኢሠአማ ፅ/ቤት እንዲከፈት።

ሁለተኛ፣ መሠረታዊ በሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ስምምነት መኖር እንዳለበት። ለዚህም፡-

ሀ) ደርግ ኅብረተሰባዊነት የተባለውን መሥመሩን ትቶ፣ የብሔራዊ
ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራምን መቀበል እንዳለበት፤

ለ) አንድ ፓርቲ የሚለውን አስተሳሰብ ለመተው ዝግጁ መሆን እንዳለበት
እና ዲሞክራቲክ  መብቶች መልቀቅ እንዳለባቸው፤

ሐ) በብሔሮችና በኤርትራ ጥያቄ ላይ የሚከተለውን ፖሊሲ መለወጥ
እንዳለበት እና፣

መ) የሚቋቋመው ፅ/ቤት ከደርግና ከሌሎች መንግሥታዊ ተቋዋሞች ነፃ
ሆኖ የሚሠራ ተቅዋም መሆን እንዳለበት።

ደርግ፣ ለትብብር አምቺ የፖለቲካ አካባቢን ስለመፈጠር የተነሱትን ጥያቄዎች፣ በጣም ባጭሩና "ችግር አይደሉም" በሚል መለሰ። ከዚህ በኋላ የቀረው፣ ደርግ ተጨባጭ እርምጃዎችን በመውሰድ ለትብብር የተዘጋጀ መሆኑን ማሟላቱ ነበር። እነርሱንም በኅዳር/ታህሣሥ ወራት በወሰዳቸው እርምጃዎች ገሀድ አደረገ። ዋና ዋናዎቹ፡-

ሀ) ኅዳር 2 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ታወጀ፤ የኢሠአማ ቢሮ ተከፈተ፤

ለ) ኅዳር 25 የመስከረም 19ኙ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተነሳ፤

ሐ) በዚሁ ዕለት ከመስከረም ጀምሮ ታስረው የነበሩ ከ100 በላይ የሚሆኑ
ተራማጅ ምሑራን፣
26 የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎችና 18 የመምሕራን ማኅበር መሪዎች
ተፈቱ፤

መ) ታህሣሥ 4 የገበሬ ማኅበራት ማጠናከሪያ አዋጅ ታወጀ፤

ሠ) ታህሣሥ 8 በዘመቻው ላልተካፈሉ ዘማቾች "ምሕረት" ታወጀ።

የተጋበዙት ምሑራን ታህሣሥ 4፣ 1968 ዕለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራምን፣ የዲሞክራቲክ መብቶችን እና የፅ/ቤቱን ማቋቋሚያ አዋጆች ለማርቀቅ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድነት ሲሰበሰቡ፤ ደርግ "ችግሮች አይደሉም" ብሏቸው የነበሩት እርምጃዎች ተወስደው ነበር። መኢሶን እርምጃዎቹን በአዎንታዊ ገምግሞ ዓባላቱን በፅ/ቤቱ ውስጥ ለማሠማራት የወሰነውም፤ ደርግ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች በይፋ ከወሰደ በኋላ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም እና የፅ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ በሚያዝያ 1968 ታወጁ። የኢሕ አፓ አመራር በተጠቀሱት የዲሞክራሲያ ዕትሞች አሁን ደግሞ፡-

"ከፕሮግራሙ ጋር አብሮ የወጣውን የአደራጅ ፅ/ቤት ልንቀበል
አንችልም"

በማለት፣ ፅ/ቤቱን ተቃወመ። አያይዞ፡-

"ፕሮግራሙን የምንቀበለው አብዮቱ ከተጀመረ ወዲህ እንደተገኙት ማናቸውም የሕዝብ ድል አድርገን እንጂ"

ያለ ቢሆንም፤ መልሶ፡-

"እንደ ሕብረት ፕሮግራም አድርገን አንቀበለውም" እያለ፤ ጨርሶ ባልቀረበው የ"ሕብረት ግንባር ፕሮግራም" ላይ በማተት ራሱን ከፅ/ቤቱ አገለለ። ወይንም፣ ከጥቂት ወራት በፊት "ለአብዮቱ ዕድገት የጋት ታህል እንኳን መንገድ የሚከፍት ሁኔታ ከተፈጠረ... በዛ ሁኔታ ለመጠቀም መሞከር በአብዮቱ ውስጥ የምንጫወተው ሚና የጣለብን ግዴታ ነው" ያለውን አቋም፣ መልሶ ውድቅ አደረገው። ፕሮግራሙ "የሕብረት ፕሮግራም" አልነበረም። ለ"ግንባር" ምሥረታ የጠራም አልነበረም። በፅ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ውስጥ በዘጠኝ ነጥቦች እንደተዘረዘሩት፤ የፅ/ቤቱ ሕጋዊ ተግባሮች እና ሥልጣን የሚከተሉት ነበሩ፡-

ሀ) ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሥራ ላይ የሚውሉበትን መመሪያ ማዘጋጀት፤

ለ) የዲሞክራሲያዊ መብቶችን አዋጅ ማስፈፀም፤ ይዞታቸውን መተርጎም፤

ሐ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን መከታተል፤

መ) የሕብረተሰብዓዊነት ፍልስፍና እንዲስፋፋ የሚረዱ ፅሑፎችንና መመሪያዎችን በልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ቋንቋዎች አዘጋጅቶ በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች በየክፍለ ሀገሩ፣ በየአውራጃው፣ በየወረዳውና በየቀበሌው እንዲዳረሱ ማድረግ፤

ሠ) የሠፊውን ሕዝብ የበላይ ገዥነት የሚያረጋግጥ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚቋቋምበት አመች ሁኔታ እንዲፈጠር ማገዝ፤

ረ) በዚህ መሸጋገሪያ ጊዜ ለሥራ ለቅልጥፍና እንዲያመችና ለአብዮታዊ እርምጃዎች መሰናክል እንዳይሆን ያለው የቢሮክራሲ አቋም በሠፊው ሕዝብ ትግል የሚለወጥበትን መንገድ መጠቆም፤

ሰ) የፖለቲካ ት/ቤቱን በበላይነት ማካሄድ፤

ሸ) የሠፊውን ሕዝብ የመደራጀት ጥረት ለማገዝ የፖለቲካ አንቂዎች በውጭና በሀገር ውስጥ የሚሰለጥኑበትን መምሪያ፣ እቅድና ፕሮግራም ማዘጋጀት፤

ቀ) ለሥራው የሚያስፈልጉትን ሠራተኞች መቅጠር።

የፅ/ቤቱ የመጀመሪያ ሥራዎች ሁለት የፖሊሲ ሠነዶችን ማዘጋጀት ነበር። አንደኛው፣ የኤርትራን ጉዳይ በሰላማዊ/ፖለቲካዊ መንገድ ለመፍታት የሚያግዝ የፖለሲ ሠነድ ነበር። ሁለተኛው፣ የዲሞክራሲ መብቶች አዋጅ ረቂቅ ነበር።

የኤርትራን ጉዳይ በሚመለከተው፣ "የዘጠኝ ነጥቦች የፓሊሲ ሠነድ" የተባለው የሰላማዊ መፍትሔ ፖሊሲ ሠነድ ግንቦት 8፣ 1968 ዕለት ይፋ ተደረገ። በፖሊሲውም መሠረት፣ ደርግ ለመጀመሪያ ጊዜ ከግንባሮቹ ጋር በቀጥታ ለመወያየት ዝግጁ መሆኑን በይፋ ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ አሳወቀ። በተጨማሪም፣

ሀ) የኤርትራ የፖለቲካ እስረኞች እንደሚፈቱ እና፤

ለ) በኤርትራ ላይ ታውጆ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንደሚነሳ

አሳወቀ፤

ሐ) የሚመለሱ ስደተኞችን መልሶ ለማቋቋም፣ የፈራረሱ የኢኮኖሚ ተቅዋሞችን መልሶ ለማንቀሳቀስ እና በሥራ ላይ የሚያውል "የኤርትራ ጉዳይ ልዩ ኮሚሽን" ተቋቋመ።

የዘጠኝ ነጥብ ፖሊሲውን በሥራ ለማዋል፣ ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ሰኔ 2 ዕለት "ለውይይት አመች የሆነ ሁኔታ ስላለ" በማለት በገለፁት መሠረት ታጠፈ። የሚመለሱ ስደተኞችን መልሶ ለማቋቋም እና የፈራረሱ የኢኮኖሚ ተቋሞችን መልሶ ለማንቀሳቀስ፤ ከመስከረም 28፣ 1994 እስከ መስከረም 27፣2006 የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት በነበሩት በመቶ አለቃ ግርማ ወልደጊዮርጊስ የሚመራ "የኤርትራ ጉዳይ ልዩ ኮሚሽን" ሰኔ 30 ዕለት ተቋቋመ። ከግንባሮቹ ጋር ውይይት ለመገናኘት እና ውይይት ለመክፈት፣ በሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ የተመራ እና ኃይሌ ፊዳ አባል የነበረበት ቡድን ወደ አስመራ ሄደ። ፖሊሲውን ለጎረቤት አገሮች ለማሳወቅ በማለትም፤ በሻለቃ ብርሃኑ ባይህ የሚመራ እና የመኢሶን አባል የነበረው አቶ ተስፋዬ ታደሰ የተካተተበት ቡድን ወደ ሱዳን፣ ሊቢያ፣ ደቡብ የመን፣ ግብፅ፣ አልጀሪያ፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ኩዌትና ሰሜን የመን ተጓዘ። ይሁንና፣ ግንባሮቹ እንኳን ለመወያየት ለመገናኘትም ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው፤ ሙከራው ተቋረጠ።

የዲሞክራሲያዊ መብቶችን መለቀቅ በሚመለከተው፣ እስከሚታወጅበት ጊዜ ድረስ በዲሞክራሲ እና በብሔሮች መብቶች ጥያቄ ላይ አገር አቀፍ ውይይት ተከፈተ። በየመሥሪያ ቤቱና በየሥራ ተቋሞች ውስጥ ሁሉ የውይይት ክበቦች ተቋቋሙ። የመንግሥት የመገናኛ ዘዴዎች (ጋዜጦች፣ የራዲዮ ጣቢያዎች እና የቴሌቪዥን መድረኮች) ለነፃ ውይይቶች ክፍት ሆኑ። በተለይም "የአብዮት መድረክ" በተባለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ እና "ሕዘብ እንዲያውቀው" በተባለው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዓምዶች ላይ ሠፊ ውይይቶች ተካሄዱ።

በሌላ በኩል፣ የፅ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ "የሠፊውን ሕዝብ ንቃት እና መደራጀት ማገዝ" ባለው መሠረት፣ በየካቲት 66 የፖለቲካ ት/ቤት አጭር ዕድሜ ዘመን ከ6ሺህ የማያንሱ ተማሪዎች ተሳተፈ ሆኑ። ከ20ሺህ የማያንሱ የገበሬ ማኅበራት ከታች ወደላይ እየተደራጁ መጥተው፣ የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበርን መሠረቱ። የኢትዮጵያ ሠረተኞችም፣ የእንዱስትሪ ማኅበር በተባሉ ሰባት ማኅበራት ሥር ከታች ወደላይ እየተደራጁ መጥተው፣ የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበርን መሠረቱ። በከተሞችም፣ ከ5,000 ኗሪዎች በላይ በሚገኙባቸው 246 ከተሞች ውስጥ ተቋቁመው የነበሩት 1,791 የከተማ ቀበሌ ማኅበራት፣ በወረዳ እና በከፍተኛ ማኅበራት እየተደራጁ መጡ።

ይሁንና በዚሁ ጊዜ፣ በመኢሶን እና በኢሕአፓ መሀከል በየጋዜጣዎቻቸው፣ በአብዮት መድረክ፣ በውይይት ክበቦች፣ በየሴሚናሮች እና በየስብሰባዎች ላይ ይካሄዱ የነበሩት ውይይቶች እና ክርክሮች በአንድ በኩል የተወሰነ አዎንታዊ ውጤቶችን ያስገኙ ቢሆኑም፤ በሌላው በኩል የጭቅጭቅ፣ የስም ማጥፋት፣ የእንካ ሰላንትያ፣ የተራ ውሸት እና የተራ ስድብ ማዛመቻ ባሕርይ የነበራቸው ንትርኮች ሆኑ። ይህ አሉታዊ ገፅታም፣ በኢትዮጵያ ስለሚሰፍነው ዲሞክራሲያዊ ሕይወት፣ እንኳን የደርግ አባሎችን ቀርቶ ሌሎች ማኅበራዊ ክፍሎችንም ያላሳመነ ሆነ። እንደዕውነቱም ከሆነ፣ ድርጅቶቹ ቢያንስ በኤርትራ እና በዲሞክራሲ ጥያቄዎች አኳያ በደርጉ ላይ የጋራ ግፊትን ለማድረግ ያልበቁ ብቻ አልነበሩም። የኢሕአፓ አመራር ከመስከረም 12፣ 1969 ዓ.ም. አንስቶ "የግድያ ሂደት" ያለውን የፖለቲካ ግድያ በሥራ ላይ ማዋል ከጀመረ በኋላ እንዲያውም፤ የአብዮቱ ደጋፊ ኃይሎች በግድያ ፖለቲካ የሚጠቁበት ድባብ መስፈን ያዘ።

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የፖለቲካ ግድያ መፈፀም መጀመሩ፣ የዲሞክራሲያዊ መብቶችን መለቀቅ የዚያኑ ያህል አስፈላጊና አጣዳፊ ያደረገ ጉዳይ ነበር። ይሁንና፣ "መብቱ የሚለቀቀው እንደዚህ ለመጨራረስ ከሆነ..." በሚል፤ ተረቅቆ የነበረው የዲሞክራሲያዊ መብቶች አዋጅ ከመሳቢያዎች ሳይወጣ ቀረ። በሚቀጥለው ክፍል እንደምንመለስበት ግን፤ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች አለመለቀቅ ዋናው ምክንያት፣ አብዮታዊ ሰደድ የተባለው የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ድርጅት ከጥር/የካቲት 1969 ዓ.ም. አንስቶ ብቸኛው የሥልጣን ባለቤት ሆኖ መውጣቱ እንደሆነ በጥንካሬ መገለፅ አለበት።

በሚከተለው ክፍል፣ በቅድመ እና በድኅረ ጥር/የካቲት 1969 ሁኔታዎች እና በመኢሶን የትግል ስልት ለውጥ ላይ ተመልሼ በአጭሩ አትታተለሁ። መኢሶን ትብብሩን ስለማቋረጡ የሚዛመተው ወሬ "ፈረጠጠ"፣ "ቀኝ መንገደኛ" ወዘተ. ከሚሉት አያልፍም። ወይንም፣ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታዎች አካቶ እና በማስረጃዎች

አስደግፎ ለመተንተን የሚደረገው ጥረት አሁንም አነስተኛ ነው። ከመቀጠሌ በፊት ግን፣ ስለመኢሶን ትብብር ተደጋግመው በሚነገሩ ሦስት ትችታዊ አስተያየቶች ላይ አጭር አስተያየቶችን እሰጣለሁ። አንድኛው ትችት፣ “መኢሶን ከፋሺስታዊ የወታደር አገዛዝ ጋር መተባበር አልነበረበትም” የሚል ነው። ሁለተኛው፣ “ከወታደራዊ አገዛዝ ዲሞክራሲን መጠበቅ የዋህነት ነው” የሚል ነው። ሦስተኛው፣ “መኢሶን በሥልጣን ጥያቄ የተሳሳተ አመላካከት ነበረው” የሚል ነው።

የመጀመሪያው ትችት ከጅምሩ የሚነሳው፣ አብዮት እየተካሄደ መሆኑን ባለመቀበል እና እንዲያውም ፋሺስታዊ የወታደር አገዛዝ ሰፍኗል ከሚል አመለካከት ስለሆነ፤ በወቅቱ የነበሩትን ነባራዊ የአብዮት እና ፀረ አብዮት አሰላለፍ እና ትንቅንቆች አይመለከትም። እንደዚሁም ደግሞ፤ ተከፍተው በነበሩት ሕጋዊ መድረኮች መጠቀም ይገባ/አይገባ እንደሆን አይመለከትም። መኢሶን፣ አብዮት በመካሄድ ላይ መሆኑን የተቀበለ ስለነበር፤ በአንድ ወገን በወቅቱ የነበረው የፀረ አብዮቱ ኃይሎች ጥቃት እና የውጭ ኃይሎች በሚለግሷቸው ድጋፍ እየበረታ እንደሄደ ገመገመ። በሌላም በኩል፣ ከፅ/ቤቱ መቋቋም ጋር ተያይዞ የተከፈቱት ሕጋዊ መስኮች ለሠፊው ሕዝብ ንቃት እና ድርጅት መጎልበት የሚያግዙ መሣሪያዎች እንደሆኑ አመነ። ደርግ ከላይ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔዎች በይፋ ካሟላ በኋላ፤ ለመተባበር ወሰነ። ለአብዮቱ መግፋት አመቺ የትብብር ሁኔታዎች እስከነበሩ ድረስ ተባበረ።

ሁለተኛውን፣ “ከወታደራዊ አገዛዝ ዲሞክራሲን መጠበቅ የዋህነት ነው የሚለውን” ተራ ትችት ብሎ ማለፍ ይቻላል። ከንጉሡ ነገሥቱ ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ የሚደረገው ትግል በየዋህነት የሚደረግ ትግል አይደለም። ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ የሚደረገው ትግል እንዲያውም፤ ዲሞክራሲያዊ መብቶች በስፈኑባቸው አገሮችም፤ ለመብቶቹ መስፋት እና መዳበር የሚደረግ ዝንተ ትግል ነው።

ስለሦስተኛው፣ “መኢሶን በሥልጣን ጥያቄ የተሳሳተ አመላካከት ነበረው” ስለሚለው ትችታዊ አስተያየት ዛሬ መመለስ አይስፈልግም። ዛሬ ዛሬ “መኢሶን ያለመስዋዕትነት ሥልጣን የመጭበጥ አባዜ የተጠናወተው ድርጅት ነበር” እየተባለ በዩቲዩብ በሚሠራጨው ንፁህ ውሸት ላይም፤ መመለስ አይስፈልግም። መኢሶን ከአመራሩ ጀምሮ መስዋዕትነትን የተቀበለ ድርጅት ነው። በሥልጣን ጥያቄ ረገድ የነበረው አመለካከት የሚከተለው፣ በሰኔ 17፣ 1968 ዓ.ም ሰሕድ ቁጥር 42 ዕትም ውስጥ እንደተገለፅው እንደነበርም፤ ይታወቃል።
“የመንግሥት ሥልጣን የጉልበት ጥያቄ ነው። ሥልጣንን የበለጠ የተዘጋጀ፣ የተደራጀ እና የታጠቀ ይወስዳታል እንጂ፤ በአቦ ሰጡኝ ማንም እጅ አትገባም። ሠፊው ሕዝብ እነዚህን ሦስት መሠረታዊ ዝግጅቶች ሳያሟላ የፈለገውን ያህል ቢታገል፣ የትግሉን ፍሬ ጠላቶቹ ይሰበስባሉ እንጂ፤ እርሱ ሥልጣንን ሊይዝ አይችልም። ሠፊውን ሕዝብ ዝግጅቱን ትተህ ሥልጣን ለመያዝ ታገል ማለት፣ ይበልጥ የተዘጋጁትን ጠላቶችህን ሥልጣን ለማስያዝ ታገል ማለት እንጂ፤ ሌላትርጉም የለውም።”

## የትግል ሥልት ለውጥ

1968 ዓ.ም. በሁለት ሁኔታዎች መከሰት ምክንያት ተወጣጥሮ ወደመገባደድ አዘመመ። አንደኛው፣ የአብዮቱ ተቃዋሚ ኃይሎች ከውስጥ እና ከውጭ በከፈቱት ከባድ ጥቃት ምክንያት የሰፈነው ውጥረት ነበር። ሁለተኛው፣ በደርግ ውስጥ በተፈጠሩት ሁለት ጎራዎች መካከል መካሄድ በጀመረው ግልፅ እና ስውር ሽኩቻ ምክንያት መከሰት የጀመረው ውጥረት ነበር። የደርግ ውስጥ አንደኛው ጎራ፣ ከግንቦት/ሰኔ 1968 ዓ.ም. ጀምሮ እየተደራጀ የመጣው የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም አብዮታዊ ሰደድ ጎራ ነበር። ሁለተኛው፣ የመቶ አለቃ ዓለማየሁ ኃይሌ እና የሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤል ጎራ ነበር።

## የ1968 መጨረሻ እና የ1969 መጀመሪያ

ኢዲሕ ከ1968 መጨረሻ ወራት አንስቶ በሁመራና በመተማ አካባቢ የጦር ኃይሉን ከሱዳን አስገባ። በጥቅምት/ታኅሣሥ ወሮች እንቅስቃሴውን በተለይም በጎንደር አስፋፋ። ራሳቸውን "ሻለቃ" ብለው የሾሙት አጠናው ዋሴ፣ ግራዝማች አየለው ቸኮል እና ሌሎች የቀድሞ ፊውዳሎች፣ ፈረሰኛ፣ ጉልተኛ፣ ጭቃ ሹም፣ ወዘተ. በመባል ይታወቁ የነበሩትን የቀድሞ የገጠር ሹማምንት አሰልፈው በጭልጋ አውራጃ ተንቀሳቀሱ። በኅዳር አጋማሽ ላይ ከጎንደር ደቡብ በጎርጎራ፣ በአይከል፣ በደርጊ አካባቢ እና ከአይከል ወዲያ እስከ መተማ ድረስ ያለውን አገር በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉ። ሌሎች፣ በዋግሹም ነወጠ መሪነት በጎንደር ዙሪያ አውራጃ ተነሱ። በወገራም፣ ለብዙ ዓመታት የአውራጃው አስተዳዳሪ በነበሩት በቢትወደድ አዳነ መኮንን መሪነት ተንቀሳቀሱ። የኢዲሕ ጦር ታህሣሥ 7 ሰቲት ሁመራን ያዘ። በዚህም ጊዜ ሌ/ኮ ፍስሐ ገብረ ሕይወት የተባሉት የሁመራ ጦር አዛዥ ከከተማው ባንክ 250ሺህ ብር ዘርፈው እና ሠራዊቱን አስኮብልለው ከኢዲሕ ጦር ጋር ተቀላቀሉ።

የኤርትራ ግንባሮች በመስከረም/ታኅሣሥ ባደረጓቸው እንቅስቃሴዎች ከኤርትራ ከተሞች ከረንን፣ አቆርዳትን፣ ሰናዓፌን እና ሌሎችንም ከተማዎች ... ያዙ። የናቅፋን እና የኦምሀጀርን የጦር ሠፈሮች ከበው ከባድ የማጥቃት እርምጃዎች ወሰዱ። በምስራቅና በደቡቡ፣ የሶማሊያው መሪ ጀ/ል ሲያድ ባሬ በአንድ በኩል ከጅቡቲ ነፃ መውጣት ጥያቄ ጋር በተያያዘ እና በሌላ በኩል የኦጋዴን ግዛት ይገባኛል በሚል ተንቀሳቅሰው፣ ፀረ-ኢትዮጵያ ቅስቀሳቸውን አፋፋሙ። በተለይም በባሌ፣ በሲዳሞና በሐረርጌ ሰርጎ ገቦችን እያጠናከሩ አሰማሩ። ለምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጭ ግንባር እና ለአቦ ዋቆ ጉቱ ሶማሌ አቦ ቡድን ሰፊ ድጋፍ ሰጡ። የሱዳኑ መሪ ጀ/ል ኑሜሪ የአፍሪካ የኢኮኖሚክ ድርጅትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ከአዲስ አበባ እንዲነሱ በማለት የቀረቡትን ጥያቄዎች የሚደግፉ መሆናቸውን ገለፁ። የሶማሊያ መንግሥት የፀጥታ ሹም ቱርኪ እቢን አብዱል አዚን በዚሁ ጊዜ ካርቱም ድረስ ሄደው ባደረጉት ንግግር፣ ደርጉን "ከጎረቤት አገሮች ጋር ለመተባበር ችሎታ የሌለው ጨቋኝ መንግሥት" በማለት ከሰሱ።

ሰሜን የመንም፣ "የኢትዮጵያ አውሮፐላኖች ግዛቴን ይሰልላሉ፤ መንደሮቼን ይደበድባሉ፤ ይህንን ብቻየን ለመቋቋም አልችልም፤ የአረብ ሊግ አገሮች እንዲተባበሩኝ እጠይቃለሁ" እያለች እስከ መከሰስና ድጋፍ እንዲደረግላት እስከመጠየቅ ሄደች። ጀ/ል ኑሜሪ ታኅሣሥ 24 ዕለት ካድጉሊ እስከምትባለው የጠረፍ ከተማ ድረስ መጥተው ባደረጉት ንግግር "ኢትዮጵያ ወረራ እያዘጋጀችብኝ ነው" እያሉ ከከሰሱ በኋላ፤ በሱዳን ከሚገኙት ስደተኞች መሀከል ከ100,000 የማያንሰውን አስታጥቀው ለመላክ የተዘጋጁ መሆናቸውን አሳወቁ። እንደዚሁም የአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮሚሽን እና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ፅ/ቤቶች ከአዲስ አበባ እንዲነሱ ጠየቁ። ጥር 22 ቀን በሰጡት መግለጫም፣ ለኤርትራ ግንባሮች ሙሉ ድጋፍ የሚሰጡ መሆናቸውን አጠንክረው አስታወቁ። በታኅሣሥ 27 አምባሳደራቸውን ከአዲስ አበባ አስጠሩ። የካርቱም/አዲስ አበባ የአየር ግንኙነቶች የተቋረጡ መሆናቸውን አሳወቁ። ኢዲሕ በኦምዱርማን የራዲዮ ጣቢያ እንዲገለገል ፈቀዱ። በዚሁ በታኅሣሥ ወር፣ በሐምሌ 1968 ከግብፅ መንግሥት ጋር ተፈራርመውት የነበረውን የጋራ የመከላከያ ውል አደሱ። በፍጥምጥሙ ሥነ-ሥርዓት ላይ ለኢዲሕ እና ለሻቢያ ግልፅ የመሣሪያ እና የፋናንስ ድጋፍ የምትሰጠው እና የሱዳን/ግብፅ የጋራ መከላከያ ውል በቀጥታ የማይመለከታት ሳዑዲ አረብያ በታዛቢነት እንድትሳተፍበት ተደረገ። ጥቅምት 23፣1969 ዕለት አስተዳደራቸውን የመሠረቱት የአሜሪካው ፕሬዚደንት ካርተርም፣ ምዕራባውያን አገሮችን አሰልፈው በደርግ ላይ መዝመት ጀመሩ።

በተመለከቱት ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ በአንድ ወገን የደርግ ውስጥ ጎራዎች ፍጥጫ እየጋለ ሲሄድ እና፤ በሌላ ወገን የኢሕአፓ አመራር "የግድያ ሂደት" ያለውን የፖለቲካ ግድያ ከመስከረም 12 አንስቶ በከተሞች ውስጥ በሥራ ላይ ማዋል ሲጀምር፤ ብዙዎች የደርጉን የመጨረሻ ቀኖች

ቆጠሩ። ቢሮክራሲውም በአንድ ወገን፣ የሆነ ያልሆነውን እየጨማመረ እና እያጋነነ ማውራቱን ሥራው አድርጎ ተሰለፈ። በሌላው ወገን፣ ከአንዱ ወይንም ከሌላው ጋር ለመሰለፍ መሽቀዳደም ያዘ።

የምዕራቡ ዘመቻ ከጎንደሩ የኢዲሕ እና የኤርትራ ግንባሮች ጥቃት እና በደቡብ ከጀመረው የሶማሊያ ሰርጎ ገቦች መጉረፍ ጋር ተዳምሮ፤ የአብዮቱን ደጋፊ ኃይሎች ወደተከላካይነት ገፋ። የአብዮቱ ደጋፊ ኃይሎች የዚያኑም ያህል፣ "አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ይሻገር"፤ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይለቀቁ"፤ "ትጥቅ ለሠፊው ሕዝብ" የሚሉትን ጥሪዎች በማስተጋባት ተሰለፉ። የሚያሳዝነው እንበልና፣ 1969 በተቃራኒው፣ የአብዮቱ ደጋፊ ኃይሎች የባሰውን የተሰነጣጠቁበት እና የፖለቲካ ግድያ እና መጠፋፋት ዕለታዊ የሆኑባቸው ዓመት ሆኑ። ውሎ አድሮ፣ የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም አምባገነናዊ አገዛዝ ምሥረታ የተከናወነባቸው ዓመት ሆነ።

## የደርግ ውስጥ ጎራዎች አሰላለፍ እና ሽኩቻዎች

የደርግ ውስጥ የሻለቃ መንግሥቱ እና የመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ/ሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤል ጎራዎች ከግንቦት/ሰኔ 1968 ዓ.ም. አንስቶ በአብዮታዊ ሰደድ አመሠራረት ምክንያት እየተሻኮቱ እንዳሉ፤ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ የደርግን አወቃቀር የሚለወጥ ሃሳብ በሐምሌ 1968 ዓ.ም. ለደርግ ስብሰባ አቀረቡ። ሃሳባቸው እንደሚታወሰው፣ ደርግ በፓርቲ ዓይነት ይዋቀር የሚል ነበር።
በደርግ ውስጥ የነበሩት ሁለት ጎራዎች በአንድነት ተሰልፈው ሐምሌ 6 ዕለት በወሰዱት እርምጃ የሻለቃ ሲሳይ ሀብቴን ሙከራ አከሸፉ። እንደተወራውም ከሆነ፤ ጎራዎቹ በዚያች ዕለት በአንድነት የተሰለፉት፣ እነሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ እነሱንም ጭምር አስወግደው የሲቪል እና የወታደሮች ከፍተኛ ባለሥልጣኖችን መስተዳደር የማቋቋም (የመፈንቅለ መንግሥት) ዕቅድ ነበራቸው በማለት እንጂ፤ ከግንቦት/ሰኔ 1968 ዓ.ም. ጀምሮ በጎራዎቹ መካከል ያቀነቀነው ግልፅና ስውር ሽኩቻ ስለተዘጋ አልነበረም። ጎራዎቹ በሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ ላይ ከወሰዱት እርምጃ በኋላ እንዲያውም፤ ከዕለት ወደ ዕለት እየተወሳሰበ እና እየተካረረ ከሄደ ሽኩቻ ውስጥ የገቡ ነበሩ። የልዩነታቸው መነሻ የፖለቲካ መሥመር ወይንም የርዕዮተ ዓለም ልዩነት አልነበረም። ይልቁኑም፣ ሻለቃ መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ የተባለው ድርጅት በመሠረቱበት ጊዜ፣ እነመቶ አለቃ ዓለማየሁ/ሻምበል ሞገስን ከድርጅታቸው አመራር የማግለል እርምጃ ስለወሰዱነበር።
ሻለቃ መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድን ሲመሠርቱ፣ እነመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌን ጨምሮ ብዙ የደርግ መሪ አባሎች መሥራች አባል ነበሩ። ይሁን እንጂ፣ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም የሊቀ መንበርነቱን ሥፍራ ለራሳቸው ሲይዙ፤ እነመቶ አለቃ አለማየሁ/ሻምበል ሞገስን "እናንተ በደርጉ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ አላችሁ" በማለት ከአብዮታዊ ሰደድ አመራር አገለሉ። በነርሱም ፈንታ፣ ለእርሳቸው ታማኝ የሆኑትን የደርጉን ዝቅተኛ አባሎች እና ሌሎች መለዮ ለባሾችን (ለገሠ አስፋው፣ ገሠሠ ወልደኪዳን፣ ታምራት ፈረደ፣ ውብሸት ደሴ፣ ገዛኸኝ ወርቄ፣ ደምሰው ካሳየ፣ ብርሃኑ ከበደ፣ ድንቁ፣ ነጋሽ፣ ጌታቸው ሽበሺ ወዘተ…) የድርጅቱ መሪ አባሎች አድርገው አስቀመጡ። እነመቶ አለቃ ዓለማየሁ፣ ሻለቃ መንግሥቱ እነርሱን በማግለል የውሰዱትን እርምጃ በተገቢ ተጠራጠሩ። በደርግ ውስጥ እና ከደርግ ውጭ የተደራጀውን የሻለቃ መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ ጎራ ወደ መፋለም አቀኑ።
1968 በዚህ ዓይነት የሁለቱን የደርግ ውስጥ ጎራዎች ወደ ግጭት ማዝመም አርግዞ ተዘጋ። 1969፣ የጎራዎቹ ትንቅንቅ እየጋለ የሄደባቸው ወራት ሆኑ። ከእንግዲህ የማይታወቅ ነገር ከነበረም፤ የጎራዎቹ ፍልሚያ መች፣ በምን ዓይነት እና በየትኛው ሠፈር አሸናፊነት እንደሚያበቃ እንጂ፤ አሰላለፋቸው አልነበረም። ይሁንናም ደግሞ፣ የኢሕአፓ አመራር የሁኔታዎች ዳሰሳ፣ ከ1968 መጨረሻ አንስቶ የሄደበት ራስን በራስ አግዛፊ ፕሮፓጋንዳ እና የፖለቲካ ግድያ ዘመቻ መጀመሩ እንደሚሆን፤ አልታሰበም ነበር።

የመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ/ሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤል የመጀመሪያ እርምጃ፣ የኢሕአፓ አባል የነበሩት እነመቶ አለቃ አምሃ አበበ እና ታምራት ወልደ ማርያም "የሥውር ፓርቲዎችና ንቅናቄዎች፣ አንድነትና ልዩነት፣ በግንባር ጥሪ ላይ ያላቸው አቋም ማጠቃለያ አስተያየት" በሚል ርዕስ አዘጋጅተው በሰኔ 20፣ 1968 የበተኑትን ፅሑፍ አርመውና አስፋፍተው በደርጉና በሠራዊቱ ውስጥ ሰኔ 25 ዕለት ማሰራጨት ነበር። ከእንግዲህም ጀምሮ፣ በቅስቀሳ እና በድርጊት ከኢሕአፓ አመራር ጋር ወደ መቀራረብ እና መተባበር አመሩ። የሰኔው 20 ፅሑፍ እንደሚታወሰው፣ የኢሕአፓ አመራር ስለራሱ ድርጅታዊ ጥንካሬ የሚሰጣቸውን መግለጫዎች ቃል በቃል እየገለበጠ፡
"ፕሮፓጋንዳው በመላ አገሪቱና በዓለም-አቀፍ ደረጃ የተስፋፋ መሆኑ፣ እርምጃው በመቀነስ ፈንታ በመጨመሩ፣ በብዙ አካባቢዎች ያስታጠቃቸው ኃይሎች መኖራቸው፣ ሠፊው ሕዝብ መፈከሩን መደገፉ፣ ኢሕአፓ በብዙ ሥፍራዎች ሕዝቡ መሀከል ሰርጎ ለመግባት ችሏል።"

የሚል እና፤ ኢሕኢፓ ጠንካራ እና ሠፊ ሕዝባዊ ድጋፍ ያለው ድርጅት መሆኑን የሚያትት ነበር። ሆኖም ግን፤ እነመቶ አለቃ ዓለማየሁ ከኢሕአፓ አመራር ጋር ወደመተባበር ያመሩት የኢሕአፓን ርዕዮተ ዓለም እና የፖለቲካ መሥመር ስለተቀበሉ ነበር ለማለት አይቻልም። ይልቁኑም፣ ውጫዊ ድጋፍ ያስፈለጋቸው ስለነበር እና የኢሕአፓ አመራር ስለወቅቱ ሁኔታ እና ስለራሱ ኃያልነት ያሠራጭ የነበረውን ራስን በራስ አግዛፊ ፕሮፓጋንዳ እንደዕውነታ ስለወሰዱት ነበር። የኢሕአፓ አመራር የወቅቱን የደርግ ውስጥ ሁኔታ እና የሥልጣን አቀማመጥ ያነበበው፡
"የሚሞት አውሬ እንደሚንፈራገጥ ሁሉ፣ በውድቀት ዋዜማ ላይ የሚገኘው የጥቂት መኮንኖች እና ባንዳዎቻቸው ፋሺስታዊ መንግሥት የሞት ሞቱን እየተንፈራገጠ ነው"
እያለ እና፤
"ሻለቃውም ከሠፊው ሕዝብ ቀርቶ፣ ከሠፊው ደርግ እንኳን ተነጥሏል። ይህ፣ ለሻለቃውም ሆነ በጎን ለቀጠራቸው ባንዳዎች እጅግ አስጊ ሁኔታ ፈጥሯል"

እያለ ነበር። ራሱንም የገመገመው፤
"ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ሁኔታ የወለደው አብዮታዊ ፓርቲ፣ ታጋይና መሪ ድርጅት መሆኑ አንድና ሁለት አያሰኝም። ታጋይ ላብ-አደሮችና ወታደሮች፣ ታጋይ ወጣቶችና ተራማጅ ምሑራን ያቀፉት፣ እነዚህንም በሥርዓት ያቀፈ፣ በጠቅላላው ሠፊ ሕዝብም ሙሉ ድጋፍ ያገኘ ፓርቲ መሆኑን በአብዮት ግብር ደግሞ ደጋግሞ ተረጋግጧል"

እያለ ነበር። ኢሕአሠ የተባለውን ሠራዊቱንም ያቀረበው፣ "ፋሺስታዊውን ጦር የሚቋቋም እና የሚሰብር ሕዝባዊ ጦር" አድርጎ ነበር።

የኢሕአፓ አመራር ከእግዲህም፣ መስከረም ሁለትን "የፋሺዝም ፅልመት የነገሠበት ዕለት" በማለት እያወገዘ በዓሉ እንዳይከበር ቀስቀሰ። ሠራተኞች ለመስከረም 12 ዕለት ጠቅላላ የሥራ ማቆም እርምጃ እንዲወስዱ ጠራ። መስከረም 5 "ጦርነቱ ታውጇል" በሚል ርዕስ ባወጣው የዲሞክራሲያ ቅፅ 3፣ ቁጥር 9 ዕትም፡
"ኢሕአፓ በዚህ የፍልሚያ ወቅት ስም ማጥፋትንና ለሻለቃ መንግሥቱ ወታደሮች መጠቆምን የተቀጠሩበት ሙያቸው ያደረጉትን ባንዳዎች ከመሀከሉ ለይቶ ከሚፈፅሙት ተግባርና ከሚያደርሱት በደል ጋር ተመጣጣኝ የሆነውን አፀፋውን መስጠቱ አይቀርም"

እያለ፣ "ነጭ ሽብር" የተባለውን የፖለቲካ ግድያ አወጀ። ሠራተኞች ጠቅላላ የሥራ ማቆም እርምጃ እንዲወስዱ በጠራበት የመስከረም 12 ምሽት፤ በሻለቃ መንግሥቱ ላይ የግድያ ሙከራ አደረገ። መስከረም 15 ዕለት፣ አምስት ወጣት ተማሪዎችን መርካቶ አካባቢ በመኢሶን ወጣት ድርጅት (ኢአወን) የጥናት ክበብ ስብሰባ ላይ

እንዳሉ በጥይት ፈጀ። መስከረም 21 ዕለት፣ ዶክተር ፍቅሬ መርዕድን እና የፅ/ቤቱ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ባልደረባ የነበረውን ጌታቸው እንግዳን ገደለ። ከዚህም በኋላ፤
"የከተማ የትጥቅ ትግልን ("የግድያ ሂደትን") በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አስፈላጊና የሚቻል መሆኑን አምነን የጀመርነው ነው"

ባለው መሠረት፤ የፖለቲካ ግድያን ከዕለት ዕለት እየፈፀመ ቀጠለ።

የተጠቀሱትን የኢሕአፓ አመራር ገለፃዎች ወደ ቀላል ቋንቋ ብንተረጉማቸው፤ የኢሕአፓ አመራር "ከሥልጣን ደጃፍ በራፍ ላይ ቆሜ የምገኝ ነኝ" የሚል አመለካከት እንደነበረው ላለመገንዘብ አይቻልም። በዚህ አኳያ የሚያስገርም ነገር ከነበር የሚያስገርመው፤ እነመቶ አለቃ አለማየሁ/ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል የኢሕአፓ አመራርን የሁኔታዎች ንባብ፣ ራስን በራስ አግዛፊ ፕሮፓጋንዳ  እንደዕውነታ መውሰዳቸው ነበር። የፖለቲካ ግድያ ዘመቻውን እንደጥንካሬ መመልከታቸው ነበር። ምክንያቱም፣ የወቅቱ ሁኔታ "ሻለቃው ተነጥሎ አልቆለታል" ለማለት ከቶም የሚያስችል አልነበረም። ሻለቃው በዚህ ጊዜ ከአቻዎች መሀከል የመጀመሪያው አንደኛው እንጂ፤ "የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣንን" ሥፍራ የያዙ ሰው አልነበሩም። በነዚያ የ1968 የመጨረሻ ቀኖች ወቅት በዕርግጥ ለማለት ይቻል የነበረውም አንደኛ፣ ሁለቱ ጎራዎች በየፊናቸው ጥንካሬ እስከሚሰማቸው ድረስ ይተቃቀፉም ይጋጩም ነበር። ሁለተኛም፣ ሁለቱም የውጭ አቃፊን እና አጠናካሪን ለመላበስ ይሯሯጡ ነበር።

ሻለቃ መንግሥቱ በአንድ ወገን ከወዝ አደር ሊግ ጋር በመሆን አብዮታዊ ሰደድን ማጠናከር ያዙ። ድርጅታዊ መረባቸውን በአብዮታዊ ሰደድ አባልነት እና በሹመት በሚያስጠጓቸው የሠራዊት እና የቢሮክራሲ ክፍሎች ውስጥ ዘረጉ። በሌላው ወገን፣ "አብዮቱ ከተከላካይነት ወደአጥቂነት ይሻገር፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይለቀቁ፣ ትጥቅ ለሠፊው ሕዝብ" የሚለውን ጥሪ እያስተጋቡ፣ ከኢማሌዲሕ ጋር ያላቸውን ግንኙነት አዳበሩ። የዚህ አንደኛው ውጤት "የተራማጆች ሕብረት ኮሚቴ" የተባለው የኢማሌድሕ መሥራች ኮሚቴ ጥር 22 ዕለት መቋቋም ነበር።

እነመቶ አለቃ ዓለማየሁ/ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል በበኩላቸው፣ በአንድ ወገን በተለይም ከቢሮክራሲው ጋር ያሏቸውን ግንኙነቶች እና ትስስሮች አጠናከሩ። በሌላው ወገን፣ ለኢሕአፓ የሚሰጡትን የፖለቲካ ቅስቀሳና የሎጅስቲክ ድጋፍ አጠናከረው፤ የመሣሪያ መጋዘኖችን በተዘዋዋሪ እስከ ማሰበርና መሣሪያዎችን እያስወጡ ለኢሕአፓ አመራር እስከ መስጠት ተሻገሩ። የኢሕአፓን ፅሑፎችና ባንዲራዎች በየሥፍራው ለመበተን፣ ለመለጠፍና በኤሌክትሪክ ገመዶች ላይ ለመስቀል በተለይም አንዳንድ የፖሊስ ሠራዊት ክፍሎች እንዲተባበሩ አደረጉ።

በወቅቱ ሁለቱ የደርግ ውስጥ ጎራዎች ፍጥጫ ያልተወጠረ አንድም የፖለቲካ ድርጅት፣ መደብ እና የመደብ ክፍል፣ ሕዝባዊ ድርጅት እና ማኅበራዊ ኃይል አልነበረም። በአካባቢያቸው ለነበረ እና የዕለት ተዕለቱን ግለት ያስተውል ለነበር ደግሞ፤ በጎራዎቹ መካከል ወደግጭት የሚያመራ ሁኔታ እይተፈጠረ እንደመጣ ግልፅ ነበር። መኢሶን ከዚህ ግምገማ በመነሳት፣ የሁለቱ የደርግ ጎራዎች መጋጨት እንዳይደርስ ጣረ። ይህንንም ያደረገው፣ የግጭቱ ውጤት ከሁለት አንድ እንደሚሆን ስላመነና ራሱን ለመከላከል ጭምር ነበር። አንደኛ፣ ሻለቃ መንግሥቱ ካሸነፉ፣ በደርጉ ውስጥ የረባ ተፋላሚ እንደማይኖርባቸው እና ውሎ አድሮ በመኢሶን ላይ እንደሚዞሩ። ሁለተኛ፤ እነመቶ አለቃ ዓለማየሁ/ሻምበል ሞገስ ካሸነፉ የመጀመሪያው ተጠቂ መኢሶን እንደሚሆን፤ ወይንም የኢሕአፓ አመራር ከታች የጀመረውን የፖለቲካ ግድያ እነመቶ አለቃ ዓለማየሁ በመንግሥት ደረጃ እንደሚቀጥሉት። ሦስተኛ እና በመጨረሻም፣ የአንዱ ወይም የሌላው ጎራ ማሸነፍ፣ የኢትዮጵያን አብዮት ከመጨንገፍ ሂደት ውስጥ እንደሚያስገባ።

የጎራዎቹን ሽኩቻ ለማርገብ እየተጣረ እንዳለ፤ እነመቶ አለቃ ዓለማየሁ/ሻምበል ሞገስ፣ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ በሐምሌ 1968 አቅርበውት የነበረውን የደርግ መዋቅር ለወጥ ሃሳብ ታኅሣሥ 20 ዕለት በተካሄደው የደርግ ስብሰባ ላይ አቀረቡ። ስብሰባው ሲዘጋ፣ ደርግ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ (40 አባሎች) እና ቋሚ ኮሚቴ (17 አባሎች) በተባሉት አካሎች ተዋቅሮ፣ በፓርቲ ዓይነት የተደራጀ ሆነ። በሥልጣን ክፍፍሉ ረገድ፣ ሻለቃ መንግሥቱ የደርጉ አንደኛ ምክትል ሊቀ መንበርነትን እንደያዙ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ተደረጉ። ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ሁለተኛ ምክትል ሊቀ መንበር እንደሆኑ፤ የሚሊሽያው ትጥቅ፣ ንቃት እና ድርጅት ኃላፊ ሆኑ። ሊቀ መንበሩ ብ/ጀ ተፈሪ በንቲ ርዕሰ ብሔር እና የጦር ኃይሎች ጠቅላላ አዛዥ ከመሆናቸውም በላይ፤ የደርግ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የማዕከላዊ ኮሚቴ እና የቋሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ሆኑ። መቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ የሶስቱም አካሎች ዋና ፀሐፊ ሲሆኑ፤ ሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤል የፖለቲካና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ሆኑ። ኮ/ል አሥራት ደስታ የማስታወቂያ እና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሆኑ። ሌሎቹ የደርግ አባሎች የክፍለ አገሮች የበላይ በላይ አስተዳዳሪዎች እየተደረጉ ተሾሙ። አንዳንዶቹ (ሻለቃ ደበላ ዲንሳ - አዲስ አበባ እና አካባቢው፣ ካሣየ አራጋው - ሸዋ፣ ዘለቀ በየነ - ሐረርጌ፣ ጴጥሮስ ገብሬ - ሲዳሞ፣ ሻለቃ መላኩ ተፈራ - ጎንደር፣ እሸቱ ዓለሙ - ጎጃም፣ ሻምበል አሊ ሙሳ - ባሌ፣ ተሰማ በላይ - ከፋ፣ ንጉሴ ፋንታ - ወለጋ) ነበሩ።

ይሁን እንጂ፤ የእነመቶ አለቃ ዓለማየሁ/ሻምበል ሞገስ የታኅሣሠ 20 ለውጥ እና ሹመት የወር ያህል ዕድሜ እንኳን በቅጡ አልቆጠረም ነበር። ለጥር 26 ስለዕድገት በኅብረት ዘመቻ ለመወያየት ተጠርቶ በነበረ የደርግ ስብሰባ ላይ፤ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም “ለምሳ ያሰቡንን ቁርስ አደረግናቸው” ባሉት እርምጃ፣ የመቶ አለቃ ዓለማየሁ/ሻምበል ሞገስን ጎራ አስወገዱ። ይሁንና፣ ጥር 26 የሌላ በእጅግ የተወሳሰበ ትንቅንቅ የመጀመሪያ ዕለት እንጂ፤ የልዩነቶች ማብቂያ ዕለት አልሆነም። እንዲያውም ቢባል ትክክል ነው፤ ከጥር 26 በኋላ ሁኔታዎች ሲቀያየሩ እና ውስጣዊ እና ውጫዊ አሰላለፎች ሲለዋወጡ፣ የሳምንት ዕድሜ እንኳን አልተቆጠረም ነበር። አንደኛው፣ በኢማሌዲሕ አባል ድርጅቶች መካከል የተፈጠረው ልዩነት ነበር። ሁለተኛው፣ የሶማሊያን ወረራ ተንተርሶ መጉረፍ በጀመረው የሶቪየት ኅብረት እና የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ድጋፍ ምክንያት የተፈጠረው የውስጣዊ እና ዓለም አቀፋዊ አሰላለፍ እና የኃይል ሚዛን ለውጥ ነበር።

ጥር 27 ሠፊ ሕዝባዊ ሰልፍ በአብዮት አደባባይ ተካሄደ። ሻለቃ መንግሥቱ በቀይ ቀለም የተሞላ ጠርሙስ እየሰባበሩ፣ “አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸግሯል”፤ “ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይለቀቃሉ”፤ “ሠፊውን ሕዝብ እናስታጥቃለን” እያሉ ደሰኮሩ። “ዝግ ጉባዔ” የተባለው የደርግ ጠቅላላ ስብሰባ ከጥር 30 እስከ የካቲት 4 ድረስ ተካሄደ። ስብሰባው የካቲት 4 ዕለት ሲዘጋ፣ “የደርግን እና የሚኒስትሮችን ምክር ቤት ሥልጣን እና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ” (የመጀመሪያው የታህሣሥ 20ው የነመቶ አለቃ አለማየሁ/ሞገስ ነበር) የሚል አዋጅ ታወጀ። ደርግም አሁን ደግሞ፤ የታኅሣሥ 20ውን የነመቶ አለቃ ዓለማየሁ/ሻምበል ሞገስን የፓርቲ ዓይነት አደረጃጀት እንደያዘ፤ በጠቅላላ ጉባዔ፣ በማዕከላዊ ኮሚቴ (አሁን ግን 32 አባሎች) እና በቋሚ ኮሚቴ (አሁን ግን 16 አባሎች) ተዋቀረ። ሻለቃ መንግሥቱ ራሳቸውን የሦስቱም አካሎች ሊቀ መንበር አደረጉ። በተጨማሪም ርዕሰ ብሔር፣ የጦር ኃይሎች የበላይ አዛዥ፣ የሚኒስትሮች፣ የመከላከያና የፀጥታ ምክር ቤቶች ሰብሳቢ ሆኑ። ኮ/ል አጥናፉ አባተ ምክትል ሊቀ መንበር እና የሠራዊቱ እና የሚሊሺያው የንቃት፣ የድርጅትና የትጥቅ ኃላፊ እንደሆኑ ቀሩ።

የደርጉ ዋና ፀሐፊነት ሥፍራ፣ የአብዮታዊ ሰደድ/ወዝ አደር ሊግ ድርብ አባል በነበሩት በሻምበል ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስ ተያዘ። ፍስሐ ደስታ (አስተዳደር)፣ ብርሃኑ ባይህ (ውጭ ጉዳይ)፣ ተስፋየ ገብረ ኪዳን (መከላከያ)፣ ገሠሠ ወልደ ኪዳን (ኢኮኖሚ)፣ እንዳለ ተሰማ (የቋሚ ኮሚቴ ጉዳይ ኃላፊ)፣ ካሳሁን ታፈሰ (ፀጥታ)፣ ለገሠ አስፋው (የወታደራዊ ፖለቲካ ጉዳዮች)፣ ውብሸት ደሴ (ፍርድ)፣ ታምራት ፈረደ (ማስታወቂያ)፣ አዲስ ተድላ (የሚሊሺያ ጉዳዮች)፣ ገዛኸኝ ወርቄ (የሚሊሺያ የፖለቲካ ጉዳዮች)፣ ተካ ቱሉ (ሕዝብ ደህንነት)፣ ጌታቸው ሽበሺ (ዘመቻ) እየሆኑ ተሾሙ። ሌሎች እንደ ብርሃኑ ከበደ ያሉትም፣ የምርመራ ክፍል ኃላፊ ተደረጉ።

ሌሎቹም፣ እነመቶ አለቃ አለማየሁ/ሞገስ የሰጧቸው ሹመት እየፀደቀላቸው ከሞላ ጎደል በየነበሩበት ክፍለ ሀገሮች የበላይ በላይ አስተዳዳሪዎች ሆነው እንዲቀጥሉ ተደረጉ። በሲቪል ቢሮክራሲው ውስጥም፣ መኢሶን "የሹመት ኮክቴል" ያለው ሹመቶች ተደረጉ።

ከጥር 30 እስከ የካቲት 4 የተካሄደው የደርግ "ዝግ ጉባዔ"፣ የሻለቃ መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ "ሕጋዊ" መፈንቅለ መንግሥት የተፈፀመበት ጉባዔ ነበር። የካቲት 4ም፣ በደርግ ውስጥ ከአቻዎች መሀከል የመጀመሪያው የነበሩት ሻለቃ መንግሥቱ፤ አንደኛው ሆነው የወጡበት ዕለት ነበር። ወይንም፣ ደርግ የፈረሰበት እና መንግሥታዊ ሥለጣን በአብዮታዊ ሰደድ ድርጅት ሊቀ መንበር በሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም የተያዘበት ዕለት ነበር።

ከእንግዲህም፣ ወዝአደር ሊግ እና ማሌሪድ የሚባሉት የኢማሌዲሕ አባል ድርጅቶች፣ የሻለቃ መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ ተለጣፊዎች ሆነው መወናኘት ያዙ። ከፍተኛ እና መሀከለኛ መለዮ ለባሽ እና ሲቪል ቢሮክራሲም፣ ወደ አብዮታዊ ሰደድ ጎራ መከንበል ያዙ። በዚህ ላይ የሶማሊያ ሰርጎ-ገቦች በምሥራቅ በኩል እየሠረጉ ሲገቡ፤ ብሔራዊ አሰላለፎችን የለወጠ አጠቃላይ ሁኔታ ሰፈነ። ከውጭ በኩል፣ የፕሬዚደንት ካርተር አስተዳደር በኢትዮጵያ ላይ የመሣሪያ ማዕቀብን ሲያውጅ እና ሶቭየት ኅብረት እና የምስራቁ ዓለም አጋሮቿ ከሻለቃ መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ መንግሥት ጋር ወደመተባበር ሲያመሩ፤ ኢትዮጵያ እና አብዮቷ ከአዲስ ምዕራፍ ውስጥ የገቡበት ሁኔታ ተፈጠረ።

የሶማሊያ ወረራ እየገፋ ሲመጣ በአንድ ወገን፣ የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያምን እና የሠራዊት/ስቪል ቢሮክራሲውን ትቅቅፍ የሚያጠናክር እና፤ በሌላውም ወገን፣ በኢትዮጵያዊ አገር ወዳድነት የተቀሰቀሰውን ሠፊው ሕዝብ፣ ከመንግሥት ጀርባ ያሰለፈ ሁኔታ ሰፈነ። በዚህ ላይ የሶቭየት ኅብረት እና አጋር መንግሥቶቿ የመሣሪያ እና የቴክኒክ ድጋፍ የጎረፈውን፣ ሚሊሺያ የተባለው አዲስ ሠራዊት የተቋቋመውን እና የአብዮታዊ ሰደድ የፀጥታ ኃይል በአዲስ እየተገነባ የደረጀውን ያህል፤ የሻለቃ መንግሥቱን እና የሠራዊት/ስቪል ቢሮክራሲውን ትቅቅፍ አዋቅሮ የሚከድን ሁኔታ ተፈጠረ። በሌላ በኩል ሻለቃ መንግሥቱን ከአብዮቱ ደጋፊ ኃይሎች ነፃ የሚያደረጋቸው ሁኔታ እየሰፈነ መጣ። የኢትዮጵያ አብዮት በሠራዊት/ሲቪል ቢሮክራሲው እጅ ውስጥ ከመግባት አንስቶ እስከ ብሔራዊ ነፃነት ጥያቄ ድረስ ባሉት ጉዳዮች ሁሉ ከወሳኝ ምዕራፍ ውስጥ ገባ። ከእንግዲህም ጀምሮ ደግሞ፤ በኢማሌድህ አባል ድርጅቶች መካከል ከቀድሞም የነበረው ልዩነት እየሰፋ ሄደ።

ከእንግዲህም ማለት ይቻላል፤ የአብዮቱ ዕጣ የሚወሰነው በአንድ በኩል፣ የመንግሥትን ሥልጣን በጨበጠው የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም አብዮታዊ ሰደድ እና አብዮታዊ ሰደድ አባል በሆነበት የኢማሌድኅ ድርጅት ውስጥ እንደሚኖረው ወይንም እንደማይኖረው ውስጣዊ ዲሞክራሲ እንደሚሆን ግልፅ ይሆናል። በሌላውም በኩል፣ በዲሞክራሲያዊ መብቶች በይፋ መለቀቅ ወይንም አለመለቀቅ እንደሚሆን የዚያኑ ያህል ግልፅ ይሆናል። እዚሁ ላይ ከላይ እንደተመለከተው ግን፣ በዚያች የጥር 26 ዕለት እርምጃ ወሳጁ የእነመቶ አለቃ ዓለማየሁ/ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል ጎራ ቢሆንም ኖሮ፣ የአብዮቱ ዕጣ አሁንም የሚወሰነው፣ በአንድ በኩል፣ በእነመቶ አለቃ ዓለማየሁ/ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል በፓርቲ ዓይነት በተዋቀረው "ደርግ" እና በአብዮቱ ደጋፊዎች መካከል እንደሚኖረው ወይንም እንደማይኖረው ትብብር እና፤ በሌላውም በኩል፣ በዲሞክራሲያዊ መብቶች በይፋ መለቀቅ ወይንም አለመለቀቅ እንደነበር፤ የዚያኑ ያህል ግልፅ ነበር።

ልዩነቶቹን ለመፍታት የተካሄዱት ተደጋጋሚ የኢማሌዲሕ ስብሰባዎች ወዝ አደር ሊግ፣ ማሌሪድ እና አብዮታዊ ሰደድ በአንድ ጎራ ተሰልፈው እና መኢሶን እና ኢጭአት በሌላ ጎራ ተሰልፈው ከመወያየት ይልቅ የተደነቋቆሩባቸው ስብሰባዎች ሆኑ። መኢሶን፣ ልዩነቶቹን በነፃ ለመግለፅ እና ለማሳወቅ የሚያስችሉ ሁኔታዎች እስካሉ ድረስ በማለት፣ በኢማሌዲሕ ውስጥ የነበረውን ተሳትፎ ቀጠለ። ይሁንና በተጓዳኝ፣ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም "አብዮታዊ መሪያችን"፣ "የአብዮቱ ማዕከል"፣ "ከቆራጡ አብዮታዊ መሪያችን ጋር ወደፊት"፣

"አማራጭ የሌለው መሪያችን" እየተባሉ የሚሞገሱበት ምዕራፍ ተከፈተ። መኢሶን የሻለቃ መንግሥቱን "የአብዮት ማዕከልነት" እንዲያውቅ መጫን ተጀመረ። መኢሶን ይህን አለመቀበሉን ካሳወቀም በኋላ፣ ሠፊ ፀረ-መኢሶን ቅስቀሳዎችን ማካሄድ ዕለታዊ ሆነ። ከዚህም ባለፈ፣ የመኢሶንን አባላት እና ወዳጆች መግደል እና ማሠር ተያዘ። ይህንንም፣ መኢሶን የትግል ስልቱን ባሳወቀበት መግለጫ ውስጥ፡-
"የታወቁና በሕጋዊ ሥራ የተሰማሩ የመኢሶን ጓዶችን አንድ በአንድ እየገደሉ ለመጨረስ እንደወሰኑና ይህንን ፋሺስታዊ ዓላማቸውን ከሥራ ላይ ማዋል እንደጀመሩም መኢሶን ደርሶበታል"

በማለት ገልፆት ነበር። በመጀመሪያ ከተገደሉት መካከል የሐረርጌ ክ/አገር የሕዝብ ድርጅት ፅ/ቤት አባል የነበረው አብዱላሂ ዩሱፍ እና የትራንስፖርትና መገናኛ ሠራተኞች ሊቀ መንበር የነበረው የሲቪል አቪየሽኑ ፀጋየ የኋላው ነበሩ። ከዚያም፣ ከ20 የማያንሱ የመኢሶን አባሎች፣ ወዳጆች እና የሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች በደደር ተገደሉ።


መኢሶን በመፈጠር ላይ ያሉትን ውስጣዊ እና ውጫዊ የአሰላለፍ ለውጦች እና በሥልጣን አቀማመጥ ደረጃ ወደ ሻለቃ መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ እየተዳፋ የመጣውን የኃይል ሚዛን ለመገምገም የንቅናቄውን ሠፊ ኮንፈረንስ ጠራ። በመጋቢት 1969 በተካሄደው ኮንፈራንስ ላይ ከዚህ በላይ በተመለስንባቸው በድኅረ ጥር 26 ሁኔታዎች ላይ ከተወያየ በኋላ፤ ከሚያዝያ 1968 ጀምሮ ከደርግ ጋር  የነበረውን ትብብር ለማቋረጥ እና የትግል ስልት ለውጥ ለማድረግ ወሰነ። ነሐሴ 14፣ 1969 ዓ.ም. ዕለት፣ ትብብሩን አቋረጠ።

ፖለቲካ ተለዋዋጭ (dynamic) ነው። በአብዮት ዘመን ደግሞ፤ በሰዓታት ይለዋወጣል። የፖለቲካ ትግል ስለዚህም፤ አንፃራዊ የትግል ሥልትን እየተለሙ መታገልን ይጠይቃል። መኢሶን የየወቅቱን ነባራዊ ሁኔታዎች፣ ፖለቲካዊ/ማኅበራዊ አሰላለፎችን እና የኃይል ሚዛን ከስሜት እና ከድፍን መግለጫዎች በራቀ እየገመገመ እና እንፃራዊ የትግል ሥልት እየቀየሰ የአብዮቱን መግፋት ለማገዝ ታገለ። ስለመኢሶን ሲተረክ ከላይ የተታወሱትን ሁኔታዎች እና ዕውነታዎች ያላካተተ ትረካ፣ በምንም መመዘኛ የተሟላ እና ሚዛናዊ ሊሆን አይችልም። ነባራዊ ሁኔታዎችን እና ሂደቶችን ሳያካትቱ ከሚቀርቡ ድፍን ትረካዎች እና ከቅስቀሳ መግለጫዎችም፤ የሚቀሰም ትምህርት አይኖርም።

# ከመኢሶን ስህተቶች

## በቅድመ አብዮት ዘመን

መኢሶን ሐምሌ 26፣ 1960 ዓ.ም. በጀርመን አገር፣ በሐምቡርግ ከተማ በሚስጥር ተመሠረተ። ለምሥረታው ዝግጅት እና ጥሪ በዶ/ር ወርቁ ፈረደ እጅ ተፅፎ በጥር 24፣ 1960 የተላከው ማስታወሻ የሚከተለው ነበር።


27-2-68

ውድ ወንድም!

መሥራች ዓባላቱ 25 ሲሆኑ፤ በምሥረታው ጉባዔ ላይ የተሳተፉት 17 ነበሩ። ምሥረታው የተጠናቀቀው፣ ቃለ ጉባዔ ያዥ የነበረው ኃይሌ ፊዳ፣ በቃለ ጉባዔው ደብተሩ ውስጥ እንዳሠፈረው እንደሚከተለው ነበር።

"የተመረጠው የንቅናቄው ስም። የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ -መኢሶን።

"የመኢሶንን ደንብና ፕሮግራም ተቀብዬ ሙሉ አባልነት እጠይቃለሁ እያለ እያንዳንዱ አባል ተነስቶ ከጠየቀ በኋላ፤ ሊቀ መንበሩ (ዶ/ር ወረቁ ፈረደ) 'የምትቀበሉ እጃችሁን አውጡ' አለ። አባሎችም ሆንን። በሐምቡርግ ከተማ፣ በጀርመን አገር በዚህ ቀን (6/8/68 ኢ.አ.) አሥራ ሰባት ኢትዮጵያዊያን ተገናኝተን የሕይወታችንን ዓላማ ቀየስን። የዛሬ ዓመት፣ አሥር ዓመት፣ ሀያ ዓመት .... የት እንደርስ ይሆን?[19]

የመጀመሪያ ዋና ፀሐፊ ሆኖ የተመረጠው ኃይሌ ፊዳ ነበር። ፅ/ቤቱ በ1965 ዓ.ም. ወደአገር እንዲገባ ሲወሰን፤ ዶ/ር ወረቁ ፈረደ ሁለተኛው ዋና ፀሐፊ ሆነ። ሦስተኛው፣ ዶ/ር ከበደ መንገሻ ነበር።

መኢሶን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ሶሻሊስት ንቅናቄ ነበር። እንደተመሠረተም፣ የውጭ እና የአገር ውስጥ አካላትን አቋቋመ። በዚህም መሠረት፣ የምሥረታው ጉባዔ አባላት ከነበሩት መካከል ዶ/ር ወርቁ ፈረደ፣ ዶ/ር ተፈራ ወንዴ እና ዶ/ር ያየህይራድ ቅጣው ወደኢትዮጵያ ተመልሰው በኢትዮጵያ ከነበሩት ከዳንኤል ታደሰ እና ከመስፍን ካሱ ቡድኖች ጋር ተዋሃዱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፤ ዶ/ተረፈ ወልደፃድቅ፤ ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድ፣ ዶ/ር ኃይለገብርኤል ዳኜ፣ ታምራት ከበደ፣ ሔኖክ ክፍሌ፣ ሲሳይ ታከለ፣ እና አበራ የማነአብ ገቡ። ዶ/ር ከድር መሀመድ የሱዳንን ድርጅታዊ አካል ለመመሥረት ወደካርቱም ሄደ።

ይሁን እንጂ፣ ከ1960 እስከ1966 በነበረው የአምስት ዓመት የቅድመ አብዮት ዘመን፣ መኢሶን ያደረጀው የሰው፣ የድርጅት፣ የግንኙነትና የፋይናንስ አቅም በጣም ዝቅተኛ ነበር። ወይንም፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ንቅናቄ በየካቲት 1966 ሲፈነዳ፤ የንቅናቄውን ስፋትና ጥልቀት የሚመጥን አቅም አልነበረውም። ለምን? የቅድመ አብዮቱ የዓምስት ዓመት ዘመን በቂ የመደራጃ ዓመታት አልነበሩም ወይ? ሦስት ዋና ምክንያቶች ነበሩ ለማለት ይቻላል።

አንደኛ፣ ውጋገን ይባል በነበረው የውስጥ ልሳኑ የሚያዝያ 1965 ዓ.ም. ዕትም ውስጥ እንደታተው፤ መኢሶን ከንጉሠ ነገሥቱ በኋላ ሊደርሱ የሚችሉትን የለውጥ ዓይነቶች ያነበበው እንደሚከተለው ነበር።

"...በአሁኑ ጊዜ፣ 'ንጉሠ ነገሥቱ በመጋቢት ወር ይሞታሉ' የሚለው የህንዱ ኮከብ ቆጣሪ ንግርት ስላለ፣ የከበርቴውና ንዑስ ከበርቴ ክፍል ለሦስት ወር የሚበቃውን ቀለብ በመሸመት ላይ ነው ይባላል። ንግርቱ ያው የተለመደው ቢሆንም፤ የከተሜው ሀብታም መሸበር የአገሪቱ ጊዜያዊ ሁኔታ ያልረጋ መሆኑን ያመለክታል። በዚህ ላይ የአልጋወራሹ መታመምና የመንግሥት የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች የመታመማቸውን ወሬ በየዕለቱ በሠፊው ማሰራጪታቸው፤ ይህንን አጠራጣሪና አስጊ ሁኔታ ያባብሰዋል። (ያም ሆነ ይህ) ንጉሠ ነገሥቱ ሲሞቱ የሚከተለው ምንድነው?

"...አልጋወራሹ ቀድመው ካልሞቱ እሳቸው ይነግሣሉ። ለጥቂት ቀኖች ወይም ሳምንታት በየከተማውና በየገጠሩ ግርግር፣ ሽሚያ፣ መገዳደል ይኖር ይሆናል። በተለይ የብሔር እና የኃይማኖት ጭቆናዎች በጠነከሩባቸው ክፍለ አገሮች መፋጀት ጭምር ሊመጣ ይችላል። ከዚያ ወዲያ ግን ፖሊሱና ሠራዊቱ ፀጥታ ማስከበሩ አይቀርም።

(ከገዥ መደቦቹ ክፍሎች መሀከል) ከሁሉ ኃይለኛ የሚመስለው በፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ የሚመራው የገዥ መደቦች ክንፍ ሥልጣኑን ሳያደላድል አይቀርም። ሌላ ፍጹም የተለየ፣ አሁን በግልጽ ለመገመት የማይቻል ሁኔታ ሊፈጠር የሚችለው፤ ሠራዊቱ የተከፋፈለ እንደሆነ ነው። በዚህ ዓይነቱ መከፋፈል፣ ወይ በጉልታዊ ልምድ ከአንዳንድ ግለሰቦች ጋር በመሰለፍ ወይም

19

በነገድ በመከፋፈል ወይም የሠራዊቱ አንዱ ክፍል — ለምሳሌ የወጣት መኮንኖች ተደራጅቶ ሥልጣንን ለመያዝ መሞከር ሊደርስ ይችላል። ይህ ከሆነ የረጅም ጊዜ ብጥብጥን ለመጠበቅ የሚቻል ይመስለናል።[20]

ሁለተኛም፣ መኢሶን በኢትዮጵያ የወቅቱ ሁኔታ ሥርዓታዊ ለውጥ ለማካሄድ የሚቻለው በነቃ፣ በተደራጀና በታጠቀ የረጅም ዘመን ትግል ነው፤ የሚል አመላካከት ስለነበረው ነበር። ስለነበርም፤ **ትግላችን** ይባል የነበረው በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች መፅሔት "ተማሪና ምሁር ከሕዝብ ተማር፤ መልሰህም አስተምረው። ከሕዝብ ጋር በመሆን አዲሲቱን ኢትዮጵያ ለመመሥረት ታገል" የሚልን መፈክር ከፊት ለፊት አንግቦ ነበር ይታተም የነበር።

ሦስተኛ፣ የውጭ አካሉ በኋላ ኢሕአፓን ከመሠረተው ከአልጄሪያው የነብርሃነ መስቀል ረዳ ቡድን ጋር ለመተባበር ባደረገው ጥረት በተፈጠረው ልዩነት እና በተገባው ምልልስ ተጠምዶ ቆየ። ልዩነቱ ሁለቱ ወገኖች በመሣሪያ ትግል ጥያቄ ረገድ ከነበራቸው የአመለካከት እና የአካሄድ ልዩነት የመነጨ ነበር። ዋናው ልዩነትም በመሠረቱ፣ የትግል ስልትን የሚመለከት ነበር።

የአልጄሪያው ቡድን አመለካከት 'ነባራዊው (objective) ሁኔታ ለአብዮታዊ የመሣሪያ ትግል የበሰለ ነው። የሚጎለው፣ የሕሊናዊው (subjective) ሁኔታ አለመሟላት ነው። ይህንን ጉድለት ለሟሟላት አንድ ድርጅት በቶሎ ተፈጥሮ አብዮታዊ የመሣሪያ ትግል በአስቸኳይ መጀመር አለበት። አብዮታዊ የመሣሪያ ትግሉን ለመጀመርና ለመምራት ጥቂት የተዳራጁ አብዮታዊያን ይበቃሉ' የሚል ነበር። መኢሶን 'ነባራዊ ሁኔታው የበሰለ ቢሆንም፤ አብዮታዊ ትግል የጥቂት ተደራጀን የሚሉ ታጋዮች ሥራ አይደለም። ሕሊናዊውን ሁኔታ በአንፃራዊ ለሟሟላት፣ ሠፊ የማንቃት፣ የማደራጀት፣ የግኑኙነት ሥራዎችን መሥራት እና የፋይናንስ አቅምን የማጎልበት ሥራዎች መሠራት አለባቸው። ከዚህ ሥራ በፊት ወደ መሣሪያ ትግል ማቅናት፣ ትግሉን ዞሮ ዞሮ የመሣሪያ ጡንቻ ታዛዥ ያደርጋል' የሚል ነበር። እንደሚታወቀው ግን፣ ልዩነቱ ከመኢሶን እና ከአልጄሪያው ቡድን ያለፈና የዘመኑ የ3ተኛው ዓለም የለውጥ አራማጆች በብዙ የሚከራከሩበት ልዩነት ነበር።


በ60ዎቹ ዘመን ስለአብዮት እና የመሣርያ ትግል ጥያቄ ይካሄድ በነበረው ዓለም አቀፍ ውይይትና ምልልስ ውስጥ፤ አንደኛው ወገን የማኦ ትሴ ቱንግ መንገድ የሚባለውን የነቃ፣ የተደራጀ እና የተራዘመ ሕዝባዊ የጦር ትግል (protracted peoples war/struggle) የሚደግፍ ነበር። ሁለተኛው፣ ፈረንሳዩ ሬጂስ ደብሬ "ፎኮዪዝም" በማለት ያስተዋወቀውን እና "ጥቂት የነቁ ታጋዮች ይበቃሉ" ይል የነበረውን የቼ ጉቫራ መንገድ የሚደግፍ ነበር። እንደሚታወሰው፣ ቼ ጉቫራ ጥቂት ታጋዮችን አስከትሎ ወደኮንጎ ሄዶ ነበር። ሆኖም ብዙም ሳይቆይ፣ ወደ ቦሊቪያ አቀና። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በዚ ዝያው ተይዞ ተገደለ። ልዩነታቸው ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ መኢሶን የመጀመሪያውን መንገድ የተቀበለ ሲሆን፤ የአልጄሪያው ቡድን በኋለኛው የፎኮዪዝም መንገድ ለመሄድ የተነሳሳ ነበር።

በዚሁ የመሣሪያ ትግል ጉዳይ ላይ ብንቆይ፤ በ1968 ዓ.ም. የኢሕአፓን አመራር የጨበጠው የተስፋዬ ደበሳይ/ዘርዑ ክኸሸን/ክፍሉ ታደሰ ቡድን፣ "አብዮት የግድያ ሂደት ነው" እስከማለት ድረስ ሄደ። የኢሕአፓን ወጣቶች በግድያ ፖለቲካ እና "በሕዝባዊ አመፅ" (insurrection) ትግል አሠማራ። ይህ የኢሕአፓ አመራር መንገድ አሁንም ደግሞ ግን፤ በ60ዎቹ ዘመን አብዮታዊ ነን ይሉ ከነበሩ የደቡብ አሜሪካ፡ የአውሮፓ እና የፍልስጤም ወጣቶች የተቀዳ ነበር። ወይንም፣ የደቡብ አሜሪካ ቱፓማሮስ፣ የኢጣሊያው ሬድ ብሪጌድ እና የጀርመኑ ባደር ማይንሆፍ፡ እና የፍልስጤሙ ብላክ ሰፕቴምበር ቡድኖች የወሰዱት መንገድ ነበር።እንደሚታወሰው፤ የቡድኖቹ አባላት በየመንግሥታቱ የፀጥታ ኃይሎች እየተደምሰሱ ደምዛ ሳይጥሉ አልቀዋል።

---

[20] ውጋጋን፣ ሚያዝያ 1965፣ ከገጽ 13-15

የመሣሪያ ትግልን በሚመለከት የተጠቀሰው መሠረታዊ ልዩነት የነበረ ቢሆንም፤ መኢሶን የአልጄሪያው ቡድን ታጋዮች ዓባላቱ እንዲሆኑ ጋበዞ ነበር። የአልጄሪያው ቡድን ግብዣውን የሚቀበለው መኢሶን ቡድኑን እንደቡድን ከተቀበለው ብቻ መሆኑን አስታወቀ መለሰ። መኢሶን ቡድኑን እንደ ቡድን መቀበል በድርጅቱ ውስጥ አንጃ መፍጠር ይሆናል በሚል፤ ጥያቄያቸውን ሳይቀበል ቀረ። ይህንንም፣ በወቅቱ የመኢሶን ዋና ፀሐፊ የነበረው ኃይሌ ፊዳ በግንቦት 9፣ 1963 ዓ.ም. ለጠቅላይ ኮሚቴው አባላት በላከው ደብዳቤ ውስጥ እንደሚከተለው አሳውቆ ነበር። የዚህ ፅሁፍ ደራሲ ዛሬ ዞሬ ስመለከተው፣ መኢሶን ከአልጄሪያው ቡድን ጋር ይደረጉ ለነበሩት ምልልሶች ጥቂት ዓባላቱንና ወዳጆቹን መድቦ፤ አብዛኛውን ዓባላቱን የመጀመሪያ ደረጃ ዕቅዶቹን በመተግበር ላይ ማሠማራት ነበረበት።



17/5/71

ለጠቅላይ ኮሚቴው ጓዶች ማስታወሻ ፡

እንደሚታወሰው ፡ ሁለተኛው የጠቅው ስብሰባ በተደረገበት ጊዜ ፡ አንዱ ገፈች በንቁና ቱው ውስጥ እንዲገባ ተወስኖ ነበር፡፡ በውጪ ነው መሠረት ዝግጅት ቢደረግ በመሃሉ አንዳንዱ ችግሮች ተፈጠሩ፡፡ ከነዚህም ችግሮች ዋነኛው የገፈቹ የራሱ መከፋፈል ነው፡፡

በዚህ ምክንያት ውጪ ነውን ከሥራ ላይ ልናውለው አልቻልንም፡፡

ይህንን ማስታወሻ ለመፃፍ የተገደድንበት ምክንያት፡ ገፈቹ በቀርጡ የራሱን ድርጅት ፈጥሮ ለማወጅ እንደሚያስብ ስለገለጸልን ነው፡፡ በኛ በኩል የዚህ አይነቱ እርምጃ በገፈቹ ቢደወሰዱ ይሻላል የሚል ምክር ተሰጥቶአል፡፡ ይሁን እንጂ ገፈቹ ያቀደውን ከሥራ ላይ ቢያውለው ለጠቅው አባሎች ወደነጋገርን እንዲያስከትል ይህችን አጭር ማስታወሻ ጽፈናል፡፡

ከወንድምነት ሰላምታ ጋር

ጸ/ቤት

የአገር ውስጡ አካል የሚንቀሳቀሰው ራሱን ከመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ለመሰወር እጅግ በጣም በመጠንቀቅ ነበር። መሠራታዊ አካሄዱ ይህ ሲሆን፤ በ1961ዓ.ም. የተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ባደረገው ተሳትፎ በደረሰው ጥቃት ምክንያት ደግሞ፣ ጥንቃቄ የተባለውን አጠብቆ ያዘ። በዚያ የመኢሶን ተሳትፎ ወቅት እንደሚታወቀው፤ አባሎች እና ወዳጆች ለእሥር ተዳረጉ። ፍርዱ ሰኔ 23፣ 1961 ሲሰጥ፣ ከተያዙበት ቀን አንስቶ ለሰባት ዓመት ከስድስት ወር በእሥራት እንዲቀጡ ተፈረደባቸው። ከአገር ውስጥ አካል ለውጩ አካል በሚያዚያ 1961 የተላከው ሪፖርት እንደገለፅውም፣ ሁኔታው የሚከተለው ነበር።

“ሔኖክ ክፍሌ፣ እሸቱ ጮሌ፣ ታምራት ከበደ እና ዶ/ር ወርቁ ፈረደ የሚባሉት ወንድሞቻችን በልዩ ካቢኔ ውስጥ ስለታሠሩ እስካሁን ድረስ ለማየትና ለማነጋገር አልቻልንም። ጥረታችን እንደቀጠለ ነው። በይርጋ ተሰማ ላይ ጭካኔ በዝቶበታል። የአማርኛውን ፅሑፍ በየጊዜው እየፃፉ ሲያዘጋጁ የነበሩት ሦስት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም (ዋለልኝ መኮንን፣ ጌታቸው ሻረው፣ ፈንታሁን ጥሩነህ) በእሥር ቤት ይገኛሉ። የማባዣው እቃ ዶ/ር ሐና ጎበዜ ቤት ተገኝቷል። ሐኪሟም (ሐና ጎበዜ) ታሥራለች። የማባዣው መኪና ከሁለት ቀናት በፊት በፎቶግራፍ በጋዜጣ ላይ ወጥቷል።”

ይሁንና፣ በነሐሴ ወር በንጉሡ ነገሥቱ “ምሕረት”ተፈቱ። የደረሰው ጉዳት ግን፣ በድርጅቱ የመንቀሳቀስ አካሄድ ላይ ብቻ ሳይሆን፤ በሕልውናው ደረጃ ጭምር መሠረታዊ ጥያቄ የቀሰቀሰ እና መኢሶንን ይበልጥ ወደሕቡዕ ያስገባ ነበር።

ይህም ሆኖ፣ የአገር ውስጡ አካል በአገር ውስጥ ከነበሩት አንዳንድ በሕቡዕ (በምሲጥር) ከተደራጁ የወጣቶች ጥናት ክበቦች ጋር የነበረው ትውውቅና ግኙኝነት እንደቀጠለ ነበር። ይሁንና፣ የሚቀርባቸው በድርጅት እና በድርጅት ስም ሳይሆን፤ በግለሰብ ደረጃ ነበር። ለዚህም ዋናው ምክንያት፣ በቡድኖቹ ዘላቂነት ላይ ዕምነት ስላልነበረው ነበር። በ1962 ከአገር ውስጥ አካል ለውጩ አካል በተላከ አንድ ሪፖርት ውስጥ እንዳለውም፤

“...እዚህም እዚያም የጥናት ቡድኖች አሉ እየተባለ ይወራል። ቁጥራቸው በርካታ ነው ይባላል። አብዛኞቹ ለስሙ ወይም በስም ብቻ አሉ የሚባሉ የእንቧይ ካብ ናቸው። አምናም ካች አምናም እንደዚሁ ብዙ የጥናት ክበቦች አሉ ይባል ነበር። ግን ምንም ዓይነት መሻሻልና ዕድገት ያደረጉ አይመስለንም። እኛ እንደምናየው እዚህ ያሉ ‘ሬቮሉሽናዊ ነን’ የሚሉት ተማሪዎች ወይም ምሑሮች ብዙ ጉድለት አለባቸው። አብዛኞቹ የአይዲዮሎጂ ዕውቀታቸው ዝቅተኛና የተወናበደ ነው። ዋናው ጉድለታቸው ግን፣ ዲሲፕሊን አለመቀበላቸው ነው። አብዛኞቹ አናርኪስት ዓይነት ናቸው። ... (እነዚህን) ደንበኛ ሬቮሉሽናዊ ማድረግ ቀላል አይደለም”።

የዓባላቱን ማኅበራዊ አቀማማጥ እና የትግሉን አውድ አገናዝቦ በየካቲት 1961 ዓ.ም. ለውጩ አካል በተፃፈ አንድ ሪፖርት ውስጥም፣ የሚከተለውን ገልፆ ነበር።

“ዋናው ችግር እስከዚህም የመንግሥትን የፀጥታ ኃይል መቋቋሙ አይደለም። ይልቁኑ የምንንቀሳቀስበት አካባቢ ተፈጥሮ ነው። ማኅበራዊ ሥፍራችን እና —ማለትም የተማርንና የመንግሥት ተቀጣሪዎች መሆናችን በዚህም ምክንያት የሚጠበቅብን ማኅበራዊ ሚና — ከገዥው መደብ አባሎችና የተማረ ከሚባለው ክፍል ጋር በየዕለቱ እንድንገናኝ ያስገድደናል። ... በዚህች የዲሞክራሲ እስትንፋስ በሌለባት አገር ውስጥ ከሰዎች ጀርባ መንሾካሾክና በሰዎች ላይ የሆነ ያልሆነውን ማውራት ይበዛል። ሹክ እያሉ ሌላውን የመወጣጫ መሰላል ለማድረግ የማይመለሱት ጥቂት አይደሉም። እኛም በጣም ተለይተን ከታየን ራዲካል የሚለው መጠሪያና መለያ እስከሚለጠፍብን ድረስ ብዙ ጊዜ የሚወስድ አይሆንም። ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያሻው ጉዳይ ቢኖር ይኸኛው ነው።”

የአገር ውስጡ አካል በሌሎቹ የለውጥና የአብዮት ኃይሎች ውስጥ (ላብ/ወዝ-አደር፣ አርሶ አደር፣ ብሔራዊ ከበርቴ፣ ንዑስ ከበርቴ፣ ሠራዊት ውስጥ) የቅስቀሳ፣ የንቃት እና የማደራጀት ሥራዎችን የመፈፀሙንም ተግባር ቅድሚያ ሰጥቶት ነበር ለማለት አይቻልም። በነሐሴ 1965 ለውጩ አካል በላከው ሪፖርት የወቅቱን የትግል አውድ የገመገመው እንደሚከተለው ነበር።

“ከሠራተኛው መደብ ውስጥ ለድርጅቱ ለመመልመል ከመሞከራችን በፊት የሠራተኞችን ሁኔታ በተጨበጠ መልክ ደህና አድርገን ማጥናት አለብን። ... በጥናት ላይ ተመርኩዘን የመጠጋቱንና ውስጣቸው የመግባቱን ስትራተጂና ታክቲክ መቀየስ አለብን።”

ስለዚህም፣ በጥናቶች ላይ አተኮረ። አንዳንዳንድ ጥናቶቹ በትግላችን መፅሔት ላይ ይወጡ ነበር።[21] በገበሬው ውስጥ የመሥራትንም ጉዳይ የተመለከተው፣

> "በገበሬዎች ውስጥ ለመንቀሳቀስ በቅድሚያ ከየብሔረሰቡ የሚመጡ ታጋዮችን ማነፅና ማደራጀት አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን፤ የግዴታ ነው። ... በገበሬዎች ዘንድ በክፍለ አገሩ ሰው ካልሆነ በስተቀር፤ ውስጣቸው ለመግባት በጣም አስቸጋሪ ነው። እንዲያውም አይቻልም"

በሚል ነበር። ብሔራዊ ከበርቴውን፣ መለዮ ለባሹንና ወዘተ. በሚመለከተው፣ ከግል ግንኙነቶች ደረጃ ባለፈ ድርጅታዊ ትስስር እንደማይቻል ይገልፅ ነበር።

> "ከብሔራዊ ቡርዧው ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ቀስ በቀስ በግል ግንኙነት ካልበሰሉ በስተቀር፤ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ አይገቡም። በጣም ይፈራሉ። የወጣት መኮንኖችም ነገር እንደዚሁ ነው። በውስጣቸው ሰላዩ ብዙ በመሆኑ፣ የአገር ፍቅር ያላቸውና በመንግሥት ላይ ቂም የያዙ አንዳንዶች ቢኖሩም፤ ለመደራጀት ወይም በጥናት ክበብ ውስጥ ለመግባት በጣም የሚፈሩ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ለማድረግ የምንችለው፣ ከእነዚህ መሀከል አንዳንድ የምናውቃቸውን በግል ግንኙነት ይዞ መሥራት ነው። አንዱን ግለሰብ በአይዲዮሎጂ መሳብ ይቻል ይሆናል። አንዳንድ ጠቃሚ መረጃዎችን እንዲያስተላልፍልን እንሞክራለን። በሚፈለግበት ጊዜም ወደ እኛ ለመምጣት እስከሚችልበት ድረስ ለመሄድ ይችል ይሆናል። በአሁኑ ሁኔታ ግን ከዚህ ከግል ግንኙነት ደረጃ አልፈን የድርጅት አካል ወይም የጥናት ክበብ ለማቆም በዕውነቱ የምንችል አይደለንም።"

ባጭሩ፣ መኢሶን በቅድመ አብዮት ዘመን ይንቀሳቀስ የነበረው በጣም በጥንቃቄ፣ በጣም በዝግታ፣ እያንዳንዱን ሰው በጣም አድርጎ በማጣራትና ከእጅግም በእጅግ በመመዘን ነበር። በሌላ አነጋገር ጥንቃቄ፣ ዲሲፕሊን፣ ምስጢር፣ ፀጥታ ወዘተ. የጠቅላላ እንቅስቃሴው መመሪያዎች እስከመሆን ደረሱ። ወይንም፣ አንዳንድ ዓባላቱ እንደሚሉት፣ "መኢሶን ውስጥ ለውስጥ 'እንደ-ዔሊ እየተንፏቀቀ'" ለመደራጀትና ለማደራጀት ሲያደርግ የነበረው ጥረት፤ ካለመንቀሳቀስ ያደረሰውና አንዳንድ የመደራጀትና የመጠናከር አጋጣሚዎችን ያስመለጠው ሆነ።

የየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮት፣ መኢሶን በእንደዚህ እንዳለ ፈነዳ። ዕለት በዕለት እየተቀጣጠለ ቀጠለ። መኢሶንንም ሆነ ሌሎቹን የወቅቱን ትንንሽ ተራማጅ ድርጅቶች፣ ምሑራንና ሌሎች ተዋናዮች ሁሉ ከኋላ ኋላው የሚሮጡ አድርጓቸው ተመመ። ዛሬ ተመልሰን ስንመለከተው፣ መኢሶን ከተመሠረተበት ከ1960 ዓ.ም. አንስቶ አነሰ ሲባል የራሱን ይፋ ጋዜጣ አውጥቶ መንቀሳቀስ ነበረበት። በወቅቱ ከነበሩት አንዳንድ ተራማጅ ቡድኖች ጋር የነበረውንም ግኑኝነት ለማጠናከር በይበልጥ መድፈር ነበረበት።

**በአብዮቱ ዘመን**

የመኢሶንን የአብዮቱ ወቅት ተሳትፎ በሦስት ወቅቶችና የትግል ስልት ዓይነቶች ለይቶ ማጤን፤ ይበልጥ ወደዕውነታው ያቀርባል። የመጀመሪያው፣ ከየካቲት 1966 እስከ የካቲት 1967 የነበረው ወቅት ነው። የዚህ ወቅት የመኢሶን ዓቢይ የትግል መሥመር በአንድ ወገን ሕዝባዊውን ንቅናቄ የመደገፍና የማገዝ ነበር። የልጅ እንዳልካቸውንና የልጅ ሚካኤልን ካቢኔዎች የመቃወም፣ የተራማጆች ኅብረት እንዲፈጠር የመጣርና ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መቋቋም የመጥራት ነበር።

የጦር ሠራዊቱ ተቃውሞ እዚህም እዚያም ተሰበጣጥሮ ለመንፈቅ ያህል ካዘገመ በኋላ፤ በሰኔ 1966 ዓ.ም. በደርግ ዓይነት ተዋቅሮ ስልጣንን ጨበጠ። መኢሶንም፣ እስከ የካቲት 1967 ድረስ በነበረው የየዘጠኝ ወራት ዘመን፣ በአንድ ወገን በተቃውሞና ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት በምትኩ እንዲመሠረት በመጥራት ትግል ቀጠለ። በሌላውም ወገን፣ ከተለያዩት ተራማጅ ቡድኖች ጋር በመገናኘት፣ የተራማጅ ድርጅቶች

---

[21] "የአቃቂ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሠራተኞች ሁኔታ" (ትግላችን፣ ቁጥር 2፣ ኅዳር-ጥር 1963፣ ከገጽ 11-17)። "የአውራ ጎዳና ባለሥልጣን ሠራተኞች ትግል" (ትግላችን፣ ቁጥር 4፣ ታህሣሥ 1964፣ ከገጽ 11-32)።

ኅብረት እንዲመሠረት ጣረ። አንዳንዶቹ ቡድኖቻቸውን እያፈረሱ የመኢሶን አባላት ሆኑ። ከሌሎች አንዳንዶች ጋር ተግባራዊ ትብብር ተመሠረተ። ከአሕአፓ ጋር ለመተባበር የተደረገው ጥረት ሳይሳካ ቀረ።

ሁለተኛው ወቅት ከየካቲት 1967 እስከ ሚያዝያ 1968 የነበረው ወቅት ነው። የዚህ ወቅት የመኢሶን ዓቢይ የትግል መሥመር ሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ በሚል የታወቀው ነበር። ወቅቱ መኢሶን በአንድ ወገን፣ የጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥሪን የተወበት፤ እና በሌላው ወገን ከደርግ ጋር ቀጥተኛ ትብብር ሳይመሠርት፤ ለገጠር መሬት አዋጅ መተግበር እና ለዲሞክራሲ የታገለበት ወቅት ነበር። ሦስተኛው ወቅት፣ አንዳንድ የመኢሶን አመራር አባሎች፣ ከሚያዚያ 1968 እስከ ነሐሴ 1969 የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤት አባል ሆነው የታገሉበትን ወቅት ያጠቃልላል።

መኢሶን በዚህ በሦስተኛው ወቅት፣ በየካቲት '66 ት/ቤት እና በተላያዩ ሴሚናሮች የሕዝባዊ ድርጅቶች ንቃተ ሕሊና እንዲጎለብት ሠርቷል። የገበሬዎች እና የሠራተኞች ድርጅቶች እንዲጠናከሩ እና እንዲደራጁ ታግሏል። በአገር አቀፍ ደረጃ ተደራጅተው ጭምር ለጥቅማቸው እና ለመብታቸው እንዲታገሉ፤ የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር እና የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ፌዴሬሽን እንዲቋቋሙ አግዟል። የከተማ ቀበሌ ማኅበራት በተሻል እንዲደራጁ ረድቷል። የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ቆሞ ከኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባሮች ጋር ውይይት እንዲከፈት ጥሯል። በዚህም አኳያ፣ የደርግ አመራር "የኤርትራን ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት" በሚል የታወቀውን የዘጠኝ ነጥብ ፖሊሲ እንዲቀበል እና እንዲያወጣ በማሳመን ረገድ ዋናውን ሚና ተጫውቷል። ከመስከረም 1969 ዓ.ም. ጀምሮ በመኢሶን አባሎች ላይ በርካታ እና ያልተቋረጡ ግድያዎች በኢሕአፓ የታጠቁ የግድያ ቡድኖች እየረገፉ ስልነበርም፤ መኢሶን በመጋቢት 1969 በተካሄደው የትጥቅ ማስፈታት አሰሳ ውስጥ ተሳትፏል። የሶማሊያን ወረራ ለመከላከል በተደረገው ጥረት፣ ሕዝባዊ የሚሊሺያ አባሎችን እየመለመለ ወደ ታጠቅ ጦር ሠፈር አስገብቷል።

ይሁንና፣ መኢሶን ከየካቲት 1967 እስከ ነሐሴ 1969 በሥራ ያዋለው የሂሳዊ ድጋፍ/ገንቢ ተቃውሞ መሥመር፣ በወቅቱ በሠፊው ተከፍተው በነበሩት ሕጋዊ መስኮች እስከ መጨረሻው ድረስ መጠቀም ማለት ብቻ አልነበረም። ሂስንና ድጋፍን እንደተለዋዋጭ ሁኔታው በማፈራረቅ መታገል ማለት ነበር። እንደዚሁም፣ ገንቢ ተቃውሞን ማቅረብ ማለት ነበር። እንደዚሁም ደግሞ፣ "የአብዮትና የፀረ-አብዮት ኃይሎች ሰልፋቸውን ለይተው የሚፋጠጡበት ወቅት በእርግጥ ይመጣል" ላለው ወቅት በተለይ በሕቡዕ መንገዶች የድርጅትንና የራስን የትጥቅ ኃይል ማዘጋጀትና ለሚቀጥለው ትግል መብቃት ማለት ነበር። መኢሶን እነዚህን መሠረታዊ ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ በሥራ ተርጉሟል ለማለት አይቻልም። በዚህ ወቅት በመኢሶን የተፈፀሙትን ስህተቶች በሦስት ዓበይት ጉዳዮች ለማጠቃለል ይቻላል።

አንደኛውና ከሁሉም በፊት፣ መኢሶን ዓባላቱንና ወዳጆቹን በመንግሥት ተቋሞች ውስጥ ጭምር (መሬት ይዞታ፣ አገር አስተዳደር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ጊዜያዊ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ፅ/ቤት፣ የካቲት 66 ፖለቲካ ት/ቤት) ዘርግፎ አሰማራ። ይህን በማድረጉ በአንድ ወገን የሕቡዕ አካሉን ሕልውና በእጅግ አዳከመው። በሌላው ወገን፣ በተለይ ከደርግ ጋር "የፍጥጫው ወቅት" ሲመጣ፤ ዓባላቱና ወዳጆቹ በቀላሉ የሚለዩ፣ የሚጠቁ፣ የሚታፈሱ፣ የሚታሰሩ እና የሚገደሉ ሆኑ።

ነገር ግን፤ መኢሶን በአብዮቱም ዘመን በአንድ ወገን፣ በቅድመ አብዮቱ የሕቡዕ አመላመል ዘይቤው እንደቀጠለ የነበረ ቢሆንም፤ በሌላው ወገን በሕጋዊ መድረክ ተሳትፎው ጭምር እየደረጀ የመጣውን ያህል፣ የአመላመል መሥፈርቱና ሥርዓቱ እየላሉና እየተፋለሱ ሄዱ። ይህም በአንድ በኩል ዘገምተኛ አደራጅ አደረገው። በሌላም በኩል፣ ድርጅታዊ ጓዳውን ለመንገደኞች ጭምር የከፈተ አደረገው። በመሆኑም፣ አንዶንዶች አብዮታዊ ሰደድና የወዝ አደር ሊግ ለተባሉት ድርጅቶች እያደሩ ጭምር ከመኢሶን ከዱ። ሌሎች "ቀይ ፋና" በተባለ ድርጅት ስም ተደራጅተው መኢሶንን የሚያስጠቁና እንደተራማጅ መጻሕፍትመጻሕፍት መደብር ያሉትን ንብረቱን የሚወርሱ ጭምር ሆኑ። ሌሎችም

ራሳቸውን አገለሉ። ነገሮችን ከዚህ አኳያ ስንመለከት የሚያስገርመው፣ እንደዚህ ዓይነቱ በማንኛውም ድርጅት ላይ የሚደርስ ሁኔታ በመኢሶን ላይ መድረሱ አይደለም። ይልቁኑ በእጅግ የሚያስገረመው፤ መኢሶን በአብዮቱ ዘመን የተለያዩ የሥራ ኮሚቴዎችን (የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የወዝ አደር፣ የአርሶ አደር፣ የቢሮክራሲ፣ የሠራዊት፣ የፖለቲካ ት/ቤት) አቋቁሞ የታገለ ሆኖ እያለ፤ የፀጥታና የደህንነት ኣሓድ በጭራሽ ያልነበረው መሆኑ ነው።

ሁለተኛ፣ መኢሶን "የአብዮትና የፀረ-አብዮት ኃይሎች ሰልፋቸውን ለይተው የሚፋጠጡበት ወቅት በእርግጥ ይመጣል" ካለ አይቀር፤ የሚያፈገፍግበትን የገጠር አምባዎች በውል ማቀድና ማዘጋጀት ነበረበት። ይህንን ባለማድረጉ በነሐሴ 1969 ዓ.ም. ያደረገው የትግል ስልት ለውጥ የተዝረከረከ ሆነ። በርካታ ከፍተኛ አመራሮቹ፣ ዓባላቱና ወዳጆቹ በጥቂት ቀናት ውስጥ ተገደሉ። ታፈሱ። ለበርካታ ዓመታት እሥር ተዳረጉ። ሌሎችም ተሰደዱ። በውጭ የነበሩት ዓባላቱና ወዳጆቹም በዚያው ቀሩ። ሦስተኛና ከላይ የተመለከቱት ሁለት ጉዳዮች ውጤት ሆኖ፣ መኢሶን በተለይም የትግል ስልት ለውጥ ለማድረግ ከወሰነበት ከግንቦት 1969 እስከ ነሐሴ 1969 ባለው የአራት ወራት ዘመን በተለይም በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ይፋ ተቃውሞ ለማሰማት ያልቻለ ሆኖ ተገኘ።

አንደኛ፣ የመጋቢት 1969 ዓ.ም. አሰሳ በመካሄድ ላይ እንዳለ፣ የቀበሌ 07 ሊቀ-መንበር የነበረው ግርማ ከበደ እና ግብረ አበሮቹ ዘጠኝ የብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኞችን አረመኔያዊ በሆነ መንገድ ገድለው ሬሳቸውን ራስ መኮንን ድልድይ ሥርና መንገድ ላይ ጣሉ። ግርማ ከበደ እና ግብረ አበሮቹ መጋቢት 24፣ 1969 ዕለት በሕዝብ ፊት በአደባባይ ተረሸኑ። ነገር ግን፣ ግርማ ከበደ ግድያውን የፈፀመበትን ካላሺንኮቭ እንዴት ታጠቀ? ማን አስታጠቀው? ምን ተፈፀመ?

አበራ የማነ አብ ይህንኑ ጉዳይ አስታውሶ እንደገለፀው፤

> "(ግርማ ከበደ) ለአንዳንድ የቀበሌ መሪዎች ለራስ መከላከያ ይሰጥ የነበረው .22 ካሊቤር ፍሎቨር ሽጉጥ እንዲፈቀድለት ለከተማ ቀበሌ ማኅበራት ማደራጃ መምሪያ በፅሑፍ ጥያቄ አቅርቦ ነበር። ይሁንና፣ መምሪያው ባደረገው ማጣራት፣ የግል ባሕሪው አስተማማኝ ባለመሆኑ እና በቀበሌው አመራር ውስጥም በአሠራር አምባገነናዊ አዝማሚያዎች እንደሚታዩበት የከፍተኛ 14 የማኅበር ማደራጂያ ወኪል በመግለጡ፤ የግል ትጥቅ እንዳይፈቀድለት ተወሰነ። ግርማ ከበደ ማኅበራት ማደራጂያ በግል ቀርቦ የግል ትጥቅ እንደማይፈቀድለት ተግልጦለት በተለመደው መንግሥታዊ አሠራር መሠረት በማመልከቻው ግርጌ ይኼው ውሳኔ ሠፍሮ፣ ማመልከቻው ከማኅደሩ ጋር ተያይዞ እንዲቀመጥ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ።"[22]

ይሁንና፣ ግርማ ከበደ ካላሺንኮቭ ለመታጠቅ በቃ። ሌ/ኮ ብርሃኑ ባየህ በዚሁ የካላሽንኮቭ ትጥቅ ጉዳይ ከግርማ ከበደ ጋር አደርኩ ያሉትን ልውውጥ እንደሚከተለው ሲተርኩ ግን፤ የግርማ ከበደን ማንነት በውል ለማጣራት እንኳን አልሞከሩም።

> "አንድ ቀን ወደቤቴ ለመሄድ ወደ መኪናዬ ሳመራ፣ አንድ ወጣት ጫና ጫና እይተነፈሰ እና የሽጉጥ ቀለህ በሁለት እጁ ይዞ ዳገቱን እይለከለከ ወጥቶ መንገድ ላይ ተገናኘን።
> 'ምንድን ነው?' ብዬ ጠየቅሁት፤ ሁኔታው አስገርሞኝ።
> 'ምን በኢሕአፓ አስፈጁን እኮ! እነሱ ኦቶማቲክ ነው ያላቸው። ለእኛ ይህቺን ሽጉጥ ነው የሰጡን። ይኼውና በዚችው ስታኮስ አድሬ፣ በተአምር ነው የተረፍኩት አለኝ።'
> 'የት ነው ለመሆኑ?' ብዬ ጠየቅሁት።
> 'እዚህ ነው፤ አራት ኪሎ ቀበሌ' አለኝ።
> 'የት ነው ታዲያ የምትሄደው?' አልኩት።
> 'መከላከያ ኮሚቴ ነው፤ ሌላ መሣሪያ ቢሰጡኝ አለ።
> 'ና ቆይ' አልኩ እና በትንሽ ወረቀት ለለገሠ ማስታወሻ ፅፌ ላኩት።
> "ስሙን ስጠይቀው ግርማ ከበደ ብሎኛል። የማይረሳ ስም ነበር።"[23]

---

[22] አበራ የማነአብ፣ ለውጥ ናፋቂ ሕይወቴ፣ 2014፣ 78-79

[23] ብርሃኑ ባዩህ፣ ያልታሰበው የሕይወቴ ፈታኝ ጉዞ እና የኢትዮጵያ አብዮት ተሳትፎዬ፣ 2013፣ 439-440

አበራ ቀጥሎ እንደሚለው፣

> “ለሥራ ጉዳይ ተጠርቼ ደርግ ፅ/ቤት ሄድኩ። ከመኪናዬ ወጥቼ መንገድ ሳቋርጥ፣ ከፊት ለፊቴ ግርማ ከበደ ታጣፊ ካላንሺንኮቭ አንግቶ ከአንድ ከፍተኛ የደርግ ባለሥልጣን ቢሮ ወጥቶ በተቃራኒ አቅጣጫ መንገዱን ሲያቋርጥ ተገናኘን። ማየቴን ለማስረገጥ ሳይሆን አይቀርም፤ ጮክ ብሎ ‘ጤና ይስጥልኝ አቶ አበራ’ በማለት ሰላምታ ሰጥቶኝ አለፈ። በወቅቱ ከግርማ ከበደ ሌላ፣ በግሉ ካላሺንኮቭ የታጠቀ የቀበሌ መሪ አላውቅም። በጥበቃ ላይ ለሚሠማሩ የቀበሌ አብዮት ጠባቂዎች ደርግ የፈቀደው አሮጌ ዲሞትፎር ጠመንጃ እንጂ፤ ካላሺንኮቭ አልነበረም።”

ግርማ ከበደ የመኢሶን አባል አለመሆኑን ያረጋገጠው እና ለአብዮታዊ ሰደድ ለመመልመል ያቀደው መጋቢ ሃምሣ አለቃ ለገሠ አስፋው ግን፣ ግርማ ከበደን ካላሽንኮቭ የተሸለመ የመጀመሪያው የቀበሌ ተመራጭ አደረገው። የልብ ልብ የተሰማው ግርማ ከበደም፣ ዘጠኝ የብርሃን እና ሰላም መሥሪያ ቤት ባልደረቦችን ለየትኛውም የመንግሥት አካል ሳያሳውቅ በጥይት ተደብድበው እንዲገደሉ አደረገ። ከዚያም፣ ከግብረ አበሮቹ ጋር ወደ ትምህርት ሚኒስቴር አቀና። ሠራተኞቹን ከየቢሯቸው እያስነዳ አስወጥቶ በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። በቁጥጥር ሥር ከተደረጉት መካከል አንደኛው፣ የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አጎት ናቸው የሚባሉት አቶ አሥራት ወልዴ ነበሩ። ፀሐፊያቸው ወደደርግ ፅ/ቤት ደውላ አቶ አሥራት ወልዴ እና በርካታ የመሥሪያ ቤቱ ባልደረቦች በግርማ ከበደ ትዕዛዝ ከቢሯቸው እየተለቀሙ በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን እና ሕይወታቸው አደጋ ላይ መሆኑን ሪፖርት አደረገች። ሌ/ኮ በርሃኑ ባየህ ቀጥለው እንደፃፉት፣

> “ከመንግሥቱ አጃቢዎች አንዱ፣ የሃምሣ አለቃ ደመቀ ባንጃው፣ በሩን አንኳኩቶ ግባና ‘ጌታዬ የሊቀ መንበሩን ወንድም ያዘዋቸው አሉ። ሰው ደውሎ ቶሎ ካላስለቀቅናቸው ይገድሏቸዋል‘ አለ።
> ‘የት ነው የተያዙት?’ ስለው፤
> ‘ከትምህርት ሚኒስቴር ነው የያዟቸው። እዚያ ነው የሚሠሩት‘ አለኝ።
> ‘ይህ አደገኛ ቀበሌ’ ነዋ!
> ‘አዎ ጌታዬ። እኔ ገብቼ እንዳልነግራቸው ከእንግዳ ጋር ናቸው። እባክዎ እርስዎ ይንገሯቸው‘ አለኝ።
> ‘ማነው ስሙ?’
> ‘አሥራት ወልዴ’።
> ‘ወንድም አይደለማ’
> ‘ናቸው‘።
> “የሰውዬውን ስም በትንሽ ወረቀት ላይ ፅፌ እና መታሠሩን ገልጬ ወደቢሮው ሄድኩ። ወረቀቷን ሰጥቼው ወጣሁ። ወዲያውኑ፣ የቀበሌው ሊቀመንበር እና ሌሎችም ብዙ ሰዎች ተያዙ። አቶ አሥራት ወልዴ እና ሌሎች ብዙ ሰዎች ተለቀቁ”[24]

የአቶ አሥራት ወልዴ እና አብረዋቸው የተያዙት የሚኒስቴሩ ባልደረቦች ሕይወት የሊቀመንበሩ አንጋቾች በወሰዱት አፋጣኝ እርምጃ ሊተርፍ ቻለ። ግርማ ከበደ እና ግብረ አበሮቹ መጋቢት 24፣ 1969 ዕለት በሕዝብ ፊት በአደባባይ ተረሸኑ። የግርማ ከበደን አደገኛ ማንነት እና አካሄድ ቀደም ሲል ለከተማ ልማት ሚኒስቴር የማኅበራት ማደራጃ መምሪያ ያሳወቁት እና ቁጥጥር እንዲደረግበት የጠየቁትም የቀበሌው ተመራጮች አብረው ተረሸኑ። ነገር ግን ወዲያወኑ ደግሞ፤ የአብዮታዊ ሰደድ፣ የወዝ አደር ሊግ እና የማሌሪድ መሪዎች፣ የኢሕአፓ አመራር እና ቢሮክራሲው፣ የግርማ ከበደን አሰቃቂ ግድያ አስታከው “ግርማ ከበደ የመኢሶን አባል ነው” እያሉ አስወሩ። ተደጋግሞ እንደተገለፀው ሐቁ ግን፣ ግርማ ከበደ መቼም ቢሆን የመኢሶን አባል ሆኖ አያውቅም። ሌሎችም፣ “መኢሶን በደርግ የተፈፀመውን የእነግርማ ከበደን ርሸና አሞግሶ መግላጫ አላወጣም” እስከማለት ሄደው ጭምር በመኢሶን ላይ ዘመቱ። ሌ/ኮ ብርሃኑ ባየህም፣ ከኃይሌ ፊዳ ጋር አደረኩ ባሉት ሓተታ በሕይወት የሌለውን ኃይሌ ፊዳን እስከማማት ድረስ ሄደው ፅፈዋል። ኃይሌ የጠየቃቸው ነገር ካለ፤ “በጥድፊያ

---

[24] እንደላይኛው።

የረሸናቸኂቸው ለምንድን ነው?” ከሚል እና በወቅቱ ሁላችንም ስናነሳው ከነበረው ጥያቄ ያለፈን ጉዳይ እንዳልነበር ዕርግጠኛ ነኝ። በወቅቱ የነበረን ድምዳሜም፣ አጣድፈው የረሸኗቸው ግርማ ከበደን ካላሺንኮቭ ያስታጠቀው መጋቢ አምሣ አለቃ ለገሠ አስፋው መሆኑን ለመሸፈን እና መረጃ ለማጥፋት ነው የሚል ነበር።

ሌላም፣ ሚያዚያ 22፣ 1969 ዓ.ም. ከምሽቱ ላይ እና ሌሊቱን በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ሕይወት ተቀጨ። ሚያዚያ 22 እንደሚታወሰው፤ የአዲስ አበባ የቀበሌ እና የወዝ አደር ማኅበራት ትኩረት በማግሥቱ ለሚውለው የወዝ አደሮች ቀን (ሜይ ዴይ) መዘገጃጀት ላይ ነበር። መኢሶንም ምሽቱንና ሌሊቱን ዓባላቱን እና ወዳጆቹን ያሰማራው በሚቀጥለው ቀን በሚከበረው የሜይ ዴይ ሠልፍ ላይ የሚያዙ አርማዎችንና መፈክሮችን በማዘጋጀት እና ሠልፈኞችን በመቀስቀስና በማደራጀት ሥራ ላይ ነበር። ይሁንና፣ የኢሕአፓ አመራር ምሽቱ ላይ በርካታ ወጣቶችን “የሜይ ዴይ ዓመፅ” (insurrection) በሚል ጥሪ አነሳስቶ እና አስታጥቆ ጭምር አስወጣ። ወጣቶቹ የቀበሌ ቢሮዎችን እየወረሩ ሽጉጥ በመተኮስ፣ የእጅ ቦምብ እና ሞሎቶቭ ኮክቴል (በነዳጅ ተሞልቶ እና ተለኩሶ የሚወረወር የጠርሙስ ፈንጂ) በመወርወር አጠቁ። የቀበሌ አመራሮች ወደደርግ ፅ/ቤት እየደወሉ የመከላከያ ኃይል እንዲደርስላቸው ጠየቁ። ከደርግ ፅ/ቤት የተላኩ ወታደሮች በዚያች የሚያዚያ 22 ምሽት ከእጅግም በእጅግ ያልተመጣጠነ የአፀፋ እርምጃ ወሰዱ። በመቶ የሚቆጠሩ ወጣቶችን ገደሉ። በማግሥቱም፣ የታፈሱ እና በእሥር የነበሩ በመቶ የሚቆጠሩ ወጣቶች፣ ቡራዩ እና እንጦጦ ጫካ ውስጥ እይተወሰዱ በጅምላ ተረሸኑ። በሜይ ዴይ ዋዜማ የተካሄደው የኢሕአፓ የታጠቀ ሰልፍ እና የመንግስት ያልተመጣጠነ አፀፋ ተደማምረው ያስከተሉት የወጣቶች ዕልቂት ለመኢሶን አመራርና አባላት ድንገተኛ ዜና ነበሩ።

በርካታ የመኢሶን አባሎችና ወዳጆች በሁለቱም ጉዳዮች ላይ መግለጫ እንዲሰጥ አጠንክረው ጠይቀው ነበር። አመራሩ ግን፣ በአንድ በኩል ንቅናቄው በመጋቢት 1969 ባደረገው ኮንፈረንስ ውሳኔ መሠረት ለትግል ስልት ለውጥ አጣዳፊ ዝግጅቶችን የሚያደርግበት ወቅት መሆኑን በማስመልከት እና፤ በሌላም በኩል ድርጅቱ የሰደድን ምላሽ ለመቋቋም በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ይፋ ግጭትን መጋበዝና ድርጅቱን ማስመታት ይሆናል በማለት፤ ጥያቄዎቹን ሳይቀበል ቀረ። ወደኋላ ላይ አንድ መግለጫ ወጥቶ የነበር ቢሆንም፤ አበራ የማነአብ በተጠቀሰው መፅሐፉ ውስጥ እንዳለው፣ “ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ” እንደሚባለው ዓይነት ከመሆን ያለፈ አልሆነም። መኢሶን በራሱ ላይ የጣለው ያ ዕቀባ ዞሮ ዞሮ ስሕተት እንደነበር፤ በጉዳዩ ላይ እስከዛሬም ድረስ የሚደረጉት ምልልሶች ይመሰክራሉ። ስሕተቱ በርግጥም፤ የመኢሶን ተቃዋሚዎች በመኢሶን ላይ በሃሰት ለሚነዙት ውንጀላ ነዳጅ ያቀበለ እና ዋጋ ያስከፈለ ነበር። የኢሕአፓ ታጋዮች የነበሩ ወጣቶችም፣ የድርጅታቸው አመራር በዚያች ሚያዚያ 22 ምሽት “ሕዝባዊ አመፅ” በሚል ያካሄደው አመፅ ከባድ ስሕተት እንደነበር እየተገነዘቡ የመጡ ይመስላል።

# በ”ያ ትውልድ” ላይ ከሚሰጡት ትችቶች እና አስተያየቶች

### “ያ ትውልድ”

በ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት የተሳተፈው “ያ ትውልድ” እየተባለ ይገለፃል። ስያሜው ምንን እና እነማንን ለማመልከትና ለመግለፅ እንደሚሻ ግን፤ ግልፅ አይደለም። ወይንም እንደሚጠቀሙበት ሰዎችና ቡድኖች የተለያየ ነው። አንዳንዶች የወቅቱን የተማሪ እንቅስቃሴ በጥቅሉ ማለታቸው ይመስላል። ሌሎች በወቅቱ ዓቢይ ሚና የነበራቸውን ተራማጅ ድርጅቶችንና ምሑራንን ለማመልከት የሚጠቀሙበት ይመስላል። የኢሕአፓ አባል የነበሩ ሲናገሩና ሲፅፉ በአብዛኛው የሚያመለክቱት፤ በኢሕአፓ ሥር ብቻ የተሰለፈውን ወጣት ነው። ሕወሓት በበኩሉ “ተራራን ስላንቀጠቀጠ ትውልድ” ደርሷል። ከኤርትራ ግንባሮች እስከ ኦሮሞ፣ አፋር እና ሲዳማ፣ ባሌ እና ኦጋዴን የነበሩት የብሔሮች ቡድኖችም የየራሳቸው የ“ያ ትውልድ” ዝክሮች ይኖሯቸዋል።

በአሰያየሙ ለመግለፅ የሚፈለገው በዘመኑ ተራማጅ ቡድኖች ውስጥ ተደራጅቶ የተሳተፈውን የዘመኑን ወጣት ትውልድ ከሆነ ደግሞ፤ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ለተለያዩ የፖለቲካ ግቦች በተለያዩ መንገዶች የታገለውን የዘመኑን የኢትዮጵያ ትውልድ የሚያጠቃልል መሆን ይኖርበታል። እንደዚህም ከሆነ፤ የእያንዳንዱ ድርጅት (ኢዲሕ፣ አብዮታዊ ሰደድን እና ኢሠፓን ጨምሮ) አዎንታዊና አሉታዊ ሥፍራ እና ሚና በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮት ባሕሪይ እና ሂደት ውስጥ እየተካተተ መመርመር ይኖርበታል። ከዚህም ባሻገር ከየትኛውም ድርጅት እና ቡድን ሳይሆን ለመሬት ለአራሹ የተዋደቀው የገጠር ወጣት መታሰብ ይኖርበታል። ተቃራኒው አካሄድ ራስን በራስ ከማግዘፍ ያለፈ አይሆንም። ራስን በራስ ቡድን ኮሮጆ ውስጥ ዘግቶና አጥሮ ከመከቸች አያልፈም። ተገቢው ትምህርት ተቀስሞ እንዲተላለፍም አይረዳም።

በተጨማሪ፣ በአብዮቱ የተሳተፉት ወጣቶች ብቻም አይደሉም። ጎልማሳው፣ ሽማግሌው፣ ምሁሩ፣ ምዕመናኑ፣ ቄሱ፣ ሼሁ፣ መለዮ ለባሹ፣ አርሶ አደሩ፣ ሠራተኛው፣ ሴቱ፣ ወንዱ፣ የተሳተፉበት ሕዝባዊ አብዮት ነበር። እንደሁኔታው አባትና ልጅም ወይ በተቃራኒ፤ ያለዚያም በአንድ ጎራ የተሰለፉበት አብዮት ነበር። ገበሬዎች፣ ሠራተኞች፣ መለዮ ለባሾች አብዮቱ ያስገኛቸውን ድሎች ለመጠበቅ ደማቸውን ያፈሰሱለት፣ አጥንታቸውን የከሰከሱለት አብዮት ነበር። እነዚህን ከታሪክ ውጭ አድርጎ ስለ አንድ የኢሕአፓ "ያ ትውልድ" መተረክ፣ ታሪክን የጥቂት የማኅበረሰብ እፍታዎች ተፈጣሪና ተደራጊ ዝክር አድርጎ ማነብነብ ይሆናል። የማኅበራዊ-ፖለቲካ ተመራማሪዎች ወደታች ወርደው፣ አርሶ-አደሩና ሠራተኛው ሠፊ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ፊውዳሎችና ቢሮክራቶች ጋር ለመሬት፣ ለአርነትና ለነፃነት ያደረጉትን ትግል የሚዘከሩበት ቀን እንዲመጣ እመኛለሁ።

ነገር ግን በ1983 በኢትዮጵያና በኤርትራ ሥልጣን የጨበጡት የግንባር ድርጅቶችም "የአብዮቱ ትውልድ" አካሎች ናቸው። እንደተቀሩት ሁሉ እነሱም በአብዛኛው ከተማሪው እንቅስቃሴ የመነጩ ነበሩ። በሌላ አገላለፅ ወደሩብ ክፍለ-ዘመን የሥልጣን ባለቤት መሆናቸው ከዘመኑ ታጋይ አካልነት አያስወጣቸውም። ስለሆነም ሥፍራቸውና ሚናቸው በአብዮቱ ዝክር ውስጥ ተካቶ መታየት ይኖርበታል። እንደዚሁም ደግሞ፤ ከዚያ ትውልድ ውስጥ አብዮቱን ተቃውመው የተሰለፉም ነበሩ። ይህ በዚሁ ቢተው፤ አብዮት በአንድ የታሪክ ወቅት የበርካታ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ሁኔታዎች መገጣጠም የሚያዋልደው ክስተት እንጂ፤ የአንድ የሆነ ድርጅት "ትውልድ" ሥራ ስለአለመሆኑ በብዙ የታተበት ነው።

ነገር ግን ሌሎች ደግሞ "የአብዮቱ ትውልድ" የሚባለውን "ብርቅዬ፣ ተተኪ የማይገኝለት" እያሉ ይደርሱለታል። ሌሎችም፣ "ባዕድ ርዕዮተ ዓለምን ያመጣ"፤ "ጥርዝ ነጠቅ"፤ "አንድ ርዕዮተ ዓለም እይተከተለ የተጠፋፋ"፤ "ሕገ መንግሥታዊ ለውጥን የተቃወመ"፤ "የጥፋት መልዕክተኛ" እያሉ ያቀርቡታል። ጉዳዩ የዛሬውንና መጪውን ታጋይ የሚመለከት እንደመሆኑ፤ ከወገነተኝነትና ራስን በራስ ከማግዘፍ መንፈስ ውጭ መታየት አለበት።

## "ብርቅዬ፣ ተተኪ የማይገኝለት ትውልድ"

"ብርቅዬ"፣ "ተተኪ የማይገኝለት ትውልድ" የሚሉት አገላለፆች ችግር አለባቸው። በእርግጥ አብዛኞቹ ታጋዮች የተነሳሱት የግል ጥቅምን በመሻት አልነበረም። ለወገናቸውና ለአገራቸው ባላቸው ፍቅር ነበር። የፍራንስ ፋኖንን አባባል ልዋስና "የኢትዮጵያን ጎስቋሎች" በዙሪያቸው እያዩ ልበ ደንዳና ሆነው ለመኖር ፈቃደኛ ስላልሆኑ ነበር። በሀገራቸው ወደኋላ መቅረትና እንዲያውም በቅርብ ነፃነታቸውን ተቀዳጅተው በነበሩ የአፍሪካ አገሮች መቀደም ስለተቆጩ ነበር። በአገሪቱ ፈልተው የነበሩት የገበሬዎች፣ የሠራተኞችና የብሔሮች ትግሎች የፖለቲካና የኢኮኖሚ መልሶችን ካላገኙ፣ ለአገሪቱ ሕልውና የሚያሰጉ ሁኔታዎች ጭምር ሊከሰቱ እንደሚችሉ በማመናቸው ነበር። ባጭሩ የዜጎቿ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተረጋገጠባትን፣ ጭቆና እና ብዝበዛ የተሻሩባትን፣ ረሀብና ችጋር "የትላንት የሆኑባትን"፣ የሕዝቦቿ አንድነት የፀናባትን እና ብሔር/ብሔረሰቦቿ ተፈቃቅደው በዕኩልነትና በመከባበር የሚኖሩባትን፣

ሕዝቦቿ በጋራ የሚለመልሙባትን፣ የበለፀገችና በዓለም መድረኮች ላይ የተከበረችና የኮራች ኢትዮጵያን ስላለሙ ነበር።

የ1960ዎቹ ታጋዮች ለሕዝብ መወገን፣ ለማኅበራዊ ፍትሕ መቆርቆርና ለውጥን መሻት ተገቢ መሆኑን ያመኑና ያስረገጡ ታጋዮች ነበሩ። ለማኅበራዊ ለውጥ ባላቸው ፅናትና ድፍረት የማይነኩና የማይፈነገሉ ይመስሉ የነበሩትን የአፄውን እና የወታደራዊውን መንግሥታት የተጋፈጡ ነበሩ። በዚህም ለማለት ይቻላል፤ ለዛሬውና ለመጭው ታጋይ የድፍረት፣ የፅናት፣ የለውጥ እና የተደራጀ ትግል ፋና ወጊነትን ቅርስ ትተዋል። መንግሥት የሚባለው ተቋም በሕዝብ ፈቃድ ካልሆነ በቀር እና የሕዝብ ተዓማኒነት ከሌለው፤ ዕድሜው እንደሚያጥር አስገንዝበዋል። በድፍረት ሃሳብን መግለፅ ብቻ ሳይሆን፣ ባንፃሩም ለማኅበራዊ ፍትሕ መቆርቆር እና ለውጥን ለማምጣት መሻት ተገቢ መሆኑን አስጨብጠዋል። ከግል ጥቅም ይልቅ ለዓላማ መስዋዕትነትን ለመክፈል የወሰኑ ነበሩ። ከዚህ አንፃር "ብርቅዬ" ቢባሉ ሊያስኬድ ይችላል። እነዚህም የዛሬውና መጭው ታጋይ በአዎንታዊ ሊቀስም የሚችላቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው።

ሆኖም "ተተኪ የማይገኝለት" በሚለው አገላለፅ ለማለት የሚፈለገው ግልፅ አይደለም። ምክንያቱም በአንድ በኩል፣ "የትግል ነገር በ1960ዎቹ ትውልድ ዘመን አለቀ፤ አበቃ" የሚልን ዓይነት መልዕክት ያዘለ ነው። ወይንም የተከተለው ታጋይ በራሱ ጊዜና ሁኔታ የራሱን ትግል እንደሚያካሂድ እና የራሱን "ብርቅዬዎች" እንደሚያፈራ ያለመመልከት ነው። በሌላ በኩል "የአብዮቱን ትውልድ 'ብርቅዬነት'" በአጅጉ ያደበዘዙትን ከባድ አሉታዊ ገፅታዎች ያድበሰብሳል።

እንደሚታወቀው ግን፣ በወቅቱ የነበሩት ተራማጅ ድርጅቶች በተስማሙባቸው ወይንም ሊስማሙ በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ ለመተባበር የቻሉ አልነበሩም። ይህ ቀርቶ በጥሞና ለመነጋገርና ለመደማመጥ ያልቻሉ ነበሩ። ወይንም የሌላውን የተለየ ሃሳብና አስተያየት ለማክበርም ሆነ ባለመስማማታቸው ተስማምተው በሠላምና በመከባበር ለመለያየት የቻሉ አልነበሩም። ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ፣

> "ሁለቱ ወገኖች (መኢሶንና ኢሕአፓ) ለመወያየትና ትብብርን ለመገንባት በይበልጥ ክፍት ቢሆኑ ኖሮ፤ ልዩነቶቻቸው የማይፈቱ አልነበሩም። (እንደዚሁም ለሥልጣን) ስግብግቡ ኮሎኔል መንግሥቱ ሶሻሊሽታዊ ራዕያቸውንና ፕሮግራማቸውን መቀበሉን በተግባር እሰካሳየ ድረስ፣ እሱን ከሚገዳደር ስልት ተቆጥበው ሠፊውን ሕዝብ በማንቀሳቀስ ላይ አተኩረው ቢሆን ኖሮ፤ ኅብረተሰቡ የአስከፈው ሥርዓት ሰለባ መሆን ይቀርለት ነበር። ትውልዱም ይተርፍ ነበር።"[25]

ብለው ያሉት እጅጉን ዕውነት ነው። "ቢሆን ኑሮ" በማለት ለመቀጠል፣ ቢሆን ኑሮ ከ"ግድያ ሂደት" ላይ አይደረስም ነበር። ምናልባትም፣ የጥር 1969 ሁነት  አይደርስም ነበር። ወይንም፣ ሌላ መልክና ይዘት ያለው ይሆን ነበር።

የአብዮቱ ዘመን ታጋዮች መሠረታዊ ስህተት በእውነትም ለመወያየት አለመፈለጋቸው፣ የሌላውን ሃሳብ አለማክበርና ትብብርን ለመገንባት አለመቻላቸው ነው። ደግሞም መኢሶንና ኢሕአፓ ብቻ ሳይሆኑ፣ በኢትዮጵያ ምድር ከሳህል በረሀ እስከ ትግራይ አምባዎች፣ ከአዲስ አበባ እስከ ሲዳማ ተራሮችና የባሌ ጫካዎች የበቀሉት ድርጅቶች ሁሉ ናቸው፤ ለዚህ የፖለቲካ ብልህነትና ጥበብ ሳይበቁ የቀሩት።

ብቻ እንግዲህ ከግማሽ ክፍለ-ዘመን በኋላም ተገቢው ትምህርት የተቀሰመ አይመስልም። በተቃራኒው የቦርሳ ፓርቲዎች እና የዲጂታል ታጋዮች እየተፈለፈሉ ጭምር መወያየትና መተባበር ተወሳስቧል። የዛሬዎቹ ባለሥልጣናትና ታጋዮች፣ ከ60ዎቹ መሠረታዊ ጉድለት እና ስህተት ተምረው በጥሞና ለመነጋገርና ለመደማመጥ መጣር ይኖርባቸዋል። በሌላው የተለየ ሃሳብና አስተያየት ካልተስማሙ፣

[25] ገብሩ ታረቀ፣ The Red Terror in Ethiopia: An Historical Aberration፣ Journal of Developing Societies፣ June 2008፣ vol. 24፣ 183 (የኔ ትርጉም)።

ባለመስማማታቸው ተስማምተው በሰላምና በመከባበር ለመለያየት የመቻልን ጥበብ የራሳቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከተስማሙም፣ ለመተባበር ቀና የመሆን ስልትን መካን ይኖርባቸዋል። ከዚህም ባሻገር ሄደው፣ የ1960ዎቹም ይሁኑ የዛሬዎቹ እንደዚያ ተውሰብስበው የተገኙት/የሚገኙት ያገሪቱ የፖለቲካ ባህል ባሳረፈባቸው ማሕተም በመተብተባቸው ምክንያት ይሆን/አይሆን እንደሆነ ለመመርመር መጣር ይኖርባቸዋል።

እዚህ ላይ ግን ይህ የኋለኛው ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ጉዳይ እንደሆነ ማስታወስ ይገባኛል። ምክንያቱም ምርምሩ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ተዋናዮች ችግር በመመርመር ላይ እንጂ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ወደማላከክ የሚወስድ መሆን የለበትም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የታሪክ አጋጣሚዎች ፈገግ ባሉለት ቁጥር ስሜቱን፣ ፍላጎቱንና ምኞቱን ከማሳወቅ ቦዝኖ አያውቅም።

**"ባዕድ ርዕዮተ-ዓለምን ያመጣ ትውልድ"**

"ባዕድ ርዕዮተ-ዓለምን ያመጣ" የሚለው ሐተታ ለሆነ አገር በቀል ርዕዮተ ዓለም የሚሟገት ይምሰል እንጂ፤ ሩቅ የሚያስኬድ አይደለም። በመጀመሪያ ርዕዮተ ዓለም፣ ፍልስፍና፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ቴክኖሎጂ ወዘተ.፤ እንኳን በዘመናዊው ዓለም ቀርቶ ከጥንቱም ቢሆን ሁልጊዜም "አገር-በቀል" አይደሉም። ድንበር እያቆራረጡና ከነባር ባህል ጋር እየተዋሀዱ አሻራቸውን በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ የሚያሳርፉ ናቸው።

በኢትዮጵያም የአይሁድ፣ የክርስትና እና የእስልምና ኃይማኖቶች ይሁኑ፤ ፍትሐ ነገሥት ወይንም በተለይ ከአፄ ምኒልክ ጀምሮ የተስፋፋት ዘመናዊ ትምህርት፣ አስተዳደር፣ ባንክ እና ፋይናንስ፣ የሠራዊት አደረጃጀት፣ ቴክኖሎጂና ወዘተ ከውጭ የመጡ ናቸው። ከዝመናው ጋር በተያያዘ ሥነ ፅሑፍ፣ ሙዚቃ፣ የቅብ ስዕሎች፣ ቴያትሮች፣ የስፖርት ዓይነቶች እና ወዘተ. ሁሉ የውጭ ቀመስ ናቸው። የአስተያየቱ አስተጋቢዎች ነገሮችን የሚያዩበት መነፅር፣ ንድፈ ሃሳብ፣ ፅንሰ ሃሳብ፣ የምርምር ዘዴና ቋንቋም እንደዚሁ ከውጭ እንጂ፤ ከዋሸራ ወይንም ከዲማ ጊዮርጊስ ወይንም ከደብረ-ኤልያስ የቅኔ ትምህርት ቤቶችና ከመድራሳዎች የተገኙ አይደሉም። ባጭሩ ታሪካችን በየትኛውም ወቅት በርካታ ገፅታዎች ያሉትን ያህል፤ ተወራራሽና ተለዋዋጭ ነው። ታሪክ ማለትም ይኼው ነው።

በዚሁ ብንቀጥል፣ በአንድ ወገን "ጃፓን እንደምን ሰለጠነች"? እያሉ የወተወቱትን ቀደምት ምሑራን እያሞገሱና አፄ ኃይለ ሥላሴ በራስ ተፈሪ ዘመናቸው አውሮጳን ሲጎበኙ ባገኙት ዕውቀት ታግዘው ጭምር "ተራማጅ" የነበሩበትን ዘመን እያደነቁ፣ በሌላው ወገን የ1960ዎቹን ታጋዮች በባዕድ ርዕዮተ ዓለም አስተናጋጅነት መውቀስ የሚያስኬድ አይሆንም። የ60ዎቹ ተራማጆች በእርግጥ እንደ 1920ዎቹ ነገሥታቱን በነጠላ በነጠላ እየቀረቡ የመምከር እና አስከተቻላቸውም በማገልገል የተሰማሩ አልነበሩም። ፀረ ነጋሢ፣ የተደራጁና ሠፊውን ሕዝብ በማንቃትና በማደራጀት ለመሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ የታገሉ ነበሩ። ይሁንና አገር ወዳድነታቸውና የዝመና ደጋፊነታቸው፤ የ20ዎቹ ምሑራን ወራሾች ያደርጋቸዋል።

ማርክሲዝምን በሚመለከት ሲጀመር መቅረብ ያለበት ዓቢይ ጥያቄ የ60ዎቹ ታጋዮች ለምን ወደ ማርክሲዝም ርዕዮት አዘመሙ? የሚለው ጥያቄ ነው። ጥያቄውን ባግባቡ ለመመለስ የሚቻለውም፤ የማርክሲዝም ርዕዮት በ60ዎቹ በነበረው ዓለም አቀፋዊ ሥፍራ እና ሚና ውስጥ ተካቶ ሲዳሰስ ነው። ተቃራኒው አካሄድ፣ እንደ ማርጋሪት ታቸር እና ዶናልድ ሪገን ቀኝ ዘመሞችን እንደፃድቃን ከማየት እና፤ ግራ ዘመሞችን እንደርኩሳን ከማየት ያለፈ አይሆንም።

ማርክሲዝም በ60ዎቹ ዘመን የፖለቲካ ሥምሪትና አካሄድ ላይ ጉልህ ዓለም አቀፋዊ ባሕሪይና ሚና ነበረው። ከኩባ እስከ ቪየትናም፣ ከስዊድን እሰከ ደቡብ አፍሪካ በነበረው የዘመኑ ታጋይ ወጣትና ምሑራን ላይ ማሕተሙን ያሰረፈና ያስሠረፀ ነበር። ዓለምም ለካፒታሊስትና ለሶሻሊሽት ማኅበራዊ ፖለቲካ በሚታገሉ ጎራዎች የተከፈለች ነበረች። በጎራዎቹና በተቀናቃኞቻቸው መካከል ለፖለቲካ፣ ለኢኮኖሚ፣ ለወታደራዊ እና ለባሕል የበላይነት ከባድ ዓለም-አቀፋዊ ፉክክርና ትንቅንቅ የሚካሄድበት

ዘመን ነበር። የካፒታሊስቱ ጎራ የቺሊውን ፒኖሼና የኮንጎውን ሙቡቱ የመሳሰሉትን እና እንደ ደቡብ ሮዴዢያ (ዚምባዌ) እና ደቡብ አፍሪካ ዓይነቶቹን የዘረኛ አገዛዝ መንግሥታት የሚደግፍ ነበር። የሶሻሊሽቱ ፊና በአብዛኛው ለአገራቸው እና ለሕዝቦቻቸው ብሔራዊ ነፃነት እና አርነት ከሚታገሉት አገሮችና ሕዝቦች ጋራ የተሰለፈ ነበር።

የኢትዮጵያ ተራማጆች የሶሻሊዝምን ጎዳና የራሳቸው አድርገው የአገር ውስጡንና የውጭውን ጭቆናና ብዝበዛ በፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት መሥመር ወደ መታገል አቀኑ። ትግሉ የፊውዳሉን ሥርዓትና የምርት ግኑኝነቶች ለማስወገድ እና ለአገር ክብር እና ልዕልና ነበር። የሶሻሊዝምን ሥርዓት ለማቆም ያለሙትም፣ ሰውን ወይንም አምራች ኃይሎችን ማዕከል ያደረገ እና ለነሱ የወገነ ሥርዓትን ስለተመኙ ነበር። ካፒታሊዝምን የነቀፉት ዓላማው ትርፍ፣ አሁንም ትርፍ በመሆኑ ነበር። የምዕራቡ ዓለም፣ የአፍሪካ፣ የእስያና የደቡብ አሜሪካ ሕዝቦችን የተፈጥሮ ሀብቶች በገዢዎቻቸው አስተናጋጅነት ጭምር መመዝበሩን ስለተቃወሙ ነበር። ጨቋኝ መንግሥታትን በመደገፍ በአፍሪካ፣ በደቡብ አሜሪካና በምሥራቅ እስያ ይካሄዱ የነበሩትን አሰቃቂ ጦርነቶችና የማያባሩ መፈንቅለ-መንግሥቶችን (የኢራን፣ የኮንጎ፣ የጋና፣ የቺሊ....) ይቃወሙ ስለነበር ነው። የኢትዮጵያ ተራማጆች በዚህ ዓለም-አቀፍ አሰላለፍ ውስጥ ከካፒታሊዝም ጎዳና ይልቅ፤ የሶሻሊዝምን ጎዳና የማይመርጡበት ምንም ምክንያት አልነበረም። "ሆኖምም" ይላሉ ሌሎች ቀጥለው፤ "ጥራዝ ነጠቅ ትውልድ" ነበር።

### **"ጥራዝ ነጠቅ ትውልድ"**

"ጥራዝ-ነጠቅ" በሚል ከሚወቅሱት መካከል፣ በአጠቃላይ ስለ ፍልስፍናም ሆነ በተለይ ስለ ፖለቲካ ፍልስፍና ያላቸው ዕውቀትና ግንዛቤ አጠያያቂ የሆነው ጭምር ተሰልፈው ይገኛሉ። በነዚህ ላይ መቆየት አያስፈልግም። ይህ ስለተባለ ግን፣ በጊዜው የነበሩ አንዳንድ ወጣቶች በርግጥም ከባድ ቃላቶችን እየደረደሩና ከዚህም ከዚያም የቦጨቁትን ሐረግ እየደገሙ አይኩራሩም ነበር ማለት አይደለም። ሌሎችም ከማኦ "ቀይ መፅሐፍ" እየጠቃቀሱ "ለተራማጅነታቸው" ማሳያ ያውሉት እንደነበር ይታወቃል። በዘመቻ ጣቢያዎች "ማኦ" እየተባሉ የሚሾፍባቸው ጭምር ነበሩ። በርግጥም ደግሞ፣ ከቅፅሎች አራጋቢነትና ከመፈክሮች ደርዳሪነት ያላለፉ በርካታ ነበሩ። ደግሞ ሌሎች ርዕዮት ዓለሙን የተረዱት ቀኖናዊ በሆነ መንገድ ነበር። ሌሎችም የድርጅትና የመንግሥት ሥልጣንን መጨበጫ መሣሪያ ብቻ አድርገውት ነበር። እነዚህን እያመለከቱ የወቅቱን ታጋዮች በጅምላ "በጥራዝ ነጠቅነት" መፈረጅ ለማጣጣል ይጠቅም እንደሆነ እንጂ፤ ትምህርት ሰጪ አይሆንም። ስለ ጉደለቱና ጥልቀቱ በተጨባጭ ለማወቅ የሚቻለው በርዕሱ ላይ በሚደረግ ጥናት ነው።

ሲጀመር ርዕዮተ-ዓለሙን ጠንቅቆ ማወቅና በሱም መካን ከሁሉም የአብዮቱ ታጋይ የሚጠበቅ አልነበረም። አይደለምም። ሁለተኛ፣ ከወቅቱ ተማሪ ጥቂት የማይባሉት፣ ከንጉሠ-ነገሥቱ ዘመን ጀምሮ ርዕዮተ-ዓለሙን ለማጥናት የተጉ ነበሩ። በአብዮቱ ዘመን ሁኔታዎች ስለፈቀዱ ደግሞ፤ በይበልጥ የተሳቡትና የተነሳሱት ጥቂት አልነበሩም።

ጥቂት የተማሪዎችና ግራ ዘመም ምሑራን በ1950ዎቹ መጨረሻና በ60ዎቹ መግቢያ ላይ የጥናት ክበቦችን ማቋቋም ጀመሩ። የመጀመሪያው ምናልባትም ከ1957 ጀምሮ በሕቡዕ ተደራጅቶ በዩኒቨርስቲው የተማሪ እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሠራ የነበረው እና "ክሮኮዳይልስ" በሚል ስያሜ የሚታወቀው የማርክሲስቶች ቡድን ሳይሆን አይቀርም።[26] "ሶሻሊስት፣ ማርክሲስት፣ ኮሚኒስት" እየተባለ የሚጠቀምባቸው እና የላቀ ምንባብ እና አረዳድ የነበራቸው ግለሰቦችም ነበሩ። ከነዚህም አንዳንዶቹ አቶ ገርማሜ ነዋይ፣ ልጅ ሚካኤል እምሩ፣ ዶ/ር ወርቁ ፈረደ፣ ዶ/ር ከበደ መንገሻ፣ ፕሮፌሰር

---

[26] ባሕሩ ዘውዴ The Quest for Socialist Utopia (2014፣ 114) በተሰኘው መፅሐፋቸው ውስጥ እንደዘረዘሩት፤ የክሮኮዳይልስ ቡድን ኣባላት ብርሃነ መስቀል ረዳ፣ ዘርዑ ክኸሸን፣ ገብሩ ገብረወልድ፣ ኃይሉ ገብረዮሐንስ፣ ታዬ ጉርሙ፣ ስዩም ወልድዮሐንስ፣ ዮሐንስ ስብሃቱ፣ ሚካኤል አበበ እና ሀብተጊዮርጊስ ሙላት ነበሩ።

ሐጎስ ገብረየሱስ፤ ዳንኤል አደራ፣ ኃይሌ ፊዳ፣ ኢብሳ ጉተማ፣ ሺፈራው ጃሞ፣ ዶ/ር እንድርያስ እሸቴ፣ ዶ/ር መለሰ አያሌው፣ ዶ/ር እሸቱ ጮሌ፣ ነጋ አየለ፣ ዶ/ር ዮናስ አድማሱ እና የአንዳንድ ጥናት ክበቦች አባላት ነበሩ።

የሆነው ሆኖ ማርክሲስት/ሶሻሊስት መጻሕፍትና ፅሑፎች በኢትዮጵያ ምድር በቀላሉ የሚገኙበት ዘመን አልነበረም። በውጭ ይገኙ የነበሩት ተማሪዎችና ምሑራን በአንፃሩ ፍልስፍናውን በየሚገኙበት የትምህርት ተቋሞች ይማሩት ነበር። መኢሶንም የተፈጠረለትን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ዝነኛውን "ተራማጅ መጻሕፍትመጻሕፍት ቤት" አቋቁሞ በሺዎች የሚቆጠሩ አብዮታዊ መጻሕፍትመጻሕፍት ወደሃገር በማስገባት የበኩሉን አስተዋፃኦ አበረከተ። መጻሕፍቶቹንና ፅሑፎቹን ከየመደብሩ የሚገዙት ሳይገላመጡ ነበር። በጥናት ክበቦች የሚሰበሰቡትና የሚያጠኑት ፀሐይ እየሞቃቸው ነበር። ስለነበርም በተነፃፃሪ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ የማግኘት ዕድል ተፈጠረ።

ርዕዩተ ዓለሙ በአብዮቱ ዘመን በነፃ ለመስፋፋት ሕጋዊ አጋጣሚ አገኘ። መጻሕፍቱና ፅሑፎቹ በብዙ ሺህ እየገቡ ተሠራጩ። በፖለቲካ ት/ቤት፣ በሴሚናሮች፣ በውውይይት መድረኮች፣ በመንግሥት ጋዜጦችና በከፊል ሕጋዊ መፅሔቶች (ጎህ፣ አዲስ ፋና)፣ በራዲዮ ፕሮግራሞችና በትርጉም ዕትሞች ተስፋፋ። ሌሎችም ወደምሥራቁ ዓለም እየተላኩ የርዕዮተ ዓለሙ ተቋዳሾች ሆኑ።

ይሁን እንጂ፤ የአብዮቱ ዓመታት ድርጅቶች ለመደራጀትና ለማደራጀት በሠፊው የሚሮጡበት ወቅት ስለነበር፤ ግንዛቤው ሥር ለመስደድ አልበቃም። በዚህ ላይ "የግድያ ሂደት" የተባለው የኢሕአፓ የግድያ እርምጃና "ቀይ ሽብር" የተባለው የኮሎኔል መንግሥቱ የመንግሥት ሽብር መረን አጥተው ሲፈፀሙ፤ ርዕዮተ ዓለሙን በተመለከተ ይደረጉ የነበሩ ጥናቶችና ውይይቶች ሰለሉ። በተካሄደው የመንግሥት ሽብርም፣ የማርክሲዝም ርዕዮት ተከታይ የነበረ ወጣትና ምሁር ተገድሎ፣ ታሥሮና ተሰዶ ተነነ። አብዮቱ ያበቀላቸው የገጠር፣ የከተማና የሙያ ሕዝባዊ ድርጅቶች የመንግሥት አካሎች እየተደረጉ ነፃ ሕልውናቸውን ተገፈፉ።

የኋላ ኋላም አብዮታዊ ሰደድ፣ ተባባሪዎቹ ድርጅቶችና ግለሰቦች "አብዮታዊ መሪያችን፣ ከሊቀ-መንበር መንግሥቱ ጋራ ወደፊት" እያሉ የሥልጣን ማረጋገጫና ማጠናከሪያ መሣሪያ አደረጉት። በመጨረሻም፣ ማርክሳዊ ርዕዮተ ዓለም የኢሠፓአኮ እና የኢሠፓ ቢሮክራሲ መላበሻ ሆኖ አበቃ። ቢሮክራሲውም እግዜር ይስጥልኝን በ"ቁስ-አካል ይስጥልኝ" እየተካ ተሿሿፈበት። ሌላው ወጣት በሕወሓቱ ማሌሊት ዓይነት በትግራይ ምድር ናኘ። በ1983 "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ተብሎ፤ የሥልጣን መጨበጫና ማረጋገጫ መሣሪያ ሆነ። የኢሕአዴግ ማኅበራዊ-ፖለቲካ ርዕዮተ ዓለማዊ መመሪያ ሆነ። ስለማርክሲዝም በኢትዮጵያ ባመርቂ ለማወቅ የሚቻለው የተመለከቱት ጉዳዮች ይዘትና ክንዋኔ ባግባቡ ሲጠና ነው። "ይሁንና" ይላሉ ሌሎች፤ "ያንኑ አንድ የማርክሲዝም ርዕዮተ-ዓለም ይከተሉ የነበሩ ቢሆኑም፣ ተጋጩ፤ ተጠፋፉ።"

## "አንድ ርዕዮተ-ዓለምን እየተከተለ የተጠፋፋ ትውልድ"

ይህም እንደላይኛው የአስተዋይ ትችት ይምሰል እንጂ፤ መሠረት ያለው አይደለም። ሲጀመር ፍልስፍና፣ ዕምነት፣ ርዕዮተ-ዓለም፣ ፖለቲካ… ሁልጊዜም አከራካሪ ናቸው። ሰዎች/ቡድኖች አንድ ዓይነት የኃይማኖትም ሆነ የማኅበራዊ ፖለቲካ አመለካከት የያዙ ቢሆኑም፤ በትንታኔ እና በትርጉም መለያየት እና መጋጨት በመላው ዓለም ሁሌም የነበረ፣ ያለና ሁሌም የሚኖር ነው።

በአገራችንም በ15ኛው ክፍለ ዘመን በአባ እስጢፋኖስ ተከታዮችና በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ መንግሥት ካህናት መካከል የከረሩ ልዩነቶች ነበሩ።[27] በ19ኛው ክፍለ ዘመን በተዋህዶ አማኞች ዘንድ ሦስት ልደት፣ ሁለት ልደት፣ ካራ በሚባሉት ተከታዮች መካከል የከረሩ ፍጭቶች ተካሂደዋል። በ17ኛው ክፍለ ዘመን

[27] ጌታቸው ኃይሌ፣ ደቂቀ እስጢፋኖስ፣ 1996።

አውሮፓም፣ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት ክርስትያኖች መካከል የ30 ዓመታት ጦርነቶች ተካሂደዋል። በእስልምና አማኞች ዘንድ፣ በሱኒና በሺያ ተከታዮች መካከል እስከዛሬም ያልበረደ ግጭት ይካሄዳል። ወደ ማርክሲዝም ስንመጣ በሌኒን እና ፕሌካኖቭ፣ ቡካሪን እና ካውትስኪ፣ በስታሊኒስቶች እና ትሮትስካይቶች፣ በአልባኒያ እና ቻይና፣ ዩሮ ኮሚዮኒዝም እና ሶቪየት ኅብረት፣ በቻይና እና ሶቪየት ኅብረት፣ ወዘተ. መካከል የነበሩትን ልዩነቶች ለማስታወስ ይቻላል። በኢትዮጵያ የአብዮቱ ዘመን፣ "ያንኑ አንድ የማርክሲዝም ርዕዮተ-ዓለም ይከተሉ የነበሩት" ታጋዮች የተለያዩት አንዳንዶች አቃለው እንደሚያቀርቡት "በላብ/ወዝ-አደር" እና "በያሸንፋል/ያቸንፋል" አይደለም። የወቅቱን ሁኔታ በማርክሳዊ የትንተና ዘዴ ተንትነው በደረሱበት ድምዳሜና በቀየሱት የትግል ስልት ነበር የተለያዩት።

ማርክሲዝም ለወቅቱ የኢትዮጵያ አገራዊ፣ ቀጠናዊና ዓለም-አቀፍ ሁኔታ በሚመጥንና ለሠፊው ሕዝብ ጥቅምና ዕድገት በሚያግዝ መንገድ እንዴት በሥራ ላይ ይዋል? የተራማጆች ሚና ከረዥሙ የሕዝብ ዘላቂ ጥቅም አኳያ ምንድን ነው? ሕዝባዊ ሥልጣን ባቋርጭ ሳይሆን በአስተማማኝና በዘላቂ እንዴት የሕዝብ ይሆናል? ሕዝባዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ምን ማለት ነው? የተገኙ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የሕዝብ ድሎች ከድርጅታዊ ጥቅም ባሻገር እንዴት ይታያሉ? የኢትዮጵያ ሕዝቦች ተከባብረውና በእኩልነት የሚኖሩበት ፖለቲካዊ ማኅበራዊ ሥርዓት ምን ዓይነት ሊሆን ይገባዋል? ወዘተ በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ነበር።

የደርግ ሥርዓት ፋሺስት ነው/አይደለም? በዕድገት በኅብረት ዘመቻ እና የገጠርን መሬት አዋጅ ለመተግበር፣ ከደርግ ጋር ጊዜያዊ ትብብር ማድረግ ይቻላል/አይቻልም? ከኤርትራ ግንባሮች ጋር መተባበር ይገባል/አይገባም? በሙያ እና በሕዝባዊ ድርጅቶች ነፃነት፣ በኤርትራ እና በብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄዎች የፖለቲካ መፍትሔ፣ "በትምህርት ከድል በኋላ" ቅስቀሳ፣ በፖለቲካ ግድያ እና በከተማ ትጥቅ ትግል፣ በሕዝባዊ ሚሊሺያ አመራር፣ በውጭ ድጋፍ ፖሊሲ፣ በብሔራዊ ነፃነትና በራስ የመተማመን ጥያቄዎች ወዘተ. ዙሪያ በነበሩ የትንተና እና የትግል ስልት ልዩነቶች ነበር።

የተለያዩ የፖለተካ መስመሮችን ነደፉ፤ ተከተሉ፤ ተገበሩ። ትምህርት ሰጪ የሚሆነው በነዚህ ጉዳዮች ረገድ የነበሩት ልዩነቶች ሲስተዋሉና ሲገናዘቡ ነው። በየወቅቱ ተጨባጭ አገራዊ፣ አካባቢያዊና ዓለም-አቀፋዊ ሁኔታዎች ውስጥ ተካተው እና በመረጃዎች እየተደገፉ ሲመረመሩ ነው። አሁን ከሃምሳ ዓመታት በኋላ፣ እያንዳንዱ ድርጅት ያደረገውን (ያላደረገውን) ትንተና፣ የወሰደውን አቋምና የተከተለውን የትግል ስልት ለያይቶ መፈተሽ፤ ከወገናዊነት የፀዱ የነፃ ተመራማሪዎች ፈንታ ይሆናል።

## "ሕገ መንግሥታዊ ለውጥን የተቃወመ ትውልድ"

አሁን የአብዮቱ 50ኛ አመት በሚታሰብበት ወር፣ "ያ ትውልድ" ሕገ መንግሥታዊ ለውጥን የተቃወመ ነበር" የሚል ሂስ አዘል ጥያቄ ተደጋግሞ ሲሰነዘር ይሰማል። በእኔ አተያይ፣ ጥያቄው የፖለቲካ ለውጥን ወይንም የፖለቲካ አብዮትን ከማድረግ ምን አገዳቸው? በሚል መቅረብ ያለበት ለቅደመ 1966 ባልሥልጣኖች (ገዢ መደቦች) እንጂ፤ ለአብዮቱ ዘመን ታጋዮች አይደለም። ምክንያቱም አንደኛ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እና ምሑራን የማኅበራዊ ፖለቲካ ለውጥ (ሪፎርም) እንዲደረግ ቢያንስ ለአሥር ዓመታት ያህል በመጠየቅ ታግለዋል። ሁለተኛ፣ የየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮቱ በፈነዳበት ዓይነት የፈነዳው አንድም፤ የቅደመ 1966 የኢትዮጵያ ገዢ መደቦች እንደ እንግሊዝ እና ጃፓን ለምሳሌ፤ አንድም የፖለቲካ ለውጥ ወይንም ሪፎርም፣ ወይንም የፖለቲካ አብዮት ሳያደርጉ በመቅረታቸው ነው። ስለዚህም ነው ደግሞ፤ በአንፃራዊ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሥር ነቀል ማኅበራዊ አብዮት (radical social revolution) ወደ መሆን ያመራው። ስለዚህም፣ መጠየቅ እና መመርመር የሚገባው ይልቁኑ፤ የቅደመ 1966 ኢትዮጵያ ገዢ መደቦች የፖለቲካ ተፈጥሮ እና ይዘት እንጂ፤ "ያ ትውልድ" አይደለም። ከዚህም ጋር በተያያዘ፣ የንጉሡ ነገሥቱን ባለሥልጣናት ጭምር የፖለቲካ ለውጥ ወይንም ሪፎርም እንዲደረግ የወተወቱት ሁሉ እና ፍፃሜው መታወስ ይኖርበታል።

የሪፎርም እርምጃዎች እንዲወሰዱ ካሳሰቡት ምሑራን መካከል ቀደምቶቹ፤ በኋላ “ጃፓናይዘርስ” የተባሉት እነነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ ጳውሎስ መናመኖ፣ አቶ ከበደ ሚካኤልን የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል።[28] ከንጉሠ ነገሥቱ ባለሥልጣናት መካከል የመጀመሪያውም፤ በ40ኛው ዓመት ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልድጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ ሳይሆኑ አይቀሩም። እርሳቸው ከሥልጣናቸው ተነስተው፣ የሲዳማ አስተዳዳሪ ተደረጉ። በ1943 በቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ፣ በ1953 በነዋይ ወንድማሞቾች እና በኋላም በደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት የተሞከሩት መፈንቅለ መንግሥቶችም፤ የሪፎርም አስፈላጊነትን ጥሪ ያጮሁ ደወሎች ነበሩ። እንደሚነገረው ከሆነም ደግሞ፤ በ1958 ዓ.ም. ላንጋኖ ላይ ተሰብስበው የነበሩ አራት ባለሥልጣኖች ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው ጭምር አሳስበው ነበር።[29] ልዑል ራስ ዕምሩ ኃይለሥላሴን፣ አቶ ሀዲስ ዓለማየሁን፣ ቢትወደድ ዘወዴ ገብረሕይወትን፣ ጄ/ል ከበደ ገብሬን እና አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄን የመሳሰሉ ሊበራል ባለሥልጣኖችም፤ የሪፎርም እርምጃዎች እንዲወሰዱ በተለያዩ መንገዶች ወትውተው ነበር። የአገር አስተዳደር ሚኒስትር የነበሩት ቢትወደድ ዘወዴ ገብረሕይወት፣ በ1963 ዓ.ም. ቢያንስ የአስተዳደር ሪፎርም እንዲደረግ ጥረው ነበር። ይሁንና፣ በመኳንንቱ ተቃውሞ ሳይሳካ ቀረ። ቢትወደድ ዘወዴ ገብረሕይወትም፣ እንደ ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልድጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ የሲዳማ አስተዳዳሪ ተደረጉ።

አንዳንዶች “ቢሆንም” ይላሉ፤ “ተማሪው፣ ምሁሩ እና ተራማጆቹ ፋታ ነሷቸው እንጂ፤ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ሕገ መንግሥታዊ ለውጥ (ሪፎርም) ለማድረግ ሞክረው ነበር።” ይህ እስከተወሰነ ድረስ ዕውነት ቢሆንም፣ የልጅ እንዳልካቸውን መንግሥት በዋነኝነት ፋታ የነሳው ይልቁኑ፤ የለውጥ ሙከራቸው “ሠርገኛ ደረሰ” እንደሚባለው ሕዝባዊው አብዮት ወደ ሥር ነቀል ማኅበራዊ አብዮት አቅጣጫ ከነጎደ በኋላ የተሞከረ ለውጥ ወይንም ሪፎርም ስለነበረ ነው። በሌላውም በኩል በአንድ ወገን፣ በገዢው ክፍል ውስጥ ይካሄድ የነበረው መሰነጣጠቅ እና እርስ በርስ መጠላለፍ እና፤ በሌላውም ወገን የሠራዊቱ ከሥራቸው በማፈትለኩ ምክንያት፤ የፖለቲካ መሠረት እና ጡንቻ ያልነበራቸው ስለነበሩ ነበር።[30] ሆኖም፣ ሌሎች ደግሞ ይቀጥላሉ፤ የ60ዎቹን ታጋዮች “መዓት ያመጣ የጥፋት መልዕክተኛ ትውልድ” እያሉ ይወቅሳሉ።

### “የጥፋት መልዕክተኛ ትውልድ”

የአብዮቱ ተሳታፊ ድርጅቶች በርግጥ በርካታ ጉድለቶች ነበሯቸው። ሁሉም ስህተቶችንና ጥፋቶችን ፈፅመዋል። ስለዚህም፣ ሁሉም ተዋናይ ድርጅቶች በየደረጃው እና በግልም ሆነ በጥቅል ተጠያቂነት አለባቸው። ይሁን እንጂ የ1966 ዓ.ም.ን የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ያገነፈሉት ሁኔታዎች ከአብዮቱ ጥቂት ተራማጅ ምሑራን አዕምሮ ውስጥ የፈለቁ አይደሉም። ከየድርጅቶቹ ፍላጎት የመነጩም አልነበሩም። ዋናው ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ገዢዎች የዘመናቸው ሁኔታዎች ይጠይቋቸው ለነበሩት በርካታ የጥገና ለውጥ ጉዳዮች መለስተኛ እርምጃዎችን እንኳን በጊዜው እና በአግባቡ

---

[28] ዓለማየሁ ገዳ፣ Ethiopian Macroeconomic Modeling in Historical Perspective፣ 2004። ዓለማየሁ ገዳ፣ የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ መሠረታዊ የኢኮኖሚክስ አስተሳሰቦች፣ 2013። ባሕሩ ዘውዴ፣ Pioneers of Change In Ethiopia፣ 2002።

[29] አራቱ ባለሥልጣናት እነማን እንደነበሩ በውል አይታወቅም። አንዳንድ ምንጮች ጄ/ል ዓቢይ አበበን፣ ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያትን፣ አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያን እና ኮሎኔል ታምራት ይገዙን ይዘረዝራሉ። ሊሎች ምንጮች፣ ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት፣ ልዑል ራሥ አሥራተ ካሣ ጄ/ል መርዕድ መንገሻ እና ኮ/ል ታምራት ይገዙ ነበሩ ይላሉ።

[30] የዛሬ ሠላሳ ዓመት ገደማ ይሆናል፤ አንድ ዘመዴ “የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ድንጋይ ወርውራችሁ ጣላችሁት አይደለም። ‘ልጅ ያቦካው’” እያለ ወረደብኝ። ስንሰነባበት፣ “ጋሼ! የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ተማሪ ድንጋይ ወርውሮ ከጣለው እኮ! መንግሥታቸው በሕይወት አልነበረም ማለት ነው” ብዬው ተለያየን።

ሳይወስዱ መቅረታቸው ነው። ስለሆነም፤ የጊዜ ጉዳይ እንጂ፤ ሥርዓቱ ከፖሊሲ ቀውስ ውስጥ ሰምጦና የአገዛዙ የሥልጣን መሠረቶችና አንጓዎች ተናግተው የሚገኙበት ሁኔታ እንደሚከሰት፤ የንጉሡ ነገሥቱ ባለሥልጣኖች የነበሩ ጭምር ቀደም ሲል ጀምሮ ያስተዋሉት እና ያሳሰቡት ጉዳይ ነበር።

ንጉሡ ነገሥቱ አንደኛውንም ሳይቀበሉ እንዳሉ፣ የየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮታዊ ንቅናቄ ገንፍሎ ተነሳ። የአገሪቱ አጠቃላይ ሁኔታ እንደነበረው ለመቀጠል ከማይችልበት ጫፍ ላይ እንደደረሰ ያበሰረ ክስተት ነበር። ጥያቄዎቹ፣ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ጥያቄዎች ነበሩ። ከረሀብና ዕልቂት ፣መታረዝ፣ የጭሰኛና የሠራተኛ የምርት ግንኙነቶች መለወጥና መሻሻል፣ መሬት ለአራሹ፣ ፍትሕና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍኑ፣ የዲሞክራሲ፣ የፅሑፍ፣ የመሰብሰብና የመደራጀት መብቶች መታወቅና መከበር፤ የብሔሮች፣ የኃይማኖቶችና የፆታዎች ዕኩልነት መከበር እና የሰላምና ዕድገት መረጋገጥ ወዘተ ነበሩ።

ባጭሩ እነዚህን ነባራዊ ጉዳዮች ወደ አዕምሮ ከመጥራት ይልቅ እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከየካቲት በፊት የተደራጁና ያልተደራጁ፣ ከመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች አንስቶ እስከ የታጠቁ አመፆች የሚደርሱ ትግሎች ሲካሄዱ እንደነበር ከማስታወስ ይልቅ፤ የተማሪውን ንቅናቄና ምሁራኑን "መዓት የጠራ" አድርጎ በመፈረጅ ማቆም፤ ለዛሬውም ሆነ ለወደፊቱ አይበጅም። ለውጥ ማኅበራዊ ሕግ መሆኑን መቀበልና ተፃራሪው ከመሆን ይልቅ አራማጁ መሆን የሚሻለው ።

ይህንን ሳይቀበሉ ራስን በራስ እያንቆለጳጰሱ መተራረክ በባዶ ሜዳ መናኘት ይሆናል። ድክመቶችንና ስህተቶችን ሳይታከቱ ከመመርመር ይልቅ፤ በራስ እርካታ መጎፉነን ይሆናል። ከመጋቢት 2010 ወዲህ "አሉታዊ አስተሳሰብ" እያሉ እና "የአዕምሮ ውቅር" እያሉ መሠረታዊ የፖለቲካ ጥገናዊ ለውጦችን (ሪፎርሞችን) ከሚጠይቁ ዓቢይ ጉዳዮች ፊት መወናኘትም፤ የሰጎኗን ፖለቲካ መጫወት ነው። የጊዜ ጉዳይ ይሆናል እንጂ፤ ሁኔታዎች እንደነበረው ለመቀጠል ከማይችሉበት ጫፍ ላይ ይደርሳሉ። የለውጥ ጥያቄዎችና ንቅናቄዎች ዛሬና ነገ በማይታሰበው ሁኔታና መንገድ ይከሰታሉ። በዚያን ሰዓት፣ "ሥርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ" ለሚለው ፖለቲካ ፋታም አይገኝ።

# ለሂሳዊ ዳሰሳ እና ፍተሻ

**ማርክሲያዊ ርዕዮተ-ዓለም**

የማርክሲዝም ተከታይ የነበረው የ1960 ተራማጅና ምሁር፣ ማኅበራዊ ዕኩልነት የሠፈነበትን የሶሻሊስት ኅብረትተሰብ ለመገንባት የነበረው ተስፋና ሕልም ከዳር አልደረሰም። ማርክሲዝም ዛሬ ዛሬ በአንዳንድ አከባቢ እንዲያውም፣ እንደ አሳፋሪ ጉዳይ አንገት ሲያስደፋ ይስተዋላል። እንደሚታየው እና እንደሚሰማውም፣ የምዕራቡ ለዝብተኛ ዲሞክራሲ ፍፁም እንደሆነ ዓይነት ከጭፍን ዕምነት ውስጥ የመዘፈቅ አዝማሚያ አለ። እንዲያውም ዛሬ ዛሬ፣ ከሊበራሊዝም፣ ኔዮ-ሊበራሊዝም፣ መደመር፣ ብልፅግና፣ የአዕምሮ ውቅር፣ አሉታዊ አስተሳሰብ ወዘተ ድረስ ሁሉ፤ 'ሁሉም ያስኬዳል' በሚል መንፈስ ዓይነት እንደተመቸ እየተሄደ ያለው አንድም፤ 'ማርክሲዝም በኢትዮጵያ' በሚል ሂሳዊ ግምገማ ባለመካሄዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ትምህርትን ለመቅሰም እንዲቻል ይህ ጉድለት መታረም እና ማርክሲዝም ባጭር ጊዜ የኢትዮጵያ ቆይታው የፈየደውንና ያልፈየደውን ለተከተለው ታጋይ ማስተላለፍ ይገባል።

ማርክሲዝም የታሪክ፣ የፍልስፍና፣ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ እና የሥልጣን ጥያቄዎችን በሂሳዊ መንገድ የሚተንተን ሥነ ዘዴ ነው። ስለሆነም፤ ታሪክንና የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለመመርመር እና ለመረዳት ጥሩ የትንተና መሣሪያ ነው። ሂሳዊ ንድፈ-ሃሳብ (critical theory) እንደመሆኑም፤ ራሱን ጭምር ለመመርመር ክፍት ነው። ማርክሲዝም ይህንን ባሕሪዩን ሲገፈፍ ነው፤ ቀኖና የሚሆነው። የሥልጣን መጨበጫ መሣሪያ ብቻ የሚሆነው። የአብዮቱ ዘመን ጉድለቶች/ስህተቶች/ጥፋቶች/መጠፋፋት ዓቢይ ምንጭ አንድም፤ አንዳንዶች ማርክሲዝምን ቀኖናዊ በሆነ መንገድ መረዳታቸው እና የድርጅትም ይሁን የመንግሥት ሥልጣን መጨበጫ መሣሪያ ብቻ አድርገው፣ ወደ ተግባር ለመተርጎም በመንደርደራቸው ነበር።

ለምሳሌ ያህል፣ የአብዮቱ ታጋዮች ለመደቦች ትግል ተነሳሱ፤ ተሰለፉ። ይሁን እንጂ፣ የ1960 ኢትዮጵያ የመደቦች አቀማመጥና የዕድገት ደረጃ የተተነተነው በግርድፉ ነበር። ወይንም "ያለ መደብ ንቃተ-ሕሊና መደብ የሚባል የለም" የሚለውን ዓይነተኛ ማርክሳዊ መመዘኛ በውል ያጤነ አልነበረም። ወይንም መደብ እየተባሉ ይመደቡ የነበሩትን ማኅበራዊ ክፍሎች፣ መደብ ሊያሰኝ የሚያስችላቸውን የንቃተ ሕሊና እና የድርጅት ይዘት እና ደረጃ የመረመረ አልነበረም። ስላልነበረም፤ ትንተናዎቹ ሰዎች (መደቦች) ከመደብ ምድባቸው ባሻገር በባህል፣ በልማድና ወግ፣ በትውፊት፣ በኃይማኖትና ዕምነት፣ በዝምድና፣ በጓደኝነት እና በአብሮ አደግነት፣ በስነ-ልቦና ተፈጥሮ፣ በብሔር፣ በአገር፣ በወንዝ፣ በመንደር፣ በጎጥ እና በሠፈር ልጅነት፣ በማኅበራዊ ግኑኝነቶች መደጋገፎች፣ በዕድር፣ በዕቁብና የውለታ ግዴታዎች ወዘተ የሚተሳሰሩበትን ውስብስብ ማኅበራዊ እና ሰዋዊ ዕውነታ ያካተተ አልነበረም።

ይህ ባለመደረጉ በብዙ ሥፍራ ብዙ መደነጋገሮች ተከስቱ። ፕሮፌሰር ጴጥሮስ ቶጃ የጭድ እሳት በተባለው መፅሐፉ እንደገለፀው ለምሳሌ፤ ዘማቾችና የመንግሥት ሠራተኞች የገጠር መሬትንና የቤቶች ውርስ አዋጆችን ወደ ሥራ በሚተረጉሙበት ወቅት ጨቋኝ/ተጨቋኝ፣ በዝባዥ/ተበዝባዥ የሚባሉትን ለመለየት መወናበድ እና ችግር ነበር።[31] በሌሎች ሥፍራዎችም ጭቁን እና ተበዝባዥ የተባለው ክፍል ጨቋኝና በዝባዥ ከተባለው ጋር እየተሰለፈ ሲገኝ ብዥታዎች እና መደነጋገሮች ደረሱ። በሠራተኛውም ክፍል አንዳንድ የማኅበሩ ተቀጣሪዎች በሠራተኞች ማኅበር ስም የሚያወጧቸው ውሳኔዎች የላብ አደሩ መደብ እንደተቀዳጃቸው የመደብ ንቃተ ሕሊና እየተቆጠሩ ተዳነቁ። ከበርቴ፣ ንዑስ-ከበርቴ እና ቢሮክራሲ በተባሉት መደቦችም ላይ፤ ከባድ አሉታዊ ቅስቀሳ እና ዘመቻዎች ተካሄዱ።

የ60ዎቹ ታጋይ ሌኒንን በመከተል በግንባር ቀደም ፓርቲ ለሚመራ የላብ/ወዝ አደር አምባገነንነት መሥፈን ጠንክሮ ታገለ። ግንባር ቀደሙ ፓርቲ ግን፣ የሌኒንን ራሽያ ጨምሮ በሌሎች አገሮች እንደደረሰው ሁሉ

[31] ጴጥሮስ ቶጃ፣ የጭድ እሣት፣ 2014።

በላብ/ወዝ አደሩ ስም እና በምትኩ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ተሆነ እንጂ፤ ላብ/ወዝ አደሩ የሥልጣን ባለቤት አልሆነም። የ60ዎቹ ኢትዮጵያ የአቃቂ፣ የድሬዳዋና የአስመራ ጥቂት ላብ/ወዝ አደሮችም ከአርሶአደሩ ጋር አብረው የሥልጣን ባለቤት ሊሆኑ የሚችሉ አልነበሩም። እንዲያውም ለማለት ይቻላል፤ ያ የንጉሠ ነገሥቱንና የደርግን፣ የአብዮታዊ ሰደድን፣ የኢሠፓአኮን፣ የኢሠፓን አምባገነንነት ለመታገል የተነሳሳው ታጋይ ለሠፊው ሕዝብ መወገኑ ክቡር ሲሆን፤ ማንኛውንም ዓይነት አምባገነንነት ለመቃወም እና ለመታገል እንጂ፤ ለሌላ የላብ/የወዝ አደር ለተባለ አምባገነንነት መስፈን መታገል አልነበረበትም።

ነገር ግን  በአደረጃጀት ረገድም የተከተለው የሌኒንን ከዲሞክራሲ ይልቅ ማዕከላዊነትን የሚያጠብቀውን የተማከለ ዲሞክራሲ ነበር። ይህንንም ከወቅቱ ተራማጅ ድርጅቶች መካካል አንዳንዶቹ በግርድፉ እየወሰዱ በሥራ ላይ አዋሉት። እንዲያም ሲል የድርጅትን እና የአባል መብቶችን “የበላይ አካል/አመራር” ለሚባለው ክፍል ጠቅልሎ ያስረከበን አደረጃጀት ያዙ። ዓባላቱ ከድርጅታቸው አምባገነንነት ሥር ተዘርረው እና ታፍነው፤ “የበላይ አካል/አመራር” ለተባሉት ተገዢ ሆኑ። አንዳንዶችም ከነጭራሹ ለመሪዎቻቸው በስታሊናዊ ተክለ ሰውነት አምልኮ ዓይነት ናወዙ። “የበላይ አካል/አመራር” የሚባሉት ጥቂቶች፣ ከአባሎቻቸው ውሳኔ እና ቁጥጥር ነፃ እየሆኑ ፈላጭ ቆራጭ አመራሮችን በሂደት አነገሡ።

ክርክሮችና ምልልሶችም ገና ከአብዮቱ በፊት በጀመረው የሌኒናዊው እንካስላንቲያ/እሰጥ አገባ ዘይቤ እየተካሄዱ ገፆችን ሞሉ። ከማርክስ-ኤንግልስ-ሌኒን-ማኦ ትሴቱንግ በግርድፉ በተወሰዱ ጥቅሶች መጠዛጠዝ ጦፈ። ቅፅሎችን መደርደር፣ ስም ማጉደፍና ንፁህ ውሸቶችን ማሰራጨት እንደ “አብዮታዊ” ተግባር የሚታይበት ድባብ ሰፈነ። ሌላውን ከመነሻው “ጠላት” አድርጎ መኮነን ዕለታዊ ሆነ። እልህ መያያዝ ተከተለ።በዚህ አኳያ፣ የአልጄርያው ቡድን “የድርጅት ተግባራዊ መመሪያ” በሚል ርዕስ በነሐሴ 1964 ባወጣው ፅሑፍ እንደሚከተለው ያራምደው “የአብዮታዊ ሥነ ምግባር መመሪያ” የራሱን አሉታዊ ሚና ተጫውቶ ነበር።

> “… አብዮታዊ ሥነ-ምግባር ለአንድ አብዮታዊ የመደብ ባሕሪይ ያለው ጥያቄ ነው። ማለትም እንደተቀረው እንደማንኛውም አቋም በመደብ ትንተና ላይ የተመሠረተ ነው። ስለሆነም፤ አብዮታዊ ውሸት ዜናዎችን አያሰራጭም ማለት አይደለም። አይሸውድም፣ የጠላቶቹንም ንብረት አይወርስም ማለት አይደለም። አንድ አብዮታዊ እንደነዚህ ዓይነቶቹን (መዋሸት፣ ማታለል፣ መውረስ፣ ጠላቱን አንዳንድ ጊዜ እየፎተተ ወይም እየደለለ ማግባባት) ድርጊቶች ሲፈፅም፤ ድርጊቶቹን የሚፈፅመው ለድርጅቱና ለሠርቶ-አደሩ ሕዝብ ጥቅም ነው።”[32]

በአብዮቱ ዘመን በአብዮቱ ጥያቄዎች ላይ በሚደረጉ ክርክሮችና ምልልሶች ረገድም፤ በፅሑፎች፣ በመጻሕፍትመጻሕፍትና በቅስቀሳዎች በብዙ ይፃፍና ይነገር የነበረው ስለሶሻሊዝምና የሶሻሊስት አብዮት ነበር። ሁሉም ተራማጅ በወቅቱ ያምን እንደነበረው ግን፣ ለውጡ ወድቆም/ተነስቶም የኢትዮጵያን ነባራዊ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታና የሰውና የማቴሪያል አቅም ባገናዘበው በብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ክልል ውስጥ መቆየት ነበረበት። ይህ አለመሆኑ አብዮቱን አለጊዜውና አለሁኔታው አከረረው። የውስጥና የውጭ ተፃራሪዎችን አበራከተበት። ብዙ የለውጡ ደጋፊ የነበሩትን እና ሊሆኑ ይችሉ የነበሩትን ግለሰቦች እና ማኅበራዊ ክፍሎች አገለለ። ወደ ተቃዋሚነት፣ ወይንም ወደ ተመልካችነት ገፋ።

ከማርክሲዝም ዝክር “አብዮታዊ አመፅ” የሚለውም እንደዚሁ በግርድፉ ተወስዶ እና የኢሕአፓ አመራር “ማናቸውም ሶሻል አብዮት የሞትና የግድያ ሂደት ነውና” ባለው “ቲዎሪ” ጭምር ታጅቦ ተቀነቀነ። ራስን በራስ ማግዘፍና ሌሎችን ማኮሰስ እንደ “አብዮታዊነት” ተቆጠረ። ድርጅታዊ ትምክህት ጓነ። የኢሕአፓ አመራር እንዲያም ሲል፤ ራሱን ከድል አጥቢያ በራፍ ላይ እንደቆመ አድርጎ መመልከት ያዘ። አሸናፊው ብቻ ይጠቅልል ወደሚለው የዜሮ ድምር የፖለቲካ ቀመር ሄደ። ውሎ አድሮ፣  በ“ጠላትነት” ከፈረጃቸው

[32] Handbook on Elementary Notes on Revolution and Organization፣ 1972፣ 32 (የኔ ትርጉም)።

ባሻገር፤ ጥያቄ ባነሱ ዓባላቱ ላይ ሳይቀር የእሥር፣ በምርመራ የማሰቃየትና የሞት ቅጣት እስከመበየን ደረሰ።

በመጨረሻም ይህ ፅሑፍ ከሚሸፍነው ዘመን ውጭ በመሆናቸው አንመልከታቸው እንጂ፤ የማርክሲዝምን በኢትዮጵያ ጉዳይ አሟልቶ ለመፈተሽ ዘለቅ አድረጎ መሄድ ይገባል። ለምሳሌም፣ የኮሎኔል መንግሥቱ አንድ ፓርቲ (ኢሠፓ) አገዛዝ፣ በአብዮቱ ዘመን ያበቡት ሕዝባዊና የሙያ ድርጅቶች የመንግሥት አካል የሆኑበት ሂደት፣ የካድሬዎች፣ የሲቪል እና የሚሊቴሪው ቢሮክራሲው ሥፍራ፣ የዕዝ ኢኮኖሚው ይዘት እና አፈፃፀም፣ መንደር ምሥረታ፣ ሠፈራ፣ የእርሻ ምርት እና የፍጆት ሸቀጦች ግብይት፣ ሙስና፣ የውጭ ግኑኙነት ወዘተ ላይ ሁሉ መመለስ፤ በርካታ ትምህርትን ለመቅሰም ያስችላል።

የኅብረተሰብን የፖለቲካ-ማኅበራዊ መዋቅር በዕቅድ ላይ ተመሥርቶ መቀየር አዳጋች መሆኑ በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ነው። ይህም ለሶሻሊስት ማኅበራዊ ለውጥ በሚደረግ ትግል ብቻ ሳይሆን፤ በለዘብተኛ ዲሞክራሲና የነፃ ገበያ ካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሽግግርም ላይ የሚታይ ነው። ከሶቭየት ኅብረት መበተን እና ከምሥራቅ አውሮፓ የሶሻሊስት ሥርዓት ፍፃሜ በኋላ፤ እነ ማርጋሬት ታቸር “ካፒታሊዝም ከእንግዲህ በኋላ አማራጭ የለሽ ሥርዓት ነው” ብለው ነበር። ፍራንሲስ ፉኩያማ “የታሪክ እልባት ላይ ደርሰናል” ብሎ ነበር።

ብዙም ሳይቆይ ካፒታሊዝም በ1992 እና፣ በ2007/8 በቀሳፊ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ተዘፈቀ። ድህነት፣ ሥራ አጥነትና የሕዝቦች ማኅበራዊ ኑሮ መዛባትና መራራቅ ታየበት። ቀጣዩ ዘመን ጦርነቶች እና ሽብርተኝነት የተስፋፉበት ዘመን ሆነ። በየአራትና አምስት ዓመታት የሚደረጉ ሰላማዊ የሚባሉ የፓለቲካ ምርጫዎች በሁከትና በአመፅ የታጀቡ ሆኑ። ዛሬ እየተነሱ/እየተመነደጉ (emerging) በሚባሉት አገሮች (ደቡብ ኮሪያ፣ ሲንጋፖር፣ ቻይና፣ ህንድ፣ ብራዚል…) የሚነገርለትም የመንግሥታዊ ካፒታሊዝም ከፍተኛ ዕድገት፤ ከኢኮኖሚ ቅዝቃዜ እና ሙቀት ቀውሶች ነፃ አይደለም። ይህን ሁሉ የሥርዓት ችግር መዋቀራዊ እንዳልሆነ አድርጎ ማለፍ እና የቀድሞውን ሶሻሊስት ሥርዓት መክሰም መዘዘኛ እና ተጠያቂ አድረጎ መተቸት ብቻ “አውቆ የተኛ” እንደሚባለው መሆን ነው።

በድኅረ-1983 ኢትዮጵያ የበቀሉ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች “ከውጭ የመጡትን” እና የገበያ ኢኮኖሚ፣ ልማታዊ ካፒታሊዝም፣ ሊብራል ዲሞክራሲ፣ ሴንተሪስት፣ ሶሻል ዲሞክራሲ ወዘተ. የሚባሉትን እና “አገር በቀል” የሚባለውን የብልፅግና ፓርቲ የማኅበራዊ-ፖሊቲካ ርዕዮቶች እንደሚከተሉና ምድባቸውም ካንዱ ወይ ከሌላው እንደሆነ እየገለፁ ናቸው። የውጭ መንግሥታት፣ ፓርቲዎች፣ የፋይናንስ ድርጅቶች፣ ባለሀብቶች እና የወንጌል ክፍሎችም፤ በኢትዮጵያ ምድር አምሳያቸውን ለማግኘትና ለመወዳጀት አልሰነፉም። ስለዚህም፣ የዛሬውና መጭው ታጋይ እነዚህንና የመሳሰሉትን የማኅበራዊ-ፖሊቲካ ርዕዮቶች ምንነት፣ የአብዮቱ ታጋይ ከነበረው የማርክሲስት ግንዛቤ በተሻለ እንዲያጠና፣ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ እና አቅም ጋራ እያገናዘበ አጥብቆ እንዲጠይቅና እንዲመራመር ያስፈልጋል። ፈረንጆች “ስለፖለቲካ ደንታ ከሌለህ ፖለቲካ እንዳሻው አድርጎ ያበጅሃል፤ ይጫወትብሃል” ይላሉ።

### የብሔሮች መብት

የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት በመሠረቱ፤ ብሔሮች በእናት ቋንቋቸው የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመማር፣ የመዳኘት መብቶች ረገድ ያሏቸው መብቶች ይታወቁ፤ ይከበሩ ማለት ነው። ብሔሮች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር እና ባህላቸውን፣ ዕምነታቸውን፣ ትውፊታቸውን፣ በዓለቶቻቸውን፣ ወጎቻቸውን እና ታሪካቸውን ለማጎልበት ያሏቸው ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይታወቁ፤ ይከበሩ ማለት ነው። እነዚህን የመጀመሪያ ደረጃ ዲሞክራሲያዊ መብቶች በአገዛዝ ሥርዓቱ ከተነፈጉ፤ ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን የመጠየቅ እና ለመብታቸው መታወቅ እና መከበር የመታገል መብት አላቸው ማለት ነው። ጥያቄያቸውና

ትግላቸው መልስ አልባ ከሆኑ ደግሞ፤ የመገንጠልን ጥያቄ የማንሳት እና እስከመገንጠልም የሚያደርስ መብት አላቸው ማለት ነው።

የቅድመ አብዮት ዘመን የኢትዮጵያ ተራማጅ ምሑራን እና ድርጅቶች የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ከቡድን መብቶች መካከል አንዱ ዲሞክራሲያዊ መብት እንደሆነ የተቀበሉ ነበሩ። መብቱ የመገንጠል መብትንም የሚጨምር መሆኑንም፤ በመርሆ ደረጃ ያወቁ ነበሩ። የኢትዮጵያ ብሔሮች አንድነት በመፈቃቀድ፣ በዕኩልነት፣ በመከባበር፣ በጋራ ዕድገትና ጥቅም፣ በጋራ ልማት እና ብልፅግና ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የታገሉ ነበሩ። አቋሙ፣ በመኢሶንና በኢሕአፓ ፕሮግራሞች ወስጥም የተካተተ ነበር።

የኢትዮጵያ ተራማጅ ምሑራንና ድርጅቶች በዚህ የዲሞክራሲያዊ መብት አረዳድ የኢትዮጵያ ብሔሮችን ዲሞክራሲያዊ መበት በማወቃቸው፤ በብዙ ይወቀሳሉ። አንዳንዶች፣ የኢትዮጵያ ተራማጆችና ምሑራን በኢትዮጵያ የብሔሮች ጥያቄ ላይ በወሰዱት አቋም አገሪቱን የመከፋፈልና የማፈራረስ ፖለቲካ እንደቀሰቀሱና እንዳስፋፉ እያተቱ ይወቅሳሉ። "የጥፋት መልዕክተኛ ትውልድ" በሚል የሚሰነዘረው አንድም፤ የአብዮቱ ዘመን የኢትዮጵያ ተራማጅ ምሑራን እና ድርጅቶች የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት በወሰዱት አቋም ምክንያት ነው። ሌሎችም "እንዲያውም" ይላሉ፤ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጅ ምሑራን ጥያቄውን ባያነሱት ኖሮ፣ ለብሔር መብት ይታገሉ የነበሩት ወገኖች አይደርሱበትም ነበር እስከማለት ድረስ ሲያትቱ ጭምር ይደመጣሉ። በነዚህኞቹ ላይ መቆየት አያስፈልግም። ሌሎችም፣ "መብቶቹ በመንግሥታዊ አዋጅ ተከልክለው ኢያወቁም ነበር እኮ!" እያሉ ይሞግታሉ። እነዚህኞቹ፣ ጥያቄው የተነሳው መብቱ በአዋጅ እና በሕግ ተደነግጎ ስላልታወቀ እና ስላልተከበረ እንደነበር ባያስተውሉ ይሆናል። ሁኔታው ወይንም፤ "በአዋጅ እና በሕግ ተከልክሎ የተደነገገ በሕግ የተከለከለነው። በአዋጅና ሕግ ያልተከለከለ አይፈቀደም" እንደሚባለው ዓይነት እንደነበር ባያስተውሉ ይሆናል።

ሌሎች ደግሞ፣ "ከማርክሲዝም ዝክር የተወሰደ" በማለት ይተቻሉ። ከነዚህ መካከል አንዳንዶቹ አስተያየቱን የሚሰጡት ጥያቄው ከማርክሲስቶች ባለፈ በዓለም-አቀፍ የመርሆ መግለጫዎች እና ውሎች ውስጥ የተካተተ መብት መሆኑን ባያስተውሉ ይሆናል። ሌሎችም፣ በዚያው "ከባዕድ የመጣ" በሚለው መንፈስ፣ "ከማርክሲዝም የተወሰደ" እስከተባለ ድረስ አቋሙ ከወዲሁ (ዘመኑ በማርክሲዝም ላይ የሚሰነዘረው በትር የበረታበት ዘመን ነውና) ውጉዝ ይሆናል ከሚል ቀላል ስሌት በመነጨ ነው። እነዚህኖቹ አተኩረው ቢመለከቱ ግን፤ መብቱ በ1945 የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ውስጥ ይገኛል (አንቀጽ 1/2)። እንደዚሁም፣ በ1959 ዓ.ም (1966) ዓለም-አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች እና በኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህል ውሎች ውስጥ። የኛው ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝም፣ ከመቶ ዓመት በፊት እንደሚከተለው መክረው ነበር፡-

> "...መንግሥት አንዱን ነገድ አጥቅቶ ሌላውን ነገድ ለመጥቀም ሥራው አይደለም። አስተካክለን ካሰብን ዘንድ፣ መንግሥት መቆሙ ለሕዝቡ ነው። ጥረቱ ሕዝቡን ሁሉ በትክክል ለመጥቀም ያልሆነ መንግሥት ሊቆም አይችልም። ላንዱ ነገድ ወይንም ለጥቂት ሰዎች ማድላት ለመንግሥት የሚገባው ሥራው አይደለም።"[33]

የ1960ዎቹ የኢትዮጵያ ተራማጆችና ምሑራን ከተጠቀሰው የነጋድራስ ገብረሕይወት ምክረ ሃሳብ በተለየ መንፈስ የተብከነከኑ አልነበሩም። ወደዕውነታው እና ጭብጥ ሂደቱ በአጭሩ ብንመለስም፤ የብሔሮች ጥያቄዎችና ንቅናቄዎች የኢትዮጵያ ተራማጆች የተመለከተውን አቋም ከመያዛቸውና ከማስተጋባታቸው በፊት የነበሩ ናቸው። ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ ባቀረቡት አንድ ፅሑፍ እንዳሉት፤

> "የጥያቄው ዋነኛ የረጅም ጊዜ መንስዔ ከአፄ ምኒልክ የግዛት ማስፋፋት ሂደት በተጓዳኝ የሰፈነው የብሔረሰብ ጭቆና ነው። .... በተለይ በደቡቡ የኢትዮጵያ ክፍል ጭቆናው ብዙ ገፅታዎች ነበሩት።

[33] ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ እንደላይኛው፣ 3።

የአስተዳደር ነፃነት ከማጣት አንስቶ፣ መሬት እስከ መነጠቅ፣ በባርነት እስከ መጋዝ ዘልቋል። በባርነት መጋዝን በተመለከተ በተለይ በወላይታ፣ ከፋና ጊሚራ የደረሰው እልቂት ከባድ ጠባሳ ትቶ አልፏል። ከዚህ ተያይዞም፣ የብሔረሰቦቹ ባሕልና ቋንቋ ተዋርዷል። በትግራይ ደግሞ ላይ ከተጠቀሰው ዓይነት ጭቆና ይልቅ ከአፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ ከማዕከላዊ ሥልጣን መገለል ቁጭት አሳድሯል።... ኋላ በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ በጥያቄው መፍትሔ ላይ የሐሳብ ልዩነት ቢፈጠርም፤ በጭቆናው ነባራዊነት ላይ ሙሉ ስምምነት ነበር።”[34]

ፕሮፌሰር ባሕሩ በተጠቀሰው ፅሑፋቸው ቀጥለው እንደሚሉትም፤

> *“ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች ተራማጅ ኃይሎች ይህን እንቅስቃሴ ኢትዮጵያውያን ለዲሞክራሲና እኩልነት የሚያደርጉት ትግል አጋር ለማድረግ በማሰብ በጦርነት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ ማግኘት እንዳለበት ማመን ጀመሩ። ... ይህን መርሆ ሲደግፉ በተለይ ያተኮሩ የነበረው በኤርትራው የአርነት ትግል ላይ ነበር። ዕምነታቸውም፣ ኤርትራውያን እስከ መገንጠል ድረስ ላላቸው መብት ዕውቅና በመስጠት ትግላቸውን የመላው ኢትዮጵያ ትግል አጋር ለማድረግ እና ለችግራቸውም በዚያው ማዕቀፍ ውስጥ መፍትሔ ለመሻት ነበር።”*

ወቅቱ በተጨማሪም፣ አንዳንድ የተማሪ ማኅበራት አባላት የነበሩ ኤርትራዊያን፣ የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን እያቋረጡ የኤርትራ ግንባሮችን ወደመቀላቀል ያቀኑበት ወቅት ነበር። የአንዳንድ ብሔሮች ተወላጅ ተማሪዎችም በዚያው በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የየራሳቸውን የጥናት ክበቦችን እየመሠረቱ ወደመደራጀት ያቀኑበት ወቅት ነበር። እነዚህም ለምሳሌ ያህል፣ ለ12ኛ ክፍል መልቀቂያ በሚሰጠው ፈተና ለአማርኛ ቋንቋ ዕውቀት ይሰጥ በነበረው ከፍተኛ ሥፍራ ምክንያት የሚበሳጩ ነበሩ። አንዳንድ እንዳመጣ ይነገሩ በነበሩት አስነዋሪ፣ ጋንጢጥ፣ አንኳሳሽ እና አቃቃሪ አባባሎች የሚማረሩ ነበሩ።

በአገሪቱም፣ ከ1950ው የሜጫ ቱለማ ሲቪል ንቅናቄ አንስቶ እስከ ባሌው የመሣሪያ ትግል ድረስ የሚካሄዱ የብሔር እንቅስቃሴዎች ነበሩ። እንደዚሁም በመረዳጃ ስም የተቋቋሙ የጉራጌዎች፣ የሲዳማዎች፣ የሱማሌዎች፣ የአፋሮች፣ የአደሬዎች እና ወዘተ እንቅስቃሴዎች ነበሩ። ከተለያዩ ብሔሮች የሚመጡትን ተማሪዎችና ምሑራን ባቀፈው የዩኒቨርስቲ ማኅበረሰብ ውስጥም፣ የብሔሮች ጥያቄ በተለያዩ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች እየተነሳ እስከ አካል ግጭት ያደርስ ነበር። ከዚያው ከዩኒቨርሲቲ አካባቢ ርቆ ሳይሄድም፤ ዓመቱን እየጠበቀና ጥምቀትን እየቆጠረ በጃንሆይ ሜዳ በተለያዩ የብሔሮች የዘፈን ቡድኖች መካከል ይነሱ የነበሩትን ግጭቶችን ለማስታወስ የሚቻል ነው።

የዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሁኔታ እና የየብሔሮቹ እንቅስቃሴዎችና ትግሎች ለኢትዮጵያ ተማሪዎችና ምሑራን የተሰወሩ አልነበሩም። ከ1953 አንስቶ በኤርትራ ይካሄድ የነበረው ጦርነትም። እንደዚሁም፣ ከሶማሊያ መንግሥት ጋር የተደረጉት ጦርነቶች። ስለዚህም፤ ጉዳዮቹን በቅርብ ይከታተሉና ያጤኑ የነበሩት ጥቂት የነቁ ተማሪዎችና ምሑራን የብሔሮችን ጥያቄ ጉዳይ ማንሳታቸው የሚያስደንቅ ሊሆን አይችልም። የ1950ዎቹ ዓመታት የፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግሎች የፋሙበት ዘመን የነበሩትን ያህልም፤ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ጥያቄ በአፍሪካ፣ በእስያና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ደረጃዎች ትኩስ የውይይት ርዕስ ሆኖ የተነሳበትም ወቅት ነበር። ይህም፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እና ምሑራን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት በሚለው ጥያቄ ላይ በበለጠ እንዲያስቡ አድርጓቸው ነበር። ሌላም፣ የዩኒቨርሲቲ አገልግሎት ይባል በነበረው በየአካባቢው ይሠራጩ ነበር። በየሄዱበት ይሰሟቸውና ያዩዋቸው በነበሩት በደሎች የተነኩ ነበሩ።

የተመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ ተደምረው የብሔሮችን ጥያቄ አንደኛው የኢትዮጵያ መሠረታዊ የዲሞክራሲ ጥያቄ አደረጉት። ስለሆነም፤ የአገር ውስጥና የውጭ ተማሪ ማኅበሮች ገና ከ50ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ጀምረው በጥያቄው ላይ መወያየት መጀመራቸው እና አቋሞቻቸውን ማስተጋባታቸው። ከዚህ አኳያ

---

[34] ባሕሩ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አሻራ በብሔረሰብ ጥያቄ ላይ፣ 2013።

በ1961 እና በ1962 ዓ.ም. በታገል መፅሔት ላይ ስለብሔር ጥያቄ ይወጡ የነበሩት ፅሑፎች፣ ከቲዎሪ አንፃር እስከዚህ ብዙ ጉድለት የሚወጣላቸው አልነበሩም። በሌላውም ወገን፣ የታጋዩን ወጣት ንቃተ ሕሊና ማዳበር በሚለው የወቅቱ የትግል መሥመር ክልል ውስጥ ተካተው መታየት ያለባቸው ናቸው።

አብዛኞቹ የወቅቱ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆች የብሔሮችን መብት የተመለከቱትና ያወቁት፤ እንደማንኛውም መታወቅና መከበር እንዳለበት አንድ የዲሞክራሲያዊ መብትና ጥያቄ ነበር። ይሁን እንጂ፤ አንዳንዶቹ ፅሑፎች ከተማሪ ንቅናቄ ሥፍራና ሚና አልፈው በመሄድ ተማሪውን ለትጥቅ ትግል ጠሪና ቀስቃሽ ሆነው በመውጣታቸው ደግሞ፤[35] ስህተት አልተፈፀሙም ላለማለት አይቻልም።

ወደታሪኩ በአጭሩ ብንመለስ፤ በተማሪ ማኅበሮች ደረጃ የመጀመሪያዎቹ ውይይቶች የተደረጉትና ውሳኔዎች የተላለፉት በ1959 (በብሔራዊ የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር) እና በ1960 (በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር -አኢተማ) የዩጎዝላቪያ ጉባዔ ወቅት ነበር። ከዚያም፣ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተደረሱት ፅሑፎች ቻሌንጅ በሚባለው መፅሔት ላይ በ1961 ወጡ።[36] በኅዳር 1962 ዓ.ም.፣ የዋለልኝ መኮንን እና የሌሎች አንዳንድ ፅሑፎች መወጣጣት ጀመሩ። ለጥቆም የጥላሁን ግዛውን ስም ተውሶ የተፃፋው የነብርሃነ መስቀል ረዳ ፅሑፍ ተከተለ።

በእነ እንድርያስ እሸቴ (ቱምቱ ሌንጮ) ተፅፎ በቻሌንጅ መፅሔት ላይ የወጣው ፅሑፍ፣ የኢትዮጵያን የብሔሮች ጥያቄ በጥንቱ የፊውዳል ነገሥታት እና ባላባቶች መሀከል እንደነበሩት ግጭቶች፣ ወይንም ደግሞ በቀጠናዊ/አከባቢያዊ ግጭቶች ዓይነት አድርጎ የሚመለከት እና በስልተ-ምርታዊ አተናተን ላይ ያተኮረ ነበር። ባሕሩ ዘውዴ "የዋለልኝ ቦንብ" ያሉት የዋለልኝ መኮንን ፅሑፍ፤ በአንድ በኩል ለመገንጠል የሚታገሉት የኤርትራ ግንባሮች የሶሻሊስት ግብ እስካላቸው ድረስ ወታደራዊ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ጠራ። በሌላውም በኩል፣ የብሔር እንቅስቃሴዎች አገዛዙን የሚያዳክሙ ስለሆኑ፤ መደገፍ አለባቸው የሚለውን አመለካከት አራመደ።[37] የነብርሃነመስቀል ረዳ ፅሑፍ ሌኒንና ስታሊንን በረጃጅሙ እየጠቀሰ ያተተ ነበር።

በወቅቱ በመኢሶን አባላት ይመራ የነበረው የአውሮፓ ተማሪዎች ማኅበር አመራር የብሔሮች መብት ከዲሞክራሲያዊ መብቶች አንዱና ለዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚደረገው ትግል አካል እንጂ፤ የንጉሠ ነገሥቱን ሥርዓት የመገርሰሻ እና ለሶሻሊዝም ግብ መሳካት የሚውል መሣሪያ አይደለም በሚል ተቃወመ። የማኅበሩ አባላት በአራት ጉዳዮች ዙሪያ ሠፊ ጥናቶች እና ክርክሮች እንዲያካሂዱ አደረገ። ዓባላቱ በየቅርንጫፍ ማኅበራቸው እየተሰባሰቡ ለአንድ ዓመት ሙሉ አጠኑ። ጥናት የተደረገባቸው አርዕስት (1) የ19ኛው ክ/ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥት አመሠራረትና ሂደት፣ (2) ማርክሲያዊ ትነተና ለብሔር ጥያቄ የሚያቀርበው መፍትሔ፣ (3) ከአፍሪካና ከእስያ ቅኝ ተገዢ አገሮች የነፃነት ትግሎች የሚገኘው ተመክሮ፣ (4) የብሔር ጥያቄ በዓለም-አቀፍ ሕጎች የሰብዓዊ መብቶች አካል ሆኖ መታየቱ ነበሩ።

የማኅበሩ 11ኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ በነሐሴ 1963 በበርሊን ከተማ ተደረገ። የማኅበሩን 11 ቅርንጫፍ ማኅበራት የወከሉ 150 አባሎች የተሳተፉበት ጉባዔ ነበር። ከሰሜን አሜሪካ አምስት የማኅበሩ አባሎች እና፤ በተለይም በዚያ የነበሩትን ሁለት መሥመሮች ይወክሉ የነበሩት ዶ/ር እንድርያስ እሸቴ እና ዶ/ር ሡናይ ልኬ በአንድ በኩል እና፤ "የስፓርክ" መፅሔት አዘጋጅ የነበረው መስፍን ሐብቱ በሌላ በኩል የተገኙበት ጉባዔ ነበር። እንደዚሁም፣ ከአልጀሪያው ቡድን አባሎች መካከል የ"ጥላሁን ታከለ" ፅሑፍ አዘጋጆች የነበሩት ብርሃነ መስቀል ረዳና ኢያሱ ዓለማየሁ የተሳተፉበት ነበር።

---

[35] R.R. Balsvik, Haile Selassie's Students፣1985፣ 268።

[36] Challenge፣ Vol. X, No. 1፣ 1970.

[37] "I (ዋለልኝ) am all for them, the ELF, the Bale movements, the Gojam uprising, to the extent that they have challenged and weakened the existing regime and have created areas of discontent to be harnessed later on by a genuine socialist revolution" (ዋለልኝ መኮንን፣ On the question of Nationalities in Ethiopia፣ 1962)።

እዚህም ላይ፣ 11ኛው የአኢተማ ጉባዔ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆች በብሔሮች ጥያቄ ላይ ከሚይዙት አቋም ረገድ ወሳኝና ታሪካዊ ጉባዔ ነበር ለማለት ይቻላል። አሰላለፋቸውንም በሚመለከት፣ የአሜሪካው 17ኛ ጉባዔ ውሳኔ ባለቤቶች እና ደጋፊዎች የነበሩት እነዶ/ር እንድርያስ እሸቴ እና ዶ/ር ሠናይ ልኬ በአንድ ወገን ሲሆኑ፤ ሌሎቹ በሌላ ወገን ነበሩ። በአብዛኛው ተሳታፊ ድምፅ የተላለፈው የማኅበሩ ውሳኔ፣ በወቅቱ የአኢተማ ፕሬዘዳንት በጉባዔው መክፈቻ ላይ ካደረገው ንግግር የተለየ አልነበረም።

"አንደኛ፤ ብሔሮች የገዛ ዕድላቸውን ለመወሰን ያላቸውን በምንም ዓይነት የማይደፈር መብት ያውቃል። ይህም መብት መገንጠልንም ጭምር የሚያጠቃልል ነው።

"ሁለተኛ፣ ዛሬ በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሔሮች በሙሉ የጋራ ጠላቶቻቸውን ለመደምሰስ ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊት የሆነ የትግል አንድነት እንደሚያስፈልጋቸው ያምናል። ለዚህ የትግል አንድነት ማኅበራችን ውስጥ የሚገኙ ከየብሔሩ የተውጣጡ ተራማጆች በሙሉ የማያቋርጥና የተቀነባበረ የማስተማር ትግል ማድረግ አለባቸው።

"ሦስተኛ፣ ይህ አንድነት ሊገኝ የሚችለው ብሔሮቹ በአንድነት ለመኖር ፈቃደኛ ሁነው ሲገኙ ብቻ ነው። በአንድ ሕዝባዊ መንግሥት ሥር ለመኖር የተፈቃቀዱ ብሔሮች ሙሉ በሙሉ እኩልነታቸው እንዲታወቅና የገዛ ኑሯቸውን በያሉበት በመሰላቸው ለማስተዳደር ያላቸው መብት በማያወላውል ሁኔታ መረጋገጥ አለበት።"

የብሔሮች ጥያቄ በአብዮቱ ዘመን በመንግሥት የመገናኛ መድረኮች ላይ ጭምር ሠፊና ይፋ ውይይት ተካሄደበት። እንደዚሁም የኢማሌድኅ መሥራች በሆኑት ድርጅቶች መካከል። ከኢማሌድህ መሥራቾች መካከል አብዮታዊ ሰደድ፣ ወዝ አደር ሊግና ማሌሪድ መርሆውን እንደሚቀበሉ የገለፁ ቢሆንም፤ "ተግባራዊ መፍትሔ ማቅረብ አለብን" የሚለውን አቋም ያዙ። "የራስ-ገዝ አስተዳደር" የተባለውን "ተግባራዊ መፈትሔ" አቀረቡ። መኢሶንና ኢጭአት "አጠቃላይ መፍትሔን ከማቅረብ ይልቅ፤ መርሆውን ብቻ አውቆ ለእያንዳንዱ ለሚነሳ ችግር እንደ ሁኔታው መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል" የሚለውን አቋም በመያዛቸው ከስምምነት ላይ ሳይደረስ ቀረ። ሁለቱ ድርጅቶች ይህንን አቋም የያዙበት ዋና ምክንያት፣ የሚመለከተው ወገን ሳይሳተፍበት እና ድምፁን ሳይሰጥበት፤ ከላይ በመንግሥት/በፖለቲካ ድርጅቶች የሚሰጥ እና የሚጫን ውሳኔ ጥያቄውን አይፈታም የሚል አቋም ስለነበራቸው ነበር። ወደኋላ ላይ እና ባለቀ ሰዓት ቢሆንም፤ ግቡ ሕገ መንግሥት ማርቀቅ የነበረ የብሔረሰቦች ጥናት ተቋም ተቋቁሞ፣ የኢትዮጵያን ብሔሮች ዝርዝር፣ ጂኦግራፊያዊ አሠፋፈር፣ ቋንቋ እና ባህል ያካተተ ግሩም ጥናት አጠናቅሮ ነበር።

ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ ያላት አገር ናት። ረጅሙ ታሪኳ በርካታ አኩሪ ገፅታዎች አሉት። ሕዝቦቿም የኃይማኖትና የብሔር ማንነት ያልገደባቸው የመከባበር፣ የመቻቻል፣ የመተሳሰብና የመደጋገፍ ግሩም ባህል ባለቤት ናቸው። ለአገራቸው ነፃነት፣ ክብርና ልዕልና በጋራ ለመቆም ያረፈዱበት የታሪክ አፍታ የለም። ነገር ግን፤ ረጅሙ ታሪክ የአጥቂ/ተጠቂ፣ አስገባሪ/ገባሪ፣ በዳይ/ተበዳይ፣ ገፊ/ተገፊ፣ ጨቋኝ/ተጨቋኝ፣ በዝባዥ/ተበዝባዥ ገፅታዎች እና የማንጓጠጥ እና ማንኳሰስ ባህሎች ያሉት ነበር። እነዚህ በሕያው ትውልድ አእምሮ ላይ የተጫኑ የታሪክ ሸክሞች ናቸው። ካርል ማርክስ በሉዊስ ቦናፓርት 18ኛው ብሩሜር እንደሚለው፣

"ያለፉት ትውልዶች ነባር ዘይቤ (ልማድ፣ ወግ፣ ባህል) በሕያው ትውልድ አዕምሮ ላይ የቅዠትን ያህል ከብዶ ይጫናል" እንዳለው። ፕሮፌሰር ባሕሩ በዚህ የታሪክ ሸክም ላይ ተመልሰው እንዳብራሩትም።[38]

---

[38] ባሕሩ ዘውዴ፣ 'The Burden of History፣ 1999.

የኢትዮጵያ ተራማጆች እና ምሑራን፣ ካለፈው ዘመን ተወርሶና በነባራዊነት ሰፍኖ የነበረውን የብሔሮች ጭቆና አስተዋሉ። ፕሮፌሰር ባሕሩ በፅሑፋቸው እንደገለፁት፤ “ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች ተራማጅ ኃይሎች፣ የኤርትራ እና የብሔሮች ትግሎች ኢትዮጵያውያን ለዲሞክራሲና እኩልነት የሚያደርጉት ትግል አጋር ለማድረግ በማሰብ በጦርነት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ ማግኘት እንዳለበት ማመን ጀመሩ።” ወይንም፣ የኤርትራንም ሆነ የኢትዮጵያን ብሔሮች ጥያቄዎች በጦር ኃይል ለመፍታት ከመጣር ይልቅ፤ በፖለቲካዊ መንገዶች እንዲፈቱ ጠየቁ። ታገሉ። የኢትዮጵያ ብሔሮች ዲሞክራሲያዊ መብት ታውቆ በፈቃደኝነት፣ በዕኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሠረተ አንድነት እንዲገነባ ታገሉ። ከወታደራዊ ይልቅ ለፖለቲካ መፍትሔዎች በመቆማቸውና በመታገላቸው ሊወቀሱ አይገባም።

ይህንን ለማመሳከር፣ ከንጉሡ ነገሥቱ ዘመን ጀምሮ ለ30 ዓመታት ሙሉ ስለተካሄደው ወታደራዊ መፍትሔና ውጤቱ ማተት አያስፈልግም። የሁለቱ መንግሥታት ወታደራዊ መፍትሔ የመጨረሻ መጨረሻ “አንድ ጠብመንጃና አንድ ሰው እስኪቀር ድረስ” እስከተባለው የኮሎኔል መንግሥቱ ኢሠፓ የፖለቲካ ዕብደት ድረስ የወሰደ እንደነበር ማስታወሱ ይበቃል። የንጉሡ ነገሥቱ ዘመን ወታደራዊ መፍትሔ እና የ1970ዎቹ የኮሎኔል መንግሥቱ ኢሠፓ የፖለቲካ ዕብደትም ነበር፤ የኤርትራን እና የኢትዮጵያን ብሔር/ብሔረሰቦች እንቅስቃሴዎች ያጎለበተው። ከዓመታት በኋላ ግንቦት 1983ን ያዋለደው። እስከዛሬም እያወዛገበውና የሚሊዮኖችን ዕልቂት እያደረሰ እና የኢትዮጵያን ሀብት በትሪሊዮን እያወደመ ያለው።

የ1960ዎቹ ተራማጆች መርሆውን ከመደጋገምና የሚመኟትን ኢትዮጵያ ከማስተጋባት ባሻገር፤ በአስተዳደር መዋቅር ዓይነት እና የመብቶቹን ሕጋዊ ይዘት እና አተገባበር በሚመለከቱ ጉዳዮች ረገድ ያቀረቧቸው ዝርዝሮች አልነበሩም። ሌሎቹን የቡድን (የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የሕፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የነጋዴዎች፣ ወዘተ) ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሚመለከቱ ጥያቄዎች ረገድ እና የዜጋ እና የግለሰብ መብቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮችም ረገድ፤ የተደረጉ ተጠቃሽ ጥናቶች እና ውይይቶች አልነበሩም። ይህ በዚህ ሲሆን፤ በአንድ ወገን በኤርትራ ግንባሮችና በብሔር ድርጅቶቹ እና፤ በሌላው ወገን በኢትዮጵያ ምሑራንና ኅብረ ብሔራዊ በነበሩት ድርጅቶች መካከል ልዩነቶች አልነበሩም ማለት አይደለም።

ሁለቱም ወገኖች በብሔር ጥያቄ ዙሪያ የወሰዱት አቋም በአመዛኙ ተመሳሳይ ቢሆንም፤ በቅራኔዎች አቀማመጥ ረገድ የወሰዱት አቋም ግን፤ ተመሳሳይ አልነበረም። የኢትዮጵያ ተራማጆች ምሑራን እና ኅብረ ብሔር ድርጅቶች፣ የኢትዮጵያ ዓቢይ ማኅበራዊ ቅራኔ ባገሪቱ ማኅበራዊ መደቦች መካከል ያለው ቅራኔ ነው የሚሉ ነበሩ። በብሔር የተደራጁት ድርጅቶች ግን፤ “በብሔረሰቦቿ መካከል ያለው ቅራኔ ነው” የሚለውን አቋም ያዙ። ከዚህ ዓይነቱ የቅራኔዎች አቀማመጥ የተነሳው አመለካከታቸው “ጨቋኝ እና ተጨቋኝ ብሔር” ወደተባለ አፈራረጃጀት ወሰዳቸው። የአማራውን ብሔር “ጨቋኝ ብሔር” ብለው ፈረጁት። ዓቢዩ ቅራኔ በመደቦች መካከል ያለው ቅራኔ ነው ይሉ የነበሩት የኢትዮጵያ ተራማጆች፣ ምሑራን እና ኅብረ ብሔር ድርጅቶች ግን የብሔሮች ጥያቄ እንደሌሎቹ ቅራኔዎች ሁሉ ሥርዓት ወለድ ቅራኔ እና የገዢውን መደብ ክፍሎች የሚመለከት ነው በሚለው አመላከታቸው ፀኑ። መኢሶን በተጨማሪ፣ የ1967 ዓ.ም. የገጠር መሬት አዋጅ የባለርስት እና የጭሰኛ የምርት ግኑኝነቶችን የበጣጠሰውን ያህል፤ ከብሔሮች ጥያቄ አንደኛው መልስ ያገኛል የሚለውን አመለካከት ያራምድ ነበር። በሌላም በኩል፣ የኢትዮጵያ ብሔሮችና የኤርትራ ጥያቄ በፖለቲካ መንገዶች እንዲፈታ በመታገል ቀጠለ።[39]

ሁለተኛ፡ የኢትዮጵያ ተራማጆች፣ ምሑራን እና ኅብረ ብሔር ድርጅቶች፣ የብሔሮችን ያልተገደበ መብት ያወቁትና የተቀበሉት ከላይ እንደተባለው የብሔሮች መብት ከዲሞክራሲያዊ መብቶች አንዱና ለዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚደረገው ትግል አካል አድርገው በመመልከት እንጂ፤ ራሱን የቻለ ፍፁማዊ

[39] ኃይሌ ፊዳ፣ የኤርትራን ችግር እንዴት በትክክል ለመፍታት ይቻላል?፣ ሰሕድ ቁጥር 22፣ የካቲት 4፣ 1967። ኃይሌ ፊዳ፣ የኤርትራ ጥያቄ ከምን ላይ ደርሷል?፣ አዲስ ፋና፣ ነሐሴ 1968።

መብት ነው በሚል አልነበረም። በብሔር የተደራጁት ድርጅቶች ግን፤ ከአጠቃላይ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች መካከል እንደ አንዱ ሳይሆን፤ የትግላቸው ዓላማና ግብ አድርገው ያዙት።

ሦስተኛ፣ የ60ዎቹ ተራማጆች፣ ምሑራንና ኅብረ ብሔር ድርጅቶች የኢትዮጵያን የብሔሮች ጥያቄ ከሕዝባዊው የኢትዮጵያ አብዮት ነጥለው የሚመለከቱ፣ የሚተነትኑ እና የሚረዱ አልነበሩም። በብሔር የተደራጁት ድርጅቶች ግን፤ አብዮት መካሄዱን ካዱ። ጥያቄውን በራሱና ለራሱ ፍፁም እንደሆነ ማድረግን መረጡ። አራተኛ፣ በብሔር የተደራጁት ድርጅቶች ታሪክን ለፖለቲካ ግብ ማራመጃ እያደረጉ ታሪክን ወደማኅሳቆል ጭምር አቀኑ። ከዚህም በተያያዘ፣ "የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው" የሚለውን የኤርትራ ግንባሮች "ትንተና" እስከመቀበል ሄዱ። የኦሮሞ ድርጅቶችም እንደዚሁ። በኅብረ ብሔር ደረጃ የተደራጁት ግን፣ ለብሔሮች መብት ለመታገል የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያኅሳቁሉትን የብሔር ድርጅቶችና ምሑራን አጥብቀው የሚቃወሙ ነበሩ። እንደዚሁም፣ "የኤርትራ እና የኢትዮጵያ ብሔሮች ጥያቄዎች የቅኝ ግዛት ጥያቄዎች ናቸው" ይባል የነበረውን።

ይህ በዚህ እንዳለ በ1983 የሥልጣን ባለቤት በሆኑት የብሔር ግንባሮች፣ ብሔሮች እስከ መገንጠል ድረስ ያላቸውን መብት ያካተተ "ፌዴራላዊ" ሕገ-መንግሥት አፀደቁ። በቋንቋ ክልሎች የተዋቀረ "የፌዴራል" አስተዳደር መሠረቱ። የፌዴራላዊ አስተዳደር ሥርዓት በወቅቱ በነበረው አገራዊና ቀጠናዊ ሁኔታ ተፈ.ቃቅዶ ወደ አንድ ለመምጣት የተሻለው አማራጭ የነበር ቢሆንም፤ ሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 39ን አካቶ የፀደቀ መሆኑ እስከዛሬ የሚካሄደውን ውዝግብና ግጭት ያስከተለ ሰነድ ሆነ።

አንቀፁ በመሠረቱ፣ የኢትዮጵያ ተራማጆችና ምሑራን በ60ዎቹ በድርጅት መርሆ ደደጃ ካስተጋቡትና መኢሶን እና ኢሕአፓ በየፕሮግራማቸው ካሠፈሩት የተለየ አልነበረም። ከመሠረቱም ሲታይ፣ ዋናው ጥያቄ የመለየት መብት የሕገ መንግሥት አንቀፅ መሆን/አለመሆኑ አይደለም። የሚያስገርመው ይልቁኑ፣ የሕገ መንግሥቱ አፅዳቂዎቹ የብሔር ድርጅቶች አንቀፅ 39ን ያካተቱት በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ውስጥ፣

> "በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገታችን እንዲፋጠን የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፤ በነፃ ፍላጎታችን፣ በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን ተነስተን"

እያሉም መሆኑ ነው። አንዳንድ የፌዴራል አስተዳደር ተመራማሪዎች እንዲያውም ይላሉ፤ "የመለየት መብት አንቀፅን በሕገ መንግሥት ውስጥ ማካተት የሚያመለክተው፤ በመሥራቾቹ መካከል መተማመን እንደሌለ ነው።" "የመይተማመኑ ጓደኛሞች" እንደሚባለው። ምክንያቱም፣ አንቀፁ በሕገ መንግሥት ውስጥ ተካተተ/አልተካተተ፣ የብሔሮች የመለየት መብት የማይገሠስ መብት ነው። በተጨማሪም የሚያስገርመው ደግሞ፤ የኢትዮጵያ ብሔረተኞች በአንድ በኩል እና የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረተኞች በሌላው በኩል ሆነው፤ በአንቀፅ 39 ላይ ሲመላለሱ ዓመታት መቆጠራቸው ነው። ወይንም፣ ዓቢዩ ጥያቄ የአንቀፅ 39 መካተት/አለመካተት አልነበረም፤ አይደለምም። ይልቁኑም፤ ከቶም ፌዴራላዊ እና ዲሞክራሲያዊ ሳይሆን የተመሠረተው የኢትዮጵያ "ፌዴራል" አስተዳደር፣ በምን በምን መንገዶች ተሻሽሎ፣ ኢትዮጵያ የዕወነተኛ (genuine) ፌዴራል አስተዳደር ባለቤት ትሁን የሚለው ነበር።

የፌዴራል አስተዳደር የሚመሠረተው፣ መሥራቾቹ ሲፈላለጉ፣ ሲፈ.ቃቀዱ እና ሲስማሙ ነው። የፌዴራሉ ዓይነት፣ ወደአንድ ለመምጣት (coming together) የተመሠረተ እና በአንድ ለመቆየት (holding together) የተመሠረተ የፌዴራል አስተዳደር በሚል ይለያል። የሁለቱም የፌዴራል ዓይነቶች ግብ፣ ***"በራስ ፈቃድ ላይ ተመሥርቶ አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብን በጋራ መገንባት ነው።*** ሁለቱም በተግባር ውለው የሚሠምሩት፣ የቡድን እና የግለሰብ የዲሞክራሲያዊ እና የሰብዓዊ መብት ነፃነቶች የተረጋገጡ እና የተከበሩ ሲሆን ነው። የሕግ የበላይነት እና ፍትሕ የተረጋገጡ እና የተከበሩ ሲሆን ነው። በፌዴራል መንግሥቱ ግዛት ውስጥ በነፃ የመዘዋወር፣ የመኖር፣ የመሥራት እና ሀብት የማፍራት የዜጋ መብት የተረጋገጠ እና የተከበረ ሲሆን ነው። የሀብት ተቋዳሽነት ፍትሐዊ ሲሆን ነው። በፌዴራሉ መዓከላዊ

መንግሥት እና በፌዴረሉ አካላት መንግሥታት ወይንም ግዛቶች መካከል ፍትሐዊ የሥልጣን እና የሀብት ክፍፍል ሲኖር ነው።

ወደ አንድ ለመምጣት የሚመሠረት የፌዴራል አስተዳደር፤ እንደ ስዊዘርላንድ፣ አሜሪካ እና አውስትራሊያ በነባር ሉዓላዊ መንግሥታት መካከል በሚደረግ የፌዴራል ውል ስምምነት መሠረት ይመሠረታል። በአንድ ለመቆየት የሚመሠረት የፌዴራል አስተዳደር፤ እንደህንድ፣ ስፔይን፣ ቤልጂየም፣ ናይጄሪያ እና ኢትዮጵያ በአንድ ሉዓላዊ መንግሥት ግዛት ውስጥ በሚገኙ ነባር ብሔሮች መካከል በሚደረግ የፌዴራል ውል ስምምነት መሠረት ይመሠረታል። አንዳንድ የፌዴራል አስተዳደር ተመራማሪዎች ይኸኛውን፣ ግዛታዊ ፌዴራሊዝም (territorial federalism)፣ ወይንም የብዝኃ ብሔር ፌዴራሊዝም (multiethnic/ national federalism) ይሉታል።

ወደ አንድ ለመምጣት ከተመሠረተ የፌዴራል አስተዳደር ውስጥ፣ አንዱ ወይንም ሌላው ሉዓላዊ መንግሥት ከፌዴራሉ ውል የመውጣት ሉዓላዊ መብት አለው። በአንድ ለመቆየት ከተመሠረተ የፌዴራል አስተዳደር ውል ውስጥም፤ አንዱ ወይንም ሌላው ብሔር የመለየት መብትን የማንሳት እና የመጠየቅ መብት አለው። ፍሌሚሾች ከቤልጂየም እና ካታሎናዊያን ከስፔይን ለመለየት እንደሚያቀርቡት ጥያቄ። ፍሌሚሾች እና ካታሎናዊያን የመለየት መበት ጥያቄን የሚያነሱት ግን፤ መብቱ በስፔይን እና በቤልጂየም ሕገ መንግሥቶች ውስጥ አንቀፅ ወጥቶለት ስለተደነገገ አይደለም። ፌዴራላዊ ካልሆኑ አገሮችም መካከል፣ ስኮቲሾች ከእንግሊዝ እና ኮርሲካኖች ከፈረንሳይ ለመለየት የሚጠይቁት፣ የሕገ መንግሥትን አንቀፅ እየጠቀሱ አይደለም። ለማንኛውም፣ ዛሬ በ2016 ዓ.ም. የመገንጠልን መብት በሕገ መንግሥታቸው ውስጥ ያካተቱ አገሮች ኢትዮጵያ እና የሴይንት ኪትስ እና ኔቪስ ደሴቶች ፌዴሬሽኖች ብቻ ናቸው።

በ1987 ይሁን በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ብሔሮች ጥያቄ ችግር ዋና ምንጭ፤ በኢትዮጵያ “ፌዴራል” ሕገ መንግሥት ውስጥ አንቀፅ 39 መኖር/አለመኖሩ አይደለም። የችግሩ ምንጭ ይልቁኑ፣ የኢትዮጵያን “ፌዴራላዊ” አስተዳደር የመሠረቱት የብሔር ድርጅቶች የአንድ ብሔር ድርጅትን የበላይነት ያሰፈነን ፌዴራል ያልሆነን “የፌዴራል” አስተዳደር በመመሥረታቸው ነው። ዜጎችን በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እና በአንድ ለአምስት መንገዶች ጠርንፎ የሚገዛን አሃዳዊ አስተዳደር በመመሥረታቸው ነው። ለፌዴራል አስተዳደር መጎለበት እና ማበብ የሚያስፈልጉት የቡድን እና የግለሰብ ዲሞክራሲያዊ እና ሰብዓዊ መብት ነፃነቶች ለ30 ዓመታት ሙሉ በመታፈናቸው ነው። የሕግ የበላይነት እና ፍትሕ ለ30 ዓመታት ሙሉ በመረገጣቸው ነው። ከዚህም ባሻገር፤ መሥራቾቹ የብሔር ድርጅቶች፣ አባሎቻቸው እና ጥገኞቻቸው መረን በለቀቀ ሙስና፣ የሀብት ዝርፊያ እና ጭበጣ (resource capture) ውስጥ በግላጭ በመዘፈቃቸው ነው። እንደዚያ ዓይነቱ “የፌዴራል” አስተዳደር፣ ***“አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብን በጋራ መገንባት”*** የተባለውን ለመገንባት የሚያስችል አልሆነም። አይሆንም። እንዲያውም፤ ከፅንሱ ጀምሮ ለመፍረስ የታጨ ብቻ ሳይሆን፤ በከፋፍለህ ግዛ መንግዶች ጭምር እየተተገበረ፣ የመፍረስን አደጋ አጠናክሮ ያመቻቸ “የፌዴራል” አስተዳደር ዝርያ ነው። ወይንም፣ አንድ የጋራ ፌዴራላዊ ብሔረ መንግሥትን (nation state) በጋራ ለመገንባት የማያስችል “የፌዴራል” አስተዳደር ዝርያ ነው።

በሌላ አገላለፅ፣ የተሄደበት መንገድ ዞሮ ዞሮ እንደ ንጉሠ-ነገሥቱ እና የኢሠፓ ዘመን በገዢዎች ውሳኔ ከላይ ወደታች የወረደ (አካታች እና አሳታፊ ያልነበረ) በመሆኑ ምክንያት፤ ለውጡን በሕዝባዊ ተሳትፎና በሕዝባዊ ይሁንታ የተባረከ አላደረገውም። ስለዚህም፣ ከሕገ-መንግሥቱና “ፌደራላዊ” ከተባለው አወቃቀር አንስቶ እስከ አፈፃፀሙ ድረስ በተሄደበት መንገድ ምክንያት፤ መሠረታዊ የውክልና፣ የመዋቅራዊ፣ የሥርዓታዊ፣ የወሰን፣ የማንነት፣ የዲሞክራሲ፣ የሰብዓዊ መብት፣ የሕግና ፍትሕ ጥያቄዎች እንደተነሱ ቀጠሉ። የተለያዩ ፉክቻዎች፣ ውጥረቶች፣ ግጭቶችና ጦርነቶች በተለያዩ ዓይነቶችና ደረጃዎች (በገዢው አባል ድርጅቶች መካከል፣ በገዢው ከፍል እና በተቃዋሚዎች መካከል፣ በተቃዋሚዎች መካከል፣ በፌደራል መንግሥቱ እና በክልሎቹ መንግሥታት መካከል፣ በየክልሉ የገዢው ድርጅት አባላት በሆኑትና

ባልሆኑት የብሔር ድርጅቶች መካከል፣ በየክልሉ የቋንቋ ብዙኃንና በየውስጣቸው በሚገኙት የተለያዩ ንዑሳን ማኅበረሰቦች መካከል ወዘተ.) በየጊዜው እየገነፈሉ እና እየተቀጣጠሉ ቀጠሉ።

የ2010 ዓ.ም. ለውጥ መሠረታዊ የሪፎርም እርምጃዎች እንዲወሰድ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ የመጣ ነበር። ይሁንና፣ አንዳንድ የፖለቲካ እርምጃዎች (የፖለቲካ እሥረኞች መፈታት፣ በውጭ የነበሩ ድርጅቶች ወደአገር እንዲገቡ መጋበዝ፣ ከኤርትራ መንግሥት ጋር መቀራረብ፣ የመገናኛ ዘዴዎች መከፈት ወዘተ.) ሪፎርም እየተባሉ ጭምር ከመነገራቸው ባለፈ፤ መሠረታዊ ሪፎርም ይጠይቁ የነበሩት የሕገ መንግሥት እና የአስተዳደራዊ አወቃቀር ጥያቄዎች ሳይነኩ ቀሩ። ወይንም፣ የፌዴራል ሰጥቶ መቀበል መንገድ ሳይነካ እና ሳይሄድበት ቀረ።

የ2010 ዓ.ም. ለውጥ አመራሮች መሠረታዊ ተግባርና ሥራ መሆን የነበረበት፣ የ1983 ዓ.ም. የሥልጣን ባለቤቶች ባልሄዱበት መንገድ ሄደው፣ እውነተኛን (genuine) የኢትዮጵያ ብዝኃ ብሔሮች ፌዴራላዊ መንግሥት በሰላምና በአግባቡ የመገንባት መንገድን እና ሂደቱን ማስቻልና ማሳለጥ መሆን ነበረበት። በርካታ ዕርምጃዎችን ወደኋላ ሄዶ መሠረታዊ የሕገ መንግሥት እና የአስተዳደራዊ መዋቅር እርማቶችን እና ማሻሻያዎችን የማድረግ ነበር። በእነዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች ረገድ የሚቀመጠው አቅጣጫ እና የሚወሰዱት እርምጃዎችም ነበሩ፤ ወደ የጋራ ብሔራዊ/አገራዊ ራዕይ፣ ወደ የጋራ ተስፋ መፈንጠቅ እና መኅልበት ሊያበቁና ሊወስዱ ይችሉ የነበሩት። ለዚህም፣ ግልጽ ምክንያቶች ነበሩ። አሉ።

አንደኛ እና በጣም ግልጽ ከሆነው ጉዳይ ብንጀምር፣ የ1987 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ከፀደቀ 30 ዓመታት ተቆጥረዋል። ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻል ሲጠየቅም፤ እንደዚሁ 30 ዓመታት ተቆጥረዋል። እነዚህ እውነታዎች በራሳቸው ሕገ መንግሥቱን ወደ ማሻሻል ተግባራት ለመግባት በቂ ምክንያት ነበሩ። ናቸው። ሁለተኛና ይልቁንም ደግሞ፣ ሌሎች መሠረታዊ ምክንያቶች ነበሩ። ዛሬም አሉ።

በ1987 ዓ.ም. ሕገ መንግሥት መረቀቅና መፅደቅ ሂደት ውስጥ እንደ ብሔርም ሆነ እንደ ፖለቲካና ማኅበራዊ ስብስብ "አልተሳተፍንም፤ አልመከርንም" የሚሉ ብዙዎች ነበሩ። አሉ። በሌላው በኩል፣ የሽግግሩ ቻርተር ተሳታፊ አርቃቂ እና አፅዳቂ ከነበሩት ነፃ እና ዋና ዋና የብሔር ድርጅቶች መካከል አብዛኞቹ ገና በቻርተሩ ዘመን ተወገዱ። ስለሆነም ሕገ መንግሥቱ የባሰውን አሳታፊና አካታች ባልሆነ መንገድ የተረቀቀ እና የፀደቀ ሰነድ ሆነ። "ፌዴራላዊ" ሥርዓት የተባለውም እነዚያን የሚያከሉን ሕዝብና ስብስቦች ገና ከፅንሱ አግልሎ እና አፍኖ የተዋቀረ ፌዴራላዊ ያልሆነ "የፌዴራል" ሥርዓት ሆነ። ወይም ለኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮነት በእኩልነት የመኖር እና ለሰላማቸው ይበጅ የነበረውን ዕወነተኛ የብዝኃ ብሔሮች ፌዴራላዊ መንግሥት ግንባታ መርሆዋዊ መሠረቶችን እና ሂደት ተፃርሮ የተመሠረተ "የፌዴራል" ሥርዓት ሆነ። ስለሆነም፣ 30 ያለመተማመን፣ የግጭት እና የጦርነት ክረምቶች ተቆጠሩ።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ አብዮት፣ የኢትዮጵያን አፄያዊ አገዛዝንና ፊውዳሊዝምን ካስወገደ ሃምሳ ዓመታት አለፉ። የኢሠፓ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ አስተዳደር ከተወገደና የኢሕአዴግ እና የብልፅግና አንድ ፓርቲ አገዛዞች ከቆሙ ስላሳ ሦስት ዓመታት ተቆጠሩ። ይሁን እንጂ፤ የ1966 አብዮት የባለርስት እና ጭሰኛ የምርት ግኑኙነቶችን እንደሻረው፤ ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘወዴ "ሁለተኛው አብዮት"[40] ያሉት፣ ወይንም ጆን አቢንክ "ሁለተኛው ሪፐብሊክ"[41] ያሉት የ1983 ለውጥ፤ የኢትዮጵያን ብሔሮች ጥያቄ ያለቀለትና የተዘጋ አላደረገውም።

በድኅረ 2010 የተለያዩ አሰቃቂ ጦርነቶች ተነስተው ሚሊዮኖች ለዕልቂት፣ መፈነቃቀልና ስደት የተዳረጉት እና የኢትዮጵያ የሰውና ቁሳዊ ሀብቶች በቢሊዮን የወደሙት አንድም፤ ሁኔታው ይጠይቅ በነበረው የፌዴራል ሰጥቶ መቀበል ሪፎርም መንገድ ስላልተሄደ ነው። ኢትዮጵያ ከዚህ ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት

[40] ባሕሩ ዘወዴ፣ 2014፣ 11።

[41] ጆን አቢንክ፣ The Ethiopian Second Republic and the Fragile "Social Contract"፣ 2009

የምትችለው፤ መሠረታዊ ሪፎርምን በሚጠይቁት ጉዳዮች ረገድ፤ የሰከኑ ውይይቶችን፣ ቴክኒካዊ የድርድር ስልቶችንና ከፍተኛ የሆነን የሰጥቶ መቀበልን ጥበብ የራሷ ለማድረግ የበቃች እንደሆን ነው።

ወደ 1966 አብዮት ጉዳይ ለመመለስ፤ በኢሕአፓና በመኢሶን ላይ በተገቢ ከሚቀርቡት ወቀሳዎች ዋነኛዎቹ፣ አንደኛ፣ "ነጭ እና ቀይ ሽበር" በተባሉት

በደረሰው የፖለቲካ መገዳደልና መጠፋፋት ነው። ሁለተኛ፣ በሥልጣን አያያዝ ረገድ በተከተሉት ስልት ነው። በሚከተሉት ሁለት ክፍሎች ውስጥ፣ ጉዳዮቹን በየወቅቱ ሁኔታዎች ውስጥ በአጭር በአጭሩ እያካተትኩ አትታለሁ።

## "ነጭ ሽብር/ቀይ ሽብር"

"ነጭ/ቀይ ሽበር" ውስብስብ ክስተት ነበር። በሂደቱም አንዳንድ ጊዜ የተፈፀመው ግድያ "ቀይ "ይሁን "ነጭ" ግልፅ አልነበረም። ለዚህም ራሱ የኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ የሚፈፅማቸውን ግድያዎች አንዳንድ ጊዜ የሚያስታውቀው "ነጭ ሽብር" እያለ ነበር። የኢህአፓ አመራር የሚፈፅማቸውንም ግድያዎች አንዳንድ ጊዜ የሚገልፀው፣ እንደሚከተለው "ቀይ ሽብር" እያለ ነበር።

> ጭቁኖች ለፀረ-ሕዝብ አመፅ አብዮታዊ አመፅ ምላሽ እየሰጡ ናቸው። ነጭ ሽብርን በቀይ ሽብር እየመከቱ ናቸው። ፀረ-ሕዝቦችን በከተማም በገጠርም እየደፉ ናቸው።"[42]

ሌላም ጊዜ ከከተሞች ስንቅ፣ መድሐኒት፣ ትጥቅ፣ ገንዘብ እና መረጃ ለኢሕአፓ የአሲምባ ሠራዊትና ለተለያዩት ግንባሮች አቀባይ በነበሩ የድርጅቶቹ አባሎች ላይ ደርግ የሚወስዳቸው እርምጃዎች "ቀይ ሽብር" እየተባሉ ይገለፁ ነበር። ደግሞም በሌላ ጊዜ፣ በኢሕአፓ አመራርና "አንጃ" በተባለው ቡድኑ መካከል ይካሄድ የነበረው መገዳደል "ቀይ ሽብር" በተባለው እንደተፈፀመ ይነገር ነበር። ክፍሉ ታደሰ እንደገለፀውም፣

> ከግንቦት 1969 አጋማሽ ጀምሮ እስከ ነሐሴ ድረስ ብቻ አንጃው (የብርሃነመስቀል ረዳ/ጌታቸው ማሩ ቡድን) በኢሕአፓ ላይ ያደረሰው ጉዳት፣ የሕዝብ ድረጅት ጉዳይ ፅ/ቤት በሕልውናው ጊዜ ሁሉ ካደረሰው ጉዳት እና ጥፋት በእጅጉ ይበልጣል"[43]

ክፍሉ ታደሰ በተጨማሪ፣ "አንጃ" የተባለው የኢህአፓ ቡድን "የብዙኃን መሥመር" በተባለው ፅሑፉ የኢሕአፓ አመራር (ክሊኩ) ስለሚፈፅምበት ግድያ እንደሚከተለው አስታውቆ እንደነበር ይጠቅሳል።

> ኢህአፓ የፖለቲካ ቢሮውን (የክሊኩን) መሥመር አንቀበልም ያሉትን አያሌ የድርጅቱን አባላት ንፁህ ደም አፍስሷል።"[44]

የኢህአፓ አመራር "ጠላት" ባላቸው ላይ ቀርቶ በራሱ አባሎች ላይ የፈፀማቸውን ግድያዎች "የመከላከያ እርምጃዎች" እንደነበሩ ደጋግሞ ይገልፃል። ነገር ግን ከ1968 ጀምሮ "ባንደዎችን እና ፊዳስቶችን" በ"ጠረባ ቡድኖች" ሲያስደበድብ የነበረው፣ የነሐሴውን "የግድያ ሂደት" ያወጀው፣ ግድያ የተወሰነባቸውን "የባንዳ ምሑራን" የስም ዝርዝር ለገዳይ ቡድኖቹ ሲያሰራጭ የነበረው እና፣

> የከተማ ትጥቅ ትግልን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመርኩዘን አስፈላጊነቱንና የሚቻል መሆኑን አምነን የጀመርነው ነው"[45]

---

[42] አብዮታዊ ወጣት፣ ቁጥር 9፣ (ቀን ያልተፃፈበት)።

[43] ክፍሉ ታደሰ፣ ያ ትውልድ፣ ቅፅ 3፣ 189።

[44] እንደላይኛው፣ 211፣ (ቅንፍ የተጨመረ)።

[45] ዲሞክራሲያ፣ ፋሺስቶች ሲወጠሩ፣ ቅፅ 4፣ ቁጥር 1፣ (ቀን የሌለበት)።

እያለ ሲያስታወቅ የነበረው ከሐምሌ 1968 ጀምሮ የኢህአፓን አመራር የያዘው ቡድን (ክሊክ) ነበር። አቶ ያሬድ ጥበቡ "በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመርኩዘን" የተባለውን ሲያብራራ፤ የኢሕአፓ አመራር ወደ ከተማ ትጥቅ ትግል የዞረው፣

> "የገጠሩ ገበሬ በአዋጁ የተነሳ አብዮታዊ ኃይል አይደለም። የሚታገልበት ምክንያት የለውም። አብዮታዊ ወኔው ተሰልቧል። ዋናው ትግል መሆን ያለበት በከተማ ነው።"[46]

ከሚል "ትንታኔ" በመነሳት ነበር። ትንታኔውን እና የከተማ ትጥቅ የተባለውን የተቃወሙት እነጌታቸው ማሩ አንጃ ተብለው ተፈረጁ። የሞት ቅጣት ጭምር ተበይኖባቸው አሰቃቂ ግድያ ተፈፀመባቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በኮሎኔል መንግሥቱ ላይም ግድያ ተቃጣ። ሙከራው ግን፣ የይዋጣልን ግብዣ እና የመፈቅለ መንግሥት ሙከራ እንጂ፤ "የመከላከያ እርምጃ" አልነበረም።

ከፍ ሲል እንደተባለው፣ 1968 ከፉም ለማም ይፋዊ ውይይቶች የተካሄዱበት ዓመት ነበር። 1969 ግን፣ የፖለቲክ ግድያ የተጀመረበትና የተስፋፋበት ዓመት ሆነ። በኋላ "ነጭ ሽብር" የተባለው የፖለቲክ ግድያ ጀማሪና ፈፃሚም እነብርሃነ መስቀልን አስወግዶ የኢሕአፓን አመራር የጨበጠው የተስፋዬ ደበሳይ፣ የዘርዑ ክኽሽንና የክፍሉ ታደሰ ቡድን እንደነበር አሁን አሁን ግልፅ እየሆነ መጥቷል። ቡድኑ የፖለቲካ ግድያውን የጀመረውም ገና በ1968 ዓ.ም.

> ኢሕአፓ በአሁኑ ሰዓት የሚያካሂደው በፍፁም ተራ ሽብር አይደለም። አብዮታዊ ሽብር ብቻም አይደለም። በከተማም በገጠርም የትጥቅ ትግልን ነው። ...የገጠሩ የትጥቅ ትግል በአብዛኛው የ3ኛው ዓለም አገሮች ዋነኛ የትግል መስክ ሲሆን፣ የከተማ የትጥቅ ትግልን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመርኩዘን፣ አስፈላጊነቱን እና የሚቻል መሆኑን አምነን የጀመርነው ነው።[47]

እያለ በማወጅ ጭምር ነበር። ከመስከረም 1969 ጀምሮ በግድያ ተሰማራ። በርካታ የመኢሶን አባላትንና ወዳጆችን ገደለ። ዝርዝሩ ከሞላ ጎደል፣ የመኢሶን ሰማዕታት መታሰቢያ በሚል ርዕስ በታተመው መፅሐፍ ውስጥ ይገኛል።[48]

ሌላም ግን፣ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት (ሕወሓት) በፈፀመው ተንኮል የብዙ ንፁህ ትግራዊያን ሕይወት "በቀይ ሽብር" ስም ተቀጭቷል። አቶ ገብሩ አሥራት የሚከተለውን ይተርካሉ።

> "በ1970 ዓ.ም. ቁጥራቸው የማይናቅ የትግራይ ተወላጆች ደርግን ማገልገል ጀምረው ነበር። እነዚህ በሁሉም የአውራጃ እና የወረዳ ከተሞች ሕዝቡን ያውኩ ስለነበር፤ ሕወሓት ሊይጠፋቸው ዘዴ ቀየሰ። የተቀየሰው ዘዴ፣ የሚያውኩትን ግለሰቦች ደርግ ራሱ እንዲያጠፋቸው ነበር። ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ፣ በወቅቱ የፖለቲካ ኃላፊ ለነበረው ዓባይ ፀሐዬ የተላከ ደብዳቤ አስመስሎ አንድ ደብዳቤ ተዘጋጀ። በደብዳቤው ውስጥ በኮድ ብቻ የተፃፈ የብዙ ሰዎች የስም ዝርዝር ሠፍሮ ነበር።... ስሞቹ ሆን ተብሎ በኮድ ይፃፉ እንጂ፤ የደርግ ባለሙያዎች በቀላሉ ሊፈቱት እንደሚችሉ ተደርጎ የተዘጋጀ ነበር።
>
> ሦስት ታጋዮች ደብዳቤውን ይዘው አክሱም ለሚገኘው አስተዳደር እጃቸውን ሰጡ።... ደብዳቤው ሲከፈትም፣ ኮድ የሚፈቱ ባለሙያዎች በቀላሉ ይፈቱታል። በርካታ ታማኝ የተባሉ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አድራጅ ኮሚሺን (ኢሠፓኮ) ካድሬዎች እና አስተዳዳሪዎች የሕወሓት አባላት እንደሆኑ ይረጋገጣል።
>
> ሕወሓት በዚህ ዘዴ፣ በክልሉ ቀንደኛ ተዋንያን የነበሩትን ካድሬዎች እና ታጣቂዎች በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ አደረገ። ... ደርግ ከሚሰጣቸው መግለጫዎች መሃልም፣ 'ሲያሤሩ የተገኙ የሕወሓት

---

[46] ናሁ ቲቪ፣ መጋቢት 7፣ 2016

[47] ዲሞክራሲያ ቅጽ 4፣ ቁጥር 11፣ (ቀን የሌለበት)።

[48] ጓደኞች፣ የመኢሶን ሰማዕታት፣ 2016 ዓ.ም.።

የከተማ ውስጥ አስተባባሪዎች፣ ፀረ አብዮት ድርጊቶችን ሲፈፅሙ ለመገኘታቸው ከብዙ አቅጣጫ በማያጠራጥር ሁኔታ ተረጋግጦ እርምጃ የተወሰደባቸው እና ጂሌዎቻቸውም የተያዙ ለመሆናቸው በሠፊው ሕዝብ ፊት እናረጋግጣልን' የሚሉ ነበሩ።... ከአንድ ሺህ በላይ የማኅበራት መሪዎች፣ የመንግሥት ሹመኞች፣ የኢሠፓአኮ ካድሬዎች እና ታጣቂ ሚሊሻዎች ታሥረዋል።"[49]

መኢሶን እስከ መስከረም 1969 ድረስ፣ ከኢሕአፓ ጋር በትንተና፣ በፖለቲካ መሥመርና በትግል ስልት ጥያቄዎች ዙሪያ የነበሩት ልዩነቶች የኢሕአፓን አመራር ወደ ግድያ ፖለቲካ ሊወስዱ ይችላሉ የሚል ግምት አልነበረውም። ግድያው መፈፀም ሲጀመርም፤ መኢሶንን ግራ ያጋባ፣ በውጥረት ውስጥ የከተተ ክስተት ነበር። ተደጋግሞ እንደተገለፀው፣ የኢሕአፓ አመራር "የግድያ ሂደት" በተጀመረበት ወቅት መኢሶን ለማጥቃት ቀርቶ ራሱንም ለመከላከም የሚችል አልነበረም። አመራሩ ሊሰጥ የቻለውም መመሪያ፣ "የማደሪያ ሥፍራ፣ መጓጓዣና የመግቢያ መውጫ ሰዓቶችን ለዋውጡ" ከሚል ያለፈ አልነበረም።

"ቀይ ሽብር" በሚል በኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ ድርጅት የተካሄደው የመንግሥት ሽብር በአማካይ እስከመጋቢት 1970 ድረስ ዘለቀ። የመኢሶን፣ የኢሕአፓ፣ የኢጭአት፣ የወዝ አደር ሊግ፤ የኦነግ፣ የሕወሓት፣ የኢ.ፒ.ሌ.ሌፍ.፣ የኢ.ሌ.ሌፍ፤ የኢዲሕ አባሎችና ወዳጆች፤ የቢሮክራሲውና የመለዮ ለባሹ አባሎች፣ መምሕራን፣ ነጋዴዎች፣ ወዝ አደሮች፣ ገበሬዎች እና ወላጆች... ሁሉ ተገደሉ። ከደረጉም ውስጥ መቶ አለቃ ገበያው ተመስገንን የመሳሰሉት ተገደሉ።

ይህ በዚህ ሲሆን፤ የኢህአፓን አመራር በሐምሌ 1968 የጨበጠው ቡድን ሲያሠራጭ ከነበረው "ትንተና"፣ ያራመድ ከነበረው ፖለቲካና "የግድያ ሂደት" ከተባለው መስመሩ ጀርባ የነበረው የኤርትራ ግንባሮች ሚና ምን እንደነበር ግልፅ አይደለም። በዚህ ጉዳይ የኢሕአፓ የቅድመ እና የድኅረ ሐምሌ 1968 አመራሮች መስመሮች በቅጡ ቢመረመሩ፣ አንዳንድ ጉድዮች ግልፅ ሊሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱም አንደኛ፣ እነብርሃነመስቀልን የተካው ቡድን "የግድያ ሂደት" የተባለውን ስልት የቀየሰው በሐምሌ/ነሐሴ ወር ኤርትራ ደርሶ ከተመለሰ በኋላ ነበር። ሁለተኛ፣ በኮሎኔል መንግሥቱ ላይ በተቃጣው የግድያ ሙከራ ውስጥ የኤርትራ ስኳዶች ተሳትፈው እንደነበር ግልፅ እየሆነ መጥቷል። ሦስተኛ፣ "አንጃ" የተባለው የብርሃነመስቀል ረዳ/ጌታቸው ማሩ ቡድን፣ የአዲሱን አመራር ("የክሊኩን") ትንተናዎች እና የፖለቲካ ግድያ ስህተተኛነት ለማስገንዘብ ተደጋጋሚ ጥረት አድርጎ ነበር። የሐምሌ 1968ቱ የኢህአፓ አመራር ግን፣ በዚያው ከቸቸ። አልፎም ሄዶ፣ "የአንጃውን" አባላት በግድያ ለመደምሰስ ወሰነ። ገደለ። አንደኛው፣ በጌታቸው ማሩ ላይ የፈፀመው አሰቃቂ ግድያ ነበር። ሌላውም፣ በእሥር ይዟቸው በነበረው በነይርጋ ተሰማ ላይ የተፈፀመው ግድያ ነበር። ብርሃነመስቀልም ከግድያው ለማምለጥ ያለበቂ ዝግጅት ወደመርሐቤቴ ለማፈገፍግ ተገደደ።

አንዳንድ ምሑራን እንደዚያ ዓይነቱን ፖለቲካ የትውልድ ዕልቂት "የፖለቲካ ፍጅት" (politicide) በማለት ለየት ባለ መልኩ ይተነትኑታል። "የፖለቲካ ፍጅት" የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ርዕዮተ ዓለም እና ፖለቲካ የተለየ ስለሆነ ብቻ፤ ድርጅቱን በግድያ ለመጨረስና ለመደምሰስ በመንግሥት ወይንም በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውሳኔ የሚፈፀም የፖለቲካ ግድያ ነው ለማለት ነው። በኢትዮጵያ እንደደረሰው "የፖለቲካ ፍጅት" ዓይነት ማለት ነው።

እዚሁ ላይ ግን፣ የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ ልዩነትን በስሞች ልጠፋ፣ በቅፅሎች ጅረት፣ በስድብ፣ በማስፈራራትና በድብደባ ጭምር የማፈን ዘይቤ በአብዮቱ ዘመን ብቻ የተከሰተ እንዳልነበረም ማስታወስ ያስፈልጋል። ዘይቤው ከአብዮቱ በፊትም በመጀመሪያ በአገር ውስጡ የተማሪ ንቅናቄ ውስጥ ከ1962 ጀምሮ በተስፋፋው "የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የኢትዮጵያን አብዮት ለመምራት ከሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል" ባዮችና የ"ፋኖ ተሰማራ..." ጥሪ አራጋቢዎች ዘመን አቀነቀነ። ከዚህም ጊዜ ጀምሮ ለማለት ይቻላል፤ ራሳቸውን እንደፍፁም አብዮታዊያን (ሪቮ) የካቡ ተማሪዎች ባልተከተሏቸው ተማሪዎች ላይ

[49] ገብሩ አሥራት፣ ሉዓላዊነት እና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ፣ 2006፣ 127-129

“ሳቦ” (saboteurs)፣ “አሻጥረኛ፣ ጆሮ-ጠቢ፣ የሲ.አይ.ኤ. ወኪል፣ አድር-ባይ፣ ተንታች፣ ፈሪ፣ ጆሊ-ጃክ...” የሚሉ ቅፅሎችን መለጠፍ ያዙ። አልፈውም ኃይል አስከመጠቀም ሄዱ።[50] ይኼው ዘይቤ ከ1963 ጀምሮ በውጭ አገራት በነበሩ የተማሪ ንቅናቄዎች ውስጥ ተስፋፋ። የኋላ ኋላም የአገር ውስጡን የተማሪዎች ንቅናቄ እንደከፋፈለው የውጪውንም ከፋፈለ።

በኢትዮጵያ በበቀሉ ድርጅቶች ዘንድ የተለየ አስተያየት ያላቸውን ታጋዮች በግድያ ማስወገድ የተጀመረውም ገና ቀደም ሲል ጀምሮ ነበር። የመጀመሪያዎቹ ምናልባት በኢሳያስ አፈወርቂ የተገደሉት እነ ዮሐንስ ስብሃቱ (የመንካ ቡድን) ሳይሆኑ አይቀርም። ከዚያም በኢሕአፓ፣ በሕወሓት፣ በኦነግና በሌሎቹ የብሔሮች ድርጅቶች ውስጥ የፖለቲካ ግድያዎች ተፈፅመዋል። የሕወሓትን በሚመለከተው ለምሳሌ፣ አቶ ገብሩ አሥራት በዝርዝር ተርከዋል።[51] እነዚሁ በሌላው በኩል ደግሞ፣ በጦር ኃይል ጭምር ተጠፋፍተዋል። ለዚህም በኤርትራ ግንባሮች መካከል፣ በሕወሓት እና ትሓግ፣ በኢሕአፓ እና ኢዲሕ፣ በሕወሓት እና ኢሕአፓ፣ በሕወሓት እና ኢዲሕ መካከል የደረሱትን መጠፋፋቶች ለማስታወስ ይቻላል። በዚህ አኳያ በመኢሶን እና በ60ዎቹ በኢትዮጵይ በበቀሉት ድርጅቶች መካከል አንድ ተጨማሪ እና መሠረታዊ ልዩነትም፤ መኢሶን ወደውጭ ብቻ ሳይሆን፣ ለድርጅት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ውይይት እና የጋራ ውሳኔ ክፍት ነበር። ከሌሎቹ በኢትዮጵያ ከበቀሉት ድርጅቶች በተለየም፤ በአመለካከት ሆነ በአቋም በተለዩት ዓባላቱ ላይ ይፋ የማስጠላት እና የውግዘት ዘመቻ ሆነ ግድያ አካሂዶ እና ፈፅሞ አያውቅም።

“ነጭ/ቀይ ሽበር” መች ተጀመረ? ማን ጀመረው? ማን አጠቃ? ማን ተከላከለ? ወቅቶቹ የትኞቹ ነበሩ? የእያንዳንዱ ወቅት ሂደት እንዴት ነበር? የየወቅቱ ተዋናዮች እነማን ነበሩ? የፖለቲካ-ማኅበራዊ ውጤቶቹስ የትኞቹ ናቸው?... ለሚሉት ጥያቄዎች፤ አንዳንድ የታሪክ ተመራማሪዎች የየበኩላቸውን አስተያየት ሰጥተዋል። ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ፣ ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ፣ ዶ/ር መላኩ ተገኝ፣ ፕሮፌሰር ጴጥሮስ ቶጃ፡ አበራ የማነአብ እና የመሳሰሉት ያቀረቧቸው ፅሑፎች አንዳንዶቹ ናቸው።[52]

የደረሰው ጥፋት ከባድ የታሪክ ጠባሳ ሆኖ እንደታተመ አያጠያይቅም። በሕይወታቸው የከፈሉት፣ በእሥራት የተሰቃዩት፣ በስደት የተንገላቱት ብዙ ሺህ ናቸው። በሐዘንና በሰቀቀን ማቅ የለበሱት ወላጆች፣ ዘመዶችና ጓደኞች ብዙ መቶ ሺህ ናቸው። ይህ በቀላሉ ተፍቆ ወይንም ተቃሎ የሚታለፍ አይደለም። የጠባሳው አሻራ ባንድ ወቅት “ፖለቲካና ኮረንቲ” አስብሎ እንደነበርም ይታወሳል። በታሪክ ዓይን ሲታይ ኢትዮጵያ በርግጥም ከቃሮራ እስከ ሞያሌ፣ ከአሶሳ አስከ ቶጎ ውጫሌ ምን ምን የመሳሰሉ ልጆቿን ለሁለተኛ ጊዜ በገፍ አጥታለች። የመጀመሪያዎቹ ግራዚያኒ በየካቲትና በግንቦት 1929 የጨረሳቸው የኢትዮጵያ አገር ወዳድ ምሑራን፣ አርበኞችና ምዕመናን ነበሩ።

ግራዚያኒ በየካቲት 1929 በአዲስ አበባ ከተማ በነዛው የጥቂት ቀናት ሽብር ብቻ፤ ወደ 300 ምሑራን ያህል አለቁ። ከ2000 (በእንግሊዝ ቆንሲል) እስከ 6000 (በፈረንሳይ ሚሽን) የሚገመት የከተማዋ ኗሪ ተፈጀ። በግንቦት ወር በደብረ ሊባኖስ ባካሄደው ቀጣይ ጭፍጨፋ ከ500 የማያንሱ መነኮሳትና ከ2000 በላይ ምዕመናን ተገደሉ። በ1960 መግቢያ ላይ በሳህል በረሀ በነኢሳያስ አፈወርቂ ከተገደሉት ከነዮሐንስ ስብሃቱ (የመንካ ቡድን) ጀምሮ በኢሕአፓ አመራር እና በኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ የመንግሥት ሽብር እስከተፈጁት ድረስ ቢታሰብ በሺህ የሚቆጠሩ ተገድለዋል።

---

[50] ባሕሩ ዘውዴ፣ 2014፣ 255።

[51] ገብሩ አሥራት፣ ሉዓላዊነት እና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ፣ 2006፣ 87-91

[52] ባሕሩ ዘውዴ፣ The “Red Terror” in Ethiopia። ገበሩ ታረቀ፣ The Red Terror in Ethiopia: An Historical Aberration። መላኩ ተገኝ፣ Mengistu’s’red terror’። ጴጥሮስ ቶጃ፣ The revolutionary endgame of political power: the genealogy of ‘red terror’ in Ethiopia። Jaco Wiebel፣ Revolutionary Terror Campaigns in Addis Ababa፣ 2014። Asegedew Shimeles፣ TPLF, world’s most virulent and violent crew፣ 2022።

በዚህ ላይ፤ በኤርትራ ምድር የመጀመሪያው ጥይት ከተተኮሰበት ከነሐሴ 1953 እስከ 1990ው የኢትዮጵያ ኤርትራ ጦርነት ድረስ በተካሄዱት ጦርነቶች ካንደኛው ይሁን ከሌላው ወገን በየጦር ሜዳው የቀረው ወገን ሲታከል ብዙ መቶ ሺህ ይሆናል። ይህ ሁሉ የደረሰው ከ1929 እስከ 1990 ባለው የ60 ዓመታት ዕድሜ ነበር። በአገሪቱና በሕዝቦቿ ላይ የጫነው የታሪክ ሸክምና የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ መዘዝ ግን በኢትዮጵያ ተራሮችና ሸለቆዎች ተስተጋብቶ አላበቃም።

የፖለቲካ ግድያውን አስመልክቶ "መቼም፣ የትም እንዳይደገም" በሚል ማሳሰቢያ "የቀይ ሽብር ሰማዕታት መታሰቢያ" የተባለ ቤት በአዲስ አበባ መደራጀቱ ደህና ጅምር ነበር። ይሁንና በዕቅዱ መጀመሪያ ላይ ተነግሮ እንደነበረው "መታሰቢያው "በነጭም" ይሁን "በቀይ" ሽብር" ወይንም በፖለቲካ ግድያ የረገፉትን ሁሉ ከነፎቶግራፋቸው አካቶና አስቦ መቆም ነበረበት እንጂ፤ በሥራ ላይ እንደዋለው ወገናዊ በሆነ ሕሊና ተደራጅቶ መቅረብ አልነበረበትም። ቤቱ ከነስሙ ተቀይሮ እና ቢያንስ በ1953ቱ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት የደረሰውን የፖለቲካ ግድያ አክሎ ሁሉንም የ60ዎቹን የፖለቲካ ግድያዎች አካቶ መደራጀት ነበረበት። እንደዚሁም፣ ከ1983 ወዲህ የተፈፀሙትን የፖለቲካ ግድያዎች ሁሉ አካቶ። መጠሪያውም፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ግድያዎች ሰማዕታት መታሰቢያ ቢባል ይመረጣል።

በሌላ በኩል፣ ብዛቱን የሚያሳንሱ ወይንም የሚያሳብጡ አኃዞች እንዳመጣ ሲደረደሩ ይስተዋላል። ይህም ከወገናዊነት ኮሮጆ እንዳልተወጣ ከመመስከሩ ባለፈ፤ ወደዕውነታው ለመጠጋት የሚረዳ አይደለም። በነጋድራስ ገብረሕይወት ቆንጆ አባባል እንደዚህ ዓይነቱ ወገናዊነት "አስተካክለን ካሰብን ዘንድ (በተለይም) ለመንግሥት የሚገባው ሥራው አይደለም።"

የኮሌኔል መንግሥቱ-ሰደድ/ኢሠፓኮ-ኢሠፓ ሥርዓት አንድም የሚወገዘው ፍትህን በመርገጡና ፍርደ-ገምድል ስለነበር ነው። እንደዚያ ዓይነቱ አገዛዝ "መቼም፣ የትም እንዳይደገም" ስሜቶችን ተቆጣጥሮ በታሪክ ላይ ፍርደ ገምድል ከመሆን መታቀብ ያስፈልጋል። ጎዶሎ (ፍርደ ገምድል) መታሰቢያ የሚያስተላልፈው ትምህርትና ተመክሮ ጎደሎ ነው። ሊታረም ይገባዋል። ነጋድራስ ገብረሕይወት እንዳሉት፦

> *"...የታሪክ ትምህርት ግን የሚጠቅም የዕውነተኛ ታሪክ ትምህርት ሲሆን ነው። ዕውነተኛንም ታሪክ ለመፃፍ ቀላል ነገር አይደለም። የሚከተሉትን ሦስት የእግዚአብሔር ስጦታዎች ያስፈልጋል። መጀመሪያ ተመልካች ልቦና፤ የተደረገውን ለማስተዋል። ሁለተኛ የማያደላ አእምሮ፤ በተደረገው ለመፍረድ። ሦስተኛ የጠራ ቋንቋ አገባብ፤ የተመለከቱትን እና የፈረዱትን ለማስታወቅ።*[53]

የ60ዎቹን የፖለቲካ ግድያዎች በሚመለከተው፣ የኢሕአፓ አባላት የነበሩ ታጋዮች ከሐምሌ 1968 ጀምሮ የኢሕአፓን አመራር የጨበጠው ቡድን (ክሊክ) በኢሕአፓ ስም የፈፀማቸው የፖለቲካ ግደያዎች ከባድ ስህተትና ጥፋት እንደነበሩ ቢያምኑና ቢቀበሉ፤ ትምህርት ሰጪ ይሆን ነበር። ራሴም ነገሮችን በዚሁ መንፈስ ተመልሼ ሳስላስል፣ መኢሶን በነበረው ሁኔታ ውስጥ ራሱን ለመከላከል የወሰዳቸው እርምጃዎች ትክክል እንደነበሩ ባምንም ቅሉ፤ ጥያቄው በኮሎኔል መንግሥቱ አብዮታዊ ስደድ ባለሥልጣኖች ተደመጠ/አልተደመጠ ሕጋዊ ጎዳናዎች እንዲከበሩ አለመጠየቁና አለመታገሉ ስህተት ነበር። እንደዚሁም የኢሕአፓ አመራር አዳመጠም/አላዳመጠም፣ ተስማማም/አልተስማማም፤ መኢሶን አመራሩን እንደምንም ቀርቦ የግድያ ፖለቲካውን እንዲያቆም መሞከር ነበረበት።

---

[53] ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ *ሥራዎች*፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2002፣ 36።

## የፖለቲካ ግድያ እና የፖለቲካ ሥልጣን

የፖለቲካ ሥልጣንን በግድያ መነጣጠቅ፤ በኢትዮጵያ በየጊዜው የተነሱት የሰሜን፣ የደቡብ፣ የምሥራቅና የምዕራብ የኢትዮጵያ አካባቢያዊ መንግሥታትና ገዢዎች ዓይነተኛ የፖለቲካ አካሄድ ሆኖ የዘለቀ ነው። ይህንንም ለማስተዋል ወደ ዮዲት፣ የዛገዌ፣ የምሥራቅ ኢትዮጵያ ሡልጣናት፣ የሸዋ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ (የጊቤ) መንግሥታት እና አባ-ዱላ/አባ ሞቲ፣ የየጁ ወረ-ሴኽ ሥርወ መንግሥት እና ዘመነ መሣፍንት ርቆ መሄድ አይስፈልግም። የአፄያዊ ግዛት አራማጆች ወደነበሩት አፄ ልብነድንግል እና ኢማም አህመድ ኢብራሂም (አህመድ ግራኝ)፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ እና አፄ ምኒሊክ መመለስም አይስፈልግም። በምናውቃቸው አባቶቻችን ዘመን በአቤቶ ኢያሱ እና በራስ ተፈሪ መካከል የተከሄዱት ረጅም የሥልጣን ንጥቂያ ጦርነቶች በእጅግ ያስከፈሉ እንደነበሩ ማስታወሱ ይበቃል። ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በተሰኘው መፅሐፋቸው በአንድ የሰገሌ ጦርነት የደረሰውን ብቻ እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> "በውጊያው ላይ ከሁለቱም በኩል የሞተው ወታደር 15ሺህ የቆሰለው 20ሺህ ያህል ነው። ይኸውም በአድዋ ጦርነት የሞተውንና የቆሰለውን በቅርብ ሂሳብ ዕጥፍ ያደርገዋል። በአድዋ ጦርነት ከኢትዮጵያዊያን በኩል ሰባት ሺህ አምስት መቶ ስድሳ እንደሞተ እና 10 ሺህ እንደቆሰለ ባለታሪኮች ገልጸዋል እና ከዚሁ ጋር ማነፃፀር ነው።"[54]

ይህ በዚህ እንዳለ በታህሣሥ 1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት ተይዘው ከነበሩት 21 የንጉሡ ነገሥቱ ባለሥልጣኖች መካከል 15ቱ ተረሸኑ። ጀ/ል መንግሥቱ ንዋይ ለፍርድ ቤት በሰጡት የመጨረሻ ቃላቸው፣ "ድህውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲገሽልጡ ከነበሩት ... መካከል ጥቂቶቹን ገለል ማድረጌን ሳስታውስ... ደስ ይለኛል" ብለው ነበር እየተባለ መነገሩ፤ ግፍነቱን አይሽረውም ።

የታህሣሥ 1953ቱን የፖለቲካ ግድያ የኅዳር 1967ቱ የፖለቲካ ግድያ ከ14 ዓመታት በኋላ ተከተለው። እጃቸውን ሰጥተው እና ፍርድን እና ፍትሕን ሲጠባበቁ የነበሩ የንጉሡ ነገሥቱ ባለሥልጣኖች፣ የለውጥ አራማጆች የነበሩ ወጣቶች እና መለዮ ለባሾች በግፍ ተረሸኑ። "ፀለምት ቅዳሚት" በተባለችው በዚያች ዕለት በደርጉ የተሰጠው መግለጫ ከላይኛው እስከዚህ የተለየ አልነበረም። ደርግ ሰነባብቶ የንጉሡ ነገሥቱን ሕልፈት ሲያስታውቅ፣ ስለአሟሟታቸው በይፋ ያሳወቀው ነገር አልነበረም። እስከ ኢህአዴግ ዘመንም ድረስ፤ የተቀበሩበት ሥፍራ እንኳን አይታወቅም ነበር። ለታሪክ ማስታወሻ ያህል፤ የአቤቶ ኢያሱ አሟሟትና የተቀበሩበት ሥፍራ እስከዛሬ አይታወቅም። የኃይሌ ፊዳ እና የብርሃነመስቀል ረዳም ። እንደዚሁም የዶ/ር ተረፈ ወልደፃዲቅ፣ የአጥናፍ ዓለም ይማም፣ የኢዮብ ታደሰ፣ ከበደ ደሪባ፣ የሽመልስ ኦላና፣ የመርዕድ ከበደ፣ የአሰፋ ነመራ፣ የዲማ ጉዲና፣ የኩምሳ ካሮርሳ እና የበርካታ የመኢሶን ታጋዮች። የኢሕአፓ ታጋዮችም እንደዚሁ።

የአብዮቱ ዘመን የፖለቲካ ግድያዎች የተፈፀሙት ዙሮ ዙሮ በሥልጣን ለመቆየት ወይንም የሥልጣን ባለቤት ለመሆን ነበር። ኮሎኔል መንግሥቱ ከኅዳር 1967 ጀምሮ የሥልጣን ተፋላሚዎችን በግድያ አስወገዱ። የኢሕአፓ አመራር "የግድያ ሂደት" ያለውን የፖለቲካ ግድያ በነሐሴ 1968 አውጆ ፈፀመ። ኮሎኔል መንግሥቱ ከጥር 1969 በኋላ ከአብዮታዊ ሰደድ ውጭ የነበሩትን ለማስወገድ "ቀይ ሽብር" ያሉትን የመንግሥት ሽብር አካሄዱ።

ይህ ግልፅ ቢሆንም፤ በሐምሌ 1968 ዓ.ም. የኢሕአፓን አመራር የጨበጠው ቡድን (ክሊክ) ወደ ኤርትራ ዘልቆ ከተመለሰ በኋላ ሲያሠራጭ ከነበረው "ትንተና"፣ ያራመድ ከነበረው ፖለቲካ እና "የግድያ ሂደት" ከተባለው አካሄዱ ጀርባ የነበረው የኤርትራ ግንባሮች ሚና ምን እንደነበር ግልፅ አይደለም። በያዝነው "የነጭ እና ቀየይ ሽብር" ጉዳይም፤ የኢሕአፓን ቅድመ እና ድኅረ 1968 አመራሮች መስመሮች ለያይቶ

[54] መርስዔ ኀዘን ወ/ቂርቆስ «የሐያኛው ክፍለ-ዘመን መባቻ»፣ 177።

መመርመር እጅግ አስፈላጊ ነው። ክፍሉ ታደሰ ለምሳሌ ያህል በሐምሌ 1968 ዓ.ም. የኢሕአፓን አመራር የጨበጠው ቡድን ኤርትራ ደርሶ ሲመለስ የኤርትራን ቅኝ ግዛትነት ተቀብሎ እንደተመለሰና ሂስ እንደተደረገበት ያወሳል።

የቅድመ ሐምሌ 1968 ዓ.ም. የኢሕአፓ አመራር የመሬት አዋጅ እንደታወጀ፡-

> “ከሦስቱ ዓበይት ጥያቄዎች የመጀመሪያው በመፈፀሙ፣ ከወዝ አደሩ እና ከገበሬው አብራክ የተገኙት ጥቂት ተራማጅ መኮንኖች ለሠፊው ሕዝብ ያላቸውን ፅኑ ታማኝነት በተጨባጭ ማስረጃ በማሳየታቸው ፤ እነዚሁ የሕዝብ ወገኖች በደርጉ ውስጥ ሆነው እስከመጨረሻው እንደሚታገሉ ተስፋ እናደርጋለን።”

በሚል ከመኢሶን ባልተለየ ተስፋውን ያስተጋባ ነበር። የድሕረ-ሐምሌ 1968ቱ የኢሕአፓ አመራር ግን፤ አመራሩን ከጨበጠ ከጥቂት ወራት በኋላ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ “የአብዮቱን ዕምብርት ጥያቄ እና የኢትዮጵያ የግራ ኃይሎች ሕዝቡን የሚያሰባስቡበትንና የሚያታግሉበትን (የመሬት ላራሹ) ጥያቄ ደርግ ቀማቸው” እያለ እና “ከመሠረቱና ከፅንሱ ተራማጅና ተደጋፊ ቢሆንም …’ያዩት እንጂ አይበሉት ፍሬ’ ሆኗል” እያለ አጣጣለው። ውሎ አድሮም፣

> “ፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝምና ደርጉ አንድም ሦስትም የሆኑ ጠላቶች እንደመሆናቸው የእነዚህ ሦስት ጠላቶች መውደም ግድ ነው”

የሚለውን አቋም ያዘ። ዘማቾች ገበሬውን እየተዉ ወደከተሞች እንዲጎርፉ ጠራ። ውሎ አድሮ የፖለቲካ “ግድያ ሂደት” አወጀ። ከዚያም፣ “የከተማ ጦርነትን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመርኩዘን፣ አስፈላጊነቱን እና የሚቻል መሆኑን አምነን የጀመርነው ነው” እያለ ወደ ከተማ ጦርነትን ወደማካሄድ እና ሕዝባዊ አመፅን ወደመቀሰቀስ አመራ። የትንተና ስህተት ነበር?

በሌላ በኩል “አንጃ” የተባለው የብርሃነመስቀል ረዳ እና የነጌታቸው ማሩ ወገን የአዲሱን አመራር ቡድን (በ”አንጃው” አጠራር “የክሊኩን”) ትንተናዎች፣ መሥመርና የፖለቲካ ግድያዎች ስህተተኛነት ለማስገንዘብ ተደጋጋሚ ጥረት አድርጎ ነበር። ይሁንና የሐምሌ 1968ቱ የኢሕአፓ አመራር በዚያው ከቸቸ። አልፎም “አንጃውን” በግድያ ለመደምሰስ ወሰነ። ገደለ።

ይህን ጉዳይ አንዳንዶች እንደሚሉት “የመከላከል እርምጃ ነበር” በማለት ለመመለስ አይቻልም። ይልቁኑ፣ በወቅቱ የነበሩት የሥልጣን ተፋላሚዎች የሄዱባቸውን ሥስት የተለያዩ የሥልጣን መያዣ መንገዶች በአንክሮ መመርመር የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። አንደኛው፣ ከደርጉ ውስጥና ከውጭ በተደጋጋሚ ሲሞከሩ የነበሩት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች መንገድ ነበር። ሁለተኛው፣ ደርጉን በጦር ኃይል ለመጣልና ሥልጣንን መልሶ ለመቆጣጠር በኢዲሕ የተሞከረው መንገድ ነበር። ሦስተኛው፣ በተለይ የድህረ-ሐምሌ 1968ቱ የኢሕአፓ አመራር ቡድን (ክሊኩ) የሄደባቸውን መንገዶች ያጠቃልላሉ።

የኢሕአፓ አመራር በነዚያ የሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በመጀመሪያ ሥልጣንን በተራዘመ የትጥቅ ትግል (protracted armed struggle) ለመጨበጥ የአሲምባን ሠራዊት አቋቋመ። ጥቂት ቆይቶ፣ ሥልጣንን በፖለቲካ ግድያ እና በከተማ የትጥቅ ትግል ለመጨበጥ ተንቀሳቀሰ። ጥቂት ቆይቶ እና ከአንዳንድ የደርግ አባሎች ጋር ተባብሮ ጭምር፣ የመፈንቅለ መንግሥትን መንገድ ሞከረ። በመጨረሻም፣ ሥልጣንን በከተማ አመፅ (insurrection) መንገድ ወደመጨበጥ አቀና። በርካታ ወጣቶች ያለቁበትን የሚያዚያ 22፣ 1969 ዓ.ምን. “የታጠቀ ሰልፍ” አካሄደ። “በኢሕአፓ ታጣቂዎች ጥበቃ ይደረግለታል” የተባለው ያ “ሕዝባዊ አመፅ”፤ የበርካታ ወጣቶችን ሕይወት ያሰከፈለ ሰልፍ ሆነ። የመኢሶን መንገድ በነቃ፣ በተደራጀና በታጠቀ ረጅም ትግል፤ ሕዝባዊ ሥልጣንን ከታች መገንባትና ለሕዝባዊ ሥልጣን መብቃት የሚለው ነበር። ሕጋዊ ሁኔታዎች እስከፈቀዱና እስካስቻሉም ድረስ፤ በሕጋዊ መንገዶች ጭምር መታገል ነበር።

ወደ 1983ቱ እና 2010ሩ የሥልጣን ለውጦች በአጭሩ ብንመለስ፤ የ1983ቱ ከሠላሳ እና ከአሥራ ሰባት ዓመታት የኤርትራ እና የኢትዮጵያ ሌሎች ብሔረሰቦች የመሣሪያ ትግል በኋላ የተፈፀመ እንደነበር

ይታወቃል። እንድንቆይበት አያስፈልግም። የ2010 ዓ.ም. ለውጥ ተዋናዮች በሌላው በኩል ግን፤ "ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር" እንዳካሄዱ ደጋግመው ይገልፃሉ። ይሁንና ገለፃቸው፤ በአንድ ወገን የኢሕአዴግን አገዛዝ ለማስወገድ ለሃያ ሰባት ዓመታት ሙሉ የተካሄዱትን የተለያዩ ትግሎች የሚዘነጋ ነው። በሌላውም ወገን፣ የ2010 ዓ.ም. ለውጥ በገዢው ኢሕአዴግ ውስጥ የተካሄደ "ሰላማዊ" የድርጅት ውስጥ የሥልጣን ሽግሽግ እንጂ፤ በመግሥታዊ ሥልጣን ደረጃ ተፈፅሞ የተዘጋ ለውጥ እንዳልነበር የማያስተውል ነው። ስላልነበረም ነው፤ ከ2010 ዓ.ም. በኋላ ከትግራዩ አሰቃቂ ጦርነት አንስቶ እስከዛሬም ድረስ በተለይም በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች ውስጥ ዘግናኝ የሥልጣን ንጥቂያ ጦርነቶች እየተካሄዱ የሚገኙት።

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ነባራዊና ወቅታዊ ሁኔታ በአብዛኛው የታወቀ ስለሆነ፤ በዚህ አጭር ፅሑፍ ወደዝርዝር ገብቶ ማተት አስፈላጊ አይደለም። የሰፈነው ሁኔታ በአጭሩ፣ ለነፃና ለዲሞክራሲያዊ አገራዊ ምክክር እና ውይይት አመቺ ያልሆነ የጦርነቶች፣ የእገታዎች፣ የዝርፊያዎች፣ የመፈናቀሎች፣ የፀጥታና የደህንነት እጦት፣ የሕግ የበላይነት እና የፍትሕ አለመኖር፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት፣ በገፍ የመታሠር እና የመሰቃየት፣ በነፃ የመዘዋወር መብቶች መታገድ፣ የወንጀለኞች አለመያዝና ለፍርድ ያለመቅረብ ሁኔታ ነው። ተደምሮ ተቀንሶ የሚቀርበው ጥያቄም፣ ኢትዮጵያ ከአፍራሽና ለሕልውናዋ አሥጊ ከሆነው አሳሳቢ ሁኔታዋ ውስጥ እንዴት ትውጣ? ምን ይደረግ? የሚለው ነው።

ስለዚህም ብዙዎች፣ የሰላም እና የዕርቅ ውይይቶች እና ድርድሮች እንዲደረጉ አበክረው ይጠይቃሉ። ሌሎች፣ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም በተደጋጋሚ ይጠራሉ። ሌሎችም፣ የሽግግር መንግሥታት በክልሎች ደረጃ ሁሉ ይቋቋሙ እስከማለት ድረስ ሄደው ይጠይቃሉ። ሌሎችም ደግሞ፤ የዛሬው አገዛዝ በትጥቅ ትግል ከተወገደ በኋላ እያሉ፣ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ናቸው። ባለሥልጣኖቹ በአንድ በኩል፣ ለውይይት እና ድርድር በራችን ክፍት ነው እያሉ ይመልሳሉ። ይሁንና፣ ጭብጥ እና ይፋዊ እርምጃዎች ሲወሰዱ አይታይም። ተደረጉ ስለሚባሉ ውይይቶች እና ድርድሮችም፤ የተሟሉ ማሳወቂያዎች እና መግለጫዎች አይሰጡም።

ባለሥልጣኖቹ ስለውይይቱም፣ አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሟል እያሉ ይመልሳሉ። በሌላው በኩል በአንድ ወገን፣ አገራዊ ምክክሩን የተኩ እስኪመስል ድረስ የተለያዩ "ስብሰባዎች" እና "ወይይቶች" እዛም እዛም ይካሄዳሉ። በሌላው ወገን፣ ለአገራዊ ምክክሩ ስኬት የሚያስፈልጉት አመቻች ሁኔታዎች (ሰላም፣ ፀጥታ እና ደህንነት፣ የሕግ የበላይነት እና ፍትሕ፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እና ነፃነቶች፣ በነፃ የመዘዋወር መብት እና ወዘተ) አልሰፈኑም። ኮሚሽኑም፣ በርካታ ሥፍራዎችን ለመድረስ እንዳልቻለ እያሳወቀ ነው። ለፖለቲካ ሥልጣን የሚደረገው ትንቅንቅ አሁንም እንደቀድሞው፤ የፖለቲካ ግድያ እና የሠራዊት ጡንቻ ጉዳይ ሆኖ ከትግራይ እስከ ባሌ፣ ከጋምቤላ እስከ ሐረር እየተካሄደ ነው።

ይህ መንገድ ኢትዮጵያን ለተራዘሙ ውጊያዎች፣ ዕልቂትና ውድመት ዳርጎ፣ የሕዝቦቿን ስቃይ አና ሰቆቃ የሚያራዝም እንደሆነ ገሃድ ነው። ሁኔታው ከዚህ አንፃር ሲቃኝ፣ ካለፉት የጦርነት መንገዶች የተቀሰመ ትምህርት አለ ለማለት አይቻልም። አንዳንድ ወገኖች እንደሚገምቱት እንዲያውም፤ የዛሬው አካሄድ ኢትዮጵያን ከእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ዘፍቆ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል ይችላል። ተደጋግሞ እንደተነገረው ግን፤ ከተራዘሙ ውጊያዎች፣ ዕልቂትና ውድመት ሆነ ከእርስ በእርስ ጦርነት የሚያተርፍ አንድም ዜጋ እና አንድም ብሔር አይኖርም። ዞሮ ዞሮ በንግግር እና በድርድር በአንድ ወይንም በሌላ መንገድ እንደሚቋጭም የሚታወቅ ነው። ስለዚህም፤ ለሁሉም ወገን የሚበጀው ይልቁኑ፤ የጋራ ወደፊትን በጋራ ለመገንባት ከወዲሁ ተነጋግሮ እና ተወያይቶ፣ ተስጣጥቶ እና ተቀባብሎ፤ ተማግኖ እና ተማምሎ በአዲስ እና ዕውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ፌዴራል ውል ለመተሳሰር መነሳሳት እና መሥራት ነው።

"ጦርነት እና የፖለቲካ ግድያ በሥልጣን ተፋላሚዎች መካከል ሲካሄድና ሲፈፀም የኖረ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ነው" የሚለውን አስተያየት የሚሰጡ ጥቂቶች አይደሉም። ሁለት ጉዳዮች ቢስተዋሉ ግን፤

ምክንያቱ የፓለቲካ ባህል ከመሆን ይልቅ፤ የዲሞክራሲ፣ የሕግ የበላይነት፣ የፍትሕና የሰብዓዊ መብቶች መኖር/አለመኖር ጉዳይ መሆኑን ላለመገንዘብ አይቻልም። በመጀመሪያ፣ ከኢትዮጵያ ነገሥታትና አፄዎች ዘንድ በዘመናቸው ያልነበረውን ዲሞክራሲያዊ ሥራዓትና ዲሞክራሲያዊ የሥልጣን ሽግግር ለመጠበቅ አይቻልም። ወይንም፣ ለዲሞክራሲያዊ አገዛዝና ለዲሞክራሲያዊ የሥልጣን ሽግግር ጥያቄ የሚደረገው ትግል እየተስፋፋና እየተጠናከረ የመጣው፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተቋቋመ በኋላ እና በፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ዘመን ነው። ተመሳሳይ ትግል በኢትዮጵያም እየተናሳሳ የመጣው በአማካይ ከ50ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ነው።

ሁለተኛ ግን፣ በተለያዩት የኢትዮጵያ ለውጦች የጫጉላ ወቅቶች ዘመን በነፃ የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት እና ለምርጫ የመወዳደር ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይብዛም ይነሰም ሰፍነው ነበር። በነዚህ የዲሞክራሲ ብልጭታዎች ዘመን ለሥልጣን ጭበጣ የተካሄዱት እንቅስቃሴዎች ይብዛም ይነስም ሰላማዊ ነበሩ። ይህ ዕውነታ በራሱ፤ ጥያቄው የዲሞክራሲ፣ የሕግ የበላይነት፣ የፍትሕ እና የሰብዓዊ መብቶች መኖር/አለመኖር እንጂ፤ የባህል አለመሆኑን አስረግጦ ያስረዳል። “የባህል ነው” የሚለው አረዳድ በእኔ ዕይታ እንደውም፣ የጫጉላ ዘመናቸውን በጨረሱ ቁጥር ፀረ ዲሞክራሲ አገዛዛቸውን ለማስፈን ለማይሰንፉት ገዢዎች ይጠቅም እንደሆን እንጂ፤ እየወደቁና እየተነሱ ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለፍትሕ እና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ለሚታገሉት የኢትዮጵያ ልጆች አይበጅም።

# ማጠቃለያ

በድኅረ አብዮቱ ወጣት የታሪክ ግንዛቤ ላይ በአብዛኛው እየተሠረፀ ያለው፣ የአብዮቱ ዘመን ታጋዮች ፅንፈኛነትና የእርስ በእርስ መተላለቅ ትረካ ነው። ይህ የማይካድ ቢሆንም፤ የአብዮቱ ታጋዮች በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ አብዮት ተሳታፊና ሠሪ እንደነበሩ እንዲታወስ ያስፈልጋል። ስለነበሩም፤ ስህተቶችን ለመፈፀም የተጋለጡ ነበሩ።

እነዚያ ታጋዮች የአብዮት ተሳታፊና ሠሪ ሁነው የተገኙት፤ ለኢትዮጵያ ያላቸውን በጎ ሕልም፣ ተራማጅ ርዕዮተ ዓለም፣ ሕዝባዊ ወገናዊነት፣ የፖለተካ ፕሮግራማቸውን እና ፅናትን ይዘው እንጂ፤ በግብታዊ ለፈነዳው ሕዝባዊ አብዮትና በተከታታይ ለተከናወኑት ከባድ ለውጦች የሚመጥን ድርጅታዊ አቅም፣ ልምድ፣ ተመክሮና ብስለት ኖሯቸው አልነበረም። በሌላው ወገን አብዮቱ የፈነዳው እና የተካሄደው የትላንት ኅብረተሰቧ በኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም ድርና ማግ ዓይነት በተፈተሉባት ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር። ከታሪክና ከንጉሠ ነገሥቱ ዘመን በተወረሱ ከባድ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ጥያቄዎች (የመሬት፣ የረሃብ፣ የኤርትራ እና የብሔረሰብ፣ የዲሞክራሲ....) በተወጣጠረች ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር። ደርግ የተባለው ወታደራዊ ቡድን ብቸኛው የሥልጣን ባለቤት የሆነው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነበር። የተለያዩ ነፃ አውጭ ግንባሮች ጠንክረው በተንቀሳቀሱበት እና የፖለቲካ ግድያዎች ዕለታዊ በነበሩባት ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር። የጎረቤት እና የአከባቢ አገሮች በተፃራሪነት በቆሙባት እና ዓለምም ቀዝቃዛው ጦርነት ይባል በነበረው ሁኔታ ውስጥ ተዘፍቆ፣ በሁለት ተፎካካሪ ዋልታዎች ተከፍሎ በነበረበት ሁኔታ ውስጥ ነበር።

ይህም ሆኖ፤ አብዮቱ የአራት ሥር ነቀል የፖለቲካ ማህበራዊ ለውጦች አዋላጅ ሁኗል። መለኮታዊ አፄያዊ አገዛዝን ሽሯል። የአስገባሪና-ጭሰኛ ምርት ግንኙነትቶችን አስወግዷል። መንግሥትና ኃይማኖት እንዲለያዩ አድርጓል። ለዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈን ታግሏል። የዲሞክራሲያዊ ለውጥ አካል የሆነውን የኢትጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች መብት ጥያቄ ፊት ለፊት አንስቶ ከኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ጉዞ አጀንዳ ላይ አስፍሯል። ለፖለቲካ ንቃት እና ለተደራጀ ትግል ዕድገት አስተዋፅኦ አድርጓል። በአጭሩ፣ በታሪክ ዕይታ ጥቂት በሚባል የሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥልቅ የፖለቲካ እና የማኅበራዊ ለውጦችን አዋልዷል።

የዛሬው ወጣት የኢትዮጵያ የሆኑና ለ50 ዓመታት ያህል የተከማቹ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተመክሮዎች ባለቤት ነው። እንደዚሁም፣ “የሁለት አብዮቶች እና የሁለት ሬፑብሊክ” ሥርዓቶች አዎንታዊ እና አሉታዊ ምንነት ባለቤት ነው። ከዚህም አንፃር በአብዮቱ ታጋዮች የተፈፀሙትን ስህተቶች ላለመድገም የታጨ ነው። እነዚህ በራሳቸው የዛሬውን እና መጪውን ታጋይ በለውጦቹ እና ለለውጦቹ በተከፈሉት መስዋዕትነት ላይ ቁሞ ዕድሉን ብሩህ ለማድረግ እንዲተጋ የሚጠሩት የታሪክ ዕሴቶች ናቸው። ከአብዮቱ ዘመን አሉታዊ ገፅታዎች ራሱን እንዲጠብቅ አጥብቀው የሚያሳስቡት የታሪክ ፀጋዎች ናቸው።

ዘመኑ በአንድ ወገን የግሎባላይዜሽን እና የቴክኖሎጂ አብዮት ዘመን ነው። ፕሮፌሰር ማኑዌል ካስቴልስ እንደሚያስረዱት ‘እነዚሁ ግሎባላይዜሽን እና የቴክኖሎጂ አብዮቶች ዘመኑን የማንነት ጥያቄ የጎለበተበት ዘመን አድርገውታል።’[55] በተያያዘም የተለያዩ ፅንፈኛ፣ አክራሪና ሽብርተኛ የሚባሉ ኃይሎችን ያገነነ ዘመን ሁኗል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የኋለኞቹን ለመቋቋም ዓለም-አቀፋዊ ትብብሮች የሚደረጉ ቢሆንም ቅሉ፣ በኃያላኖች መካከል ለበላይነት የሚካሄደው ትንቅንቅ እንደቀጠለ ነው።

የተፅዕኖ ቀጠናዎችን ለመጠበቅ እና ለማስፋፋት የሚካሄደው ዓለም አቀፋዊ ፍልሚያ በድኅረ ሶቪየት ኅብረት ዘመን በበቀሉት በርካታ ሃያላኖች መካከል እየተካሄደ ነው። ለዚህም ባንድ ወገን የአወሮፓ ኅብረት እና የሰሜን አትላንቲክ ቃል-ኪዳን አገሮችን (ኔቶ) ክልል ወደ ምሥራቅ (ጆርጂያ፣ ዩክሬይን) ለማስፋፋትና በሌላውም ወገን የቻይናን መስፋፋት ለመገደብ የሚካሄዱትን ዓለም አቀፋዊ ግብግቦች አሉ።

[55] ማኑዌል ካስቴልስ፣ The Power of Identity፣ 1997።

በማኅበራዊ ፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ረገድ ሊበራል፣ ኔኦ-ሊበራል፣ የመንግሥት ካፒታሊዝም በሚባሉት ዙሪያ የሚካሄዱትም ትግሎች፤ የዚሁ የዛሬው የበላይነትን ለማስረገጥ የሚካሄደው ዓለም አቀፋዊ ትግል አካል ናቸው። እንደዚሁም በምዕራቡ ዓለም የፋይናንስ ተቋሞች እና ብሪክስ በሚባሉት አገሮች መካከል እየተካሄደ ያለው ትግል። ግቡም ዙሮ ዙሮ እንደበፊቱ ዓለምአቀፋዊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የወታደራዊ የበላይነትን ለማስረገጥ ነው። አሁንም እንደቀድሞው፣ የአገሮችን የተፈጥሮ ሀብት ለመቀራመት እና ለገበያ ቅርጫ የሚደረግ ዓለም አቀፋዊ ትንቅንቅ ነው።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ በርካታ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የመንግሥት ካፒታሊዝም በሚባለው ጎዳና ብሔራዊ የተፈጥሮ እና የሰው ካፒታላቸውን እያሰባሰቡ ለኢኮኖሚ ዕድገት እና ለልማት እየጣሩ ይገኛሉ። አንዳንዶቹ እየተነሱ/እየወጡ/እየተሸጋገሩ ያሉ አገሮች በሚል እየተገለፁ ናቸው። ይህ ሁኔታ እየተነሱ/እየወጡ ያሉትን አገሮች ባንድ ወገን ከዓለም አቀፉ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የገበያ ፉክክር ውስጥ አስገብቷል። በሌላውም ወገን፣ የብሔራዊውን የትግል አጀንዳ ለዲሞክራሲያዊ መስኮች መስፋት፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ለፍትሕ እና ለሕግ የበላይነት፣ ለመልካም አስተዳደር እና ለማኅበራዊ አቋዳሽ ፖሊሲ እንዲሆን አድርጓል። ሌሎች ባንድ ወገን እጅግ አውዳሚ በሆነ የሽግግር ማዕበል ውስጥ ይገኛሉ። ደግሞ ሌሎች ከተለያዩ ፅንፈኛ፣ አክራሪ እና ሽብርተኛ ከሚባሉ ኃይሎች ጋር እየተናነቁ ናቸው።

የኢትዮጵያን ቀጠናዊ ሁኔታ በሚመለከት ሁለት ዓቢይ ሁኔታዎች በግልፅ ይታያሉ። ባንድ ወገን ባለፉት ሦስት አሥርተ-ዓመታት መረጋጋት የተሳናቸው ሁለት አዳዲስ አገራትና መንግሥታት (ኤርትራና ደቡብ ሱዳን) ተፈጥረዋል። ሱማሌ ለሁለት ተከፍላ አንደኛው አካሏ ለዕውቅና እየተጣጣረ ነው። ሌላው አካሏ፣ “የወደቀ” መንግሥት ተምሳሌት ሁና እንደተንገራገጩች ናት። በሱዳን የተነሳው ጦርነት ማብቂያ አይታይም። የተለያዩት የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምሥራቅ ግጭቶችም ገና ለረጅም ዘመን የሚቆዩ ናቸው። በሌላው ወገን በጅቡቲ አንፃራዊ ሠላመና መረጋጋት አለ።

ኢትዮጵያ የኃይል ማመንጫ ኀተራ በመሆን ላይ ነች። ከዚህ ለመድረስ ሊሠራ የሚገባውን የውስጥ ኀብረት ፖለቲካ እና የውጭ ዲፕሎማሲ ሥራ አሳንሶ ለመገመት የሚቻል አይደለም። የአባይን የሚያክል ግድብ “በእኛው” ለመሥራት የተነሳች አገር መሆኗ በተለይ ለኢትዮጵያ ሕዘቦች እና ባጠቃላይ ለድሃ አገሮች እና ለዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋሞች የሚያስተላልፈውንም መልዕክት አሳንሶ መገመት አይቻልም። በልማት ፖሊሲ መስክ “ራስን በራስ መቻል፤ በራስ መተማመን” እየተባለ የሚወሳውን መሠረታዊ የልማት እና የልዕልና ፅንሰ ሃሳብ በተግባር ለመተርጎም እየተጣረ እንደሆነ የሚያመለክት ነው።

ነገር ግን “በእኛው” በራሱ ሩቅ አይወስድም። “በእኛው” ትርጉም የሚኖረው፣ ሰላምና ፀጥታ ሰፍነው የሕዝቦቿ ደህንነት ሲጠበቅ እና ሲከበር ነው። የአንዱ ብሔር መብት የሌላው ብሔር መብት ድንበር ላይ ሲቆም ነው። የአንዱ ዜጋ መብት የሌላው ዜጋ መብት ድንበር ላይ ሲቆም ነው። ያላሰለሰ አሳታፊነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ሲኖር ነው። የድርጅት ካድሬ ቢሮክራቶች፣ ቴክኖክራቶች እና አስተዳዳሪዎች ፈጣሪ አድራጊነት እና ኪራይ ሰበሳቢነት ዘመን ሲያበቃ ነው። የጥቀመኝ ልጥቀምህ ድር እና ማግ ተተርትሮ ሲበጣጠስ ነው።

እነዚህ ሁኔታዎች በራሳቸው የዛሬው ታጋይ የትግሉን ግብ፣ ሠልፍና ስልት፣ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ውስጣዊ ሁኔታዎች ከቀጠናዊው፣ አህጉራዊው እና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ጋር በውል አገናዝቦ መቀይስ እንዳለበት ያመለክቱታል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ለአገሩ እና ለወገኑ የምትሆነዋን ኢትዮጵያ ወደፊት ተመልካች በሆነ መንፈስ እንዲያስብ አጥብቀው ያሳስቡታል። ይህም በዋናነት፣ የአገሪቱን እና የሕዝቦቿን ስትራቴጂያዊ የጋራ ጥቅሞች ወደፊት ተመልካች በሆነ መንፈስ ማስተዋል እና መቅረፅ ማለት ነው። እንዲያም ሲል በዜጎቿ፣ በብሔሮቿ እና በኃይማኖቶቿ ሰብዓዊና ዲምክራሲያዊ መብቶች መታወቅና መከበር አንድነቷን ላፀናች እና ውስጣዊ ሰላሟን ለጠበቀች፤ የአገሪቱን እና የሕዝቦቿን ስትራቴጂያዊ የጋራ ጥቅሞች ማዕከል አደረጎ በተቀየሰ ስትራተጂ ዓለም-አቀፋዊ እና ቀጠናዊ ሥፍራዋን ላረጋገጠች እና የፖለቲካ ሥልጣን

እንደየሁኔታው በመጋራት እና በመፈራረቅ ለሚሽጋገርባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ተግቶ እንዲታገል ይጠሩታል።

የአብዮቱ ታጋይ ምሑራንና ተራማጆች አገር ወዳድና ለሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም እና መብት የወገኑ ነበሩ። ታሪክን እና የፖለቲካ ማኅበራዊ ጉዳዮችን ለማጥናት እና ለማወቅ በእጅግ የተጉ ነበሩ። ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን እና የሶስተኛው ዓለም ሕዝቦችን ትግሎች በቅርብ የሚከታተሉ እና ወገንተኛነታቸውን የሚገልፁ ነበሩ። እንደዚሁም "የባዕዶቹን" የማኅበራዊ ፖለቲካ ፍልስፍና ለመካን የሚጥሩ ነበሩ።

የዛሬው ትውልድ ከነዚህ ጉዳዮች አዎንታዊ ትምህርቶችን ለመቅሰም ይችላል። ለምሳሌም ዛሬ ሊበራሊዝም፣ ኔኦ-ሊበራሊዝም፣ ሶሺያል ሊበራል፣ ሶሺያል ዲሞክራሲ፣ ልማታዊ ካፒታሊዝም... የሚባሉትን የማኅበራዊ/ፖለቲካ ርዕዮተ ዓለሞች እና ስለፅንሰ ሃሳቦች ሥፍራና ሚና፣ ጥንካሬና ድክመት ለማጥናት እና ለማወቅ እንዲተጋ ያስፈልጋል። እንደዚሁም ከአምባገነን አገዛዞች ወደ ዲሞክራሲያዊ እና የሕግ የበላይነት ሥርዓት የተሳኩ እና ያልተሳኩ ሽግግሮችን ያደረጉ አገሮች የሄዱባቸውን መንገዶች ለማጥናት መጣር ይኖርበታል።

ነገር ግን ስለ ማርክሲዝምም "የመጨረሻው ቃል" ገና አልተነገረም እንደሚባለው፤ ከሶቪየት ኅብረት መፍረስም በኋላ ቢሆን በማርክሲዝም ጥያቄ ላይ የሚደረጉ ውይይቶች እና ክርክሮች በትምህርት ተቋሞች፣ በፈላስፎች፣ ኢኮኖሚስቶች፣ የፖለቲካ እና የማኅበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች እና ምሑራን መካከል እንደቀጠሉ ይገኛሉ። ክርክሮቹን ለመከታተል እና ለማወቅ መጣር ያስፈልጋል።

የአብዮቱ ታጋዮች ልዩነቶችን ከማጉላት ይልቅ ለመግባባት፣ ፍጹም ትክክለኛነትን ከማሳየት ይልቅ በትዕግስት ለመወያየት የሚጠበቅባቸውን አላደረጉም። ከጥሞና ውይይቶች ይልቅ እሰጥ አገባው ያመዘነ ነበር። በቅድሚያ የእኔ እምነት ብቻ ፍፁም ትክክለኛ ነው ብሎ በዕርግጠኝነት መመልከት ለነፃ እና ለግልፅ ውይይት እንቅፋት ነው። ለነፃ ውይይት ራስን መርምሮ የራስን ሕሊና ነፃ ማድረግ እና ለመታረምም ለመማማርም ፈቃደኛ መሆን ያስፈልጋል። ራስን እንደ ሁሉን አዋቂ ብፁእን፣ በሃሳብ የተለዩትን ደግሞ እንደርኩሳን እና ጠላት መመልከት ስህተት መሆኑን መረዳት ይገባል። ልዩነቱ ከሃሳብ ጋር ሳይሆን ከግለሰቦች ጋር እንደሆነ አድርጎ መውሰድ፤ ሌላውን ዝም ለማሰኘት እና ስም ለማጥፋት የሚያቀነቅን እና ከአጥፊና ጠፊ የፖለቲካ ሽክርክሪት ውስጥ የሚያስገባ አካሄድ ነው።

የውግዘቶች ድርዳሮ፣ የስሜቶች ኩርኮራ፣ ጥላቻን ማንቦግቦግ እና የመዓት መጣ ትንግርቶችን ማዛመት፤ በፍርሃት እና በጭንቀት ነገሮ ፖለቲካ ተሰሚነትን ለማግኘት መጣርን እንጂ፣ በሚያቀርቡት ብሔራዊ/አገራዊ የፖለቲካ ማኅበራዊ የፖሊሲ አማራጮች የበለጡ እና አሳማኝ ሆኖ መገኘትን አያመለክትም። "ሁሉንም፣ አለዚያ ምንም" የፖለቲከኛ ፖለቲካ አይደለም። ንቀትን እና ጥላቻን በማራገብ እና ራስን በራስ በሚያገዝፍ ፕሮፓጋንዳ የሚመራ ፖሊቲካም አሳሳች እና አደገኛ ነው።

የፖለቲካ አስተሳሰቦች እንደሁኔታውና ተርጓሚዎቹ ተለዋዋጭ እንደሆኑና ተመርምረው እንደሚታረሙ መገንዘብ ከቀኖናዊነት በሽታ ይከላከላል። ለለውጥና ለማሻሻል ሁልጊዜም የመንግሥትን ሥልጣን ለመጨበጥ ሽቅብ ብቻ ማየት ከስር ከሲቪሉ ኅብረተሰብ ሊገኙ የሚችሉትን አሳንሶ ማየትን ያስከትላል። ከዚህም አንፃር አንዳንድ ዕድገቶችና ማኅበራዊ መሻሻሎች ሲታዩ፤ ፈረንጆች እንደሚሉት "ብርጭቆው ግማሽ ሙሉ ነው ከማለት ይልቅ ግማሽ ጎዶሎ ነው እንጂ" እያሰኘ የአሉታዊ ምንባብ አስተጋቢ ያደርጋል።

የዛሬው ጥያቄዎች፣ ቅራኔዎች፣ ውጥረቶች፣ ሽኩቻዎች... ዙሮ ዙሮ የሚያመለክቱት በብሔራዊ/አገራዊ እና በክልሎች ደረጃ የፍትሕ እና የሕግ የበላይነትን መከበር፣ የዲሞክራሲ መስኮችን መስፋት፣ የመልካም አስተዳደር እና የማኅበራዊ ተቋዳሽነት ፖሊሲዎችን መራመድ፣ የዜጋ፣ የግል እና የቡድን መብቶች መጣጣም፣ መገንባት፣ መደርጀትና መከበርን አስፈላጊነት ነው።

ኢትዮጵያ ባለፉት 50 ዓመታት ዘመን ሁለት አምባገነን አገዛዞች የተወገዱባት አገር ብትሆንም፤ እንደሌሎቹ ተመሳሳይ አምባገነን አገዛዞችን እንዳስወገዱ አገሮች (ስፔይን፣ ፖርቹጋል፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ፖላንድ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ቺሊ፣ ብራዚል...) ዲሞክራሲ ሥርዓት የሰፈነባት እና የሕግ የበላይነት የተከበረባት አገር ከመሆን ሩቅ ናት። ኢትዮጵያ እንደዚሁም፣ ውስጣዊ ገዥነት (embedded autonomy) ካላቸው የመንግሥታዊ ተቋሞች እና የነፃ ሲቪል ማኅበራት ባለቤት ከመሆን ሩቅ፤ እጅግ በጣም ሩቅ ናት።

ስለዚህም የዲሞክራሲ ሥርዓት እና የሕግ የበላይነት ጥያቄዎችን መደጋገምና ለጥያቄዎቹ መታገል የማይታለፍ ነው። ይሁን እንጂ፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ተግዳሮት ከዚህ ባለፈ ከገዢዎቿ ፖሊሲዎች የተሻሉ እና አሳማኝ የሆኑ ዝርዝር የማኅበራዊ ፖለቲካ ፖሊሲ አማራጮችን ማቅረብ ይጠይቃል። ለዚህም ከሁሉም በፊት፣ በየመስኩ የተደረጉ እና ነባራዊውን ሁኔታ የሚያንፀባርቁ የባለሙያዎች ጥናቶችና ምክረ ሃሳቦች ባለቤት መሆን ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ነው፤ በቴክኒክ የተሻሉና የበለጡ የፖሊሲ አማራጮች ባለቤት መሆን የሚቻለው። ምናልባትም በተቃዋሚዎች መካከል እየተቋጠረ ከሚፈታው፣ እየደረሰ ከሚበተነው የትብብር/ቅንጅት /ኅብረትና ውህደት... ሽክርክሪት ውስጥ ለመውጣት የሚቻለው።

የዛሬውና መጪው ታጋይ ከአብዮቱ ዘመን ድርጅቶች የአደረጃጀትና የአመራር ስህተቶች የተማረ መሆን አለበት። ከላይ ስለ አብዮቱ ዘመን ድርጅቶች አደረጃጀትና አመራር ባጭሩ ከተዳሰሰው ግልፅ እንደሚሆነው፣ ድርጅቶች ውስጣዊ የዲሞክራሲ አሠራር የሌላቸው ከሆኑ፣ ወደ ጥቂት ሰዎች አምባገነንነት ያመራሉ። ይህ ሃቅ የዛሬውንና መጪውን ታጋይ ለአሳታፊ፣ ለአካታች፣ ለግልፅ እና ለተጠያቂ የድርጅት አመራር እና አስተዳደር እንዲታገል ይጠራዋል። የከረሩ የማኅበራዊ ፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ፍጭትና የግጭት ጠሪ ፖለቲካ ሰለባ እንዳይሆን ነቅቶ እንዲጠብቅ ይጠሩታል።

የለውጡ ጥያቄ አሁንም፣ ሕገ-መንግሥቱ አገራዊ/ብሔራዊ ተቀባይነት እና ቅቡልነት ባለው ሕገ መንግሥት እንዲሻሻል ነው። የኢትዮጵ "ፌዴራል" አስተዳደር አወቃቀር አገራዊ/ብሔራዊ ተቀባይነት እና ቅቡልነት ባለው የፌዴራል አስተዳደር ሥርዓት ተሻሽሎ እንዲቆም ነው። ሁለቱም ማሻሻሎች፣ የፌዴራል ሰጥቶ መቀበል (federal bargain) በሚባለው ሥርዓታዊ አካሄድ እና በቴክኒካል መንገዶች ሊስተናገዱ እና ሊፈቱ የሚችሉ ናቸው። ይህም በቅድሚያ እና ከሁሉም በፊት፤ በአዲሲት ዲሞክራሲያዊት እና ፌዴራል ኢትዮጵያ አብሮ የመኖርንና የጋራ ወደፊትን በጋራ ለመቅረፅ፣ ለማቆም እና ለመገንባት የቆረጡ፣ የተነሳሱ እና የደፈሩ የፖለቲካ እና የመንፈሳዊ አመራር መሐንዲሶችን ይጠይቃል።

አንዳንድ የኢትዮጵያ ብሔረተኞች ዛሬ በ2016 ዓ.ም. የሚታገሉት ከ50 ዓመታት በፊት ለተሻረው አፄያዊ አገዛዝ በሞመገት እና "ወርቃማው ዘመን" የሚሉትን በማሞካሸት ጭምር ነው። አንዳንድ የብሔር ድርጅቶች ዛሬ በ2016 ዓ.ም. አጥብቀው እንታገላለን የሚሉትም፣ የኢትዮጵያ ልጆች ከ50 ዓመታት በፊት ባደረጉት ትግል ታሪክ የሆነውን አፄያዊ አገዛዝ እና፤ ከ30 ዓመታት በፊት እነሱው ራሳቸው በአብዛኛው የሻሩትን የብሔር ጭቆና ነው። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የአፄ ምኒልክም ይሁን የአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ኢትዮጵያ አይደለችም። የ1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት እና የ1983 ዓ.ም. ለውጥ ሂደቶች እንዳበጇት አድርገው የተበጀች ኢትዮጵያ ናት። ከነዚያ ዓመታት ወዲህ ብዙ ክረምት አልፏል። ኢትዮጵያ ብዙ ወንዞችን ተሻግራለች።

የነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝን ቆንጆ አባባል አሁንም ልዋስና፣ "እስተካክለን ካሰብን ዘንድ" የድኅረ 1983 ዓ.ም. ኢትዮጵያ፣ የየብሔር ወገናቸውን የፖለቲካ ማኅበራዊ መሠረታቸው አድርገው የተፈለፈሉ

የቢሮ፣ የደራሽ (arrivist)[56]፣ የጥገኛ እና የአቀባባይ ከበርቴ (comprador)[57] መደቦች በፍጥነት የደረጁባት እና የየራሳቸውን የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ሥፍራ እየያዙ የመጡባት አገር ሆናለች። የብሔር ነጋዴዎች እና ባለሀብቶች (ethnic entrepreneurs)፣ ለሥልጣን እና ለሀብት ጭበጣ (resource capture) የሚሸቀዳደሙባት አገር ሆናለች። ስለዚህም፣ የዛሬው የኢትዮጵያ ዓቢይ ቅራኔ አሁንም እንደቅድመ 1966 ዓ.ም. ኢትዮጵያ፤ በኢትዮጵያ ብሔሮች መካከል ያለው ቅራኔ አይደለም። በድኅረ 1983 ዓ.ም. በፈጣን ክንዋኔ ተፈልፍለው በተደላደሉት ገዢ መደቦች እና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ያለ ቅራኔ ነው። ትግሉም፣ የብሔርን ስም እያውለበለ እና የኃይማኖትን ካባ እየደረበ ጭምር ይከሄድ እንጂ፤ በሁለቱ ጎራዎች መካከል በተለያዩ መንገዶች የሚካሄድ ትግል ነው።

በዚህ ትግል ውስጥ፣ የድኅረ 1983 ዓ.ም. ገዢ መደቦች እና የፖለቲካ ተዋናዮች በአንድ በኩል፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በትላንቱ ሞገስ እያጎፈኑና እና፤ በሌላውም ወገን በትላንቱ ቁስል እያቦዙ በድኅረ 1983 ለተቀዳጁት የመደብ ሥፍራቸው እና ጥቅም እየተሟሟቱ ናቸው። ለዚህም፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአንድ ወገን፣ በእጅግ በተካኑት የከፋፍለህ ግዛ ሥርዓተ አገዛዝ፤ ከብሔር እስከ ኃይማኖት፣ ከታሪክ እስከ ሰንደቅ ዓላማ፣ ከወሰን እስከ ማንነት እያናጩ እና እያጋጩ ይታገላሉ። በሌላው ወገን እና እነሱ ከሌሉ አገሪቱ እንደምትፈርስ እያወጁ ይታገላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ግን፣ አሁንም እንደ ቅድመ 1966 ዓ.ም.፣ እንደ1983 እና እንደ2008 ዓመተ ምህረቶች ለዲሞክራሲ፣ ለዜጎች እና ለብሔሮች በዕኩልነት አብሮ መኖር ፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለሕግ የበላይነት እና ፍትሕ፣ ለማኅበራዊ ፍትሕ እና ተቋዳሽነት፤ ለሰላም እና ደህንነት፣ ለጋራ ልማት እና ብልፅግና የሚደረግ ትግል ነው። አሁንም እንደበፊቱ፣ ያለፉትን ሥርዓታት ጉድለቶች ነቅሶ እና አርሞ፣ ለዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ብሔረ መንግሥት ግንባታ የሚበጀውን መሠረት ለመጣል እና ለማዋቀር የሚደረግ ትግል ነው።

የቀድሞዎቹ ገዢዎች የፖለቲካ ለውጥ/ሪፎርም/አብዮት ማድረግ ተስኗቸው ተወግደዋል። በዚህች አጭር ፅሑፍ ከተታወሱት የፖለቲካ ታሪካችን ውስጥ ሊቀሰም የሚገባውም ትምህርት፣ የፖለቲካ ለውጥ/ሪፎርም/አብዮት የዘገየውን/ያልተፈፀመውን ያህል፤ የለውጥ ጥሪ ንቅናቄ ዛሬ ማንም በማያስበው መንገድ እንደሚፈነዳ ነው። ያ ሰዓት፣ እንደ1966ቱ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሆነ፣ እንደ1983ቱ ወይንም ደግሞ እንደ 2007ቱ እና በ2008ቱ ዓይነት እንደማይሆን ግን፤ በዕርግጠኝነት ለመናገር ይቻላል።

የዛሬዎቹ ተዋናዮች ወቅቱ የሚጠይቀው የፖለቲካ ለውጥ/ሪፎርም/አብዮት መሆኑን ተገንዝበው እና ለከፍታው በቅተው ከተገኙ፤ ኢትዮጵያ ቴክኒካል ፍኖቱ ለሚጠይቀው የዕውቀት እና የተመክሮ ሀብት ድሃ አይደለችም። በቂ የፖለቲካ፣ የሕገ መንግሥት፣ የኢኮኖሚ፣ የፋይናንስ፣ የአስተዳደር፣ የሕግ፣ የኃይማኖት፣ ወዘተ ባለሙያዎች ባለፅጋ ናት።

---

56 ደራሽ (arrivist) ከበርቴ በ"ከኔ በኋላ" አስተሳሰብ ደፍጥጠው እና አጋበሰው የሚከብሩን ግለሰቦች ለመግለፅ የሚውል ቃል ነው። ቴሳዎረስ person who has recently acquired unaccustomed status, wealth, or success, especially by dubious means and without earning concomitant esteem" በማለት ይገልፃቸዋል።

57 ጥገኛ ከበርቴ (comprador) የሚውለው፣ በተጠጋቸው የውጭ ባለሀብቶች እና በአገሩ አምራቾች መካከል ሠፍሮ፣ በድለለ እና በማዋዋለ የተሠማገራውን የከበርቴ ክፍል ለማመልከት ነው፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት እና ፅሑፍት


- ሃሊዴይ ፍሬድ እና ማክሴን ሞሊይኔክስ፤ The Ethiopian Revolution. London, 1981
- ሐዲስ ዓለማየሁ፣ ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል? 1974
- ሕይወት ተፈራ፣ Tower in the Sky. Addis Ababa, 2012
- ሌፎር፣ ረኔ፣ Ethiopia: An Heretical Revolution፣ 1983
- መረራ ጉዲና፣ The Elite and the Quest for Peace, Democracy፣ WMU፣ 2001
- መሳይ ከበደ፣ Radicalism and Cultural Dislocation in Ethiopia, 1960-1974፣ 2008.
- መሳይ ከበደ፣ Ideology and Elite Conflicts: Autopsy of the Ethiopian Revolution፣ 2011
- መርስኤ ኀዘን ወ/ቂርቆስ (ብላታ)፣ የሐያኛው ክፍለ-ዘመን መባቻ፣ አዲስ አበባ፣ 1999
- ማርካኪስ ጆን እና ነጋ አየለ፣ Class and Revolution in Ethiopia. Red Sea Press, 1986.
- ሞሐመድ ሓሳን፣The Oromo of Ethiopia: a History1570-1860. Red Sea Press, 1994.
- ሳራ ቮግሃን እና ትሮንቮል፣ The Culture of Power in Contemporary Ethiopian Political Life፣2003 ስታህል፣ ሚካኤል፣ Ethiopia: Political Contradictions in Agricultural Development፣ 1974
- ሽዋብ ፒተር፣ Ethiopia: Politics, Economics and Society. Lynne Riemmer Publishers, 1985.
- በረከት ሀበተሥላሴ፣ Conflict and Intervention in the Horn of Africa፣ 1980
- ባሕሩ ዘወዴ፣The Quest for Socialist Utopia፣ 2014.
- ባሕሩ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ 1847 – 1983። አዲስ አበባ 2003.
- ባሕሩ ዘውዴ፣ «Documenting the Ethiopian Student Movement»
- ባሕሩ ዘውዴ፣ Pioneers of Change in Ethiopia፣ 2002
- ባሕሩ ዘውዴ፣ Society, State and History: Selected Essays፣ Addis Ababa 2008
- ባሕሩ ዘውዴ፣ The "Red Terror" in Ethiopia
- ባሕሩ ዘውዴ፣ The Burden of History፣ 1999
- ባልሳቪክ፣ አር. አር፣ Haile Selassie's Students፣ 1985
- ብርሃኑ ባይህ (ሌ/ኮ)፣ ያልታሰበው የሕይወቴ ፈታኝ ጉዞ፣ ሳይንስ አካዳሚ ፕሬስ፣ 2013
- ተፈራ ኃይለሥላሴ፣ Ethiopian Revolution 1974-1991፣ Rutledge፣ 1997
- ታደለች ኃይለሚካኤል፣ ዳኛው ማነው? 2012
- የራስወርቅ አድማሴ፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፍጅት መንሳኤዎችና የዘር ማጥፋት ፍጀት አደጋ፤ በ"ያለመቻቻል ፖለቲካ ሰማዕታት፤ መቼም እንዳይደገም" ውስጥ፤ ጥር 1998 ዓ.ም.
- አለማየሁ ገዳ፣ Ethiopian Macroeconomic Modeling in Historical Perspective፣ 2004። ባሕሩ ዘውዴ፣ Pioneers Of Change In Ethiopia፣ 2002
- ዓለማየሁ ገዳ፣ የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ መሠረታዊ የኢኮኖሚክስ አስተሳሰቦች፣ 2013
- አበራ የማነ አብ፣ ለውጥ ናፋቂ ሕይወቴ፣ አዲስ አበአ፣ 2014
- አቢይ አበበ፣ (ጀ/ል) ፣ አውቀን እንታረም፣ ኤል ፖሊግራፊኮ፣ 1955
- አስማማው ኃይሉ፣ ከደንቢያ፣ ጎንደር፣ ዋሽንግተን ዲሰ
- አስማማው ኃይሉ፣ ኢሕአሠ 1964-70፣ 2003
- አንዳርጋቸው ጥሩነህ፣ The Ethiopian Revolution 1974-1987፣1993

- አንዳርጋቸው አሰግድ፣ በአጭር የተቀጨ ጉዞ -መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ፣ 1991/2020
- አንዳርጋቸው አሰግድ፣ ቅን ፍላጎት እስካል መንገድ አለ፣ 2012
- አዲስ ሕይወት፣ Ethiopia from Autocracy to Revolution፣ London 1975
- አዲስ ተድላ (ሌ/ጀ)፣ በገጠመኞች የታጀበ የሕይወት ጉዞ፣ 2014
- እሸቱ ጮሌ፣ «Under Development in Ethiopia»
- ኬለር ኤድሞንድ፣ Revolutionary Ethiopia: From Empire to People's Republic፣1989.
- ክላፐሃም ክሪስቶፎር፣ Transformation and Continuity in Revolutionary Ethiopia፣ 1988.
- ካሕሳይ አብርሃ፣ የአሲምባ ፍቅር፣ 2013
- ክፍሉ ታደሰ፣ ያ ትውልድ ቅጽ I እስከ III ኮኸን ጂ. ኤም. እና ዲ. ዌይንተራብ፣ Land and Peasants in Imperial Ethiopia: 1975.
- ወርቁ ፈረደ፣ ዕድገት ብሎ ውድቀት፣ የወታደር ሶሻሊዝም፣ 1990
- ወልደልዑል ካሳ፣ The Party፣ 2022
- ዳዊት ወልድጊዮርጊስ፣ Red Tears፣ Red Sea Press፣ 1989
- ጂልክስ ፓትሪክ፣ The Dying Lion: Feudalism and Modernization in Ethiopia፣ 1975.
- ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎች፣ 2002
- ገብሩ ታረቀ፣ Ethiopia Power and Protest. Peasant Revolts in the Twentieth Century፣1996
- ገበሩ ታረቀ፣ The Ethiopian Revolution፡ War in the Horn of Africa፣ 2013.
- ገብሩ ታረቀ፣ The Red Terror in Ethiopia፣ 2008, vol. 24.
- ግሪንፊልድ፣ ሪቻርድ፣ Ethiopia: A new Political History፣ 1965.
- ግርማይ አብርሃ፣ « ከደርግ ማሕደር»
- ጓደኞች፣ የመኢሶን ሰማዕታት፣ 2016
- ጴጥሮስ ቶጃ፣ Genealogy of 'red terror' in Ethiopia
- ጴጥሮስ ቶጃ፣ የጭድ እሣት፣ አዲስ አበባ፣ 2014
- ፋሲካ ሲደልል፣ የሻምላው ትውልድ፣ 2014
- ፍስሐ ደስታ (ኮ/ል)፣ አብዮቱ እና ትዝታዬ፣ 2015
- ፍቅረስላሴ ወግደረስ (ሻ)፣ እኛና አብዮቱ፣ 2013